ለ እ ና ቴ

ለወይዘሮ የሺ ሐብተማርያም

መ ታ ሰ ቢ ያ

*From the Library of*

***ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ***

***FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES***

ሰ ኔ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም

June, 1991

# ምሥጋና

ስለምንም ይሁን መጽሐፍ ብቻ እንድጽፍ ይገፋፉኝና ያበረታቱኝ ከነበሩት ጓደኞቼ አቶ ታደሰ እርገጤና መምህር እሰፋው ዘለቀ ዛሬ አብረውኝ ባይኖሩም ድጋፋቸውና ማበረታቻቸው ከመቃብር በላይ ውሎ ለዚህ በጎ ተግባር ጊዜዬን ፍላጎቴን መስዋዕት እንዳደርግ ስለረዳኝ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው።

ለአንድ ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ እስር ቤት እንደ እህት እንደ ወንድም ሆነው በምክራቸው ያጽናኑኝና ምግብ ያቀብሉኝ የነበሩት ወጣቶች ከነወላጆቻቸው ለዚህ መጽሐፍ በቀጥተኛ መንገድ አስተዋፆኦ ያበረከቱ ናቸውና የእኔ ብቻ ሣይሆን የወገንም ባለውለታ ይሆናሉ።

ውሎ አድሮ መልከም ለመሥራት ጤንነት ዋነኛውን ሥፍራ የሚይዝ ሲሆን በበሽታ ተይዤ በሶማሊያ እስር ቤት እንደሞቱት ወገኖቼ ልሞት ስችል ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ማንኛውንም ሥራ በመሥራት መድኃኒት በመግዛት የረዱኝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የወገንን ፍቅሬንና ስሜቴን ይበልጥ ስለቀሰቀሱት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ መጽሐፍ አስተዋፆኦ አላቸው።

ችግሬን እንጂ ደስታዬን ላልተካፈሉት ዘመዶቼና ጓደኞቼ ላለቸው ትዕግስትና ለማይወለውለው ፍቅራቸው ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ምንም እንኳን ዕቀዴ ሰፊ ምኞቴ ከፍተኛ ቢሆንም ስለሃገሬ ያለኝ እውቀት ውስን በመሆኑ «ሩቅ አሣቢ ቅርብ አዳሪ» አድርጎኛል። ሆኖም «ረጅም ጉዞ ከአንድ እርምጃ ይጀመራል» ይሉ «ስንትአየሁ በሃገሬ» ጅምሬ ሊሆን ነው።

ይህ መጽሐፍ ተጽፎ አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት እንዲኖረው የአማርኛ የድርሰት ማቀነባበሪያውን መረሐ ግብር (Amharic Word Processor) ከማቀረብ ባሻገር ባለመስልቸት ምክራቸውን ለለገሡኝ የዳሽን የዕደጥበብ (Dashen Engineering Company) ባለንብረቶች ምሥጋናዬ ከፍተኛ ነው።

ታደለ . መኩሪያ.



# መግቢያ

በዚህ አጭር ድርሰት ከሚያዚያ ፲፱፻፷፯እስከ ፲፱፻፸፬ ዓመተ ምህረት ከኢትዮጵያ እስከ ሶማሊያ ወገን በወገን ላይ ባዕድ በሃገር ሕዝብ ላይ ሲፈጽሟቸው ያየሁትን ግፎችና በደሎች ለማቀረብ ሲሆን፤ ግን እንዴ ያየውን ሌላው ሳያየው ስለሚችል ለሁሉም ያለፈው ተረስቶ ከቀረ መጪውን መተንበይ ስለሚያስቸግር ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በመጽሐፍ መልክ አቀርቤዋለሁ።

ለመጽሐፉም መፃፍ ዐብይ ምክንያት ያለፉት እስከፊ፣ አሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታዎች እንዳይደገሙ ለመጠቆም ነው። «በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል» የሚለውን የአበው አነጋገር ምርኩዝ በማድረግ ያለፉት ድርጊቶች ተረስተው ተረት ሆነው እንዳይቀሩ በማሰብ ቃላት የተደረጉትን ተግባራት በትክክል ለአንባቢያን እንዲገልጹ ተቀነባብረው ቀርበዋል። የታየውን በካሜራ ቀርፆ የማስቀረቱ ዕድል ገጥሞ ቢሆን ኖሮ የቱን ያህል ግለሰቦችንም ሆነ ግለሰብን ማሣመን በተቻለ ነበር።

መጽሐፉን ስጀመር እንደ ፎቶ ፊቴ ላይ ድቅን ካሉብኝ ድርጊቶች ጥቂቶቹ፤

[] ማታ ተለይቼው ጠዋት እስከሬኑ በሆስፒታል ታዛ ሥር በጠረጴዛ ላይ እጋድመውት ያየሁት መምህር፤

[] በከፍለሃገር የተመደው የደርግ አባል በመኪና ሕፃኗን ገጭቶ አባትዬው ሲጮኽ አዳሃሪ በማለት ሽጉጥ ሲመዝ ፤

[] በአንድነት ሰዎች በጥይት ተደብድበው ከተቀበሩበት ጉድጓድ ጀብ እስከሬናቸውን አውጥቶት የበላውን በልቶለት አልታኘክ ያለውን በየሜዳው ጥሎት በአካባቢው ትምህርት ቤት የሚገኙት ሕፃናት የሟቾችን የሰውነት ክፍል ከበው ሲመለከቱ፤

[] አዲስ አበባ ከተማ ዐባይ ምንጭ በራፍ ላይ ከመኪና አውጥተው የገደሉት ወጣት ሰውነት፤

- [] ሐብተጊዮጊስ ድልድይ አፋፉ ላይ የከተራ ዕለት በ፸ ዓመተ ምህረት ታቦት አስቀመው ፋሲል ከሚበላው ቡና ቤት በራፍ ላይ የመቱት ወጣት ሁኔታ ፤

- [] ከስድስት ኪሎ ዮኒቨርሲቲ በራፍ ላይ የገደሉት መምህር፤ በየአውቶቢሱ ማቆሚያ የተጣለውን ራስ እያነሱ ከመኪና ሲጭኑ፤

- [] ወጣቱ በጀርባው ተጋድሞ እንደገና ደብ እሳት ሲነድበት ፤

- [] በአንድ ሌሊት ከነበርኩበት ቀበሌ ለግድያ ተመርጠው ከወጡት ወጣቶች ውስጥ የለበሰውን ኮት ሲያስወልቁት፤ «ለሃገሬ ሕዝብ ከዚህን የተሸለ ነገር ትቼለት እሄድ ይሆን» ሲል የተናገረው መምህር አኳኋን፤

- [] የአምስት ዓመት ሕፃን ወንድሟን ልጠይቅ ከቀበሌ የመጣች ከኮለኔል መንግሥቱ አበት እግር ላይ ተጠምጥማ ልጃቸው ወንድሟን እንዲፈታለት እንዲያማለዷት ስትጠይቅ፤ ያየሁት ሁኔታ ድርስቴን እስከ ማጥናቀቅበት ጊዜ ድረስ ወደአእምሮዬ እየመጣ ያስቸገረኝ ነበር።

- [] በሶማሊያ ብሔራዊ የጸጥታ ጽሕፈት ቤት እስር ቤት ውስጥ ከሐረር ክፍለሃገር በምርኮ ስም የተያዘ የሕዝብ ደህንነት መኮንን የሰውነት ሁኔታ፤

- [] በሶማሊያ ትልቁ እስር ቤት «ሴንተራሌ» ታስረው የነበሩ ኢትዮጵያውያን በተቅማጥ በሽታ ተይዘው በአንድ ጉርድ በርሜል ውስጥ እይኑ ምድራቸውን ለመውጣት ያደርጉት የነበረው ርብርብ፤

- [] የሚሰጣቸው ምግብ በቂ ካለመሆኑ የተነሳ ማዕዴ የቀረበበትን በርሜል አጋደመው ሲሟጥጡት ፤

- [] በሰንበ ነቀርሳ የሚሰቃዩት ሕክምና አጥተው ማታ ተኝተው ጠዋት ሬሳቸው መታየቱ፤



- [] መምህሩ ለስልሳ ቀን ምግብ አቁሞ ችግሩን ለበላይ ለማስማት ሞክሮ እንዳልተሳካለት ሲረዳው በመጨረሻም ወገኖቼ እሩዱኝ በማለት ሁለት እጆቹን መዘርጋቱ

ሲታወሰኝ መፃፌን አቁሜ ለሁለት ለሦስት ቀን ሐሣቤ እስኪረጋጋ ጊዜ እንድወስድም የተገደድኩበትም ወቅት ነበር።

በእርግጥ የሰው ልጅ ባለማውቅ ይሁን በማወቅ በራስ ወዳድነት ብዙ ግፍና በደልን በግለሰቦችም ሆነ በብዙሃን ላይ ሊፈጽም ይችላል። በርከት ያሉ ግለሰቦች ተመሳሳይ ደርጊቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ፤ ግን በደል መፈጸማቸውን ሳይረዱት ያልፋሉ። እንደነዚህ ያሉ ተግባራት በተደጋጋሚ እንደይፈጸሙ የምሁራን ብዕር ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ከአንዳንድ ታታሪ ግለሰቦች ሥራ ለመረዳት ተችሏል።ሆኖም ስለ ሃገር በውጭ ቋንቋ በመጥኑም ቢሆን ተጽፎ ቢቀርብም ተነባቢነቱ ለጥቂቶችና በደርጊቱ ተከፋዮች ሳልነበሩ በመሆኑ ወገን ያነባቸው ዘንድ ቀደም ተከተሉን በመጠበቅ ከመንደር እስከ ትልቅ ከተማ ከዚያም በገጠር እልፎም በጐረቤት ሃገር በቦታው ተገኝቼ ያየሁትን በመጽሐፉ ውስጥ ገልጫለሁ።

በመጽሐፉም ውስጥ በጊዜው በወገን ላይ የተፈጸሙትን በደሎች ሲገለጹ ቀድመ አብዮት የተደረጉትን በማዘመድ ማብራሪያ ሰጥቼበታለሁ።

ከላይ በተገለጹት ዓመተ ምህረቶች ውስጥ ስለነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ግለሰቦችን በሚና በማጫወት የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ እንዲገልጹ አድርጌአለሁ።

ለኢትዮጵያውን በውጭም በግቢም የመከራ ዘመናቸው እንደነበር የሚጠቁሙ ተግባሮችን ከሥፍራው ሲፈጸሙ የታዩትን እንዳለ ቀርበዋል።

በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች አብዛኛው እውነተኛ ሰዎች ሲሆኑ የእንዳንድ ግለሰቦችን ስም ከመግለጽ ይልቅ ሞያቸውን በመጥቀስ ታልፏዋል። ታሪኩን የጀመርኩበትን ሥፍራ ግልጽ አላደረኩትም፤ ግን የተገለጹት ሥፍራዎች በሙሉ በትክክለኛ ስማቸው ነው።

## ፩

ጎረቤቴ በመስከት እንኪከቶ አንድ መምህር በማታው እንደተገደለ አርድቶኝ ተመልሶ ሄደ። ሁኔታውን አምኖ መቀበል አቅቶኝ ቅዥት ነው፣ በማለት ተመልሼ ተኛሁ።ትንሽ ቆየት ብላ ሠራተኛዋ የመኝታ በሬን እንኳከታ ጓደኞዬ መሞቱን ስትነግረኝ እርግጠኛ መሆኑን አምኜ ከአንቅልፌ ተነስቼ  አስከሬኑን ከኖሩበት ሥፍራ ሄድኩ። ወሩ ሚያዚያ ዘመኑ ፷፯ ነበር።

የመምህሩን የአስፋውን አስከሬን በትልቅ ጠረጴዛ ላይ ከሆስፒታሉ ክሊኒክ ታዛ ሥር በስተምዕራብ በኩል አኑረውታል። ባለቤቱ አለሚቱ የሁለት ወር እድሜ ያለውን ሕፃን ልጃቸውን በጀርባዋ እዝላ አስከሬኑን እየዞረች ታለቅሣለች።መምህራን ጓደኞቹ ፈንጠር ብለው ቆመዋል። እኔም የአስፋው ሞት አልዋጥልህ ብሎኝ የለበሠውን ጃኬት ገለጥ አድርጌ ብመለከተው ዋ! የቀኝ ጎን አጥንቶቹ ደቀዋል።የቀረው ሰውነቱ ከሰል መስሏል።

በወቅቱ መምህሩን ማን ገደለው ብሎ መጠየቁ አላስፈላጊ ሲሆን፣የክፍለሃገሩ የጽጥታ ሠራተኞች ግን ለምርመራ ጥቂት ቡርጌሶችን  ማሠራቸው ከሥፍራው ተነገረ።የአካባቢው ሕዝብ ግን የሚያውቀው ነገር ቢኖር በፖሊስ ምርጥ የእግር ኳስ ቡድንና በተማሪዎች ቡድን መከከል በተፈጠረው አለመግባባት አንድ ተማሪ በሽጉጥ ተመቶ በመገደሉና ሁለተኛው በመቁሰሉ ፣ ሁኔታውን በጊዜው ለነበሩት ባለሥልጣኖች እንዲያቀርቡ ከተመረጡት መምህራንና ተማሪዎች አንዱ መሆኑን ብቻ ነበር።

አስፋውና የቀሩት ተመራጮች ከክፍለሃገሩ ምክትል አስተዳዳሪና የለውጥ ሐዋሪያ የእስር አለቃ ዘንድ ቀርበው በመረጣቸው ሕዝብ ስም አቤቱታውን ሲያቀርቡ፣አስፋውም በግንባር ቀደምትነት የሁኔታውን አሰቃቂነት ጠቁሞ፣ በተጨማሪም በአካባቢው ተወልደው ለሚያድጉት ለሉትም  ታዳጊ ወጣቶች ሊያስከትል የሚችለውን የእስፖርት ስሜት መቀዝቀዝ አስመልክቶ ሲገልጽ ፣ ሕዝቡም ከዳኝነት መዛባት ተነሥቶ ባለው መንግሥት ላይ እምነት ሊያጣ እንደሚችል አስረዳ።

በአጠቃላይ ተመራጮቹ ይዘው የቀረቡት አቤቱታ የገደለ



ይሙት ወይም ይደን ለማለት ሣይሆን ዳኝነት ተጓድሏል፣ የሃገሪቱ ሕግ ተጥሷልና ማንኛውም ሰው በሕጉ መሠረት ይፈጸምለት ለማለት ነበር። ምክትል አስተዳዳሪውም ሁኔታውን ማዳመጥ እንጂ አቋም ሊወስድ አልቻለም። በጊዜው ግን በማንኛውም መሥሪያ ቤቶች ጣልቃ በመግባት ውሣኔዎችን ይሰጡ የነበሩት በአካባቢው የፖሊስ ባልደረባዎች የተመረጡ ንዑስ ደርጎች በመሆናቸው፣ መምህራን፣ተማሪዎችና የአካባቢው ሕዝብ በትክክል ጉዳዩን ያይልናል ብለው የገመቱት ምክትል አስተዳደሪውን ስለነበር የሚታየውን ፍርጥርጥ አድርጎ እንዲነግራቸው አጥብቀው ቢጠይቁት፣ የታየውን ሃሣብ በትክክል ለመግለጽ በአጠገቡ የተመደበውን የእስር አለቃ በመፍራት ለአቀረቡት መጠይቆች ተገቢውን መልሶች  ከመስጠት ተቆጥቦ  በማድበስበስ ሲያልፋቸው፣ የእስር አለቃው ግን «የተፈጸመው የግድያ ወንጀል  በፖሊሱ ባልደረባ ሣይሆን በመሬት አዋጅ ባኮረፈ አደሃሪ ነው»፣ በማለት ድምዳሚውን ሲሰጥ፣ተመራጮቹም ገዳዩ ማን መሆኑን ከነሙሉ ማስረጃው ሲያቀርቡለት የሚታየውን ከመግለጽ ይልቅ ስለኢትዮጵያ አብዮት በሚል ርዕስ ቅስቀሳ መሰል መግለጫ ሲሰጥ በግሉም ለአብዮቱ የአበረከተውን አስተዋፅኦ ገልጦ፣ በተጨማሪም ከአብዮት በፊት የጅማ ክፍለሃገር የወህኒ ቤት ዘበኛ በነበረበት ዘመን የተፈጸመበትን በደል ማብራራት ጀመረ።

በመጨረሻም ተመራጮቹ ለመረጣቸው ሕዝብ ከባለሥልጣኖች ምን መልስ ተሰጠን ተብለው ቢጠየቁ፣የእስር አለቃ ሰጠኝ በመቻከል፣ «መምህራንን ንቃት እንድንሰጣቸው በጽሕፈት  ቤታቸው እንዲሰበሰቡ ንገሯቸው» ሲል፣ ምክትል አስተዳዳሪው በግል ሊያደርገው የሚችለው ነገር ቢኖር «አዲስ አበባ ለሃገር አስተዳደር መሥሪያ ቤት ደውሎ ሁኔታውን መግለጽ፣ ገለልተኛ የመርማሪ ክፍል በአሥቸኳይ እንዲላክ ማሳሰብና ለዋናው አስተዳዳሪ ለሸለቃ ሲመጡ፣ ያቀረባችሁትን አቤቱታ ማቅረብ ይሆናል፣»ብሎ ተመራጮቹን አሰናበታቸው።

ምክትል አስተዳዳሪውም በገባው ቃል መሠረት ሁኔታውን ለማጣራት አራት የምርመራ ጓዶች ከአዲስ አበበ መጥተው፣ ተመራጮቹን ሰብስበው ከአነጋገሩ በኋላ መምህራኑን  ለማናገር ስለሚፈልጉ በጽሕፈት ቤታቸው ኢንዲገኙ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ያስተላልፉሉ።በስተላለፉት ጥሪ መሠረት፣ በአካባቢው ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን በሙሉ በስብሰባው ተገኝተው፣ ባለሥልጣኖቹም ስለመጡበት ጉዳይ ከመናገራቸው አስቀድመው ስለኢትዮጵያ አብዮት  በሚል ርዕስ፣የመርማሪዎቹ መሪ ሻለቃ ደበላ ዲንሣ መግለጫ ሲሰጥ፣በሃገሪቱ ውስጥ ስለሚገኙት መደቦች ትንታኔውን ያቀርባል።በአቀረበው የመደብ ትንታኔው መሠረት የወታደሩን ክፍል ከደም አደርነት መደብ ሲመድበው መምህራኑን ግን የወቅቱ አብዮት ተፃራሪና አደሃሪያን መሆናቸውን ሲያጋልጥ፣ እነርሱ ግን የአውታም ሆነ የአሉታ መልስ ከመስጠት ተቆጥበው ሲያዳምጡ

ሳሉ ሃሣቡን ጠበብ አድርጎ የሥራ ማቆም አድማቸውን ለመበተን ቀደኛውን እናቱን መምታት ብቻ ነው ብሎ ሲናገር ሁኔታው አቅጣጫውን ለወጠ። ንግግሩን ያጤነች ፤ መምህርት ለሽለቃው ንግግር በተረት እንዲህ ስትል መለሰች።«ሰውዬው ቀደም ሲል ሴትዮቱን ለምዷት ኖሮ ባል ከቤት የሌለ መስሎት በጓሮ በር ዘው ብሎ ሲገባ ደንግጣ ብትጮኽ ባልተቤት ቢጠይቅ የሚከኤልን ጽዋ እነሣ ብዬ የገብሬን እነሣሁ በማለት መለሰች ይበሳል»።ሽለቃም ተረት እንደሚወድ ጠቁሞ «ባል ሚስትን በልምጭ ሲመታት በተሰቀለው ብላ ብትማጠነው ቀና ብሎ ቢመለከት ጉማሬ አለጋ ተሰቅሎ ቢያይ፤ ይህ ይሸልሸል በማለት ድብደባው ቀጠለ።» በማለት ሽለቃው ተረቱን በተረት ሲመልስ፤ በሽለቃውና በመምህራኑ መካከል ነገር ተከረረ። ቅድመ አብዮት ፲፱፻፷፩ እና ፷፪ ዓመተ ምህረት የሐረር ክፍለሃገር የጸጥታ ክፍል ሽንበል በነበረበት ወቅት በተማሪዎችና በመምህራን ላይ በራሱ እነሣሺነት የፈጸማቸውን በደሎች በዝርዝር ገልጸው፤ሰዓቱንና ቀኑን በመጥቀስ በሐረር መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ ከነፖሊሶቹ በመግባት በአንድ ዕጩ መምህር ላይ ቀይ መለዮ በማድረጉ ብቻ ከሚኒስት በማለት ክልት አርባ አምስት ሽጉጡን መምዘዙን ያስታውሰው እንደሆነ ጠቅሰው ሲጠይቁት እናም እንዴትስ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደ ሶሺሊዝም ሊለወጥ እንደቻለ እንዲገልጽላቸው በጥያቄ መልክ አቀረቡለት። ሽለቃው ያልጠበቀው ነገር ስለሆበት በጣም ሲናደድ፤ የሕዝብ ደህንነት በሚል ስም የመንግሥት ተቃዋሚ የሆኑትን ክፍሎች አፋኝ ድርጅት ሃላፊ በነበረበት ወቅት ስለተገደለው የዮኒቨርሲቲው ተማሪ መኮንን ሐጎስ የሚያውቀው ጉዳይ ካለ በማለት በድጋሚ ጥያቄ ሲያቀርቡለት፤ በአጠቃላይ መምህራን ሲ. አይ.ኤ ናችሁ ሲ.አይ.ኤ ጥቁርም ሊሆን ይችላል፤ በማለት ከነናቸው። መምህራንም «በአለፈው ዘመን ከሚኒስት በአሁኑ ጊዜ ሲ.አይ. ኤ ከሆንን መች ነው እውነተኛ ኢትዮጵያውያን የምንሆነው?» በማለት ቢጠይቁት መልስ ከመስጠት ተቆጥቦ በግል በራሱ ሕይወት ላይ ስለመጡበት ተናደና ተቆጥቶ ምንም አይነት ውይይት እንደማያደርግ ወስኖ ስብሰባውን ከምንም ላይ ሳይቋጨው ወደአዲስ አበባ ይመለሰል። በጊዜው መምህራን በወንጀለኛነት ያቀረቡት ባለሥልጣን በደርግ ውስጥ የአስተዳደር ክፍል ሃላፊ እጄ ኃይለ ሥላሴን ከዙፋናቸው ያወረዳቸው እርሱ መሆኑ ቢነገርም ቀደም ብለው በሚያውቁት ዘንድ ከ«ድል አጥቢያ አርበኛ» ሌላ የሰጡት ስም አልነበረም።

በአካባቢው ስለተፈጠረው ውዝግብ መፍትሔ እንዲፈልጉ የተላኩትን የመርማሪ ጓደች መርቶ የመጣው ባለሥለጣን እርሱ ራሱ እነደወነጀለኛ በመቆጠሩ የመጡበትን ጉዳይ ሣይቋጩት ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ በሄዱ ፤ በሁለተኛው ቀን የፖሊስ ሄሊከፐተር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደአካባቢው ትመጣለች። እነደአጋጣሚ የአይሮፐላን ማረፊያው ከከተማው መካከል በመሆኑ ሕዝቡም ቀደም ሲል ያላየው ስለሆነ አንድ ነገር እንደሚፈጠር ለመገመት ያስችል



ነበር። መምህራንና ተማሪዎችም ከጥንት የሽለቃው ሕይወት ታሪክ ተነስተው እንደለመደው አነጣጣሪ ተኳሽ ሰከብን በማለት ሲተቹት፤ቤተሰብም ልጆችን በጊዜ ወደ ቤት እንዲመጡ ሲያስጠነቅቁ ከፖሊስ መሥሪያ ቤት የቅርብ ዘመድ የነበራቸውም ክፍሎች እንናተ ልጆች ራሳችሁን ጠብቁ በመባል ምክር የተለገሣቸውም ነበሩ።

ያም ሆኑ ይህ ከወገን ጠላት ማምለጥ አይቻልምና ሄሊከፕተሯ በመጣች በሁለተኛው ቀን መምህሩ ተገደለ። ሄሊከፕተሯም መምህሩን በገደለው ግለሰብ ተመታለች በማለት በቆየ ውሸታቸው ትንሽ ካወናበዱ በኋላ ተልኳችውን ፈጽመው ለሚጠብቃቸው ሹመት ወደ አዲስ አበባ ሄዱ። ከእዚያንማ በኋላ ደርጎች በአየሮፐላን ሰው እየለኩ ያስገድላሉ የሚለው ዜና በሰፊው ስለተነገረ በድርቅ ለተጎዱት አከባቢዎች እህል ያመላልስ የነበረውን የአየር ኃይል አይሮፐላን እንኳን ሲመጣ አምኖ መቀበል አልተቻለም።

## ፪

የመምህሩን እስከሬን አፈር ማልበስ ሃላፊነት ያለባቸው ቤተሰቡና ጓደኞቹ ከፖሊሱ መሥሪያ ቤት ሬሣው እንዲሰጣቸው ቢጠይቁ እንደማይሰጣቸው ሲነገራቸው፣ ወላጆቹ አርማቸውን እንዲያወጡ ለአባትና እናቱ ጅማ፣ ለአጎቱ አዲስ አበባ ተደወለላቸው። እነርሱም አስከሬኑ አዲስ አበባ እንዲመጣላቸው በመጠየቃቸው፣ የአከባቢው ሕዝብና መምህራን ገንዘብ በማዋጣት አይሮፕላን ተከራይተው አስከሬኑን አዲስ አበባ ለወላጆቹ ለመውሰድ ማቀዳቸውን ጠቁመው እንዲሰጣቸው ዳግመኛ ቢጠይቁ መሥሪያ ቤቱ በራሱ መኪና እንደሚወስደው ተነገረ።

መምህሩ ከሞተ አስራ ስምንት ሰዓታት አልፈውታል። ሐዘንተኛው ሬሣውን ከበ ማልቀስ ብቻ ሆነ። መምህራንም ያ የቀድሞው ሞራላቸው ሲከሰከስ፣ አስከሬኑን የያዙት ባለሥልጣኖች በወቅቱ ሬሣውን ማጉላላታቸው ለቀሩት ጓደኞቹ መቀጣጫ ቢመስልም፣ በአጠቃላይ ግን በራሳቸው በተተኪው ትውልድ ሕይወትና በሃገሪቱ ሕዝብ ላይ መጫወታቸው በጊዜው አልተከሰተላቸውም።እንነሀ የሚጫወቱባቸው ግለሰቦች በነጋታው ከልጆቻቸው ጎን እንደሚቆሙ አልታያቸውም። ሆኖም መምህራን በአከባቢው የሚፈጸሙትን ኢሰብአዊ ድርጊቶች እየተመለከቱ በእድር ባይነት እየሠሩ ደመወዛቸውን እየተቀበሉ ቢቀመጡ ምንም ነገር እንደማይደርስባቸው ቢረዱትም በአኗያው የሞያው ስም የተሰጣቸ ሰዎች አብይ ተግባር ያ እንዳልሆነ ይረዱታል። ግን ደከማ ሞራልን ይዞ ከተማሪ ፊት ቆሞ ማስተማርና ቶራጥና ጠንከራ ሞራል ይዞ የማስተማር ልዩነት አልተያቸውም።በአጠቃላይ የአከባቢው ሕዝብ አይቶት ሰምቶት የማያውቀው ነገር ስለሆነ መጨረሻው ምን ይሆን? በማለት በእንክሮ ይጠባበቃል።

በመጨረሻም የቀኑ መምሸት ታይቶ የፖሊስ ማክ መኪና ለአስከሬኑ ማጓጓዣ እንደተፈቀደላቸው ተነገሮ፣ የሹፌሩንና የመኪናውን ነዳጅ ዋጋ ከፍለው አስከሬኑን ጭነው ወደ አዲስ አበባ ጉዞአቸውን አደረጉ።የሟች ባለቤት የሙት ልጇን አቅፋ እርሱም ያን ምንም ጠብ የማይልበትን ጡቷን እየተናነቀው አራት መቶ ሃምሣ ኪሎ ሜትር የሚሆነውን ርቀት ተያያዙት።እናቷ ከጎኗ ተቀምጠዋል ፣ የሟች ጓደኞች ግማሾቹ አስከሬኑን በያዘው ሣጥን ላይ ሲቀመጡ የቀሩት በመኪናው ወለል ላይ ተቀምጠው፣ እስፋው የሚናገራቸውን ቁምነገሮች እያወሱ ባለቤቱም እሬሣውን እየተመለከተች አልፎ አልፎ እያለቀሰች ሰማዩ ደም ሲመስል ከመቂ ከተማ ደረሱ።ከዚያንም ለአንድ ሰዓት እንደሚቆይ ተነገሮ አይር ለመቀበል ብዙዎቹ



ከመኪናው ሲወርዱ፣ በዚያን አጋጣሚ አብሮቶ በኮሚቴ አባልነት የተመረጠው እውነቱ ከአለሚቱ ዘንድ ተቀምጦ ፣ እስፋውና እርሱ ራሱ የሚመጣውን አደጋ ተነጋግረው በጊዜ ወደየቤታቸው መግባት እንዳለባቸው እምነው መለያየታቸውን ጠቅሶ በምንስ ምክንያት ዳግመኛ ወደቡና ቤት እንደተመለሰ ቢጠይቃት፣ እሷም ባገለደመችው ነጠላ እንባዋን እየጠራረገች «የእስፋውን ፀባይ የምታውቀው ነው፤ ሁኔታዎችን አይጠራጠርም። ጓደኞችህ ከአዲስ አበባ መጽሐፍት ስለላኩልህ መጥተህ እንድትወስድ ተብሎ ሰው ተላከበት እርሱም የሚሠራውን ሥራ አስቀምጦ መውጣቱን ብቻ ነው የማስታውሰው» በማለት አስከሬኑ ያለበትን ሣጥን እየተመለከተች «የእስፋው ነገር አከተመ፣ ምንዋጋ አለው? ለሰው ልጅ ነፍስ ሲያር ሲበግን የራሱንም ሕይወት አጥቶ እኔንም የዘላለም ፀጽት ጥሎልኝ ማሙሽንም ያለአባት ትቶት አለፈ።» በማለት እንባዋን ታዘረዋለች።

የተሰጠው የአንድ ሰዓት ገደብ አብቅቶ ጉዞቸውን ቀጥለው፣ ልክ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን አዲስ አበባ ሲደረሱ፣የቀኑ ተረኛ ሆስፒታል ምንሊክ ስለነበር አስከሬኑ ለምርመራ ከዚያን ተወሰደ።ከአዲስ አበባ ኗሪ የሆኑት ዘመዶቹና የአስራ አራቱ ክፍለ ሃገራት መምህራን ተወካዮች ይጠባበቁ ኖሮ አስከሬኑ ከመኪናው ሲወርድ እየዩ ሆነ። አስከሬኑም ለምርመራ ከላቦራቶሪው ክፍል ሲወሰድ እጅበው የሄዱትም ጓደኞቹ በስብሰባ ላይ ለሚገኙት የአስራ አራቱ ክፍለሃገራት መምህራን ተወካዮች ሁኔታውን ለማስረዳት ከማሕበሩ ጽሕፈት ቤት ከስድስት ኪሎ ተገኙ።

ጅማ ላይ በክረምት ወራት ሊደረግ ለታሰበው ጠቅላላ ስብሰባ ዝግጅት የተሰበሰበው የአስራ አንደኛው ንዑስ ጉባኤም ሁኔታውን በጹሑፍ እንዲያቀርቡ በጠየቃቸው መሠረት አቅርበው፣ ጉባኤውም ከሌሎች አጠቃላይ መጠይቆች ጭምር በሥልጣን ላይ ለነበሩት ለብርጋዴር ጅንራል ተፈሪ በንቲ እንደሚያቀርቡላቸው ተነገራቸው።

የአስከሬኑም ምርመራ አብቅቶ ከቀጨኔ መድኃኒትዓለም አከባቢ ከአጎቱ መኖሪያ ቤት ሲወሰድ፣የምርመራው ውጤት ግን አልተነገረም። ለሁሉም የሚጠበቁት አባትና እናቱ ከሰዓት በኋላ ከጅማ አዲስ አበባ ደረሱ። ከዚያንማ በኋላ ምኑ ቅጡ የእናት እንባ ልጅን ይመልስ ቢሆን ኖሮ ብዙዎች በተመለሱ ነበር ግን አልሆነም።የእስፋው ዓለሙ ነው ተባለ። አልቃሽም በየተራ ሙሾዋን ደረደረች።በጊዜው ከሚደረደሩት የማልቀሽ ግጥሞች ጥቂቶቹ ይህን ይመስላሉ።

ወንድ የወለዳችሁ እርማችሁን አውጡ ፣
ለእኔ አላማረኝም የአይን አገላለጡ ።
ሸማኔ ለልብሴ ቀይ ጥለት ግልበት ፣
የጅቡን ትራፊ እለቃቅምበት ።

ለቅሶ ደራሹም ፈንጠር ፈንጠር ብሎ ቆሞ የሚተማመነው ክፍል የሁኔታውን አስቃቂነት በመግለጽ እይ ጉድ ብለው ከንፈሮቻቸውን መጠው ወይው! ለራሴ በማለት በተመሰጦ ወደፊት ሊመጡ የሚችሉትን አደጋዎች ዋውጠንጠን ብቻ ሆነ።

በመጨረሻም የአከባቢው ኗሪ ሕዝብ የአስራ አራቱ ክፍለ ሃገራት መምህራን ተወካዮች ጓደኞቹና ወላጆቹ ሆነው ለምንጊዜውም አስከሬኑ ከሚያርፍበት ከቀጨኔ መድኃኒያዓለም ቤተክሪስቲያን ሲደረሱ፤ ጀንበሯዋ ለመጥለቅ አዘቅዝቃለች፤ ሐዘንተኛው ተዳክሟል፤አስከሬኑ ሁለት ቀን ሆኖታል፤ ሁሉም ለይመለስ ሲረዳው ቶሎ ቀብሮ ለመመለስ የተቻኮለ ይመስላል፤ቄሶቹም ፍታቱን አብቅተው፣ ቄሱም መቃብሩን ባርከው አ አዳም አፈር ነህና ወደአፈር ተመለስከ ብለው አፈር ቆንጥረው ከአስከሬኑ ሣጥን ላይ ሲበትኑ፤ አፈር አልባሹም ክፍል በአፋጣኝ አፈር ሲመልስ ባለቤቱን አለሚቱንና እናቱን ያየ በእውንቱ ጥይቷ ከአስፋው ሰውነት ላይ ስታርፍ ምን ያህል እንደአሣመመችው በትክክል ለመግለጽ ቢያስቸግርም እነርሱን መመልከቱ የዘኑ ያህል ያሰቃይ ነበር።

የቀብሩም ሥነሥርዓት ከአበቃ በኋላ ሕዝቡ በቤተክሪስትያኑ ቅጥር ግቢ ከሚገኘው ትልቅ ዛፍ ሥር ተቀምጦ፤ የሟች አባት ተነስተው «ወገኖቼ ሟሪ ቀባሪ እያሣጣችሁ ውለታችሁን እምላክ ይከፈለችሁ፤በእኔ የደረሰው ግፍ በማንኛችሁም ላይ አይድረስ፤ ልጂ በወገን ጥይት በሃገሬ መሬት ላይ ሲገደል ማየቱ ለእኔ እጥፍ ድርብ ሐዘኔ ነው። ሃገሬ ለእኔ የምትከፍለኝ ወለታ ይህ ከሆነ ምን አደርጋለሁ? ወገን ፍረደኝ»፤ ብለው ሲቀመጡ የአስፋውም የሕይወት ታሪክ ተነበበ።

የሚገርመው የአስፋው አባት ለልጃቸው ሐዘን ደራሽ የተናገሩት ንግግርና የመከንን ሐጎስ አባት የተናገሩት ንግግር አንድ መሆኑ ነው። የመከንን አባት ሐረር ቅዱስ ሚከኤል ቤተክሪስትያን ለልጃቸው ቅብር ለተገኘው ሕዝብ የተሰማቸውን ሐዘን ሲገልጹ የአማርኛ ንግግራቸው አሳረክ ብሏቸው በትግረኛ የተናገሩትን ንግግር አጠገቡ ከተቀመጠው እጩ መምህር እውነቱ እንደተረዳው ይህን ይመስል ነበር። «የሃገሬ ውለታ ይህ ነው? የአቶጎ ውጫሌ አሸዋ የጭናክስን ሜዳ የጠጣሁት የጭው ውኃ ፍረደኝ አጋዴን ፍረደኝ ዋ! ልጅ በልምጭ ይቀጣል ልጅ ይመከራል ልጅ ይገሠፃል እንጂ ልጅ እንደጠላት በጥይት ይመታል?» በማለት ሐዘናቸውን ገልጸው ነበር። እውነቱም ከአምስት ዓመት በፊት የተፈጸመውን ድርጊት በጊዜው ከሚያየው ጋር በሐሣቡ ሲያወጣ ሲያወርድ በአጠገቡ ተቀምጦ የነበረው የጅማ ክፍለሃገር የመምህራን ተወካይ ከበበ በቅርብ አስፋውን በዮኒቨርሲቲ ያውቀው ኖሮ የእርሱን ርሁሩህነት ሰው



ወዳድነቱን ገልጾ፤ የተሰማውን ሐዘን ዋጥ አድርጎ «አስፋው ዕድለኛ ነው ፤ አባት እናቱ ባለቤቱ እኛ ጓደኞቹ ቆመን ቀበርነው፤እኛ ግን የራሳችንን መቃብር ቆፍረን የምንቀበርበት ቀን ወደፊት ይመጣል፤» ብሎ ከበበ ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምህረት ግንቦት አንድ ቀን የተናገረው አልቀረም። ከበበና አራት ጓደኞቹ በ፲፱፻፷፰ ዓመተ ምህረት ከጅማ ተይዘው ለምርመራ ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ከቀረቡ በኋላ ከርቸሌ ተወሰደው አንድ ቀን አድረው በለሊት አዋሽ በረሃ ተወስደው የራሳቸውን መቃብር ቆፍረው መቀበራቸውን ሲሰማ በእውነቱ እንዳንድ ሁኔታዎችን ከአጀማመራቸው መተንበይ ያስችል ነበር።

## ፫

የአስፋው ወላጆችም የልጃቸውን ልጅና ባለቤቱን ይዘው ወደ ጅማ ሲሄዱ አስከሬኑን አጅበው የሄዱትም መምህራን ከዚያው በየአቅጣጫው ተበታተኑ። ቀደም ሲል በተገደለው ተማሪ ስም እንማርም አናስተምርም ያሉት ተማሪዎችና አስተማሪዎች በመሣሪያ አስገዳጅነት የለሸቀ ሞራላቸውን ይዘው ወደሥራ ገበታቸው ተመለሱ። የአካባቢው ኗሪ ሕዝብም ወደፊት የሚመጡት አስከፊ ሁኔታዎችን በመገምገም በየአቅጣጫው ተጎዳኙ። ቅዋሚች በየአቅጣጫው እየተባበሱ ሲመጡ በአከበቢው ዘምተው የነበሩት ተማሪዎች ነግ በእኔ ነው በማለት ዘመቻውን እያቋረጡ ወደመጡባቸው አካባቢዎች ተመለሱ። ቀደም ሲል በደስታ ተቀብሏቸው የነበረው ሕዝብም እንደደርግ መልከተኛ ቆጠራቸው። ሰውን መግደሉ መፍትሔ ይሆናል ብለው ያሰቡት ባለሥልጣኖች ነገሩ እየተባባሰ ሲመጣ ሲያዩት ነገር ማብረጃ ብለው ሌላ ነብስ አጠፉ። ካለ ጡረታው አብል በስተቀር ምንም ንብረት የሌለውን ሸንበል ከከተማው ምንም ያህል ከማይርቁ የቀድሞ ወዳጆቹ ዘንድ እንዳለ ሊሸፍት ነው በማለት የነበረበትን ቤት በበንብ አቃጥለው በቤት የነበሩም በሁኔታው ተደናግጠው ከቤት ሲወጡ ጠብቀው ሸንበሉን ገድለው አሬሣውን አምጥተው ልክ የመምህሩን የአስፋውን ካኖሩበት ጠረጴዛ ላይ አኑረውት የመምህሩ ገዳይ ተገደለላችሁ መጥታችሁ እንድትመለከቱት ተብሎ ለአካባቢው ትምህርት ቤቶች መልክት ተላለፈ። ማንም አምኖ የተቀበለው አልነበረም። ሆኖም የሸንበሉ ልጆች በትምህርት ቤቱ ስለነበሩ የሐዘናቸው ተካፋይ ለመሆን መምህራን ከሥፍራው ተገኙ። እውነቱም ከጓደኞቹ ጋር ቆሞ ሁኔታውን በአንክሮ ሲመለከት፤ የቀበሌው ኗሪ የሆኑት አዘውት ለብቻው ነጠል አድርገው ወስደውት «ልጄ ይህንን ነገር አምነህ ተቀበልከው?» በፍጡም እንኳስ እኔ የሦስት ዓመት ሕፃን አምኖ አይቀበለውም ፤ ሲላቸው ፤ ጎሽ ብለው እየተገላመጡ ከሥፍራው ሃምሣ ሜትር ርቀት ወስደውት «ስማ ልጄ እንደው እርስ በእርሳችን ደም ሲያቃቡን እንጂ አስፋ የልጆቹን አስተማሪ አይገድልም። እኔና አስፋ በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ ለስላሣ ዓመት ሠርተናል። በደቡብ ክፍለ ሃገራት ያልሰራንበት ጣቢያ የለም። በራሽን ብቻ ያገለገልን የሃገሪቱ ልጆች ነን። ሸንበልነቱንም በከተማ ሕፃናትን እየገደሉ ወይም ወሬ በማቀበል ያገኘው እንዳይመስልህ ብዙ የወሰን ጦረነቶች ላይ አበረን ውለናል። በፖሊስ ስም ሁሉንም በጅምላ አንድ አድርጋችሁ እንዳትወስዱ አንተን ስለማውቅህ ትንሽ የተነፈስሁ መስሎኝ ነው።» ይህን ተናግረው ለመሮከርም ዳዳቸው። በአከባቢው ጆሮ ጠቢዎች ሊላኩ ስለሚችሉ ብሦታቸውን ዋጥ እንዲያደርጉት ቢነግራቸውም ምንም ሊቆጣጠሩት አልቻሉም። እሳቸውም በያዙት ከዘራ መሬቷን እየመቱ ቀረርቶ ያሰሙታል ቀረርቶዎ በጊዜው ይህን



ይመስላል።

«ይሙት ጎበዝ ፈሪ ይኑር ብሸው
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው።»

እርሱም ሊያጽናኗቸው ሞከረ። እሣቸውም መልሰው «ልጄ እኛስ የደጉን ዘመን ኑርነው፤የመከራውንም ዘመን እጅ ለእጅ ተያይዘን አለፍነው። የእንናተ ግን በጣም የሚያሣዝን ነው። ወገን ወገንን ልጆች አብረው እየዋሉ አባትን መግደል ከየት የተገኘ ትምህርት እንደሆነ አልገባኝም። ሕዝባችን ጥሩ ወግና ባሕል አለው። ጥፋተኛን በዘመድ በሃገር ሽማግሌ መምከር ማስመከር ትልቁ የሕብረተሰባችን ችግር መፍቻ ዘዴያችን ነው። ሮጦ መሣሪያ በወገን ላይ ማንሣትን ያየነው በእንናተ ዘመን ነው። የዘመኑ መኮንኖችም የሚማሩት ትምህርት በእኛ ሕብረተሰብ ላይ የተመረኮዘ አለመሆንን በቀላሉ ከሚፈጽሟቸው ተግባሮች መረዳት ይቻላል። በእኛ ጊዜ እርስ በእርስ መጠራጠሮች አልነበሩም። ለማንኛውም ለምትቀርባቸው ይህ በአስፋ ላይ የተነዛው የውሸት ወሬ መሆኑን አስረዳቸው።» ብለውት ተለያዩ።

የመምህሩ ገዳይ ተገደለ በማለት በሬዲዮ ተነገረ፤በአዲስ ዘመን ጋዜጣም ታትሞ ወጣ። ለአካባቢው ሕዝብ ግን ሦስተኛ ሐዘኑ እንጂ ደስታው አልነበረም ፤ የተነገረውን የውሸት ፕሮፓጋንዳ አምኖ አልተቀበለውም።መምህራን ተማሪዎች ለሸንበሉ ቤተሰብ የተሰማቸውን መሪር ሐዘን ገለጹ። የአካባቢው ኗሪ ሕዝብም ለወትሮው በሞት ለሚለዩት ወገኖቹ የሚያደረገውን በሙሉ አደረገ። ግን በወቅቱ ማንም መልስ ያላገኘለት ጥያቄ ቢኖር መምህሩንና ጡረተኛውን ምን አገናኛቸው የሚለው ነበር። በወቅቱ ከተነዛው ዜና እንደተሰማው የደርግ አባል መስሎት ገደለው ተባለ። የማያረጅ ውሸት ፲፱፻፷፪ ዓመተ ምህረት «መኮንን ማን ገደለው?» ብሎ የሐረር አካባቢ ሕዝብ ሲጠይቅ አንድ ትምህርት ቤት የሚየስተምረውን መምህር እንደገዳይ አቀረቡለት። አስፋውንም እንደገደሉ ሌሊት አንዱን መምህር እንደገዳይ ለማቅረብ ሞክረው ነበር። እንደአጋጣሚ የያዙት መምህር በአካባቢው የማይኖር ለዳግማይ ተንሣይ ወላጆቹን ለመጠየቅ በዕለቱ ከአዲስ አበባ የመጣ መሆንን ሲረዱት ውሸቱ የማይሰራ መሆንን ሲገነዘቡት አውጥተው ይለቁታል። ከዚያንም በኋላ ነው የሚገድሉት ሰው ማደን የጀመሩት። ሸንበሉም በአካባቢ በጅግንነቱ የታውቀ ስለሆነ ተፈልጎ ተገደለ።

## ፬

በወቅቱ ይፈጸሙ የነበሩትን ሕግ ወጥ ተግባሮችን በመመልከት የከተማውና የገጠሩም ሕዝብ በየአቅጣጫው ተሰደደ። ወጣቱ ገበሬ ወሰን እየጣሰ ወደ ጎረቤት ሃገር ሲሄድ፤ ቀደም በነበረው አስተዳደር ፍትሕ ተጓድሎብናል በማለት ሲታገል የኖረ ሕዝብ ነበርና የባሰ ሁኔታ መምጣቱን ሲመለከት ከበረሃ ገባ። ወደሶማሊያ የሄዱት ክፍሎች መሣሪያ ታጥቀው በመምጣት በዱር መሸጉ። ዘመቻ በገጠሩ ሕዝብ ላይ ተጀመረ። የገጠሩ ግድያ እንደከተማው ቀላል አልነበረም። የአንድ ሃገር ሕዝብ ከአንድ መንግሥት በተገዛ መሣሪያ እርስ በእርሱ ተጨፋጨፈ። የሶማሊያም መሪዎች ደመኛችሁን ተዋጉበት በማለት ሃይማኖትን እንደዋና የቅሬኔ መሣሪያ በመጠቀም ደርጎች ያያዙላቸውን እሣት ቤንዝን የማርከፍከፍ ያህል ነበር። የሃገራችንም አስተዳዳሪዎች በቀላሉ በሕዝብ ተሣትፎ በውይይት ሊፈቱ የሚችሉትን ጥቃቅን የአስተዳደር ድክመቶች ከማርም ይልቅ በአጉል ውሸትና ትዕቢት ያልሆኑ ነገሮችን እንደሆኑ የሆኑትንም እንዳልሆኑ በማቅረብ ከዕለት ወደዕለት ሕዝቡን ለእሣት ማገዱት። በተለይ የደርግ አባሎች የሃገራቸውን ሕዝብ ምንነት ጠንቅቀው የሚያውቁ አይመስሉም። እንኳንስ በሃገሪቱ ልጆች በውጭ ሃገሮችም ኢትዮጵያውያን በአስፈራርቾ ይገዛሉ ያሉ አልነበሩምም ወደፊትም አይኖሩም። ደርቡ በጽሕፍት ቤታቸው መሣሪያውን አትመው ያውጡት ይመስል እንደ ጦጣ ዛፍ የሚወጣ ታንክ እናመጣለን በማለት ፎከራቸውና ማስፈራርቾ ሲያደርጉ፤ ሕዝቡ ከሶማሊያ የአሥራ አምስት ቀን ተጉዞ በመጣው መሣሪያ አካባቢውን አጥለቀለቀላቸው። ልማት ቆመ፤ የመሣሪያ ንግድ ተጧጧፈ። ጥይት እንደበቆሎ በጣሣ እየተሰፈረ ተሸጠ ። ከሕዝቡ ቀደም ሲል ያለውን መሣሪያ የፍየል ወጠጤ በማዘፈን ቢወስዱበትም፤ የተሻለ ዘመናዊ መሣሪያውን ምንም ወጪ ሣያወጣ ከሶማሊያ መንግሥት አገኘው።

ቀደም ብለው ከዚህ ሁሉ ውጥቅጥ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ሕዝቡ ጸጥ ለጥ ብሎ ከመገዛት ሌላ ምንም በለውጡ ላይ ያሣየው ቅዋሜ አልነበረም። ሌላው ቀርቶ በደርግ ላይ ቅስቀሳ ያደርግ የነበረው ኢ.ሕ.አ.ፖ እንኳን የድርጅት መዋቅር አልነበረውም። ሕዝቡንና የነበረውን መንግሥት ሆድና ጀርባ ያደረጉት በአካባቢው የተመደቡት የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችና የደርግ አባሎች ነበሩ። ሕዝቡም ንብረቱንና መሣሪያውን ተቀምቶ ስለነበር የሚፈጸሙበትን ግፎችና በደሎች በለውሣሥ ከመቀበል በስተቀር በጊዜው ምንም አማራጭ አልነበረውም። ሌላው ቀርቶ ሚስቶቻቸውን በፖሊስ ሹማምቶች የተነጠቁ መምህራን መኖራቸው ለአካባቢው ሕዝብ የአደባባይ ምስጢር ነበር። የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችም



ቢሆኑ ምንም አይነት ተቃውሞ ከሕዝብ ስለአልተሰነዘረባቸው ሱሣቸው የእንዱን ብሔረሰብ ክፍል ከሌላው አጋጩት ። ርካሽና ጠባብ ፖለቲክ ተጀመረ። ፖለቲካም የሥራ ጠል መሰብሰቢያ በመሰ አዳሪዎች መጠጊያ የሚል አተረጓገም በአካባቢው ሕዝብ ተሰጠው። የደረግ አባሎም አሊ ሙሣ ምን ሠራህ ተብሎ እንዳይጠየቅ በሰበብ በአስባቡ የከተማውን ሕዝብ መጨፍጨፍ ጀመረ።

የሠራተኛን ቀን ምክኒያት በማድረግ ሚያዚያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓመተ ምህረት አስራ ሁለት ሰዎች በተንቀሣቃሹ የደርግ አባል ትዕዛዝ ይመታሉ። ከተመቱት ሁለቱ የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ፤ አንደኛው ነጋዴ የቀሩት ገበሬዎች ነበሩ። አንደኛው የመንግሥት ሠራተኛ የደቡብ ክፍለሃገራት የቴሌ ኮሚኒኬሽን ግንኙነት ሃላፊ ሲሆን ፤ የደርግ አባሉ ወደ አዲስ አበባ ስልክ ለመደወል ያቅዳል። በጊዜው መስመር መቋረጡንና ሠራተኞች በጥገና ላይ መሆናቸውን በስልክ ሲመልስለት፤ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ከመሥሪያ ቤቱ በመሄድ ሥራ አሥኪያጁን በጥያቄ ሲያራውጠው፤ እርሱም የችግሩን ተደጋጋሚነት ገልጾ «መፍትሔውም ግንኙነቶች በቀጥታ በሽቦ መሆናቸው ቀርቶ በማይክሮዌቭ ሲሆን ብቻ ነው፤» በማለት ማብራሪያ ሲሰጥ የደርጉም አባል «እስከ ዛሬ ያልገባበት ምክንያት በብሮክራሲ መጓተት አይደል?»፤ በማለት ፤ ከሊበር ሽጉጡን መዞ ሲያሥፈራራው፤ ሥራ አሥኪያጁም ሁኔታው አስደንግጦት ስለመሣሪያው አጠቃቀምና ስለወጪው መግለጫ ሲያቀርብ መሣሪያው በሥራ ላይ እንዲውል የሚያደርገው እርሱ ሣይሆን ራሱን የቻለ የቴክኒክ ክፍል እንዳለ ጠቆሞ፤ ጥናቱም ተናቅቆ ሥራውም በቅርብ እንደሚጀምር ያብራራለታል። ሃላፊውም ምንም እንኳን እውነትን ያዘሉ ምክንያቶችን ቢያቀርብ በወቅቱ በብሮክራሲ ስም ብዙ ሰዎች አዲስ አበባ ተመተው ስለነበር የደርጉም አባል ድርሻውን ለመወጣት እምኖ አድርጎታል።

ሁለተኛው የመንግሥት ሠራተኛ የክፍለሃገሩ የእርሻ ልማት ሥራ አስኪያጅ ሲሆን የተመታው በኤኮኖሚ አሻጥር ነበር። ነጋሽ ላይ አሻጥር ተብሎ የተነገረበት ወንጀል በጊዜው በአዋጅ የተወረሱትን ሰፋፊ እርሻዎች ተረክቦ በተወረሱ የእርሻ መኪናዎች እርሶ ስንዴ ዘርቶ የሠራተኛና የነዳጅ ወጭውን አስቀርቶ የቀረውን ምርት በደረሰኝ ለቤሔራዊ ሐብት ልማት መሥሪያ ቤት አስረክቦ የሚንስተሩም መሥሪያ ቤት ምርቱን ወደ አዲስ አበባ ሲያስጭን ቆይቶ፤ ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ጥቂት ምርት በግንኙነት መቋረጥ ምክንያት ሣይጫን በመጋዘን ይቀራል። በታው በልማት የታወቀ ስለነበር ለጉብኝት የደርጉ አባል ከሥፍራው፤ ይሄዳል። የአካባቢው የገበሬ ማሕበር በመጋዘን ያለውን ስንዴ በብድር ስም ተሰጥቶት ሰብሉን ሲሰበስብ የሚተካ መሆኑን ጠቁሞ የደርጉን አባል ይጠይቃል። የደርጉም አባል ያስቀመጠውን ሲጠይቅ ገበሬው በቅርብ

የሚያውቀው ነጋሽን በመሆኑ ይነግሩታል። በነጋታው ጋዜጠኛ ወደ አከባቢው መጥቶ በካሜራ ተቀርጾ የኢኮኖሚ አሻጥር በማለት በሀገሪቱ መገናኛ ዘዴዎች በሙሉ ይሰራጫል። የእርሸው ሥራ ሃላፊም ያለእንደች ጥያቄ ተይዞ ከእስር ቤት ይጨመራል። በመጨረሻም የተወራበትን በሙሉ ውሸትነትና በሃላፊነት እንደማያስጠይቀው እያረጋገጠ ሲመጣ የአሥወሩት ክፍሎች ዋሽነታቸው እንዳይገለጥ የተመታ ነበር።

ነጋዴውም እንደተወራበት አሻጥር ፈጥሮ አልነበረም። ከነአከቴውም በዚያን አከባቢ አይኖርም። ግለሰቡ የሥጋ ክብት ነጋዴ በመሆኑ በጽጥታው መደፍረስ ምክንያት ከብት አቅራቢዎች ወደገበያ ስለማይመጡ ያለሥራ የተቀመጠ ግለሰብ ሲሆን፤ የተመታው ግን አደስ አበባ ሁለት መቶ ኩንታል በርበሬ በመጋዘናቸው አስቀምጠዋል በመባል ነጋዴዎች በመገደላቸው በክፍለ ሃገሩም የነጋዴ አሻጥረኛ መገደሉ ነበር። ገበሬዎቹም ቢሆኑ እንኳንስ ሞት እስራት የሚያስወስንባቸው ወንጀል አልፈጸሙም።

ሕዝቡ ለውጡን የተመለከተው ልማት ተስፋፍቶለት የራሱ አስተዳደሪ ሆኖ በራሱ መተማመንን አግኝቶ የሚኖር መስሎት ነበር። ግን ሁኔታዎች ተለውጠው ፍረሃት ጥርጣሬ አድርባይነት በራስ ያለመተማመን ራስን በትክክል ያለመግለጽ በሰፈው ተስፋፍተው ይታዩ ነበር። ከሚፈጸሙት ግፎች ተነስተው ፍጹም ባእለው መንግሥት ላይ እምነት ጠፋ። የሐገር ፍቅርም እየጠፋ ሄደ። ልጅ ተውልደ የሚያድግበት ሕብረተሰብ መስሎ ያለመታየቱ ቤተሰብ የመመሥረቱም ሁኔታ አጠራጣሪ እየሆነ መጣ። እንኳንስ ታዳጊው ወጣት አባት እናት ጠቅላለው ሕብረተሰብ ፍራቻ ላይ ወደቀ። ተንቀሣቃሽ ተብለው የተላኩትም የደርግ አባሎች ከቀዬው ድረስ እየሄዱበት የማስፈራርቾ ፕሮፖጋዳ ሲነዙበት አከባቢውን እየለቀቀ ሄደላቸው። በአንድ የአውራጃ ከተማ ስድስት ሺ ሕዝብ በሚኖርበት አስር ሰዎችን አውጥተው ሲመቱ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ከሶማሊያ መሣሪያ ታጥቀው ከዱር ከመሸጉት ሕዝቦች ዘንድ ሄደው ተቀላቀሉ። አስሩም ሰዎች የተገደሉት ይህ ነው በማይባል ወንጀል ሲሆን፤ ለምሳሌ የአውራጃው የእርሻ ልማት ሠራተኛ በቡና ቤት የያዘውን መኝታ ለደርግ አባሉ አለቅም በማለቱ አናርኪስት ተብሎ ሲመታ፤ ሌላው ደግሞ ሃጂው ከመካ ይዞት የመጣው አንድ የአረብ ብር በቁራን መጽሐፉ ውስጥ ስለተገኘ ብቻ ወደአረብ ሃገር ገንዘብ ያሸሻል በመባል ይገደላል ። ሕዝቡ እንኳንስ ኃይለ ቃልና ግድያ ተፈጽሞበት የወታደር የደንብ ልብስ ለብሶ ጥሩ ሐሣብ ቢያቀርቡለት እምኖ ለመቀበል ጊዜ የሚውስድበት ነው። በጊዜው ሥልጣን ላይ የነበሩት የወታደሩ ክፍሎች በቅን ልቡና ያሳጤኑት ነገር ቢኖር ራሳቸው በቀድሞው አስተዳደር የቅርብ ሠራተኛ ሆነው ለዘመናት የነበሩትን የአስተዳደር ድክመቶች ለማወቅ የወሰደባቸውን ዘመን ያለማወቅና ባንፃሩ ትናንት



ከሥልጣን ስለውጡ ብቻ ሕዝቡ አሚን ብሎ ይቀበለን ብለው መፍጨርጨራቸው ነበር። በዚያኑም ያህል እራሳቸውን በቃለት ድርድር ሸፍነው የተቀመጡ አሉ። ስም ለማጥፋት ሣይሆን ጥሩ መሪ መርጦ ለማውጣት ከሆነ ነፃ መድረክ መፈቀድ ነበረበት። ከዚያም በኋላ ሌላውን ለማደራጀትም ለማስተማርም ይደረስበት ነበር።

በአጠቃላይ የሰው ልጅ ነፍስ በጣም ረከሰ። በየአቅጣጫው ግድያ ብቻ ሆነ። አንድ ቀን የደርጉ አባል ሬንጅሮቨር መኪናውን ሲያሽከረክር አንዲት ሕፃን ልጅ በመንገድ ላይ ስትጫወት ገጭቶ ይገድላታል። ያንን የተመለከተ ግለሰብ «እነዚህ ሰዎች መንጃ ፍቃድ ማይኖራቸው ነውን? መኪና የሚያሽከረክሩት» ብሎ ሲጠይቅ ሌለኛው «የትኛው ኢንሹራንስ ነው ኢንሹር ለማድረግ መንጃ ፍቃድ የሚጠይቃቸው» በማለት ይመልስለታል። «ለዚያውስ ኢንሹራንስ አስፈላጊነቱ ለማን ነው? ከእነርሱ ሕይወት በስተቀር ሌላው ፍጡር ሕይወት ያለው አይመስላቸውም። በተዘዋዋሪ የራሳቸውንም ሕይወት የረሱት ይመስላል። ያም ሆነ ይህ የምንነጋገረው የሰው ልጅ ሕልውና በተከበረበት አከባቢ ያለውን ወግና ሥርዓት ነው። ሕዝባችን ግን ለዚያ አልታደለም፤ በገመድ የፍጥኝ እየታሰረ በሚገደልበት ሕብረተሰብ ውስጥ ይህን አይነት ጥያቄ መጠየቁ ያለአሥፈላጊ ነው።»

በወቅቱ በየምክንያቱ የሚመቱት የሃገሪቱ ልጆች ይቀበሩ የነበረው በእስረኛ በተቆፈረ አንድ ጉድጓድ ውስጥ ሲሆን ብዙም ከመኖሪያ ቤቶች አከባቢ አይርቅም። ለምሳሌ እነነጋሽ ተቀብረው የነበርው ከአንድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አከባቢ ሲሆን ጅብ የበላውን በልቶ የራስ ቅላቸውን እጆቻቸውን መሐል እግሮቻቸውን በአከባቢው ጥሎት ስለነበር ሕፃናት ከበው «ይህ የነጋሽ እጅ ነው ይህ የአስፋው ነው በማለት ከወላጆቻቸው የሰሟቸውን ስሞች በሙሉ ይጠራሉ።»እውነቱም ከዚያው አስተማሪ ስለነበር የሚባለውን በአንክሮ ያዳምጣል። ምን ዓይነት መምህር ይህንን አእምሮ ሊለውጠው እንደሚቻል ጊዜ ይፍጠረው ከማለት ሌላ ምን ይደረጋል? በጠቅላላው ጉዳቱ ለሟቾችና ለወላጆቻቸው ብቻ ነው ብለው የሚያስቡ ጥቂት የዋሆች ይኖሩ ይሆናል፤ ግን ጉዳቱ ድርጊቱን ለፈጸሙት ክፍል ጭምር መሆኑን ካለፉት መረዳት ይቻላል ። በእርግጥ ያድራጊዎች ቤተሰቦች በዚያን አይኖሩም በማለት ይጽናኑ ይሆናል። ግን ነገ በእኔ የሚለውን የአበው አነጋገር ቢያጤኑት መልካም ይሆናል።

## ፭

በየአቅጣጫው ሕዝቡን በመተንከስ ንብረቱን ሃገሩን እየተወ እንዲሰደድ አደረጉት። የቀረውም ቢሆን ያለፍራቻ ለመኖር በጊዜው በተዘረጉት የፖለቲካ ድርጅቶች መሰተፍ በአካባቢው ለተቋቋመው የንዑስ ደርግ አባሎች ከመጠጥ ቤት ጠብቆ ጠርሙስ ውስኪ ማውረድ ለዋናው ደርግ አባል ከአካባቢው የተወረሱትን ማር፣ ቅቤና ምኩቱን በሚቀርቡት ግለሰቦች በኩል ለቤተሰብ አዲስ አበባ ማስጫን በመጠኑም ቢሆን የመኖር ዋስትና ማግኛ ዘዴዎች ነበሩ። የቀረው ሕዝብም ቢሆን የሠርቶ መኖር መብቱ አልተጠበቀም። ሌላው ቀርቶ ቀደም ሲል በተደረገባቸው ጥቃት ዳግም እንዳይፍጸምባቸው በመፍራት ጸጥ ብለው የሚያስተምሩትን መምህራንና የሚማሩትን ተማሪዎች በማጋለጥ ስም ሥራ ማስፈታት ሲጀመሩ፤ ሁኔታው እያደር ፀረ-ሥራ እየሆነ መጣ። የሚሠራውንም አደሃሪ ቀድም ሠርተው ያፈሩትንም አቆርቋዥ በማለት የስም ማጥፋት ዘመቻ ተደረገ። በማንኛውም አቅጣጫ ሥራ ቆመ። በራስ ሠርቶ መኖር እንደወንጀል በመቆጠሩ ሕዝቡ እጁን አጣምረው እንዲቀመጥ ተገደደ። ቀድሞውን ቢሆን በአካባቢው ይህ ነው የሚባል ሰዎችን ቀጥሩ የሚያሰራ የግል ድርጅት የለም ማለት ይቻላል። ትልልቆቹ የሥራ መስኮች መጠጥ ቤቶችና የእህል ወፍጮ ሲሆኑ፤ እነዚያም እንደ ትልልቅ ንብረቶች ተቆጥረው ተወርሰዋል። ባለንብረቶቹም በቅርብ የተገኙት ከእስር ቤት ሲጪመሩ ሌሎቹም አካባቢው እየለቀቁ ተሰደዋል። በአካባቢው የቀሩት የመንግሥት ሠራተኞችና የቤት ሠራተኞች ብቻ ሲሆኑ የተቋቋመው ንዑስ ደርጎም ሥራው የቤትና የቡና ቤት ሠራተኞቹን መደኘት፤ መጥጥ ያልጋበዛቸውን ባለንብረት አደሃሪ ብሎ ማሰር ነበር።በሕዝብ ማደራጀት ስም የተላኩት የደርግ መልከተኞችም ሕዝቡ ወደልማት እንዲያተኩር ከማድረግ ይልቅ በጎሣና በቤሔረሰብ በመከፋፈል ያፋጩት ጀመር። ወጣቱንም በአካባቢው ምንም መዋቅር እንኳን ሣይኖረው ፤ እንደቀሩት የከፍለሃገራት ከተማ ወረቀቶች ተበትነው ሳይታዩ የኢሕአፖ አባሎች አሉና አጋልጡ በማለት ቁም ስቅሉን ያሣዩታል።በእርግጥ አንዳንድ ግለሰቦች አዲስ አበባ ለራሳቸው ጉዳይ ሄደው የተበተነ ወረቀት ይዘው ሊመጡ ይችላሉ ግን ስለኢሕአፖ የአካባቢ ሕዝብ የሰማው ከደርግ አባሎችና ከሕዝብ ድርጅቶች ውገዛ ሲሆን፤ ያም ሆኖ ከነበረው መንግሥት ጋር ፍልሚያ የሚያደርግ ድርጅት በአጠገባቸው ከሚያይቸው ፀረ-ሕዝብ ፀረ- ሥራ ሰይሻል አይቀርም በማለት ድጋፋቸውን ያጸባርቃሉ። የሕዝብ ድርጅት ሠራቶኞች ሆኑ የደርግ አባሎች በቅን ልቦና እንኳን የሚቀርቧቸውን ቢሆን ከማዋርድና ከማራከስአልተቆጠቡም። ሕዝቡም በግልጽ ቅዋሜን በግልጽ አሣየ።ሃገራችንም በውጪ ጠላት ተወረረች ተብሎ በመነገሩ፤ «ወሰናችንን እናስከብር የተወሰደብን መሣሪያ ይመለስልን



ከልጆቻችን ቀድመን እኛ እንዝመት እንሙት ወሰን መጠበቁን እናሰያቸው አስተዋዮች ከሆኑ ፈለጋችንን ይከተሉ፤» በማለት አባቶች ሲጠይቁ አደሃሪያን በመባል በልጆቻቸው ባልጆሮች በሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች በደርግ አባሎች መሣሪያ ተመዘዘባቸው። ድርጊቱን ያጤኑ አዛውት ሁኔታው አሣዝኖቸው «ምን ያደርጋል ዓሣ ከምኑ ይሸታል ቢባል ካእናቱ» ተብሎ የለም ብለው ይተርታሉ።

ቀደም ሲል ቅዋሜዎች በተናጠልና አንድ ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ሆኖ ሳለ፤ ውሎ አድሮ ግን ሁኔታው የሚቀጥልና ያለው መንግሥት መመሪያ መሆኑን ሕዝቡ ሲረዳው በግልጽ ቅዋሚ ማስማቱን ይመርጣል።መምህራንና ተማሪዎች በግንባር ቀደምትነት በአካበቢው የነበሩትን የመንግሥት ተጠሪዎች ፀረ-ሕዝብነታቸውን ከሚሰሯቸው ተግባራት ተነስተው ሲያጋልጡ፤ በጊዜው የሥልጣን ጥያቄ ሣይሆን የሕልውና ጥያቄ ነበር። ነፍስሕን ሊያጠፋት ሲመጣ ባለሕ ነገር ሁሉ ተከላከል ይመሥላል። ትዕግሥት መጠኑን አለፈ ከማለት ደረጃ ተደረሰ። ከመንግሥት በኩል ቀደም ሲል አተኩረውበት የነበረውን የሕብረተሰቡን ክፍል ተወት አድርገው ተማሪዎችንና መምህራንን ማደን ጀመሩ። እያፈሱ ከእስር ቤት ሲመጪመሩ ቀደኛ ዋቸው የሚባሉትን የት እንደሚየደርሷቸው አይታወቅም ነበር። የመጪረሻው ስደት የመምህራን የእርሽ ልማት ሠራተኞችና የተማሪዎች ሆነ።

## ወኔ

የእስፋውና የነጋሽ የቀሩት ወገኖች ያለምክንያት መመታት ትምህርት የሰጣቸው ተማሪዎችና መምህርራን የነበረውን መንግሥት ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር ሆነው ለመታገል በየአቅጣቻው ተሰደዱ።ከተሰደዱት ወጣቶች አንዱ እውነቱ ከዓለማ ጓደኞቹ ጋር ለመሥራት ወደአዲስ አበባ ይሄዳል። ሆኖም ግን የአዲስ አበባውም ውጥረት ከክፍለ ሃገር የከፋ እንጂ የተሻለ አልነበረም።የቀበሌ ተመራጮችና ካድሬዎች በማንኛውም ጊዜና ሰዓት የማንንም ቤት ገብተው ማሰስ አውቶብስ አስቁሞ መፈተሽ፤ መታወቂያ መጠየቅ ቋሚ ሥራቸው ነበር። ከአንዱ ቀበሌ ወደሌላው ሄዶ ማደር አይፈቀድም።ከክፍለ ሃገር አዲስ አበባ ከዘመድ ማረፍ አይቻልም። ካረፈም ከቀበሌ ወስዶ ማስመዝገብ ግዴታ ነበር።

እርሱም በእንግድነት አርፎ የነበረው ቀድሞ ከሚያውቃቸው ጓደኞቹ ዘንድ ሲሆን እነርሱም በነበረው ውጥረት ምክንያት ለብዙ ጊዜ መጠለያ ሊሰጡት አልቻሉም። ባአጋጣሚ አሰሳዎች ቢከሄዱና ከእነርሱ ዘንድ ቢገኝ ተይዞ ወደመጣበት ክፍለሃገር ተወስዶ ሊመታ ስለሚችል እነርሱንም ስለሚያስገኛቸው፤ በጊዜ ሥፍራውን እንዲፈልግ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመው በደመውዝ ወቅት መጥቶ እንዲወስድ ነግረው ያሰናብቱታል። ጊዜው ቀውጢ ነው። በማንም መፍረድ ያስቸግራል። ጓደኛ ከዳኝ ዘመድ ጠላኝ ተብሎ የሚወቀስበት የሚወገዝበት ወቅት አልነበረም።ሁሉም የራሱን ሕይወት ለማከረም የሚሯሯጥበት ዘመን ሆኖ ተገኘ።

እውነቱም አዲስ አበባ የቀድሞዋ አዲስ አበባ ሆና አላገኛትም። ቀደም ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ወጣቶች ፀጉራቸውን አፍሮ አበጥረው ታኮ ጫማቸውን ተጫምተው፤ ዘመን አመጣሹን አለባበሣቸውን ለማሣየት ወንድና ሴት ሆነው ከአራቱ ማዕዘናት ወደመሐል ፒያሣ ሲጓዙ፤ ከግራ ተቀኝ ካሉ ምግብ ቤቶች የሚተነው የጥሩው ወጥ ቅመም ሽታ፤ ከአካባቢው ሙዚቃ ቤቶች በድምፅ መስጫ መሣሪያ የሚተለለፋው ጣመ ሙዚቃ፤ እነዚያ ውብ ሴቶቻችን ያ የዘመኑ ካውያ ያልነካውን ፀጉራቸውን ሸብልለው የስንዴ ክምር አስመስለው፤ የሃገራችን ደርዚ የሠራውን ጥበብ ቀሚሣቸውን ለብሰው ኩታቸውን ደርበው፤ በብስኩት በምግብ በመጠጥ ቤቶች ሕዝብን ሲያስተናግዱባት ትታይ የነበረችው አዲስ አበባችን ያ ሁሉ ቀርቶ፤ ወጣቱ በካቴና ታስሮ የቀበርከውን ወረቀት አውጣ እየተባለ፤ ሲገፈተር፤ ባቅላባ፣ ብስኩት፣ ምግብ፣መጠጥ ቤቶች በካድሬ በቀበሌ ተመራጮች በኩባ ወታደሮች ተሞልተው፤ የባሕል ምግብ ቤቶች ተዘግተው ውብ ሴቶቻችን ለእንጀራ ጋጋሪነት ሥጋ ሜዳ ተወስደው፤



ፒያሣ የጅብና የታንክ መመለለሻ ሆና አዲስ አበባችን ፍጹም አበባ መሆኗ ቀርቶ ጠውልጋ ልትረግፍ የደረሰች አበባ መስላ ያገኛታል።

እርሱም እንደቀሩት ከየአቅጣቻው ተሰደው አዲስ አበባ እንደመጡት ወጣቶች ከአንዱ አልቤርጎ ወደሌላው በመዘዋወር ያድራል። ችግሩም ጠና ሲልበት ከቀድሞ ጓደኞቹ ዘንድ በመሄድ የገንዘብ ዕርዳታዎችን ይጠይቃል። እነርሱም ቢሆኑ በወቅቱ በሕብዕ ይታገል ከነበረው ድርጅት ከኢሕአፖ ውስጥ ይታገላል ብለው ስለሚጠረጥሩት ብዙም አብረውት አይዝናኑም።እርሱም አማራጭ ስለሌለው እንጂ የጓደኞቹን ስሜት ይረዳዋል። ቶርጠውም አትምጣብን ለማለት በደህናው ዘመን የቱን ያህል ርሁሩህ ለጓደኛ አዛኝ በችግራቸው ተገኝ መሆኑን ያውቁታል። በመጣም ቁጥር የአለፈው ጊዜ ትዝ እያላቸው የአእምሮ ዕረፍት ይነሣቸዋል። እርሱም ቢሆን እነርሱ ይኖሩት የነበረውን አይነት ኑሮ መኖር እንደሚችል ያውቀዋል። ግን በወቅቱ በነበረበት አከባቢ በቅርብ ሲፈጸሙ ያያቸውን ኢሰባአዊ ተግባሮች በነበረው መንግሥት ላይ ጥላቻን ስለአሳደሩበት ቅዋሜውን በመቀጠሉ እንደዚያን ያለ ኑሮ እንዲደኖር መገደዱን ያውቀዋል እምኖም ተቀብሎታል። ከዚያን የተለየ ግን ሕዝብ በተሰበሰበበት መፈከር አስምቶ ግለሰቦችን ፀረ-አበዮተኛ ብሎ እጋልጦ ከደሃው ገበሬ የተሰበሰበውን ገንዘብ በወሩ መጨረሻ ፈርሞ መቀበል የዚያን ያህል ቀላል እንደሆነ ይረዳዋል።

ያም ሆነ ይህ በጊዜው በአዲስ አበባ በነበረው መንግሥት ላይ ይሰነዘሩ የነበሩት ቅዋሜዎች የአእምሮ እረፍት የሚሰጡ ነበሩ። ወጣቶች በግልጽ በሲኒማ፣ በሻይ ቤቶች በእስፖርት ሜዳዎች የነበረውን መንግሥት ያወግዛሉ። እናቶች ሣይቀሩ የሥርዓቱን እስከፊነት በማውገዝ ስላማዊ ሰልፎችን በየቀበሌዎቻቸው ያደርጋሉ። የውግዘ ጽሑፎች በስፋልቶችና በግድግዳዎች ላይ ተጽፈው ስለሚገኙ ሕዝቡ በቀላሉ ያነባቸዋል። ምንም እንኳን ውጥረቱ የከፋና የከረረ ቢሆንም የወጣቱ ሞራልና ያየውን በግልጽ መቃወም መቻሉ በራሱ ላይ ያለውን መተማምን መግለጫ ምልክቶች በመሆናቸው ከወታደራዊ መንግሥት ተወካዬች የቀበሌ ተመራጮችና ካድሬዎች በስተቀር የሚቃወመው አልነበረም።

## ፯

በወጣቱና በቀበሌ ተመራጮ መካከል ይደረግ የነበረው ፍልሚያ፤ በደቡብ የሶማሊያ ጦርነት የሰሜን ሕዝብ እንቅስቃሴ በሥልጣን ላይ የሉትን መሪዎች ውጥረት ላይ ጣላቸው። በአኪያው የአዲስ አበባ ፖሊስ ጣቢያዎች ቀበሌዎች በእስረኛ ተሞሉ። የጊዜው መሪዎችም የተቻላቸውን ያህል እያወጡ ሲመቱ፤ ደጋፊዎቻቸው የነበሩት ከድሬዎችና የቀበሌ ተመራጮች ይመታሉ።ሆኖም ግን በማን እንደተመቱ አይታወቅም። ከመንግሥት በኩል በመግለጫ መልክ እንደሚተላለፈው ግን ኢሕአፖ እንደሆነ ይነገራል። ኢሕአፖም በወቅቱ ሃላፊነቱን ወስደ በልሣኖቹ የሰጠው መግለጫ አልነበረም። ይከሄዱ ከነበሩት ጠቅላላ ሁኔታዎች ተነሥተው ሃገሪቱ ከትልቅ ውድቀት ላይ እንደምትደርስ ሁሉም ከሚቀርበው ባልጀራው ጋር ይተነብያል።በሁሉም አቅጣቻዎች ለችግሩ መፍትሔ ተብለው የቀረቡት ለሚነሱት ችግሮች መሣሪያ ማንሣት ከእስር ቤት መጨመር ብቻ ነበር። የውስጡን የአስተዳደር ድክመት ተመልከተው ሊወሩን ላቀዱት የውጭ ጠላቶች ስም ወጣቱ ገበሬ እየተመለመለ ከሥጋ ሜዳ ገባ። የሃገር ጉዳይ ነውና« ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር ተባለ።»እናት ሚስት ልጆች ያለአጋዥ ቀሩ። በጊዜው የሚወራው ጦርነት ግድያ ብቻ ሆነ። ሌላው ቀርቶ ሲኒማ ቤቶች ይታዩ የነበሩት ፊልሞች ጦርነትን የሚያጸባርቁ ነበሩ። ለምሳሌ «ከድል ወደ ድል» የሚለውን የቻይናዊያን ፊልም የተመለከተ ወጣት ይከሄዱ የነበሩትን ትግሎች እንደሚመስሉ አድርጎ ወሰዳቸው።ይህም ሰኔ ፲፱፻፷፱ ዓመተ ምህረት ነበር።

በአዲስ አበባ ውጥረት ሲኖር በክፍለሃገር ያለው ውጥረት ገብ ይላል።ሌላው ደግሞ ምልሻውን ከገጠር ስለሚመለመል የሚፈጽሟቸው ግድያዎችና እስሮች በመጠኑም ቢሆን ይቆማሉ።እላይ በተገለጸው ዓመተ ምህረት ሰደድ የተባለው የወታደሩ ክፍል የፖለቲካ ድርጅት የአባላት ምልመላ የተጧጧፈበት ወቅት ስለነበረ ለክፍለሃገራት ውጥረቶች መላላት ሌው ምክኒያት ነበር። በአኪያው ቀደም ሲል በመኢሶን በወዝ የተመለመሉት የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች መውጫ መግቢያ ያሣጡት ወጣት ጠቅላሎ የሰደድ አባል ስለሆነ፤ የደርግ አባሎችም የሰደድ አባል ስለነበሩ የሕዝብ ድርጅቶችን እያፈሱ ከወሀኒ ሰለጧመሯቸው በመጠኑም ቢሆን ጊዜአዊ እፎይታዎች ነበሩ። ለሕዝብ ድርጅቶች በወቅቱ የወጣላቸው መፈክር ቢኖር «አብዮት ልጇን ትበላለች» ነበር። የደርግ አባሎችም ቀድም ለተሰሩት ጥፋቶች መኢሶኖችና የወዝ ሊግ አባሎች እንደሆኑ ለሕዝብ ማጋለጥ ሲየደርጉ፤ ለምሳሌ የእርሻ ሚንስትር ሠራተኛ የነበረው ነጋሽ የታሰረበትን እስር ቤት የደርጉ አባል ሲጎበኝ በእስር ቤቱ አጥር ግቢ ውስጥ የለማውን



ልማት አድንቆ ማን እንደአለማው ሲጠይቅ የተገደለው ነጋሽ እንደሆነ ሲነገረው አሳስተውኝ ነው ከማለት ሌላ የሰጠው መልስ አልነበርም።

ምንም እንኳን በክፍለሃገራት ያለው ውጥረት የላላ ቢመስልም፤ በአዲስ አበባ ግን ከደርግ ጋር ኢሕአፖ ያደርገው የነበረው ትንንቅ የሞት የሽረት ነበር። ደርግም በሚያደርገው የጠቅላላ የአፈሳ እስሮች በመጠኑም ቢሆን ኢሕአፖን ይጎዳዋል ። የአባላት ግንኙነቶች ይቋረጣሉ በጓደኞች የሚረዱ ወጣቶች የገንዘብና የመኝታ ችግር ላይ ይወድቃሉ። ከቤተሰብ የሚኖሩትም ወጣቶች ቢሆኑም ከቀበሌ እስር ለማምለጥ የነበራቸው አማራጭ የመጨረሻዋን የከተማ እውቶብስ ተሣፍረው ከበይና ከጥሻ ማደር ወይም ከመቃብር ቤቶች ሄደው እዲተኙ ይገደዳሉ።

ያም ሆነና አዲስ አበባ ሄዶ የነበረው እውነቱ የሚየውቃቸውና የሚገናኛቸው ጓደኞቹ እየታሰሩና እየተገደሉ ስለተለዩት ለመጨረሻ ጊዜ በሥራ ላይ በነበረበት ዘመን ጓደኛው ከነበረው ከአድማሱ ዘንድ የአልጋውንና የምግብ ገንዘብ ለመጠየቅ ይሄዳል። የአጥሩን በር አልፎ ከቤቱ ደጃፍ ሲደርስ አካበቢው ጭር ብሎ ያገኘዋል። በበሩ መዝጊያ ላይ የመብራት ኃይል የማስጠንቀቂያ ወረቀት ተለጥፏል። በአካባቢው ለብዙ ቀናት ሰው እንደአልተዘዋወረበት ይገምታል። በፍጥነት አካበቢውን ለቆ ይሄዳል። ከዚያንም ራቅ ብሎ ከሚኖረው ከአድማሱ ጓደኛ ዘንድ ሁኔታውን ለማጣራት ይሄዳል። አድማሱ ተጠቁሞበት ከቤት ተወስዶ ከሰድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ከከአሣችስ መታሰሩን ይነግረዋል። እውነቱም ከሰድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሲደርስ እድማሱም ከመጸዳጃ ቤት እያነከሰ ወደክፍሉ ሲገባ ያየውና እጁን ሲያውለበልብለት ፤ እርሱም እፃፉውን በመመለስ ወደ ክፍሉ ዘልቆ ይገባል። እውነቱም ቀርበው ባለመነጋገራቸው እየተጸጸተ በነጋታው አንድ ነገር ይዞ መጥቶ እንደሚጠይቀው ወስኖ ወደመርከቶው ይሄዳል። ሌሊቱ አልነጋልህ ብሎት በሃሣብ ስለአድማሱ ሲያወጣ ሲያወርድ ምንም እንቅልፍ በዓይኑ ሣይዞር ፤ በነጋታው ዳቦውን ገዝቶ በወረቀት ጠቅልሎ ከፖሊስ ጣቢያው ደርሰ አድማሱን እንዲያቀርቡለት ቢጠይቅ ከደርግ ጽሕፈት ቤት እንደተወሰደ ይነግረዋል። በወቅቱ አንድ የተያዘ ሰው ከደርግ ጽሕፈት ቤት ተወሰደ ማለት ድምዳሜው ተገደለ ማለት ስለነበረ እውነቱም ስለአድማሱ ሞት ምንም ሣይጠራጠር በይበልጥ ለማርጋጋጥ ቀደሞ መታሰሩን ከነገረው ግለሰብ ዘንድ ይሄዳል።ከእርሱም እንደተረዳው አድማሱም ደብደበው ስለበዛበትና ሕመሙን ከሚቆጣጠረው በላይ ሆኖ ስለአገኘው ራሱን በራሱ ገላግሎት አደረ። እስከሬኑንም ከምኒልክ ሆስፒታል ከሬሳ ቤት አኑረውት ስለነበር፤ ኪሱቹን ስንበረብር ከለበሰው ጃኬት ውስጥ ይህችን ማስታወሻ ትቶልን እልፏል ብሎ ነግሮት፤በጊዜው ለሐዘኑ ተሰባሰበው የነበሩት ጓደኛሞቹም ማልቀሱ ዋጋ እንደሌለው አምነው ዳግም የቀበሌ

ተመራጮች ቢመጡ ተለቃቅመው ከእስር ቤት እንደሚጨምሯቸው ገምተው በአፋጣኝ ለአድማሱ ወሰጆች ናዝሬት እርማቸውን እንዲያወጡ የሚነግሩበትን ዘዴ ተመካከረው ከዚያው ተበተኑ።

በጊዜው ራስን በራስ ማጥፋት ከቀበሌዎች ጋር ግንባር ለግንባር እየተታኮሱ መሞት የቀኑ ትዕዛዝ ነበር። በአፋኝ ጓዶች፣በካድሬዎችና በቀበሌ ተመራጮች ተይዞ ጡትን እየተቆረጡ እግር በዘይት እየተጠበሱ ጀርባን በቤንዝን ተርከፍክፎ እየተቃጠሉ ከመሞት እየተታኮስን መሞት ይሻለናል ብሎ ወጣቱ የመረጠበት ወቅት ነበር።ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ የከፍተኛ አስራ ሁለት የልጃገረዷቱን ጡት መቁረጥ የከፍተኛ ሦስት በዘይት መጥበስ የከፍተኛ ሃያ በቤንዝን አርከፍክፎ ማቃጠል ከደርግ ጽሕፈት ቤት በከራ ጣቶችን መቁረጥ እርግጠኛ መሆኑን ለመጥቀስ እንጂ፤ ሃያ አምስቱም ከፍተኞች የራሳቸው የሆኑ የማሰቃያ ዘዴዎች ነበሯቸው። ሌላው ወጣቱ በቀበሌዎችና ከካድሬዎች እጅ ከመውደቅ የራሱን ሕይወት በራሱ እንዲያጠፋ ሞራል የሰጠው የኢሕአፓ መከከለኛ ኮሚቴ አባል ነበር የሚባለው ተስፋዬ ደበሣይ ሕይወቱን ከፎቅ ተወርውሮ መስዋዕት በማድረጉ ወጣቱም ተስፋዬ ለአመነበት ሞቶ ማስተማርን አስተምሮናል በማለት በዓላማቸው ጸንተው የሞቱ ብዙዎች ነበሩ።



## ፫

እውነቱም ዋናው ከጓደኛው ዘንድ የሄደበት ምክንያት የገንዘብ ዕርዳታን ለመጠየቅ ቢሆንም ከእርሱ ችግር የጓደኛው ሁኔታ በጣም አሣዛኝና ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ስለአገኘው ለማንም ሳይነግረው ወደ መርካቶ ተመለሰ፤ በነጋታው ባለው ገንዘብ ተሳፍሮ በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ከሚያውቀው ጓደኛው ከጎጃም ክፍለሃገር ከፈለገሕይወት ከተማ ለመሄድ ይወስናል። ጉዞውን ይጀምረው እንጂ ከነበረው ቁጥጥርና ፍተሻ አልፎ ከማሪቆስ ከተማ እደርሳለሁ የሚለው ተስፋ በጣም የመነመነ ሲሆን፤ፍተሻው ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ የጀመረ፤በክፍለ ሃገሩ መስመር ላይ በሚገኙ ከተማዎች በሙሉ ቁጥጥሩ ጠበቅ ያለ ሆኖ፤ በጎጃም ክፍለሃገር ዐባይን ተሻግሮ ከደጀን ከተማ ከዚያንም ማሪቆስ ለመግባት አስር ኪሎ ሜትር ላይ ከሚገኘው ከአውራ ጎዳና ከንፐ ቁጥጥሩ በጣም የጠበቀ ሲሆን አጋጣሚው ባለፈው ቀን አንድ ሰው ስለተመታ ነበር። እውነቱም ምንም እንኳን ብዙዎቹን ፍተሻዎች ቢያልፋቸውም ከማሪቆስ ከተማ አውቶቡስ ጣቢያ ይደረግ የነበረውን ለማለፍ ትልቅ ችግር ፈጥሮበት ነበር፤ ሆኖም እንደአጋጣሚ ሽንጣው ሲፈተሽ የአንድ ዘመድ የሆነ የፖሊስ መኰንን ፎቶ በማየታቸው ብቻ ይለቁታል።

እርሱም በማግስቱ ከጓደኛው ዘንድ ከፈለገ ሕይወት ለመሄድ ወስኖ የመኝታ ክፍል ተከራይቶ ሽንጣውን ከክፍሉ አኑሮ የማሪቆስን ከተማ እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ቀደም ይሰራበት ከነበረው ክፍለሃገር አብረው ያስተምሩ የነበረውን መምህር ያገኘዋል። እርሱም በዚያን ቀውጢ ጊዜ በእንደዚያን ባለ አካባቢ በመገናኘታቸው ደንግጦ፤ በደህናው በሥራ ወቅት እንዳልመጣ ተረድቶት፤ በአንክሮ ሲመለከተው፤ እውነቱም በጓደኛው ፊት ላይ የሚነበበውን የድንጋጤ ስሜት በማጤን ብዙ አብሮት ላለመቆየት ስለፈለገ ተሰናብቶት ለመሄድ ሲነሣ፤እርሱም አብሮት ተነስቶ የአረፈበትን አልቤርጎ እንዲያሳያው ጠይቆት ወደቡና ቤቱ ተያይዘው ይሄዳሉ።ጓደኛውም ስለአመጣጡ ይጠይቀዋል ። እርሱም ከጓደኛው ዘንድ ከፈለገሕይወት ጥቂት ቀናት አሣልፎ ለመመለስ መሆኑን ይገልጽለታል።ጓደኛውም በቀጥታ ለምን ሥራህን ለቀቅ ከማለት ስለአስፋውና ነጋሽ እስዛኝ ሞት መስማቱን ይነግረዋል። የእነሱ ሁኔታ እንዳይገጥመው ክፍለሃገሩን ከለቀቀ መቆየቱን ይገልጽለታል።«ያኔ በየከቲት ያሽቃበጥንበት ለወጥ መልሰ ራሳችንን እያጠፋን ነው። ምን ታደርገዋለህ?» ብሎ ንግግሩን ሲያቆም፤ ሁለቱም አገጮቻቸውን በእጆቻቸው ደግፈው በመተከዝ ላይ ሳሉ የመኝታው ብር ይንኳኳል፤ እውነቱም ከወነበሩ ተነስቶ የመኝታውን በር ሲከፍት፣አራት የታጠቁ ፖሊሶች ከክፍሉ ይገባሉ፤ ሁለቱንም ጓደኛሞች መታወቂያቸውን ከጠየቋቸው በኋላ ሽንጣውን በርብረው ምንም ነገር ስለአላገኙ ወጥተው ይሄዳሉ። የማሪቆሱ መምህር እንደዚያ ያለ ሁኔታ ሲገጥመው የመጀመሪያ ጊዜው

ስለነበር በጣም አድርጎ ይደነግጣል። ፖሊሶቹም ከወጡ በኋላ እንደተጣለ ሰው ጓደኛሞቹ ተዘጋግተው ይቀመጣሉ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጓደኛው በዚያን ሁኔታ ከፈለገሕይወት ለመሄድ መዘጋጀቱን ይጠይቀውና እውነቱም የማይቀር መሆኑን ሲያረጋግጥለት፤ እንደርሱ አስተያየት ወደአዲስ አበባ መመለሱ የሚሻል መሆኑን ጠቁሞት ከደረሰው ጠዋት መጥቶ እንደሚሸኘው ነግሮት ወጥቶ ሄደ።

እውነቱም የጓደኛውን ምክር ከምንም ጉዳይ ሳይለው በጊዜ በተከራየው አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ ዕቃዶቹን ሲያወጣ ሲያወርድ ከቆየ በኋላ በምንም ዓይነት ከፈለገሕይወት እንደማይቀር ወስኖ ይተኛል። በነጋታው በአውቶቡስ ተሳፍሮ ወደፈለገሕይወት ጉዞውን ሲያደርግ፤ በመንገድ ላይ የገበሬ ማሕበራት ተመራጮች አድፍጠው አውቶቡስ እያስቆሙ መታወቂያ ይጠይቃሉ፤ኪሶችንም ይፈትሻሉ፤የአውቶቡሱን ውስጥ ሣይቀር ያስሳሉ። የገበሬ ማሕበር አባላቱ ማንበብና መጽሐፍ ስለማይችሉ የሆነ ፎተግራፍ አሳይቶ ማለፍ ይቻል ነበር። እንደአጋጣሚ አንድ ቄስ ለጊዜው ያልጠመጠሙ መስቀላቸውን ይዘው የተነሱትን ፎቶግራፋቸውን ከማሕደራቸው አውጥተው ያለኝ መታወቂያ ይህ ነው የምሄደውም ዳንግላ ልጄ ወንድልጅ ስለወለደች ለመጠየቅ ነው ብለው ለፈታሹ ሲነግሩት የገበሬ ማሕበር አባሉም አባቴ ይግቡ ግድየለም ብሎ ያስገባቸዋል። እርሳቸውም እግዚአብሔር ያክብርልኝ ብለው ከተቀመጡ በኋላ፤ ከአጠገባቸው ወደተቀመጠው እውነቱ ዞር ብለው «አያ እኛ በጊዜያችን እንዲህ ያለነገር አይተን አናውቅም፤ጠላት እንኳን ደፍሮ ዐባይን ተሻግሮ ይህችን አንባችንን እንዲች ብሎ አረገጣትም። ዛሬ በእኛ ልጆች በሃገራችን መሬት ላይ እንዳንዘዋወር ዘመድ እንዳንጠይቅ የውስጥ ሱሪያችን ሣይቀር አስወልቀው ይበረብሩን ጀመር።ምን ያደርጋል? የእሣት ልጅ አመድ ሆነና ቀረ ታሪካችን» ብለው ሲያበቁ እውነቱም ድምፁን ለዘብ አድርጎ «አባቴ አሁንም ጎጃም አይከፋም አዲስ አበባን ቢያዩ ምን ይሉ ይሆን? ከጎጃምስ መስቀል ክብር ኖሮት ለማለፊያ አገለገለ፤ ሸዋ ታቦት የተሸከመ እንኳን ክብር አጥቷል» ብሎ ይነግራቸዋል። እርሳቸውም መልሰው «አይምሰልህ ሸዋ አድብቶ እንጂ አጥቶት እንዳይመስልህ» በማለት ውይይታቸውን ያበቃሉ።

እውነቱም ጓደኛውን በደህና ቢያገኘውም በፈለገሕይወት ውሎ የማደሩ ነገር የሚያስተማምን አልነበረም ። በተለይ መምህራን በደቡብ እንደተደረገው በወገንህ በኤርትራ ሕዝብ ላይ ሊያዘምትህ ነው ብለው በጊዜው የሚካሄውን የሚሊሻያ ጦር «ለእናት ሃገር ጥሪ» ምልመላ እንዳያከሽፉበት በተለይ የምሁሩ ክፍል ላይ ይደረግ የነበረው ቁጥጥር በጣም የጠበቀ ስለሆነ ከለሥራ ከተገኘ ዘመቻውን ለማክሸፍ የተሰማራ አናርስኪት ተብሎ ስለሚገደል በአፋጣኝ



የሚፈልገውን ገንዘብ ይዞ ወደ አዲስ አበባ ይመለሳል።

ከጎጃም ክፍለ ሃገር ተመልሶ ምናልባት የምተዋወቃቸው ጓደኞቼን ሲያልፉ ሲያገድሙ በገኛቸው በማለት ከትራያዚዝ ሻይ ቤት ከደጎል አደባባይ ሻይ ይዞ ሲዝናና ከልጅነት እስከ እውቀት ጓደኛውን ሁሴንን ከሌላ እርሱ ከማያውቀው ግለሰብ ጋር ከትሪያኖን ቡና ቤት ወጥተው ወደመርካቶ አቅጣጫ ሲሄዱ ያያቸዋል። የሻይውን ሂሣብ ከፍሎ በሩቅ ሲከታተላቸው ከኬቨ ሻይ ቤት ሲደርሱ ወደ ግራ ሲታጠፉ፤ብዙ ሣይሰወሩበት በፍጥነት በመሄድ ጓደኛውን ይዞ ያናግረዋል። ሁሴንም እንደቀሩት ጓደኞቹ የመሸበር የመደናገጥ መልክ አይታይበትም፤ እውነቱንም ሲያናግረው በጣም በመዝናናትና በልበሙሉነት ሲሆን እንደውም በእውነቱ ፊት ላይ የመደንገጥና የመሸበር መልክ ይታይበት ነበር።ሰዓቱ የምሣ ሰዓት ስለነበር ደህንነታቸውን እየተጠያየቁ ከአንድ መለስተኛ ምግብ ቤት ገብተው፤ ምግብ ከአንበ ውኃ ጋር በሁሴን አዘዥነት ቀርቦ፤ እነርሱም ምግባቸውን በመመገብ ላይ ሳሉ አራት ወጣቶች ከቡና ቤቷ ገብተው ከሁሴን ሰላምታ ተለዋውጠው፤እርሱን ፍለጋ እንደመጡ ጠቅመው እነርሱም በአፋጣኝ ምግባቸውን ተመገበው ሰባቱም ሰዎች ተያይዘው ሽቅብ ወደ አዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ያመራሉ።በወቅቱ በዚያን ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ እንኳንስ ሰባት ሰዎች ይቅሩና ከሁለት በላይ ከሆኑ ወዲያውኑ በተወርዋሪ ጓዶች በሚሏቸው ታፍነው ይወሰዱ ስለነበር፤ እውነቱም ካለፉት ጊዜያት ልምዶቹ ጋር ሲያስተያየው ይሄኛው ፍጹም እንቆቅልሽ ነበር የሆነበት። እንደውም አንደኛው ደበስ ብሎ ካሜራውን ከኪሱ አውጥቶ ፎቶ ሊያነሣቸው መፈለጉን ይገልጽላቸዋል። እውነቱም ድርጊቱ አጠራጥሮት ከወጣቶቹ ጋር ፎቶ ላለመነሣት ይገለሳል። ሁሴንም የእውነቱን ራሱን ማግለል ተመልክቶ «አንተ ሁሌ ተጠራጣሪ ነህ እነዚህ በቅርብ ከውጪ ከሚደ የገቡ ጓዶች ናቸው አስተዋውቅሃለሁ» ብሎ ጀርባውን መታ አድርጎት ተያይዘው ወደፒያሣ አመሩ።

ወጣቶቹም ከሁሴን ዘንድ የመጡት እርሱንና ጓደኛውን ምሳ ለመጋበዝ ኖሮ ከፒያሣ ከጆንበር መውጫ ቡና ቤት(Sunrise) ገብተው፤ የቡና ቤቱም ሠራተኛ የምግብና የቢራውን ትዕዛዝ ተቀብሎ በጥሩ ሁኔታ ተሰርቶ ቀረበ፤ እውነቱ ጥርጣሬ ገባው። በወቅቱ በስደት ላይ ይገኙ የነበሩት የኢሕአፖ ደጋፊዎች እንኳንስ ቡና ቤት ገብተው ክትፎና ቢራ አዘው ሊመገቡ ይቅርና ለሻይና ለደረቅ ዳቦ ገንዘብ ማግኘቱ በጣም ችግር ነበር። በጎጃም በረዳ አካባቢ ለሚገኙ የአሥራ አምስት ሣንቲም ምግብ ቤቶች ገንዘብ ከተገኘ በጣም በሽበሽ ነው ሲባል፤ ያለበለዚያ ግን ረሃብ እንዳይሰማ የአምስት ሣንቲም ሎዝ ወይንም በየመንገዱ ላይ ተቀቅሎ የሚሸጠውን የበቆሎ እሸት ተመግቦ ውኃን ጠጥቶ መተኛት ነበር። እውነቱም የጓደኛውን ጓደኞች የገንዘብ አወጣጥ ሲመለከተው ምናቸውም የደርግ ተቃዋሚዎች አይመስልም።

እንዳለውም ከሜዳ ይዘው የገቡት ገንዘብ ሊሆን ይችላል በማለት እራሱን ያሣምናል።

ሁሴን ከሌሎች ግለሰቦች ቀጠሮ ስለነበረው ተያይዘው ከላንቻ ቡና ቤት ከኢጣሊያን ሠፈር ይሄዳሉ። ከቡና ቤቱ ሲደርሱ በጣም የተጎሣቆሉ ወጣቶች የለበሷቸው ልብሶች በጣም ያደፉ የተቀዳደዱ የጫማዎቻው ሶሎች የተጣመሙ፤ ፀጉራቸው ያልተበጠረ ግን የሰንደደ ባርኔጣዎች ደፍተውባቸው ከቡና ቤቱ ተቀምጠው ያገኛቸዋል። እነርሱም ከቡና ቤቱ ሲደርሱ ውጭ ውጩን ይመለከቱ ስለነበር እውነቱና ሁሴንን በፈገግታ ተቀብለዋቸው መቀመጫ አስፍተውላቸው ተቀመጡ ። እውነቱም ከሰው የተቃጠረበት ሰዓት ስለደረሰበት ከሁሴን ከመርከቶ ቀጠሮ ተሰጣተው ተለያዩ።

እርሱም ከመርከቶ ከአንድ ሻይ ቤት አንድ በራድ ከቡሽ ጋር አዞ የጓደኛውን ሁኔታ ሲያሰላስል ከአድማሱ ሞት በፊት ግንኙነት የተቋረጠባቸውን ጓደኛውን ልክ ለመፈቃቀጃ በተሰጣጡት ሰዓት ከሻይ ቤቱ ሲገባ ያየዋል። በፍጹም ሊያምን አልቻለም ጓደኛውም እንደዚያው በወቅቱ ጓደኛሞች ተጠፋፍተው ሲገናኙ ደስታቸው ከመቃብር እንደተነሱ ያህል ነበር። ምክንያቱም ማታ ተለያይቶ ጠዋት አድሮ የመገናኘቱ ነገር በጣም አጠራጣሪ ሲሆን የእርስ በእርስ ያለው ፍቅርም በቀላል የሚገመት አልነበረም። ጓደኛውም ተጨማሪ ቡሽ አዞ «እራት ሻይ ነው ወይ ብሎ አሹፎ ሲጃራውን አያይዞ ምነው ሊቀመንበሩ ከመርከቶ ሕዝብ ላይ እጆቹን ቢያነሣ» ብሎ ይቀልዳል ። እውነቱም የተጠፋፉበትን ምክንያት ይጠይቀዋል።መሉጌታም በቀበሌአቻው በተደረገው አሣሣ ታፍሶ ከአራተኛ ፖሊስ ጣቢያ መታሰሩን ይነግረዋል። እንዴት እንደወጣ ሲጠይቀው ወንድሙ የከባድ መኪና ሹፌ ስለሆነ ለጣቢያው አዛዥ አንድ ኩንታል ጤፍ ከጎጃም አንድ ኩንታል ከሰል ከጅማ ከቤቱ ወስዶ ሲያወርድለት፤ በአሥራ አምስት ቀኑ ከፍርድ ቤት ሣልቀርብ ተፈታሁኝ። የእስር ቤቱ ሁኔታ አታንሰው ሲዖል ነው በማለት ያጫውተዋል። በዕለቱ ምንም አብረው የሚሰሩት ሥራ ስለሌለ፤ ባለፈው ጀምረውት የነበረውን የጊዜውን አገብጋቢ ሁኔታ ከበላይ አካል ወርዶ ከሚያወያያቸው ግለሰብ ጋር ሆኖ ለመወያየት ቀጠሮ ተሰጥታተው ተለያዩ። እውነቱም ከሁሴን ከተቃጠሩበት ሻይ ቤት ቀድሞ ለመገኘት ከሥፍራው ይሄዳል



## ፱

ሁሴንም በቀጠሮው መሰረት ልክ በሰዓቱ አብሮት ከነበረው ግለሰብ ጋር ከሻይ ቤቷ ደርሰው፤ ሁሴንም ቀና ብሎ የሻይ ቤቱን ሰዓት ተመልክቶ የእናርክ ድስፒልን ነው በማለት ቀልዶ ተቀመጠ።እውነቱም ሌላ በራድ እንዲመጣላቸው ቢያዝ ሁሴን በይበልጥ ተዝናንተን እንድንወያይ ቡና ቤት እንከራይ የሚለውን ሐሣብ አቀረበ። እውነቱም መታወቂያ ይጠይቁናል በማለት ሐሣቡን ሰጠ ሁሴንም እናሣያቸዋለን በማለቱ ተስማምተው ከመርካቶ ከአንድ ቡና ቤት የመኝታ ክፍል ተያዘ። አንድ ዙርባ ጫት ተገዛ ፍራሹ ከወለሉ ወረደ ውዱ ተወጋ ዊንስተን ሲጃራው ከበንሰን በርነሩ ጋር ከፍራሹ ተቀመጠ ጫቱ በሁሴን ተረመሰ ሦስቱም ሚርቃናውን ለማምጣት ያንን ቀዩን የወሊሶ ጫት ምንም ገራባ የማይወጣለትን እያጢረሩ ተርዚናቸውን ሞሉ። ሁሴንም አንዷን ለምለም የጫት ቅጠል አንስቶ፤ ጫት ለኢትዮጵያ አብዮት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል መከበር ያለበት ቅጠል ነው በማለት ውይይቱን ይከፍታል።

«ወርቃማውን ጊዜአችንን ያጠፋንበት ከዋሮአችን ተፈናቅለን የሰው እጅ ያያንበትና አልፎም ተርፎም እራሣችንን ችለን የማናድር መስለን እንድንታይ የደረሰንበት ብሎም ብዙ ጓደኞቻችንን ያጣንበት ድርጅት መፍረሱን ሰምተሃልን?» በማለት እውነቱን ይጠይቀዋል። እርሱም የመስመር ለዩነት መፈጠሩን አውቃለሁ ግን ፈረሰ የሚለውን ሰሰማ ይህው ከአንተ የመጀመሪያዬ ነው በማለት ይመልስለታል። ከልሰማህ ታሪኩ እንደዚህ ነው ።«ከሕዝብ ተምረን እናስተምራለን በማለት ከየአቅጣጫ ለጭቁኑ ሕዝብ እንታገላለን ብለው ሜዳ የገቡትም ወደነበሩበት እየተመለሱ ነው።ቀደም ብሎ ኢሕአፖ የደርግ ደጋፊ የነበሩትን ፀረ-ሕዝብ በማለት መግቢያ መውጫ ስታሳጣቸው ይደግፏት የነበሩት ክፍሎች አሁን ጩርሰ የሉም። ወጣቱም ቢሆን ግንባር ለግንባር ከተቃዋሚዎቹ ጋር ያደርገው የነበረው ፍልሚያ እንዲያው በጀብደኝነት እንጂ የሩቅ ጊዜ ጥቅምና ጉዳቱን ተረድቶት አይደለም። በአሁኑ ጊዜ እፍኝ የማይሞሉ ግለሰቦች የምጣኔ ሐብት ምንጩን የያዘውንና ከግር ጠፍሩ እስከ ፀጉር ጫፉ የታጠቀን መንግሥት ሕዝብን ለአመጽ አዘጋድቶ ከሥልጣን አወርዳለሁ ብሎ መታገል ከንቱ ውዳሴ ነው።»ተመልከት ይልና አብሮት ከመጣው ወጣት እጅ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ተቀብሎ በሰሜን ከደርግ ጋር ይዋጋ የነበረ ሻለቃ በአሰሻ ጓዶቹ ተደመሰሰ የሚለውን ዜና ያስነብበዋል።

እውነቱም ጓደኛው ቀደም ብሎ ይከተለው ከነበረው የፖለቲካ መስመር በመለወጡ ተደናግጦና ተግርሞ እርሱንም ከኢሕአፖ ከተገነጠሉት በወቅቱ ዘመናዊያን እየተባሉ ከሚጠሩት ክፍሎች መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም። ሆኖም ቀደም ሲያውቀው ይከተለው ከነበረው የፖለቲካ መስመር መገለሉን ተረድቶት «ትግል

በቃኝ ማለትህ ይመስለል?» ብሎ ሲጠይቀው፤ «በማምንበት መስመር ገብቼ እሰራለሁኝ።» «እንዴትስ ሊሆንልህ ይችላል? ቀደሞ የምትቃወማቸውንና ስትታገላቸው ከነበሩ ብዙ ሕዝብ መጨፍጨፋቸውን እያወቅህ አብረሃቸው ስትሰለፍ የሕሊና ፀጸት አይሰማህምን? ደግሞስ የቀድሞ ጓደኞችህን ተደርበህ ለማጥፋት ትሰለፋለህስ ወይስ ለይተህ ትተዋቸዋለህ?» ሁሴንም ያያዘውን የዊንስተን ሲጃራውን ጢስ ወደ ከርኒሱ እየሰደደው «በጥቅሟ እስከመጡብኝ ማንንም አልተውም ፤ አይምስልህ እንተን መሰል አንዳንድ ሞኞችና ወግ አጥባቂዎች ሐቁን ይዘው ይንገዛገዛሉ እንጂ ለብዙዎቹ ዛሬ ፖለቲክ ሸቃለ ነው። ትርፍ ወደተገኘበት መሯሯጥ ሆኖል።አሁንም አንተ በመኝታ ችግርና በምግብ እጥረት እየተሰቃየህ የምታመጣው የመንግሥት ለውጥ አይታየኝም። ከላንቻ ቡና ቤት የነበሩትን መምህራን አይተሃቸዋል ቀደም ሲል ባታውቃቸው ኖር የባለ ስድስትና ሰባት መቶ ደመወዝተኞች ነበሩ ብዬ ብልህ አትቀበለኝም።እንደዚያን ተጎሣቁለው ሕዝብን እናስተምር ቢሉ ማን ይቀበላቸዋል? እንተንም ቢሆን ሣያጋጥምህ አልቀረም ቀደም የምናውቃቸው ጓደኞቻችን ከሩቅ ሲያዩን መንገድ ሲለውጡ ከእለዚያም ታክሲ ጠርተው ሲይዙ አጋጥሞናል። ፀረ-ሕዝብ ተመታ የተባለ ዕለት ደግም እንብርታችን እስኪገለበጥ ጋብዘውን የኪስ ገንዘብ ሰጥተውን ሲሸኙን አይተናል፤ ይህን እንደ ድጋፍ ከወሰድነው ተሣስተናል። ሁሉም ሣይርበው ሣይጠማው ሣይሰራ ሥርዓቱን እንድች ብለው ሣይቃወሙትና ለመለወጥ በእዲስ ወጤታው በሆነ አመራር ለመተከት መሰዋዕትነት ሣይከፈል ጥቂቶች በሚያደርጉት መፍጨርጨር ብቻ ይህ መንግሥት ይለወጣል ብለው የሚጠብቁ አሉ። በሃገራችን ያለውን ሁኔታ ራስ ሳለው ሰው የምትነግረው ነገር አይደለም። ለመንገርም መሞከሩም ዝቅ አድርጎ መመልከት ይመስለኛል።ይቅርታ አድርግልኝና ራሴንም ማግለሌ ሣይሆን በተለይ የተማረው ክፍል የቁሣቁስ ፍቅር የሕልውናውን ቦታ የወሰደበት ይመስላል። ይህንን እንደሂስ ብታቀርብበት እንደገደልከው ይቆጥረዋል። አትታዘበኝና በተለይ እኛ ይህን በስልጣኔ ስም የውጭውን ሥርዓተ ትምህርት የወሰድነው ክፍሎች እሽ አትበሉን የንጉሥ ደሮ ነን ባዮች ነን በሌላ አኳያ የዲሞክራሲ መብት ጠያቂዎች ነን ሁለት ወደ አይሆንም። ሁሉም ነገር ከራስ ይጀምራልና፤ እንግዲህ በብርቅርቅ ነገር ሲደለል የነበረን ሰው የውጪ ኃይል ይለውጠዋል ማለት በእኔ አስተያየት የለም። ራሱን በራሱ የመለወጡና የተሸለች ሃገር መገንባቱ የያንዳንዱ ዜጋ ፍላጎት ሲሆን ችግርህን ተረድቼልሃለሁ ለጊዜው ቢደላህም ልጆችህም ሆኑ ተተኪው ትውልድ ችግር ላይ ይወድቃሉ ብሎ ለመንገር አንተ ማነህ? ከዚህ በስቲያ ግን እንደሕንድ ሕዝብ ባሕልህን ጠብቀህ እድገትህን እራምድ ብለህ ብትወተውት ትርፉ መሣቂያና መሣለቂያ መሆን ነው። እኛም ከዚህ ውጪ አይደለንም። እንደማንኛቸውም ጓደኞቻችን ከሕዝብ ተሰብስቦ በሚከፈለን ደመወዝ ተሽቀርቅረን ደስ ያለንን



መኪና ነድተን ማለፍ እንፈልጋለን ከእኛም በላይ አዋቂ የተባሉትና ሃገሪቱ በወለድ አግድ ተይዛ ያስተማረቻቸው ከዚህ የተለየ ሲያደርጉ አላየንም። ጥቂት የእራሳቸውን ጥቅም መሰዋዕት ለማድረግ የሞከሩ ቢኖሩም ምሳሌነታቸው ባይጠቀስም የሚሰሩት ዋጋ ተነስቶት እንደሞኝ መቆጠራቸውን የምናየው ሐቅ ነው ። እኔም በዚች በምኖርበት አጭር ዘመን በተቻለኝ መንገድ ሁሉ እራሴን ለማስደሰት እሞክራለሁ ። አንተም ብትሆን በአንተና በጥቂት ጓደኞችህ የወታደሩ መንግሥት ተለውጦ ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋማል የሚለውን አስተሣሰብህን ከአእይምሮህ አውጣው። እኔ የማገናኛቸው የደርጅት ሰዎች አሉ አስተዋውቅሃለሁኝ። ያለችግር ባአዲስ አበባ ሥራ ተፈልጎልህ በደህና ትኖራለህ።»

እውነቱም ጓደኛው ከቀረባቸው ሐሣቦች አንዳንዶቹ እውነትነት ቢኖራቸውም ከራሱ ጥቅም አንፃር ስለሆነ ሐሣቡን ሊያስለውጠው አልቻለም። እርሱም አብሮት የመጣው ግለሰብ ወደ ዉጭ ሲወጣ ጠብቆ፤«አሁን የገለጽሃቸው ሐሣቦች በፖርቲው ውስጥ የመስመር ልዩነት የፈጠሩት ጽንስ ሃሣቦች ሣይሆኑ ግለሰቦች ራሳቸውን ሃሳቢ አስመስለው ለማቅረብ የሚሰጧቸው ምክንያቶች ናቸው። ስለሌላው ምን ያገባናል ለራሳችን ጥሩ መስለው የሚታኙንን ተግባሮች መፈጸም ብቻ ነው። አሁንም እኔና አንተ ብቻ የመስመር ልዩነቶችን ባመጡት ጽንስ ሐሣቦች ላይ ለመወያየት ቀጠሮ ብንሰጣጣስ» ብለው በነጋታው ከፒያሣ ለመገናኘት ወስነው ይለያያሉ።

የሁሴንና የእውነቱም ቀጠሮአቸው ከፒያሣ ከመዝሸልድ በስተሰሜን ከምትገኝ ቡና ቤት ሲሆን ከተቃጠሩበት ሰዓት አስር ደቂቃ ቀድም ተገኘ።ቀዝቃዛ መጠጥ አዞ ሁሴንን በመጠባበቅ ላይ ሳለ ባለፈው ቀን በውይይታቸው ላይ የነበረና ሌላ ግለሰብ ከቡና ቤቷ ይገባሉ። እርሱም ባለፈው ቀን መጥቶ የነበረው የሰላምታ መለዋወጥ ያደርግልኛል ብሎ ከመቀመጫው ሲነሣ ግለሰቡ ተከሳትሮ ስልኩን ማዘር ሲጀምር ሁኔታቸው ስለአላማረው ውጥቶ ይሄዳል። ድርጊቱ ዋጤም ከዲስፒብሊን ውጭና ሽለነት ነው ። ሁለታችን ብቻ ሆነን እንነጋገራለን ብለው ወስነው ያውም ግለሰቡ ሣይሰማ የወሰኑትን ሌላ ሰው ጨምሮ ከቦታው መለክ ከከሃዲነት ሌላ ምንትርጉም ይሰጠዋል።እውነቱም በሁኔታው አዝኖና ከፒያሣ ሲቀጥረው ባለመጠራጠሩ በራሱ ተቆጭቶ በቡና ቤቱና በመዝሸልድ መካከል በሚያስኬደው መንገድ ሸቅብ ሲወጣ ጓደኛውን ከሌላ ግለሰብ ጋር ከግንብ ሥር ተለጥፎ ቁልቁል ሲመለከት ያየዋል። እርሱም በርቀት እጁን አውለብልቦለት እርምጃውን ይቀጥላል።

በጊዜው እርስ በእርስ መጠቋቆሞች የተጀመሩበት ወቅት ስለነበር ማንንም ማመን ያስቸግራል። ብዙዎቹ ጥቆማዎች የተጀመሩት

በጣም በሚቀራረቡና በጓደኞሞች መከከል ሲሆን ያም የሆነበት ምክንያት ሲሰጥ እርሱ ወይንም እርሷ በሕይወት ካለች ወይም ካለ በንዳ ወይም እንጃ ፀማለት አያስቀምጡንም፤ ስለዚህ እርሱንም ሆነ እርሷን ማስበላት አለብን የሚል ነበር የጊዜው መፈክር።

የወቅቱ መጠቋቀሞች ለከድሬዎች ለቀበሌ ተመራጮች የኢሕአፖ አባሎችን ከማንኛውም ሥፍራ አፍኖ ለመያዝ ወይም «ነፃ እርምጃ» ለማፋፋም አመቺ ሁኔታን ፈጠረላቸው። ከድ ሊሰራ የሚጠባበቀውን ወጣት ኪሱን ሲበረብሩት የኢሕአፖን ወረቀቶች ሲያገኙ ያለምንም ጥያቄ እርምጃዎችን መውሰድ፤ ለድርጅት ሥራ ከተሰማሩበት ወይም ከተጠለሉበት አካባቢዎች እጅ ከፍንጅ ከነማባዣ ዕቃዎቻቸው ከነጦር መሣሪያቸው በጠቋሚ መሪነት መያዝ፣ በአባላት መከከል መጠራጠሮችን እየፈጠረ መጣ። ያም ሆኖ ግን የሚተማመኑት ክፍሎች የሞት የሽረታቸውን ከመኢሶን፣ከወዝ ሊግ፣ ከሰደድ፣ ከቀበሌ ተመራጮች በቅርብ ከተገነጠሏቸው ዘመናዊያን፣ ከሚባሉት ከአፋኝ ጓዶች፣ ትግላቸውን ቀጠሉ። ከሕዝብ ድጋፍ ስለነበራቸው ተቀዋሚዎቻቸው የነበረው መንግሥት ከጎናቸው ተሰልፎ ሳለ እንኳን በጣም አድርገው ይፈሩ ነበር። ከሁሉም ግን ኢሕአፖዎችን የጎዳቸው ከእነርሱ ተነጥለው ከወጡት ክፍሎች ጋር ያደርጉት የነበረው ትግል እንደነበር በወቅቱ ይታዩ የነበሩት ሁኔታዎች ግልጽ አድርገውታል።



I

ሙሉጌታና እውነቱ ከበላይ አካል ሊያወያያቸው የመጣው ግለሰብ ሆነው በጊዜው ጎልተው በሚታዩት የድርጅቱ ችግሮች ላይ ለመነጋገር ያመቻቸው ዘንድ አደጋ የማያመጡ አካባቢዎችን ይጠቀማሉ። አራት ኪሎ ከምርጫ ውስጥ አይገባም። ቀደም ሲለም የመኢሶን አባላት መሰብሰቢያ ሲሆን በዚያኑም ላይ አረመኔው ግርማ ከበደ ክሮበላ ካሸነፉት እስከ ነብስ ጡር የጨረሰበት አካባቢ ስለሆነ ዲሞክራት አካበቢውን አይፈልጉትም። ፒያሣም ቀድሞም የከድሬች ውሎ አድሮም የዘመናዊያን መሰብሰቢያ ስለሆን በቀላሉ መጋለጥ ስለሚቻል ከምርጫቸው ውስጥ አላስገቡትም። ምንም እንኳን መድፍ የተጠመዱ ጅጥዎች ቢርመሰመሱበትም ያው መርከቶ ይሻለናል በማለት ከአንድ ቤተክሪስትያን የተጣለ አስታራቂ መስለው ውይይታቸውን ጀመሩ።

በጊዜው አንገብጋቢ የነበረው ሁኔታ ቢገለጽ የወጣቱ ከኢሕአፖ እየተሸራተተ መምጣትና የሠራተኛውም ክፍል ከነበረው ጭፍጨፋና ቁጥጥር ሙሉ በሙሉ የድርጅት ተሣትፎችን ከማስየት መቆጠቡ ሲሆን ቀደም ሲል ወጣቱ ጨርሶ ፖለቲካ ሥራዬ ብሎ በመውሰዱና በኢሕአፖም ላይ ትልቅ እምነት አሣድሮ ድርጅቱንም እንደታላቅ ድርጅት የብዙ ዓመታት የተግል ልምድ እንዳለው ገምቶ በፖርቲው መከከለኛ ኮሚቴ መከከል ልዩነቶች ተፈጠሩን ሲሰማ ያልጠበቀው ስለሆነ በጣም ተሸማቀቀ። በቋፍ የነበሩ ጥቂቶች የመስመር ልዩነት ያመጡትን ጽንሰ ሐሣቦች በውል ሳይመረምሯቸው በራሳቸው ፍላጎት ተገለሉ። የድርጅት ድስፒሊን ተጣሰ።ልዩነቱን እንደ ታሪክ ክስተት ወስዶ በሁለቱም አኳያ ተመልክቶ የገጠማቸውን ፍትትን ከመቋቋም ይልቅ ወደተራ ወሬ ተወሰደ።

ከበላይ አካል የተላከው ግለሰብ የልዩነትን መጥፎነት ገልጾ፤ ግን በማንኛውም ሃገርና ሕዝብ መከከል የፖለቲካ ግጭቶችና ፍጭቶች እንደነበሩና እንደአሉ ወደፊትም እንደሚኖሩ ያም የታሪክ ሒደት እንደሆነና ማንም እንደማያቆመው ጠቁሞ፤ «የእኛን ግን ልዩ የሚያደርገው በመሪሆው ያልተስማሙት ክፍሎች ያመኑበትንና ለሕዝብ እድገት አቋራጭ መንገድ ይሆናሉ ብለው የሚገምቷቸውን ሐሣቦች ከማቅረብ ይልቅ ድርጅታዊ ድስፕሊኑን በመጣስ በየአቅጣጫው ቀንጺል ሐሣቦች ለበታች አካላት እንዲደረሱ አደረጉ። እንደገለፃችሁት ቀድሞን ትግሉ ያገሸገሻቸው ክፍሎች እራሳቸውን አገለሉ። ያም በቂ ሆኖ ሲገኝ አንዳንዶቹ የድርጅት ጓደኞቻቸውን እጅ ከፍጅ ማስያዝ ጀመሩ። በየአቅጣጫው ድርጅቱን እንዳልነበር ለማድረግ መሯሯጥ ተጀመረ። ዋናው ሐሣብ ላይ ለመነጋገር ጊዜ ለመስጠትም አልተፈለገም። ይህን እንግዲህ ማንም ገለልተኛ የሆነ ግለሰብ የሚያየውና የሚገመግመው ነው። ለሁሉም አጥፊውንና አልሚውን ታሪክ ወደፊት ይፍረደው እላለሁኝ። ሌለ ማሰብ ያለብን

ደግሞ ብዙዎቻችን ኢሕአፖ ከመመስረቱ በፊት የነበርንና የፍትሕን መጓደል የሃገራችንን የመሬት ሥርኢት ሲቃወሙ ተቶኩሰበቻ በወደቁት ወገኖቻችን ንጹህ ደም የነቃን እንጂ ኢሕአፖ ከተመሰረተ በኋላ ከፍውንና በጎውን ያወቅን ሰዎች አይደለንም ። በእርግጥ ወደታቀደው ዓላማ ለመድረስ በግንባር ቀደምትነት የሕዝብ መፈክሮችን የሚየስተጋበ ድርጅት ስለሚያስፈልግ ያም ሆኖ በኢሕአፖ መሪነት ፕሮግራሞች ወጥተው የሕዝብን ብሶቶችና መደረግ ስለሚገባቸው ተግባሮች አስመልክቶ ወረቅት መበተን ቅስቀሣዎች መደረግ ተጀመሩ። ይህም እያዋጣም ሌላ የኢትዩጲያን ሕዝብ ከረሃብ ከችግር ከጉስቁልና ከኋላ ቀርነት ወደፊት የሚያራምደው መንገድ አለ ብሎ በይበልጥ የሚያስተምር የሚማር ከሕዝብ ጎን የሚቆም ድርጅት ተመስርቶ ካለ የማንቀበልበትና አብረን የማንሰለፍበት ምክንያት የለም። ግን አሁን እንደሚታየው የነበረውን ደዝባውን ለማጥፋትና ጥቂቶችን በጥፋተኛነት ለመከነን መሯሯጦች ሲደረጉ እናያለን ይህም የተነሳንበትን ዓላማ አይገልጽም። ይበልጥ መታሰብ ያለበት ነገር ቢኖር ፖለቲካ ብቻውን የሕብረተሰብ ለውጦችን አያመጣም። ሁሉም ሰው ፖለቲከኛ መሆን የለበትም። ፖለቲከኛ ለመሆን የግድ የኢሕአፖ አባል መሆን አይኖርበትም። ማንኛውም ዜጋ በተሰማራበት ሁሉ ለሕዝብ መሰረታዊ ለውጦችንና እድገቶችን የሚያመጡ ተግባሮችን የሚፈጽም ከሆነ የፖለቲካ ሥራም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም።አሁንም በየጊዜው በሚነሱ አዳዲስ ሐሣቦች ፍጭቶችን እያደረግን ከሐሣቦች እጥረትና ከልምደች ማነስ ከአልሸነፍም ባይነት በጭፍን ግትርነት ልዩነቶችን እያሰፋን የምንሄድ ከሆነ ከምንም አንደርስም። በዚህን አይነት የምንቀጥልም ከሆነ የመሥራት ፍላጎታችንን ገለን እራሳችንም ችግር ላይ ወድቀን የሃገር ሕልውና የሕዝብ ብልጽግና የሚለው ቃል ይጠፋና ከሰው እንበ ሄደን መሣቂያ መሣለቂያ እንሆናለን። ደግሞም ከሕዝብ ወገን ሆነን እንማራለን እናስተምራለን ስንል ከመንግሥት ደመወዝ ተከፍሎን ሣይሆን በእራሣችን ፍላጎት ተነሣስተን ነው። በዚህን አይነት እንቀጥልም ብለው የተገነጠሉት ጓደኞቻችን ቀድሞውንም ቆርጠው ያልገቡበት ስለሆነ እርፈው መቀመጥ ይችላሉ ። አልቆረጡም የሚለውን ኃይለ ቃል የተጠቀምኩትም ስለተገነጠሉ ለማቋሸሽ ሣይሆን ከዚያን በኋላ በሚያሙኑበት መረሆ ተደራጅተው ከሕዝብ ጎን ሲቆሙ ባለማየቴ ነው። አሁንም እያነዳንዳችን ያለብን ሃፊነት ዋሮ ማለፍ ሣይሆን አባቶቻችን በጣሉት መሠረት ላይ እኛም እየገነባን ማለፍ ግዴታችን ሲሆን ይህ ሣይሆን ቀርቶ መጭውን ትውልድ በችግር ላይ ጥለነው ካለፍን ያኔ ነው ማናችንም ብንሆን ከታሪክ ወቀሣና ስለቃ የማናመልጠው።በአጠቃላይ ድርጅታችን በጣም ከፍተኛ ውጥረትና ተፈታታኝ የሆኑ ሁኔታዎች ገጥመውታል። በቀድሞው የአሰራር ዘዴ መቀጠሉም አደጋዎችን እያመጣ ነው። ይህንን ሁኔታ ለመቋቋም የአሰራራ ዘዴዎቻችንን ለመቀየር ተገደናል። ድርጅታዊው ድስፕሊናችን ከወትሩም ትኩርት እንዲኖረው ተስማምተናል።



ስለፖርቲው ሂሰና አስተያየቶችን ለመስሚ ውስጠ ፖርቲ ጋዜጣ እንዲኖረን አድርገናል የሚታያችሁን መግለጽ ትችላላችሁ» በማለት ውይይቱ አበቃ።

ከበላይ አካል የመጣው ግለሰብም የድስፕሊን መጠበቁን ሁኔታ ትኩረት ቢሰጠውም፣ እንደታሰበውም ሊሆን አልቻለም። እንዲተላለፉ የተሰጡ ወረቀቶችን ለተፈለገው ሥፍራ ከማድረስ ይልቅ በቁሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል፤ አንድ ለአንድ መገናኘት ሲኖርባቸው ሌላ ግለሰብ ይዞ መምጣት፤ ድርጅታዊ ተግባሮችን ላለመሥራት ምክንያቶችን መደርደር፤ አንዳንዶችን ቀጠሮ የተሰጣጡባቸውን ሥፍራዎች አስቀድሞ ለአፋኝ ጓዶች በማሣወቅ ማሲያዘች፤ ለበላይ አካል መድረስ የሚገባቸውን መልክቶች አንሾልጦ ቀደ መመልከት የመሰሉ አስነዋሪ ተግባሮች መፈጸም ጀመሩ። እንደቀድሞው ሰዓት አክብሮ ከቀጠሮ ሥፍራ መገኘት እያሰጋ መጣ። እማራጭ የነበረው ከሥፍራው ቀድሞ መገኘት ወይም ዘግይቶ መሄድ ነበር። ቀደም ሲል ካድሬዎችንና አፋኝ ጓዶችን ለመለየት ለኢሕአፖ ሰዎች እንብዛም ከባድ አልነበረም። ውድ ጫማዎቻቸውና የቆዳ ጃኬቶቻቸው ጥሩ መለያዎቻቸው ነበሩ። አፋኝ ጓዶችንም ቢሆን በሚይዟቸው ቀይ ማዝዳ ዋ ቀይ ፊያት መኪናዎች መለየት ይችሉ ነበር። ውሎ አድሮ ግን ሁኔታው የተገለባበጦሽ ሆነ። ዘመናዊያን ባስጠኗቸው መሰረት ለካድሬዎች ለቀበሌ ተመራጮች ለአፋኝ ጓዶች የኢሕአፖን አባሎች ሁኔታቸውን በመመልከት ብቻ ከሕዝብ ውስጥ እየመረጡ ያወጧቸው ጀመር። ለምሳሌ ጺሙን ያሣደገ ፀጉሩን በአጭር አፍሮ የተስተካከለ ሰሪያን ካኪ ኮት ከለበሰ ጫማዎቹ ጠመም ካሉ የተጎሣቆለ ሰውነት ካለው ያለ ምንም መጠራጠር የፖርቲው አባል ስለሚሆን ካለበት ይመታል። ለጋ ወጣት አፍሮ ያበጠረ ሲሄድ ፈጠን ፈጠን ካለ በየመንገዱ ሰዓት ከጠየቀ እርሱም ከወጣቱ ሊግ ውስጥ ስለሚመደብ ወዲያውኑ ተከቦ ይያዛል። ፀጉሩን በአጭር የተስተካከለ ወይም የተላጭ በስኳድ አባልነት ስለሚጠረጠር ከዚያኑ ይመታል። ልጃገረደች ደግሞ የዘመቻ ሱሪያቸውን ከለበሱ አፍሮ ከአበጠሩ የአደሬ ነጠላ ከለበሱ በወጣቱ ሊግ ውስጥ ስለሚመደቡ ተከበው ይያዛሉ። ሌላው እንደእናቶች ከጉልበታቸው በታች ወረድ ያለ ቀሚስ ከለበሱ ፀጉራቸውን በሻሽ ወደኋላ ሸብ ከደረጉ በእጃቸው ዘንቢል ከአንጠለጠሉ በፖርቲ አባልነት ስለሚመደቡ ከዚያኑ እርምጃ ይወሰድባቸዋል። በተጨማሪ የዜናዎች በትክክል ለአባላት ያለመድረስ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚችሉ ሁኔታውች ሣይደረግባቸው በመቅረቱ ብዙ ጉዳትን በድርጅቱ ሊያመጡ ችለዋል። ዜናዎችም መዕከላዊነት እንዲያጡና በአንደኛው ክፍል የተወራው በሌላው ክፍል ውሸት ሆኖ እንዲረጋገጥ በማድረግ ድርጅቱን ወደተራ ወሬ አስፋፊነትም መልክ እንዲኖረው ጥረትም ተደርጎበት ነበር። ያም ሆኖ ዜናዎች መዕከላዊነት እንዲኖራቸውና የተረጋገጡ መሆናቸውን ለማወቅ ለበላይ አካላት በእንቭሎብ ታሽገው እንዲቀርቡ የማድረጉ ሁኔታ በጊዜው እንደመፍትሔ ተወሰደ ነበር።

## ፲፮

ወራቱ ሐምሌ ዓመተ ምህረቱ ፷፱ ነበረ። በደርግና በሕኢአፖ መካከል ይደረግ የነበረው ፍልሚያ ግብ ያለ ሲሆን በኢሕአፖ አባላት መካከል ይደረጉ የነበሩት የፖለቲካ ፍጭቶች የተፋፋሙበትና ኢፋ የወጡበት ወቅት ነበር። በድርጅቱ ታቅፈው ከነበሩ ብዙሃን ድርጅቶች ጥያቄዎች ይጎርፉ ጀመር። የሶማሊያን ወረራ አስመልክቶ ስለረሺያኖች በኢትዮጵያ መግባት፤ ስለ ኤርትራ ጦርነት ስለኢትዮጵያ ዲሞክራትኪ አንድነት ስለግንባር ጥያቄ ስለከተማው የትጥቅ ትግል ድርጅቱ ያለውን አቋም እንዲገልጽ ጥያቄውች በአባላት በሚወኩሏቸው ግለሰቦች በኩል ይቀርቡ ጀመር። በወቅቱ ድርጅቱ ለቀረቡት መጠይቆች ያለውን አቋም ቢገልጽም በትክክል ለጠያቂው ክፍል መድረሳቸው አጠራጣሪ ሲሆን ቢደርሱም እንኳን እንዳለፉት ጊዜያት ተቀባይነታቸው ሙሉ በሙሉ አልነበረም። መለያየቶች ስለነበሩ እንደኛው ክፍል የራሱን መስመር በሚየጠናክርበት መንገድ ትንታኒዎችን ሲሰጥባቸው ፤ ከነበረው ውጥረትም አንፃር እውነተኛነቱ ቢታመንበትም እምኖ መቀበሉ ያስፈራበት ውቅት ነበር።

ምንም እንኳን መጠይቆቹ አብዛኛዎቹ በፖርቲው ፕሮግራም ውስጥ በቂ ማብራራያ የተሰጣቸው ቢሆንም ዳግም ከሌሎች መጠይቆች ጋር መቅረባቸው ያለምክንያት አልነበረም። የድርጅቱ ተፃራሪ ወገኖች ያንን አስጊና ቀውጢ ጊዜ ጠብቀው በጣም አገብጋቢና ለድርጅቱ መኖር ያለ መኖር ወሳኝ የሆኑ የፖለቲካ መፈክሮችን በማንሣት ጀመሩ። አልፎም ሕዝቡ የማይቀበላቸውንና የሚያስቆጡትን መፈክሮች እየመረጡ ድርጅቱ ከሕዝቡ ለየት ባለመንገድ እንደተቀበላቸው ለበታች አካላት ቅስቀሳቸውን ጀመሩ። ለምሳሌ የኤርትራ ሕዘብ ጥያቄ እንደ ቅኝ ግዛት ጥያቄ ተቀብሎታል በማለት ያልሆነ ቅስቀሳ ሲየደርጉ በአኳያው ደግሞ የሶማሊን ኢትዮጵያን መውረርን እንደሕጋዊነት መቀበሉንም ሣይገልጹት አልቀሩም። ሆኖም ግን ሁኔታውን በጥንቃቄና በትዕግስት ሲመረመር ኢሕአፖ የኤርትራን ሕዝብ ጥያቄ በዲሞክራሰዊ መንገድ ይፈታ ከማለት ሌላ በየትኛውም ወረቀቱ ከዚህ የተለየ አስተያየት የሰጠበት በታ የለም። የሶማሊያን ወረራ አስመልክቶ በልሣኑ በዲሞክራሲያ ቅጽ ፩ ቁጥር ፱ ታሪክን ምርኩዝ በማድረግ ሰፊ ባለመንገድ ማብራሪያዎችን ሰጥቶበታል። በተጨማሪም የሰማሌን መንግሥት የሚያወግዝና ብሎም በሃገሪቱ ወስጥ ለዲሞክራሲያዊ መብታቸው የሚታገሉትን የሕዝብ ክፍሎች እንቅስቃሴ ለማክሸፍና ለማመከን ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ ሴራ መሆኑን በማውገዝ በጹሑፍ ለተባበሩት የአፍራካ አንድት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ሲያቀርብ ግልባጨን ለአባለት በወቅቱ በትኗል። ሆኖም ግን በግንኙነቶች መቋረጦች ምክንያት ብዙዎቹ ዜናዎች ለአባላት አይደርሱም ነበር። የረሺያኖችን በኢትዮጵያ መግባት አስመልክቶ



በአጠቃላይ ድርጊቱ በአንድ ሃገር ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ከመግባት ተለይቶ የሚታይ ያለመሆኑን ጠቀሞ በሶሽል ኢፔራልዝምነቱ አውግዞ ትንታኔዎችን ሰጠበት። ከደርግ ጋር ግንባር ለሚለው ቀደም ሲል መልሶችን የሰጠበትና መሚሳት ያለባቸው ሁኔታዎች የጠቆመ ስለሆነ አልተመለሰበትም። ግን የኢሕአፖ አባሎች ምንም እንኳን በግልጽ የሃገራቸውን ወራሪዎች ለመከላከል ከደርግ ባይሰለፉም ከማንኛቸውም ሃገሪቷ ውስጥ ከሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች በላይ የሶማሊያን ወረራ ለማክሸፍ አስተዋፆአ አበርክተዋል። ለምሳሌ በደቡብ ክፍለሃገራት ሕዝቡን ወዳጅና ጠላቱን እንዲለይ እናደርገዋለን እርስ በእርስ የሚደረገውን ጭፍጨፋ እናቆማለን በማለት ከሃገሬው በመሰለፋቸው የደርግ ሰላዩች እየተባሉ የፍጥኝ ከዛፍ እየታሰሩ በጥይት የተደበደቡ ብዙ የኢሕአፖ አባሎች ነበሩ። የሶማሊያም መንግሥት ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች ምንም ከደርግ የተለየ አመለካከት አልነበረውም። እንደውም አልፈው ተርፈው ሕዝቡን እንደሚያስነሱባቸው በመጠራጠር ሰርጎ ገቦቹም አስቀድመው ሕዝቡን ይጠይቁት የነበረው ጥያቄ ቢኖር ተማሪዎች በአካባቢያቸው መኖር ያለ መኖራቸውን ነበር።

የደርግ መንግሥት የሶማሊያን ወረራ በማስምርከዝ በሃገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ድርድቶች «እናት ሃገር ተወረረች» በማለት ጥሪውን ሲየደርግ በእርግጥም ከልብ የመነጭ ሣይሆን በሃገር ስም ይቃወሙትና ለዲሞክራሲ መብቶች ለሕዝባዊ መንግሥት ይታገሉ የነበሩትን ድርጅቶች ከሕዝብ ለማጣለትና በሥልጣን ለመቆየት ሆን ተብሎ የተቀየሰ ዕቅድ ነበር። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቀው ለወረራውም ሆነ ለዚያ ሁሉ የሕዝብ እልቂት በጊዜው በሥልጣን የነበረው መንግሥትና እጅና ጓንት ሆነው አብረውት ይሥሩ ከነበሩት ግለሰቦች ሌላ ማንንም አያስጠይቅም። ወረራውም ቢሆን ከኢትዮጵያውያን ጦር ቁጥጥር አልፎ ተርፎ የውጭ ሃገር ጦር ወደ ሃገር የሚያስጋብዝ አልነበርም። የሰማሌን ወረራ አጋኖና ሃገር ፆቆረሰል ብለው ያአሰቡ የነበሩ ቢኖሩም በውቅቱ የተመቻቸው ከለውጡ የተጠቀሙና የሃገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው የማየውቁ ክፍሎች ብቻ ይሆናሉ። እውነቱ ቢነገር መደበኛው ሠራዊታችን በልብ ሙሉነት አልተዋጋም። የወታደሩ ዲሲፕሊን እንደቀድሞው አልነበረም። የበላዩን እጅ ወደላይ እያለ ማሰር ከጀመረ በኋላ እንዴትስ ተመልሶ የበላይ ትዕዛዝ ይቀበላልስ የበላይስ እንዴትስ ደፍሮ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል ሁኔታው እንዲያው የፉከከር ቤት ሣይዘጋ አደረገን ይመስላል። በአጠቃላይ በጦሩ ውስጥ አለቃና ምንዝር የጠፋበት ወቅት ስለነበረ የውጪ ጠላት መግባት ሊያስደንቀን አይችልም። የሚያስደንቀው ግን ለጊዜአዊ ጥቅም ብሎ የትውልድን ታሪክና ኩራት አፈር አልብሶ ያለውንም እንገቱን አስደፍቶ በነፃንት ተወልደው በነፃነት የምቱበት ሃገር ልጆች ናቸው ተብለው በምሳሌነት ሲጠቀሱ ፊሳቸውን ቀና እንዳሳደረጉ ዛሬ ሲሽማቀቁ ማየቱ ነው። አሁንም

ሕዝቡ እርሱ ነው እርሷ ነች የሚለው የውሸት ምክኒያቶች አቅራቢዎችንና የእዘ እንበ እልቃሾችን ወደጎን ተወት አድርጎ የራሱን ችግር በራሱ ለመወጠት መሞከርና ሊሸም ሊሽራቸው የሚችለባቸው መሪዎች ከልመረጠ በሃገሩ ስም ዘለዓለም ሲሰቃይ መኖር ያለመፈለጉን በእንድነት ካልተቃወመው ጦርነቶች ይቀጥላሉ። በወቅቱም የሕዝብ ወገኖች እስተሳሰብ ከዚህ የተለየ አልነበረም።



## ፲ ፪

በእጠቃላይ የሶማሊያ ኢትዮጵያን መውረር የምሁራን ከደርግ መንግሥት ተገንጥሎ መከብለል፤በኢሕአፖ አባላት መካከል ልዩነት መፈጠር፤ የደርግ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚያስተዳድር ጥሩ ማስተማማኛ ሆኑት። ሕዝቡም የራሱ መዉቶን፤ የልጆቹ በየመንገዱ እየተገደሉ መጣል ከጉያው እየተወሰዱ መታሰርና መበረር ቢያበግነውም ፤ የሃገሩ ሁኔታ ደግሞ ፍጹም የማያልፈው ጉዳይ ስለሆነ በሃገር ስም ከነበረው መንግሥት ጋር ተሰለፈ።መንግሥቱም ተቋሚዎችን በሙሉ እስወግደ በራሱ የቆመበት ወቅት ስለነበረ የማንም ፀይል ቢመጣ አይበግረኝም በማለት በልዩ ልዩ ስብሰባዎች ስሜቱን ገለጸ። የተቋሚዎቹን ደም እንደሚያፈስ ቀይ ቀለም የተሞሉ ጠርሙሶች ከመወርወር እስከ ሦስት መቶ ሺ ወታደር የሰሽየትን መሣሪያ በማስታጣቅ በመስቀል አደባባይ በሰልፍ እዲያልፉ እስደረገ።የከተማውንም የሕዝብ ቅዋሜዎች ለመግታት የቀድመውን የእግሪካንን መሣሪዎች ለአብዮት ጠባቂዎች አስታጠቀ።ሃገሪቱ በየትኛውም አቅጣጫ መሣሪያ በመሣሪያ ሆነች። በጊዜው ከማንኛዎችም ጠላት ተብለው ከተጠቀሱት ክፍሎች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውና መጥፋት እንዳለበት የተወሰነበት ኢሕአፖ ነበር። ያም ሆኖ በርቀት ከሚያጠቃን ጠላት ይልቅ በቅርብ ሆነው የሚያጠቁንን ጠላቶቻንን ማስወገድ ይኖርብናል በማለት ዘመቻው በሃገሪቱ በሚገኙ ትልልቅ ከተማዎች ቀጠለ።

በጥላናቸው መሰረት ኢሕአፖን ለማጥፋት በውስጥ ሃገር ትልቅ እሰሳዎችና ግድያዎች ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ እንዲከሄዱ ተወሰነ። እሰሳዎችም ቀን መሆናቸው ቀርቶ ለሊት መደረግ ጀመሩ። የወጣቱም ሊግ በየቀበሌው የኡኡታ ከሚቴ እቷቷሙ እሣሾች ከእንዱ ቀበሌ ሲገቡ የተቀረው ኡኡታውን ያቀልጠው ጀመር። አዲስ አበባ ጩኸት በጩኸት ሆነች። የቀኑም እሰሳ እንደቀድሞው በእጠቃላይ መሆኑ ቀርቶ በዘን ተከፍሎ ኃይላቸውን በእንድነት እጠናከረው ሲሆን በጣም በምስጢር የተጠበቀና ዱብዳ ነበር። ለወትሮው እሰሳዎች ሲታቀዱ እስቀድመው ስለሚሰሙ በተቻለ መንገድ ሁሉ ጥንቃቄዎች ይደረጉ ስለነበር በኢሕአፖ አባላት ላይ ከቀድሞው የተለየ አደጋ እይደርስባቸውም።

ለምሳሌ እውነቱ አንድ ከገጠር ግንኙነት ተቋርጦበት ከመጣ ጓደኛው ጋር የመኝታ ክፍል ይዘው ሳለ ቀበሌዎች ክፍሎችን እያስከፈቱ መታወቂያ እየጠየቁ የሌላችውንም ሆነ የሚጠራጠሩትን እየመረጡ ሲወስዱ ያየው የእለጋ ቤቱ ሠራተኛ ያለመታወቂያ ክፍሉን ማከራየቱን ስለሚያውቅ በእስቸኳይ ሕይወታቸውን እንዲያድኑ ይነግራቸዋል። ባእጋጣሚ የእውነቱ ጓደኛው የስኳር በሽታው ተነስቶበት ስለነበር ሌሊቱን ሲያመው ስለአደረ ጠዋት ለመነሣት አልቻለም። እልጋ ቤቱም እርሱን እንዳያስገኘው

ተነሥተው እንዲወጡለት በልመና መልክ ተማጠናቸው። ጌትነትም ፍጹም ሊቀሰቀስ ስለአልቻለ እውነቱ ራሱን እንዲያወጣ እርሱ ግን በመሞቱ ወስኖ ከክፍሉ ለመቅረት መረጠ። እውነቱም ቢሆን በዐይኑ እያየ የደህና ጊዜ ጓደኛውን በዚያን የችግር ወቅት ተቶት ለመሄድ ልቡ ስለአልቆረጠ ፤ በተቻለው መንገድ ሁሉ አሰምኖ ከአካባቢው ይዘት ሊሄድ ፈለገ። በተለይ ለአልጋ ቤቱ ሠራተኛ ሲል ከነበሩበት አካባቢ ይልቅ በመንገድ እየሄዱ መገደሉን መርጠው ከክፍሉ ይወጣሉ። አካባቢው በአብዮት ጠባቂዎችና በወታደሮች ተከቧል፤ ለወትሮው በጠዋት ይከፈቱ የነበሩት መጠጥ፣ ምግብ ቤቶች ተዘግትለዋል፤ በመንገድ አውቶቡሶች የቤት መኪናዎች አይዘዋወሩም፤ ታክሲዎች ሰው ካሣፈሩ ተሳፋሪውን አስወርደው መታወቂያውን እንዲያሳይ ይጠየቃል፤ ከሌለው ተይዞ ይወሰዳል ወይም ከተጠራጠሩትም ከዚያው ይመቱታል። ጠቋሚዎችም ከአሣሾቹ መካከል ስለሚኖሩ የሚያውቁትና ከእነርሱ ክፍል ካልሆነ ያለምንም ጥያቄ እርምጃ ይወሰድበታል። ሁለቱ ጓደኛሞች እርስ በእርሳቸው እየተጽናኑ የቡና ቤቱ ሠራተኞች በመምሰል በጓሮ በር ወጥተው ከአንዲት ጠላ ቤት ይገባሉ። ከዚያንም አሣሾቹ ባለጠላ ቤቷን ጠጭውን እንድታስወጣና እንድትዘጋ ነግረዋት ወደሌለኛው ቤት ሲያመሩ የወጣቶቹን በችግር ላይ መሆን ተረድታቸው፣ ምንም ሳትጠራጠራቸው እኔም እናንተን የመሰሰሉ ወንድሞች አሉኝ ብላ ከመኝታዋ ክፍል አስገብታቸው መጋረጃውን ጋርዳቸው በሩን ከውጪ ዘግታባቸው ከጎረቤት ትሄዳለች።

በዕለቱም እሰሰ አራት ወጣቶች ሲገደሉ በጥርጣሬና የመታወቂያ ወረቀት የሌላቸው ብዙ ሰዎች ተይዘው ከእስር ቤት ተጨመሩ። ከአራቱ ወጣቶች አንደኛው ዳቦ ከሌላ አካባቢ ገዝቶ በወረቀት ጠቅልሎ ወደ ወለጆቹ ቤት ሲገባ የተመለከተ የአብዮት ጠባቂ የሚበተን የኢሕአፖ ወረቀት ነው በማለት ተኩሶ ይገለዋል። አንደኛውንም ወጣት ተጠቁበትም እንደሆን አይታወቅም በዚያን ጭር ባለመንገድ መሣሪያቸውን ዘቅዝቀው ሲከተሉት ወጣቱም እንደሚከተሉት ተረድቶ ወደፊቱ ተሰፋ በቆረጠና በሚያሣዝን ሁኔታ ሲራመድ አንዳንዴም ገልመጥ ብሎ እየተመለከተ ውልምጥ ውልምጥ ሲል ከሚከታተሉት አንደኛው ክላሽኮብ ጠብመንጃውን አነጣጥሮ ቃታውን ቢስበው ጥይቷ ከወጣቱ እናት ላይ ስታርፍ በአፍ ጢሙ ተደፍቶ ትንሽ ሲፈራገጥ ከታየ በኋላ ጸጥ አለ። ገዳዩም ትልቅ ጀብዱ እንደሰራ በእናቱ ላይ በደፋው ኬፑ ፈቱን ሸፍኖ የመሣሪያውን ማጥበቂያ መልሶ በማንገቻው አንግቶ እየተወጣጠረ ወደሕዝቡ ተመለሰ። ባለጠላ ቤቷም የሁኔታውን መረጋጋት ተመልክታ ጌትነትንና እውነቱን በሩን ከፍታላቸው በጊዜ ማደሪያቸውን እንዲፈልጉ አሰናበተቻቸው። ያም ሆኖ በማግሥቱ ያለፈውን ቀን ግድያና እሰሰ የሚያወግዙ ጹሑፎች በየመንገዱ ላይ ተበትነው ሲታዩ በወጣቶቹም ላይ ግድያ የፈጸሙት ግለሰቦቸ በኢሕአፖ ጥይት የወደቁ አብዮተኞች ተብለው በጋዜጣ ይወጣል በቴሌቭዥን ይታያል



# ፲፫

ኢሕአፖን ለማጥፋት የተደረጉት ማናቸውም እርምጃዎች የተፈለጉትን ኢላማዎቻቸውን ስለአልመቱ በሕዳር ፸ ዓመተ ምህረት «ነፃ እርምጃ» በአዋጅ ተፈቀደ፤ ግድያዎች ያለገደብ መደረግ ጀመሩ።የሰው ሬሣ በየመጋጠሚያ መንገዶች፣ አደባባዩች፤ ከትልልቅ ቡና ቤቶች ደጃፍ፤ ከአውቶቡስ መሣፈሪያዎች ላይ ተጥሎው ይታይ ጀመር። የኢሕአፖ ደጋፊ የነበሩት ወጣቶችም በየዕለቱ ሲገናኙ የመጀመሪያ ዜናቸው ስለቀድሞው ጓደኛቸው ሞቶ መገኘት ወይም ስለአጋጠማቸው የሬሣ ቁጥር ነበር። ከመኪና ወርደው በደህና የሚጓዘውን ሕዝብ ከመምታት ሌላ ከእስርቤት አውጥተው ገለሰቡ ይሰራበት ከነበረ መሥሪያ ቤት ደጃፍ ወስደው ሲገድሉ ተማሪም ከሆነ እባቱ ከሚሰራበት አካባቢ ተወስደ ይመታል።

አንድ ቀን እውነቱና ጌትነት ከመርከቶ ከውጭ ደርድረው ከሚሸጡ መደብሮች ቆመው ሳሉ አራት ወጣቶች በጅብና በእግረኛ ወታደር ተከበው መጥተው የፍጥኝ እንደታሰሩ ፊታቸውን ወደ ግንቡ እስመልሰው በጥይት ይደበድቧቸዋል፤ ሕዝቡም መደብሩን እየዘጋ ከአካባቢው ይሄዳል። ለምን ያ አካባቢ እንደተመረጠ ሲጠየቅ የአንደኛው ሟች ወንድም ከዚያን ነጋዴ እንደነበር ተነገረ።

የ«ነፃ እርምጃ» አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በማንኛውም አከባቢዎች ሥራዬ ብሎ ለተከታተለው የተወሰነ የሬሣ ቁጥር ተጥሎ ይገኛል። የሬሣውም ብዛት እንደአካባቢ የትራፊክ ብዛት ይሆናል። ለምሳሌ በሐብተጊዮርጊስ ድልድይ፣ በተክለሃይማኖት አካባቢና በአራት ኪሎ የሚጥሉት የሬሣ ቁጥር አንድ አይሆንም። ከሐብተጊዮርጊስ ድልድይ ቀን በቀን ተመላለሹ ሕዝብ ፊት ከሚገሏቸው ወጣቶች ሌላ ከሃያ እስከ ሰላሣ ወጣቶች ተገለው ተጥለው ሲገኙ ከአራት ኪሎ ግን ከዚያ ብዛት ዝቅ ያለ ይሆናል።የቡና ቤቶች ደጃፎችና የሕዝብ መሰብሰቢያ አካባቢ ዋና የ«ነፃ እርምጃ» መውሰጃ ሥፍራ ነበሩ ።

እውነቱ ከጓደኛው ከዐባይ ምንጭ ቡና ቤት በር ላይ ተቃጥረው ኖሮ ሁለቱም በሰዓቱ ከስፍራው ይገኛሉ። ወደቡና ቤቱ ለመግባት እየተራመዱ ሳሉ አካባቢው ከመቅጽበት በታጠቁ አበዮት ጠባቂዎችና መድፍ በተጠመደባቸው ጅቦች ይከበባል። ዘልቀው ወደቡና ቤቱ እንዳይገቡ ሠራተኞቹ እንዲዘጉት ተነግሯቸው ኖሮ ጠጪው እየወጣ ስለነበር፤። ወደመጡበት እንዳይመለሱ አካባቢው በአራቱም ማዕዘናት ተከቧል።ከወደ ሐብተጊዮርጊስ ድልድይ የሚመጡት ተሽከርካሪዎች ከቁጭራ ባንክ እንዲታጠፉ ተደርጓል፤ ሽቅብ ወደ ክፍለሃገር አውቶቡስ ጣቢያ እንዳይኬድ የገባም እንዳይወጣ ከውጭም እንዳይገባ መትረየስ ተጠምዷል፤ አንድ ለሕዝብ

የተሰቀለች ቴሌቭዥን በኩል ሽቅብ እንዳይኪድ የታጠቁ አብይት ጠባቂዎች ቆመዋል። ሙሉጌታና እውነቱም ዐይን ለዐይን ተያይተው ከጥርስ ቻቸው ፈገግ ይላሉ። ባይናገሩትም ለእነርሱ የመጡ መሆናቸውን ያረጋገጡ ይመስላሉ።ቀጠሮአቸው ወረቀቶች ለመቀባበል ስለነበር የሁለቱም የኮት ኪሻቸውን ትኩር ብሎ ለተመለከተው አንድ ነገር እንደያዙ ለመገመት ያስችላል። ብዙ ጊዜ ወጣቶች እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥማቸውና ኢላማቸው እነርሱ መሆናቸውን ከአረጋገጡ መሣሪያ ካላቸው አስፈራርቶ ማምለጥ ወይም በሆነው መንገድ በራስ ላይ እርምጃ መውሰድ ነበር።ወጣቶቹም ሁኔታውን በጥንቃቄ ሲጠባበቁ አንዲት ቀይ ማዝዳ መኪና ከወደ ፒያሣ ክላክስ እያሰማች ከሥፍራው ትደርሳለች። ወዲያውኑ ከመቅጽፈት አንድን ወጣት መልኩ ይህን ይመስላል ብሎ ለመጥቀስ የሚያስቸግር የፍጥኝ በሲባጎ የታሰረ፤ከመኪናው ውስጥ አውጥተው ከጣሉት በኋላ አቶማቲክ መሣሪያ አውጥተው ቶክስ ይከፍቱበታል። ሰውነቱን ወንፊት ያደርጉታል። እውነቱና ሙሉጌታም ተጠግተው አስከሬኑን ሲመለከቱት እግሮቹ ጉበት መስለዋል፤ በእሣት መቃጠላቸው ወይም በፈላ ዘይት መጠበሳቸው አያጣራጥርም። የእጆቹ ጣቶች ተቆርጠዋል። ሕዝቡም እንዲመለከት ስለተፈቀደ እናቶች እየተጠጉ ፊቱን እየተመለከቱ «የእኔ ልጅ ይሆን? ለለየው አልቻልኩም» በማለት እንባቸውን በማዝራት ይመለሳሉ። እውነቱም ለሙሉጌታ የአስፈው ሞት ሲያገበግበን እንደበሽተኛ ውሽ የሰው ሬሳ በየአውራ ጎዳናው ከሚጣልበት መጣን ሲልው እኛም ወደዚያው ነው የምንጓዘው በማለት ይመልስለታል።

የ«ነፃ እርምጃው» ዋና ዓላማው የኢሕአፓ እውነተኛ ተከታዩቹን ለማጥፋት ብቻ ሣይሆን በይመስላል የሚጠረጥሩትን ጭምር ለማጥፋት የታቀደ ዕቅድ ቢሆንም በተግባር ፈጻሚዎቹ ዘንድ ሲደርስ ደግሞ ልዩ ልዩ ተቀጥላዎችን አስከትሏል።ይሄው በኢሕአፓ ስም ሴቶችን የ«ነፃ እርምጃ» እንወስድባችኋለን በማለት ያለፍላጎታቸው የወሲባዊ ግንኙነቶችን መፈጸም፤ አሽፈረኝ ያሉትንም አልተባበር አሉን በማለት የግድያ እርምጃ መውሰድ፤ ጥሩ መኪና የሚያሽከረክሩ ውድ ሰዓቶችን ያሰሩ ንጹህ ልብሶችን የለበሱ ቀኑ ደገዝገዝ ሲል ካገኙ ያለምንም ርህራሄ ገድለው ንብረት መዝረፍ የዕለቱ ትዕዛዝ ነበር።

የኢሕአፖን አባላት ለማጥፋት የወጣው የ«ነፃ እርምጃ» አዋጅ ከውጤቱ ሲታይ ግን ግቡን የመታ አይመስልም።እርምጃውን ወሳጆቹ ክፍሎች ይበልጥ ያተኩሩት ንብረትና ሴት ላይ ስለነበር በትልልቅ ቡና ቤቶች አካባቢ እያደፈጡ ለመዝናናት የሚሄዱትን ግለሰባች በመግደል «ነፃ እርምጃ ይፋፋም» የሚለውን ጽሑፍ በማስቀመጥ የዕለቱን ተልክአቸውን ይፈጽማሉ። በተለይ ከመርካቶ ጫጫታ ከአራት ኪሎ ውኸንብር ከካዛንቺስ ይሽለናል በማለት



የወይዘሮ በቀለችን ክትፎ ተመገበው አዝናኙን የእነአሥናቀችን ሙዚቃ ለማዳመጥ የሚሄዱትን ግለሰቦች እየጠበቁ እርምጃ እየወሰዱ «ነፃ እርምጃ ይፋፋም» የሚለውን ጽሑፋቸውን አስቀምጠውባቸው ይሄዳሉ። ለምን ከካዛንቺስ ሊሆን ቻለ በማለት በጊዜው ሲጠየቅ ብዙ ቅምጦች ከዚያን ስለአሏቸው ሕዝብን ከአካባቢው ለመግታት ሆን ተብሎ የታቀደ እንደነበር ይነገራል። እንደዚያን ያለ አካባቢ በእርነሱ አጠራር ከ«ኢሕአፖ የነፃ አካባቢ» ተብሎ ይጠራል።

የጊዜውን ውጥረትና ብሶት ለመግለጽ የሚዘፈነው ዘፈን ይህን ይመስላል።

ባንቢስን ግን ባሸገረኝ፤
ካዛንቺስ ጉዳይ ነበረኝ።

በሌላ አንፃር በ«ነፃው እርምጃው» የተጎዱት ከየክፍለሃገሩ ለፖለቲካ ትምህርት ተመልምለው የመጡ ወጣቶች ሲሆኑ እነርሱም ቀን የተማሩትን የመደብ ትንታኔ ከስድስት ኪሎ ወደ አራት ኪሎ እየተከራከሩበት ሲሄዱ የኢሕአፖ አባሎችን አገኘናቸው በማለት እየገደሏቸው የተለመደውን ወረቀት አስቀምጠውባቸው ይሄዳሉ። በተለያየ አካባቢ የተለያዩ የ«ነፃ እርምጃ» አወሳሰድ መመሪያ እንዳለ ለመግለጽ እንጅ በቀሩት አካባቢ ግድያ አይካሄድም ለማለት አይደለም።

## ፲፬

ዕለቱ ከተራ ወራቱ ጥር ፫ ዓመተ ምህረቱ ነበር። ምዕመናን መርከቶ የሚገኙትን ታቦታት አጅበው ነጋሪቱ እየተጎሰመ፣ ዲያቆናት እየዘመሩ ፣ ሕዝቡ እየጨፈረ ወደ ጃል ሜዳ በመጓዝ ላይ ሳሉ እውነቱ ጌትነትን ከስድስት ኪሎ አራት ጋብዞት ስለነበር እነርሱም ከሕዝቡ ተቀላቅለው አብረው ይጓዛሉ። ሕዝቡም ከሐብተጊዮርጊስ ድልድይ አካባቢ ሲደርስ በአራቱ ማዕዘናት በአብዮት ጠባቂና መትረየስ በተጠመደባቸው ጂፖች (ቋሚ ተጠሪ) ተከበበ፤ታቦታቱን የተሸከሙት ቀሣውስት፤ እንዳይራመዱ በታጠቁ ወታደሮች ታገዱ፤ታቦታትን በጭፈራ እያደመ ይጓዝ የነበረው ሕዝብ ጭፈራውን አቆመ፤ወጣቶቹ ለነሱ የመጡ መስሏቸው የሚያመልጡበትን አቅጣጫ ተመለከቱ። ዙሪያው ግን እንደአጥር በታጠቁ አብዮት ጠባቂዎች ተከቧል፤ የገባም አይወጣም ከውጭ ያለም አይገባም። ሕዝቡም በድንጋጤ «ታቦትን ያህል ነገር ያስቆመው ጉዳይ ምን ይሆን?» በማለት በአንክሮ የሚከተለውን ሲጠባበቅ። አንዲት ፍያት ቀይ መኪና ከወደ ፒያሣ አቅጣጫ ክላስክ እያሰማች መጥታ ከአፋፉ ላይ ከሚገኘው ከፋሲል ቡና ቤት በራፍ ላይ ሄዳ ስትቆም፤ከመቀጽበት አንድ ለጋ ወጣት እጆቹ የፍጥኝ ወደኋላ በሲባጎ የታሰሩ ከመኪናው ውስጥ አውጥተው ጥለውት፤እርሱም የሰውነቱን ክብደት መቆጣጠር አቅቶት በአፍ ጢሙ ሲደፋ፤ አንድ ረጅም የሲቪል ካፖርት የለበሰ ከለበሰው ካፖርት ኪስ ውስጥ ሽጉጡን አውጥቶ ከተደፋው ወጣት አናት ላይ ተኩስ ሲከፍትበት፤ ወጣቱም እንደታረደ በሬ ሲያጓራና ሲፈራገጥ ለሕዝቡም እገዳው ተነስቶ ጉዞ ሆነ። ሁኔታውን ያጤኑ አዘውነት ወደ ወጣቶቹ ዞር ብለው «አቡነ ጴጥሮስ ይህን የአረመኔነት ተግባር አላዩ፤»በማለት ወደፊት አመሩ። የነጋሪቱ ጉሸማ ቆመ ሕዘቡም አቀርቅሮ ወደ ጃል ሜደው ጉዞውን ቀጠለ።

እውነቱና ጌትነትም ድርጊቱን ተመልክተው፤ « ሕዝብን ለማስቆጣትና ምናልባት ቤተ ክሪስቲያናችን በአጠቃላይ በሃገሪቱ የሚካሄደውን ግድያ ይህን የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማደረግ ታወግዝ ይሆናል በማለት ሣይቀድሙን እንቀደማቸው ተብሎ ለማስፈራራት የተፈጸመ ይመስላል። ምን ያደርጋል ያለን አንድ አቡነ ጴጥሮስ ብቻ ነበር» በማለት ሮሮአቸውን ያሰማሉ።

እነርሱም ከሕዝቡ ነጠል ብለው በፒያሣ አካባቢ ሲሄዱ፤ አንዲት የቤት እመቤት ከመዝሸልድ እምድር ቤት በመስኮት የአንቲክ ዕቃ ስትመለከት፤ አንድ የኩዩባ ወታደር የደንብ ልብስ የለበሰ ጂፕ መኪና እየነዳ መጥቶ ከሱቁ በራፍ አቁሞ ሴትዮቱን ከመኪና ውስጥ ሊጭናት ሲተናነቃት፤ ባልም ከሱቁ በራፍ ቆሞ ይመለከት ኖሮ ከመቅጽበት ባልታወቀ መንገድ የኩዩባውን ወታደር መትቶ ሲዘርረው፤ አካባቢው መትረየስ በተጠመዱ ጂፖችና አብዮት ጠባቂዎች



ተከቦ፤ባልና ሚስት በአብዮት ጠባቂዎች ታጅበው ከከፍተኛ ሁለት ቀበሌ እስር ተወሰዱ። የወደቀው የኩዩባው ወታደር ከወደቀበት ተነስቶ ወደመኪናው እየሄደ ኢትዮጵያና ኩዩባ ወንድምአማቾች የቸው እያለ ከመኪናው ሲሰፈር ጌትነት ወደ እውነቱ ዞር ብሎ «የወንድም ሚስት የሚቀማ ወንድም አላየንም» በማለት ይናገራል። ባልና ሚስትም ከቀበሌ ከተወሰዱ በኋላ መታወቂያ እንዲያሣዩ በተጠየቁት መሠረት፤ባልየው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባልደረባ በሻለቃነት ማዕረግ መሆኑን የሚያመለክት መታወቂያውን ያሣያል። ቀበሌዎችም ሻለቃውን ሕግ አዋቂ ሆኖ ሕገወጥ ተግባር ለምን እንደፈጸመ ሲጠይቁት፤« ባለቤቴን ሊያጠቃት የመጣውን ወንጀለኛ መከላከሌ ሕግ ወጥ ሊያደርገኝ ይችላልን?» በማለት ይጠይቃል። «ደግሞስ ወንጀል የሠራውን ግለሰብ ለቃችሁ እኔንና ባለቤቴን ከቀበሌ ያመጣችሁበት ምክንያት አልገባኝም። ድርጊቱን እንደአንድ ሃገር ዜጋ ሆኖ ለተመለከተው በጣም የሚያሣዝን ነው፤» በማለት የተሰማውን ጥቃት ለመግለጽ ሲሞክር ከዚያው ከቆሙት አብዮት ጠባቂዎች አንደኛው ተሰምቶት «እኛን ጭቁኖች ምን አድርጉ ቱለናለህ? የእንናት ሰዎች ናቸው እንደዚህን እንድናደርግ መመሪያ የሰጡን» ብሎ የታየውን ሲገልጽ ፤ ወንበሩንም የያዘው የቀበሌ ተመራጭ በመቀጠል «ይህን መሰል ድርጊቶች ስናደርግ በራሣችን አነሳሽነት እንዳልሆነ እንድታውቁልን እሻለሁ። የዚህን ዓይነት ድርጊት ሲፈጸም ይህ የመጀመሪያው አይደለም። በዚህን ቀበሌ አብዛኛውን ጊዜ የምንደኘው ይህን መሰል ጉዳዮች ሲሆን፤እነዚህኑ ሰዎች ከዚህን በፊት የዚህኑ ዓይነት ተግባር ፈጽመው እምጥተን በቁጥጥር ሥር ብናውላቸው በአስቸኳይ እንድንለቃቸው ከደርግ ጽሕፈት ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶን፤ እንደውም እንደንተባበራቸው በሰርኩለር ተላለፈልን።» ሻለቃውም በመናደድ «ማነው መመሪያውን የሰጠው በማለት ሲጠይቅ» ከደርግ የአስተዳደር ክፍል መሆኑን ሲገለጽለት፤ «ግለሰቡን ነው ለማወቅ የፈለኩት» በማለት አጥብቆ ይጠይቃል። አንደኛው አብዮት ጠባቂም በመቀጠል «ጌታዬ በሃገር አልነበሩምን?» በማለት ይጠይቀዋል። «የምኖረው ደብረዘይት ነው» በማለት ሲመልስ፤ የቀበሌው ሹማምትም «ሻለቃዬ ፤ሻለቃ ደበላ ዲንሣ ናቸው ሲለው፤» «እይ! በሚስቶቻችን ላይ አዋጅ መውጣቱን ስሰማ ይህ የመጀመሪያ ነውና እግዚአብሔር ይስጥልኝ» ብሎ ሲመልስ ምርመራው እስከሚጣራ ከማረፊያ ቤት እንደሚቆይ ነግረውት ሚስቱን ያስናብቷታል። ውጭ ቆማ የነበረች አብዮት ጠባቂ ተጠርታ ወደማረፊያ ቤት እንድትወስደው ሲነገራት፤ እሷም ሻለቃውን ከበራፍ ስድብ ትጀምረዋለች፤ «በቃችሁ እኛን ድርብ ጭቁኖች የምታሰቃዩበት ዘመን ተመልሶ አይመጣም፤የገዛሀት መስለህ ደስ ካላት ጋር መሄድ ትችላለች፤በአባት እርስትና በሚስት የለም ዋዛ የሚለው ፉከራችሁ አልሠራም።» ሻለቃውም ንግግሯ እንቆቅልሽ ሆኖበት «እህት ነገሩን በውል የተረዳሽው አይመስለኝም ሲላት» «ለምን አላውቀውም ሚስትህን ደብድበሃት አደለምን? ተይዘህ የመጣህው»

ስትለው፤«ያልኩት ይህን ነው፤ ሄደሽ ምክንያቱን ከባልደረባዎችሽ በውል ተረጂ ይለታል፤ ሰለሴት ጭቆና ከወንድ የምጠይቅበት ምክንያት የለኝም፤በየቀኑ የምትሰሩንን እውቃለሁ፤ዘሬ በየመስኩ እኛ ድርብ ጭቁኖች ተደራጅተናልና ከእናንተ የምንጠይቀው ምንም ነገር የለም» ሻለቃውም ቃሉን ለዘብ አድርጎ «እህት ለመሆኑ የትኛው ድርጅት አባል ነሽ? እሷም ወገቧን ሰበቅ አደርጋ፤ ስንት ድርጅት አለ የሰበነክ አባል ነኝ!» ብላ ስትመልስለት፤ «አሁን ገና ችግርሽን ተረዳሁልሽ»ይለታል።

እውነቱና ጌትነት ይፈጸሙ የነበሩት ድርጊቶች በትዕግስት ከተመለከቱ በኋላ በሰባ ደረጃ አድርገው ወደ ስድስት ኪሎ ለመሄድ ከቀ.ኃ.ሥ ሆስፒታል አካባቢ ሲደርሱ አንድ የሕክምና ባለሞያዎች የሚለብሱትን ገዋን የለበሰ ከዩባዊ ከእንበሣ ቤት ፊት ለፊት ከሚገኘው እውቶቦስ ማቆሚያ ቆማ እውቶቦስ በመጠባበቅ ላይ ያለችውን ልጃገረድ ወዴት ሊወስዳት እንደአቀደ አይታወቅም ሊወስዳት ሲተናነቃት፤እሷም በአካባቢው ቆሞ የነበረው ሕዝብ ቢያስጥለኝ ብላ እየተከላከለችው ዓይኖቿን ብታቁለጨልጭ፤ ሕዝቡም አቅም እንደሌለው ገምቶ አይቶ እንዳላየ ሆኖ ወደመሬት አቀርቅሮ ይተክዛል፤እውነቱም የጌትነትን መናደድ ተመልክቶ «ጀርባውን መታ አድርጎ ጌቱ ቤሔርተኛ ነህ» ሲለው «እርሱም መልሰ ዓለም አቀፋዊ ነን የሚሉት የሚሰሩትን እያየህ እንዴትስ ዓለም አቀፋዊ እንደሆን ትፈልጋማህ» በማለት ይመልስለታል። እውነቱም በመቀጠል «ባለቤቱ ያቀለለውን እሞሌ ባለዕዳ አያነሳውም ይባላል፤ የዘንድሮውን በሃገራችን የሚሠራውን ሥራ ምኑ ተጠቅሶ ምኑ ይተዋል? ይህን እያዩ ከመቀመጥ አቅም የሚፈቅደውን እየፈጸሙ ማለፉ ይመረጣል፤» በማለት ተስማምተው ወደፊት አመሩ።



፲፭

የኢሕአፖን አባሎች ሆነ ደጋፊዎቻቸውን ለማጥፋት የተካሄደው ያለገደብ ግድያ በይበልጥ በነበረው መንግሥት ላይ ጥላቻን ከማትረፉ ሌላ ያስገኘው ውጤት አልነበረም። ወረቀት ብተናውም ሆነ የደርግ ደጋፊዎች በፀረ- አብዮተኞች ተመቱ በማለት ውገዘው እንደቀጠለ ሲሆን፤ በማያዳግም ሁኔታ ኢሕአፖን ለማጥፋት ተብሎ ጥር መጨረሻ ፸ ዓመተ ምህረት «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለው መፈክር በአዋጅ ተነገረ። መፈክሩ በልዩ ልዩ ቀለማት ባሸበረቁ ወረቀቶች ተጽፎ በማንኛውም አካባቢ ተበተነ።የአዲስ አበባ ከተማ የ«ቀይ ሽብር» መፈክር በተፃፈባቸው ወረቀቶች ተኾጎረጎረች። «ቀዩ ሽብር» ከ«ነፃው እርምጃው» በይዘቱ የተለየ ባይሆንም በቅርጹ ግን ለየት ያለ ነበር። ይሄውም በቀበሌም ሆነ በማንኛውም ሥፍራ ወጣት የሆነን በሙሉ እያፈሱ ከቀበሌ እስር ቤት ማጎር ፤ ፪፻፹፱ ቀበሌዎች ፳፩ ከፍተኛዎች ለዚሁ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ፤ከዚያንም በተቻለቸው የማሰቃያ ዜዴ ተጠቅመው ግለሰቦችን የኢሕአፖ አባሎች እስኘቶ የሚያውቋቸውን እንዲጠቁሙ ተደርጎ በማጨረሻም ከወለጅ ደጃፍና ከአደባባይ ላይ ወስዶ መግደልና መጣል ነበር። ሌላው ቀርቶ «ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም» የሚለውን የኢሕአፖን መፈክር በግድግዳዎችም ሆነ በስፋልት መንገዶች ላይ ተጽፈው ያነበቡ ሁሉ በኢሕአፖ አባልነታቸው ራሳቸውን እንዲያጋልጡ ይደረጋሉ።ወጣቱም እርስ በርሱ በመጠራጠር እኔ ብሸሽግለት እርሱ ይጦቅመኝ ይሆን በማለትና በመፈራራት እርስ በርስ መዘካዘክ ተጀመረ።ቆርጠውም እስከመጨረሻው እናወጣም ያሉትን ግለሰቦች ከተዘጋጀው መስቀያ ላይ በመስቀል ሰገፍፏው፤ የመጀመሪያዎቹ ተገራፊዎች ኋደኞቻቸውን ሣያጋልጡ ቀርተው በሚቀጥሉ ተገራፊዎች ከጠቆሙ የመጀመሪያዎቹ ያበቃለቸዋል።ማታውን አውጥተው ይመቷቸዋል።ጠቋሚዎቹም ከዚያን በኋላ ከአሉበት ሕብረተሰብ መጠላታቸውንና መገለላቸውን ሲረዱት አደገኛ ገራፊዎችና ሌሎቹም የነሱን ፈለግ እንዲከተሉ፤ያልተቆጠቡ ጥረቶችን ያደርጋሉ።

ያም ሆነ ይህ ተዕልከው በማነህ ማነህ ነፍስ ለማጥፋት ስለሆነ በየማታው ከነበሩት እስር ቤቶች ተጠቁሞባቸውም ይሁን ገና ለገና የኢሕአፖ አባል ናቸው ተብለው ሲደበደቡ የሞቱትን ጨምሮ ከእያንዳንዱ ቀበሌ ቢያንስ ሃያ ወጣቶች «በቀይ ሽብር» ስም እየተገደሉ ይጣላሉ። ልጆቻቸው የተያዙባቸው ወላጆችም በየጠዋቱ አስቀድመው የሚመለከቱት ነገር ቢኖር የልጆቻቸው ሬሣ ተጥሎ አልተጣለ እንደሆን ነበር። ከወላጆች መኖሪያ ሌላ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች አደባባዮች የአውራ መንገዶች መጋጠሚያዎች የሬሣ መጣያዎች ነበሩ።በጊዜው የሞቱትን ግለሰቦች አስመልክቶ አንድ አጠራጣሪ ሁኔታ ነበረ። ይሄውም ሬሣ እንሺዎቹ የማዘጋጃ ቤት

ሠራተኞች አስከሬኑን ከመኪናው ሲጭኑት በጣም ቀላል እንደሆነ ይታያል። ልዩ ዓይነት የመግደያ ዘዴ በእርዳታ ያገኙት መርዝ ይኑር አይኑር እስከአሁን ሲነገርም አልተሰማም ወይም ያገለጠ ሰውም አልተገኘም።

በ«ነፃ እርምጃው» ወቅት ያደርጉት እንደነበረው ሰው ከሚነግረን ራሳችን የሚደረጉትን ግፎች እንመልከት በሚለው ፕሮግራማቸው እውነቱና ጌትነት ቁርሣቸውን ከዮኒቨርሲቲው ተመግበው ወደለገሃር ለመሄድ ከዮኒቨርሲቲው አጥር በር ሲደርሱ፤የታጠቁ ገለሰቦች ከአጥሩ መግቢያ በር ከአንድ የዮኒቨርሲቲ መምህር ላይ ተኩስ ሲከፈትበት ያያሉ።በወቅቱ መምህሩ በላይ በምን እንደተገደለ ባይታወቅም መምህሩ ከአራት ኪሎ ከንፓስ አስተምሩ ሲወጣ ጠብቀው በሁለት ቮልስቫገን መኪና ተከታትለውት፤ እርሱም እንደተከተሉት በመረዳት የሬኖልት መኪናውን ፍጥነት ጨምሮ ሲነዳ፤የሚከታተሉትም የትራፊክን ሕጎች በመጣስ ከፊቱ ቀድመው ሊያስቆሙት ሲሞክሩ፤ ሳይሳካላቸው ቀርቶ፤ እንደምንም አምልጦአቸው ከዮኒቨርሲቲው አጥር በር ላይ ሲደርስ ከበር ቆሞ የነበረው፤ ዘበኛ መታወቂያ እንዲያሣይ በማለት በሩን ሲዘጋበት፤ ይከታተሉት ለነበሩት ቀርበውት ተኩስ ለመክፈት ዕድል ስለሰጣቸው፤ እርሱም እንዳላመለጣቸው ሲረዳው ቃታቸውን ከመሣባቸው በፊት የሰናይድ ኪኒኑን ውጦ በሰላም ያርፋል። እነርሱም ተልኮአቸውን መፈጸማቸውን ለመግለጽ አስከሬኑን ከመኪናው አውጥተው በጥይት ደብድበው «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለውን መፈክር አስቀምጠውበት ሲሄዱ፤የወደቀውን የበላይ አስከሬን የውጭ አገር ዲፕሎማቶች እንዳያዩት ከወደ እንጦጦ ለሚመጡትና ከአራት ኪሎ ሽቅብ ለሚወጡት ተሽከርካሪዎች መንገዱ ዝግ ሆኖ ይቆያል። የሃገሬው ሕዝብ ግን ለሱ የተዘጋጀለት ድግስ ስለነበር ለሰዓታት እንዲመለከት ይፈቀድለታል። ከአጥር ውጭ እንዳይወጡ የተከለከሉት የዮኒቨርሲቲው ተማሪዎችም በአጥር ተጠግተው የመምህራቸውን የበላይን ሬሣ ሲመለከቱ ያረፍዳሉ። ድርጊቱን ይከታተል የነበረ አንድ እንግሊዛዊ መምህር ድምፁን ከፍ አድርጎ «ፋሽዝም ይህን ይመስላል» በማለት በአጥር ላይ ለተጠጉት ተማሪዎች ንግግር ያደርጋል። አንዲት ተማሪ መፍትሔው ምን ይመስልሃል?» ብላ ትጠይቀዋለች። መምህሩም ፒፖውን እየሣበ «መንግሥታችሁን ስለደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ነፃነት ከመናገሩ በፊት በራሱ ሕዝብ ላይ የሚፈጽማቸውን ፋሽሽታዊ ተግባሮቹን እንዲያቆም ንገሩት።በደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን ግድያ ሆነ የሕዝብ ቅዋሜ የትም ሃገር ሆኖ ለመመልከት ይቻላል፤ በመጽሐፍ ይፃፋል በጋዜጣ ይወጣል በቴሌቪዥን ይታያል፤በትያትር መልክ ለዓለም ሕዝብ ይቀርባል። ከዚህ ሃገር ግን በስድስት ኪሎ የሚደረገውን ግድያና ኢሰባአዊ ድርጊቶች በአራት ኪሎ ያለው ሕዝብ የሚያውቀው አይመስለኝም። በየምሽቱ በዚህን ከተማ ከሁለት መቶ



የሚበልጡ ሰዎች ተገድለው ይጣላሉ።በዜዎቻችሁ ልታዩትም ላታዩትም ትችላላችሁ።ግን በቤታችሁ ያለው ቴሌቪዥን አንድ ደቡብ አፍሪካዊ ተገደለ በማለት ጠቅላላ ክፍለ ጊዜውን ይወስደዋል። የእናንተ መሪዎች የደቡብ አፍሪካውን አጋነው የነርሱን አገዛዝ የተሻለ አድርጎ ለማቅረብ እንጂ እውነትስ ከሰው ልጅ ሕልውናና መሠረታዊ መብቶች አንፃር ተመልክተውት አይደለም። በደቡብ አፍሪካ የዘር መድሎ አገዛዝ የተለወጠ ዕለት እነዚ ደቡብ አፍሪካን እንደማስፈራርቻ አሻንጉሊት ለሚጠቀሙበት አገሮች በዚህ አጋጣሚ ወዬላቸው እላለሁ።የሚደንቀው የጥቁር መሪዎች የራሳቸውን ሕዝቦች እንዲጮቁኑ ሕጋዊ መብቶችን የሰጣቸው ማነው? መፍትሔው ምንደነው ተብዬ ለተጠየቅሁት ጥያቄ የታየኝን በሙሉ ለመግለጽ ሃገሬ አይደለሁም ያለሁት፤አሁንም ለተናገርኩት ሐቅ ሲ.አይ.ኤ ነህ ተብዬ እበረር ይሆናል።ሆኖም ግን ያ ሬሣው እንደውሽ ሬሳ የተጋደመው ምሁር የሁላችንም አካል ነው፤በመልክ እንለያይ እንጂ እኔና እርሱ ከአንድ አካል የተፈጠርን ፍጥሮች ነን፤ በጣም ያናደደኝ አንድን ምሁር በተጨባጭ ማስረጃ አሳምኖ ብዙ ለወገን የሚጠቅሙ ነገሮችን ማሰራት ሲቻል በአልባሌ ሰዎች ልክ ማስገደሉ አግባብ አይደለም።ትምህርት ቤቶች ለምርምር ምሁራን የታያቸውን አበጥረውና አብጠርጥረው እውነትነት ያላቸውን ነገሮች በማስረጃ አስደግፈው ጠንካራ ተማሪ ወጤታዊ ዜጋ ለመፍጠር ሙሉ መብት ተነፍጓቸው በየጊዜው ለሚነሱ እንባገነኖች እንዲያገለግሉ ተጽኖ የሚደግባቸው ከሆነ ድካሙ ውጤት አልባ ነውና እናንተም ጊዜአችሁን በከንቱ ከምታጠፉ ወጥታችሁ የራሳችሁን ሥራ ብትሰሩ ይበጃችኋል።»በማለት ንግግሩን ያቆማል ተማሪዎቹም ሞቅ ያለ ጭብጨባ ያደርጉለታል።

የሬሣ እንሺ መኪና መጥታ የበላይን አስከሬን አንስታ ስትሄድ ተዘግቶ የነበረው የዮኒቨርሲቲው በር ሲከፈት ድርጊቱ ለተማሪዎቹ የአእምሮ እረፍት ስለነሳቸው የዕለቱን የትምህርት ክፍለ ጊዜአቸውን ሰርዘው በየአቅጣጫው ከግቢው ወጥተው ሄዱ።እውነቱና ጌቱም በፕሮግራማቸው መሠረት ከለገሃር ወረዱ። ሁለቱም ከቤሔራዊ እስታዲየም አካባቢ ቀጠሮ ስለነበራቸው የቀጠሮ ሰዓታቸው እንስኪደርስ ቀዝቃዛ መጠጥ ለመጠጣት ከአንድ እስታዲየም አካባቢ ከምትገኝ ቡና ቤት ለመግባት ከበራፍ ሲደርሱ ከበስተጀንበር መውጫ ከፔሌ ሙዚቃ ቤት ተብሎ በጊዜው ከሚጠራው በራፍ ላይ የአንድ ወጣት ሬሣ ተጥሎ ሲመለቱ፤ወደመጡበት ለመመለስ ሲዳዳቸው፤ ከሩቅ አካባቢውን የሚቃኙ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉን በማሰብ ዘልቀው ወደቡና ቤቷ ይገባሉ።እነርሱም የማር ብርዝ አዘው ትንሽ ከተዝናኑ በኋላ ሒሣባቸውን ለመክፈል ከመደርደሪያው ቆመው ባለ የሐዘን ልብስ የለበሱ የቤት እመቤት ከወደማጀቱ ወጥተው ሒሣቡን ለከፈላቸው መልሱን እየቆጠሩለት ስለተገድሎ ስለተጣለው ወጣት ይናገራሉ። «ያ ከውጭ ተጥሎ ያየችሁት ሬሣ የባለ ሙዚቃ ቤቱ

ወንድም ሲሆን፤እርሱም ከማዘን ይልቅ ሙዚቃውን ከጣሪያ በላይ ከፍቶ የሚያስጨፍረው ወደን እንዳይመስላችሁ በሰበብ አስባቡ ይህችን ንብረቱን እንዳይወስዱበት በመፍራት ሆን ብሎ የሚያደርገው ነው፤»በማለት ብዙ ለመናገር ሲቃጣቸው አንዲት ቀንጆ ልጃገረድ እሷም የሐዘን ልብስ የለበሰች ከወደማጅቱ ወጥታ እማዬ አላበዛሽውም ስለ ሰው ቤት ምን አግብቶሽ ነው የምትናገሪው?» በማለት እናቷን ስትቆጣ፤ እርሳቸውም መልሰው አበትሽን እንደሆን ገለውታል ቢፈልጉ እኔንም ይድገሙኝ የምፈራው ነገር የለኝም» በማለት ይመልሳሉ።

እውነቱና ጌትነት በነጋታው ከአራት ኪሎ ከቤሒራዊ ቡና ቤት ቀጠሮ ተሰጣጥተው ስለነበር እውነቱ ተነስቶ ከቀጠሮው ሥፍራ ይሄዳል። ጌትነትም በቀጠሮው ሣይመጣለት ይቀራል። ሲጠፋፋ በተደጋጋሚ ከሚፈቃቀዱበት ሥፍራ በተሰጣጡት ሰዓቶች በተከታታይ ይሄዳል።ያጣዋል። ሌላውን ጓደኛቸውን ስለእርሱ ሰምቶ እንደሆን ይጠይቀዋል። እርሱም ለራሱ ግንኙነቶች ተቋርጦበት በችግር ላይ መሆኑን ይገልጽለታል። «እንደውም ከበላይ አካል ወርደ ያነጋገረን ግለሰብ በተበላ ቤት ውስጥ ተጥለሎ ባለ የሚገባውንና የሚወጣውን ሰው እንዲጠቁሙ ያስለጠኗቸው ሕፃናት ብይ የሚጫወቱ መስለው ከቤቱ ሲገባ አይተውት ኖሮ በተሰጣቸው ቁጥር ደውለው እርሱንና ሴት ጓደኛውን እጅ ከፍጅ ይዘዋቸው፤ ከከፍተኛ ሃያ አምስት ታስረዋል ማለትን ስለሰማሁ ተበሳጭቻለሁ፤ በእውነትም ቀዩ ሽብር ለደርግ ሳይሰራለት አልቀርም» በማለት ሌላችግር እንዳለ ይነግረዋል። ጌትነት ለእውነቱ አስተዋውቆት መጠግያ ሰጥቶት የነበረውን ወጣት ስለጌትነት የሰማው ነገር ካለ በማለት ሲጠይቀው፤ እርሱም ቀጠሮ አፍርሶበት በተደጋጋሚ ከሚፈቃቀዱበት አካባቢ ቢሄድም እንዳላገኘው ይነግረዋል።እውነቱም ለመጨረሻ ጊዜ ሽንጣውን ከኖረበት ጓደኛው ዘንድ በመሄድ ስለጌትነት የሰማው ነገር እንዳለ ለማጣራት ቢሄድ፤ እርሱም በአብዮት ጠባቂዎች ታጅቦ መጥቶ የለሌት ልብሶቹን እንደወሰደ ነግሮት ለሱም ከከፍተኛ አራት ከአርጌው አይሮፕላን ማረፊያ መጥቶ እንዲጠይቀው መልክት የተወለት መሆኑን ሲነግረው፤ የተያዘውም አብረው እስታዲዮም አካባቢ በዋሉበት ዕለት ሥፍራውም ሥንጋ ተራ ቡና ቤት አጠገብ ካለው የአውቶቡስ ማቆሚያ አውቶቡስ በመጠባበቅ ላይ እንደነበረ ይገልጽለታል።

እውነቱም ዐርብ ቀን የጌትነትን መታሰር ሰምቶ እሁድ ሊጠይቀው ወስኖ ወደ ዮኒቨርሲቲው መኝታ ክፍሉ ይሄዳል።የክፍል ጓደኞቹም ከቀድሞ ሁኔታው ለወጥ ያለ መልክ በማሳየቱ ተሰምቷቸው የገጠመውን ነገር ይጠይቁታል። እርሱም ምንም እንዳልገጠመው ይነግራቸዋል።ያወጡለትን እራት ሳይመገበው ተጠቅልሎ ይተኛል።በመኝታው ላይ ተጋድሞ ስለጌትነት ጓደኛው ማሰብ ማሰላሰል ይጀምራል። በተለይ ስለእስር ቤቱ ጭንንቅ ስለአለበት የስኳር በሽታ ሲያስበው በመጀመሪያው አለንጋ እንደሚሞት በሃሣቡ ሲያወጣ



ሲያወርድ በአከፋያቸው የሚኖሩ ተማሪዎች እውነቱ ያለበትን ክፍል ያንኳኳሉ። አንደኛው ወጣት በሩን ከፍቶ ምክኒያቱን ሲጠይቅ የእውነቱ እናት መጥተው ከቁልፍ ማስቀመጫው ክፍል የሚጠብቁት መሆኑን ተናግሮ ይሄዳል።እውነቱም የእኔ እናት ከመቃብር ተነስታ እኔን አትፈልግምና ስም አሣስታችኋል በሏቸው በማለት መልክተኞቹን ይመልሣል። ተማሪዎቹም እውነቱ ተነስቶ እንዲያናግራቸው ደጋግመው በሩን ቢያኳኳ፤ በጣም ደክሞትና በጓደኞቹ መያዝ ተበሣጭቶ ስለነበር የሚደረገውን ነገር በሙሉ አላጤነውም። ለሁሉም የመኝታ ክፍል ጓደኛውን ሁኔታውን እንዲያጣራ ይልክዋል።

ለከንስ እንዚያ እየደጋገሙ በሩን ያንኳኩ የነበሩት ተማሪዎች በየጊዜው ወጣቶችን ለማስመለጥ የተደራጁ ኖሮ ዕቅዳቸውም እውነቱን ለማስመለጥ ሆን ብለው ያደረጉት ጥረት እርሱ ግን በድርጅት አብሮአቸው ይሰራ የነበሩት ጓደኞቹ በውል ስለሚያውቃቸው አንደኛው ጠቋሚ ሌለኛው ተጠቋሚ የሚሆንበት ምክንያት ስለአልታየው ሁኔታውን በችልተኝነት ሊመለከተው ችሏል። በእርግጥ ጓደኞቹ የነበረውን መንግሥት በዘፈቀደ ለመቃወም ሳይሆን የራሳቸው ሙሉ መብት በመገፈፉ ከሕዘቡ ጋር ችግሩን እንከፈላለን በማለት የገቡበት ስለሆነ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች ሆነው የሚተያዩ አልነበሩም። በመጨረሻም እውነቱ እንዲያጣራለት ልኮት የነበረው ተማሪ ተመልሶ «መያዝህ ነው» የሚለውን መልክት ሲነግረው እነርሱም ተከታትለውት ገብተው እንዳትነቃነቅ በማለት አምስት የታጠቁ ግለሰቦች መሣሪያቸውን ከራሱ ደገኑበት። በራሱ ቀበቶ የፍጥኝ አስረውት ከሦስተኛው ፎቅ ከመኝታ ቁጥር ፫፻፴፪ ከሜዳው ቴንስ አካባቢ ከሚገኘው ሕንፃ ከግራ ተቀኝ እያዳፉትና እያላጉት ሲወድቅ ሲነሣ ከደረጃው ጨርሶ ወርዶ የሚሄድበትን አቅጣጫ ለማውቅ ሲቆም አንደኛው በጥፊ ድብን አድርጎ መትቶት «በዚህን በኩል ሂድ ነው የምልህ» ሲለው አቅጣጫውን ለማጣራት ቀና ሲል ሲያስተናግደው የነበረውን ኃይሌን ረጅም ኮት ለብሶ ጣቱን በሽጉጡ ቃታ ውስጥ ጨምሮ እነጣጥሮ ይዞ ይመለከተዋል። እርሱም የሲቃና የመፀጽት ፈገግታውን ፈገግ ብሎ ሂድ ወደአሉት አቅጣጫ ያመራል። በሽጉጥ አፈሙዝ መትተውት ስለነበር ከአናቱ የሚወርደው ደም አይኖቹን ስለሸፈናቸው አንገቱን በማወዛወዝ እያስወገደ ከራስ መኩንን አዳራሽ ፊት ለፊት ካለው መኪና ማቆሚያ ሜዳ ላይ ደርሶ፤ መኪናቸውን ከዚያን አቁመው ኖሮ እውነቱን ሁለት ጠባቂዎች ተመድበውለት በአንደኛው ቮልስቫገን መኪና አሳፍረውት፤ የቀሩት በሌላኛው ተሳፍረው ፒፐሲ አካባቢ ከሚገኘው ከፍተኛ ሃያ ቀበሌ እስር ቤት ተወሰደ።

## ፲፯

ኃይለሥላሴ እውነቱን ጠቁሞ ያሲያዘበት ምክንያት ግልጽ አልነበረም በድርጅት አብረው አልሰሩም።ግን ጌትነት ኃይሌ የመኝታ ችግር ስለአለበትና በየጊዜው የወለጆቹን ቤት ቀበሌዎች እያሰሱ ስለአስቸገሩ ከአጎቱ ዘንድ ከትግራይ ክፍለሃገር እስከሚሄድበት ድረስ ከሱ ዘንድ እንዲጠለል ስለጠየቀው ምንም ሳይጠራጠረው የመጠሪያ ስሙን ነገርት የምግብ ካርዱን ሰጥቶት፤ በጊዜው የነበሩትን ችግሩች አብረው የተካፈሉ እንጂ በኢሕአፖ ድርጅት ውስጥ አብረው ተሰልፈው የሰሩ አልነበሩም። እንደኛው ስለሌላው ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ጌትነትና ኃይለሥላሴ በድርጅት ሊተዋወቁ ይችሉ ይሆናል።

የተወሰደበት ከፍተኛ ሃያ የቀበሌው እስር ቤት ከአብዮቱ በፊት የኤሌትሪክ ዕቃዎች አስመጭና አከፋፋይ ድርጅት መጋዘን ሆኖ ሳለ፤ ከለውጡ በኋላ ግን ወደእስር ቤትነት ተለውጧል። በጊዜው በቀበሌው እስር ቤት ውስጥ ከስድስት መቶ እስረኞች በላይ የታሰሩ ሲሆን፤ ከአስር ዓመት ወጣት እስከ ስድሳ ዓመት አዛውንት ይገኙበቸዋል። ከቀድሞው ድርጅት ቢሮ ነጠል ብለው ሦስት ክፍል ቤቶች በኩሽና መልክ ተሰርተው ሲገኙ፤ በዋና ቤት ውስጥ የሚገኙት ሦስቱን ክፍሎች ለተለያዩ አገልግሎቶች ተመድበዋል። ዋነኛው ክፍል የከፍተኛው ቀበሌ ካድሬ መኝታ ቤት ሲሆን፤አንዱ ክፍል ለቃል መቀበያ ሌላው ለመግረፊያ ተመድቧል። ሦስቱ ተነጥለው የተሰሩት ክፍሎች ለገራፊዎቹ መኝታነት ውለዋል። ለቤት እስረኞች በግቢው ውስጥ ካለው መስክ ላይ ከቆርቆሮ ዳስ ለመኝታ ተጥሎላቸዋል።የወንድ እስረኞች ግን የዕቃ ማኖሪያ ከነበረው መጋዘን ውስጥ እንዲተኙ ተደርጓል። በግቢው ውስጥ አንድ ሽንት ቤት ሲኖር ከላይ ሽፋን ከፍለፊት መዝጊያ የለውም። ከሰው ዐይን ለመከለል፤ በጆኒያ ሲጋረድ የተሠራውም በቱቦ ላይ ስለነበር ከእጅ መታጠቢያው የሚወርደው ውኃ ጠራርጎ ካልወሰደው እስከ አፍ ጢሙ ይሞላል። አብዛኛውን ጊዜ የውኃ ችግር ስለነበር ሞልቶ አካባቢውን ከማግማቱ ሌላ ከሽንት ቤቱ ንጽሕና ጉድለት የተራባው ዝንብ ለብዙው እስረኛ መታመም መንስኤ ሆኗል። ዝንቡ ባመጣው ተውሣክ እስረኛው በተቅማጥ በሽታ ተያዘ፤ ከሽንት ቤቱ ለመቀመጥ እንደዳበ ቤት በሰልፍ ይሆናል።

እውነቱም ከእስር ቤቱ ሲደርስ አብዛኛው እስረኛ ተኝቷል።በዕለቱ እንደእርሱ ተጠቁሞባቸው የመጡ ወጣቶች በውስጥ ሱሪያቸው ተቀምጠው ግርፋቸውን ሲጠባበቁ፤ለእርሱም በድርጅት የሚያውቃቸውን ግለሰቦችና አድራሻቸውን በጽሑፍ እንዲሰጥ ወረቀትና እስክሪብቶ ተሰጥቶት፤ የኢሕአፖ ድርጅት በአፍ ደጋፊ እንጂ በተግባር ከመዋቅራቸው ውስጥ ተመድቦ አለመሥራቱን ገልጾ፤



ኃይሌን ስለአስተዋወቃቸው ግለሰብም ሆነ ስለኢሕአፖ ድርጅት ከራሱ ከኃይሌ መረዳት ሲቻል መጠለያውንም የሰጠው እንደው ከበጎ ሥራ እንፃር እንጂ ከድርጅት አባልነት አለመሆኑን ጠቁሞ፤ ሁለቱ ግለሰቦች ግን ምን እንደሚሠሩ ይህ ነው ብሎ ለመናገር የሚያቀርበው ማስረጃ ስለሌለው ጥያቄያቸውን በኃይሌ ላይ እንዲያተኩሩ በማለት ቃሉን ይሰጣል።

ኃይሌም እውነቱን እጁን ይዞ ከበረዳ ወጥቶ «የአናርኪን ዲሲፕሊን የምናውቀው ነው፤ይልቅስ ሰውነትህን በእሳት ከሚጫወቱበትና አልፎም ከሚገድሉህ ለምን የምታውቃቸውን ጠቁመህ አታመጣቸውም» በማለት ሐሣቡን ሊያስለውጠው ይሞክራል። «እርሱም ቀደም ከነበረበት ውጥረቶች ነፃ ሆኖ እንደልቡ በእሸው ሥፍራ ሁሉ መዘዋወር እንደሚችል ሲናገር፤ ለእውነቱ የኃይሌ ሁኔታ ግልጽ ሲሆን፤ድርጊቱን እምኖበት ሳይሆን ከፍራቻ እንፃር በመሆኑ ሐሣቡን አላስለወጠውም።

ከዚያንም ልብሶቹን አውልቆ የግርፍ ተራቸውን ከሚጠብቁ ወጣቶች ጋር እንዲቀላቀል ተደርጎ፤ገራፊዎቹም ወደተቀመጠበት ሥፍራ እየመጡ «የአናርኪን ድስፒሊን የምናውቀው ነው፤የነበርንበት ስለነበረ አታታለን ይልቅስ ራስህን አጋልጠህ የምታውቃቸውን ጠቁመህ ከብዙሃኑ መቀላቀሉ ይበጅሃል።»ይህ እንግዲህ የመጀመሪያው ቅስቀሳ ሲሆን፤ የእውነቱም የግርፍ ተራው ደርሶ ከመግረፊያው ክፍል ገባ። ግርፉ የሚካሄደው በሁለት ግለሰቦች ሆኖ ተገራፊው እግሮቹና እጆቹ በኤሌትሪክ ሽቦዎች ከታሰሩ በኋላ፤።ረጂምና ሊሸከመው የሚችል ሽመል በታሰሩት እግሮቹና እጆቹ መካከል እንዲተሰለፈ ተደርጎ፤ ግራና ቀኝ ከቆሙት ተውዘግዛጊ እንጨቶች ላይ ይሰቀላል።ይህ ያስቃቀል ዘዴ «የመስፍን ፕሮጀክት ይባላል።» ዘዴውን ያበረከተው በመስፍን ስም የሚጠራ ግለሰብ ስለነበረ ነበር። በዚህ የአገራረፍ ዘዴ ብዙዎቹ የተገረፉት ሽባ ስለሆኑ፤የተሻለ ተብሎ ሌላ የአገራረፍ ዘዴ ተብሎ፤ የፍጥኝ አስር በደረት አስተኝቶ ጀርባን መደብደቡ እንደአማራጭ ቢወሰድም፤ ያደግሞ መግረፊያው አለጋ ወይም ሽቦው እየተጠመጠመ ዓይናቸውን ያጠፋቸው ጀርአቸውን የበጠሳቸው ብዙዎች ነበሩ።በግቢው ውስጥ የነበረው ጥምልል ሽቦ እየተቆረጠ ለመግረፊያ ሲውል፤ ኢሱሌተሩ እየተላቀቀ መዳቡ በተገራፊዎቹ ጀርባ ላይ እንደሸክ ይሰገሰግ ነበር።

የእውነቱም እግሮቹና እጆቹ በኤለትሪኩ ሽቦ ታሰሩ፤ረጅም ተውዘግዛጊ እንጨት በታሰሩት እግሮቹና እጆቹ መካከል እንዲተሰለፍ ተደርጎ፤ በተውዘግዛጊው እንጨት ተሰቅሎ፤ ጀርባው ተመቻችቶ፤ እውነቱን አውጣ በማለት ግራ ለግራ የቆሙት ገራፊዎች ግርፋቸውን ጀመሩት።እንደኛው ድምፁን ከፍ አድርጎ ይህ የ«እስታርሊን ብትር ነው እውነቱን እስካላወጣህ የእስታርሊንን ብትር ተቀምስዋለህ»

በማለት ድብደባው ቀጥሎ፤እየደከመውና የማቃሰት ድምፁ እየሰለለ መምጣቱን ሲረዱ ከሰቀሉበት አውርደውት ከቀዝቃዛ ውኃ ከተጠራቀመበት ጋንዳ ጨምረውት ሌሎቹን ማሰቃየታቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻም የእርሱ ምርመራ በለመጠናቀቁ ከሌሎቹ እስረኞች እንዳይቀላቀል ከቢሮው በረንዳ ላይ ከውጭ እንዲተኛ ተደረገ። በዚያን ደረቅ ሲሚንቶ ላይ አይተኛ አይቀመጥ እንዲያው የቁም ስቅሉን ሲያይ፤ በጊዜው እማራጭ የነበረው አውጥተው ቢመቱት ቢሆንም፤ ግን አልሆነም። የተገረፉት በሙሉ ከሌሎች እስረኞች ጓደኞቻቸው ተቀላቅለው የመጀመሪያ እርዳታዎችን ሲያገኙ እርሱ ግን ያ ተነፍጎታል።

በነጋታውም ከውጭ ተቀምጦ ሳለ አላፊ አግዳሚዎቹ እስረኞች ከሩቅ እየተመለከቱት ኃይሌ ከዮኒቨርሲቲ አመጠው የሚባለው ያ ነው በማለት የመጀመሪያ እርዳታቸውን ከፈር መጠጣ እያደረጉ ማለፍ እንጂ ተጠግተው ተግባራዊ እርዳታዎችን ለማድረግ አልቻሉም። ማንም እርሱ ካለበት እንዳይጠጋ በዐይን ቁራኛ የሚጠብቀው ልዩ ሰው ተመድቦለታል። ቀኑን ከማንም ሳይገናኝ በማታው ለሁለተኛው ዙር ግርፍ ይቀርባል። ምግብ ከተመገበ አንድ ቀን ተኩል ሆኖታል። የሰውነቱም ክብደት ቢበዛ ከሃምሳ ኪሎ ግራም አይበልጥም። ለሁሉም ልብሳቸውን አውልቀው ከተቀመጡት ተገራፊዎች ጋር ተቀላቅሎ፤እንደወትሮው ገራፊዎቹ እየመጡ «በራሣችሁ ከምትሟወቱ ለምን የምታውቋቸውን ጠቁማችሁ አታመጡም» በማለት የተለመደ ቅስቀሳቸውን ሲያደርጉ፤ እንዳአንዶም በውስጥ ሱሪያቸው የተቀመጡትን ልጃገረዶች ከመቀመጫቸው እያስነሷቸው ከዳሌአቸው አካባቢ መታ በማድረግ «እነዚህ ኢሕአፓዎች ብልጦች ናቸው ለራሳቸው ያውቁበታል፤ ተመልከት የመለመሏቸው ሴቶች የሚመሳሰሉትን» በማለት እየተጠቃቀሱ የተከረከሩትን ያህል ከጣሪያ በላይ ይስቃሉ።

የተማሩት ክፍሎች ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹ ከየፋብሪካውና ከወታደሩ ክፍል ያመጧቸው ገራፊዎች ከመገረፋቸው በፊት አስቀድመው መጠጥ መውሰድ ይኖርባቸዋል ያለበለዚያ ግን ጭካናዊ ተግባሩን ለመፈጸም ሕሊናቸው ሙሉ በሙሉ ስለማይቀበለው የመወላወል መልክ ያሣያሉ። ምሁራኑ ግን ነገሩን የሚያዩት ከፖለቲካው የቡድን ልዩነት ሲሆን የሥልጣን ጉጉት ጊዜአዊ ጥቅምና ብቀላም ዋናንኛውና መሠረቶቹ በመሆናቸው ሆን ብለው አምነውበት ስለሚያደርጉት ምንም ሌላ የሚገፋፋቸው ነገር አልፈልጉም።

እንደቀድሟቸው እየሰቀሉ በመግረፍ ላይ እንዳሉ ጥቆማ ተብሎ የተገረፉትን፣ ያልተገረፉትንና ለመገረፍ የተሰቀሉትን ከመግረፊያው ክፍል ውስጥ ትተዋቸው ተጠቋሚዎቹን ለማምጣት



ከላሽኮፕ ጠብመንጃቸውንና ሽጉጣቸውን ታጥቀው ተያይዘው ሄዱ። አራት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ተይዘው መጡ ሁሉም የአንድ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ነበሩ። አንደኛዋ ማዝዳ መኪና እንዳአላት ከዚያው ተነግር ኖሮ የቡዱኑ መሪ ገብረመድህን ቁልፉን ተቀበላት። ፍሬውን ሌላውን ጓደኛውን አስከትሎ መኪናዋን ለማምጣት ሄዱ። ጉዳዩ ከፍተኛ ነው ተብሎ ዋናው ካድሬ ከመኝታው ተቀሰቀሰ። ተይዘው የመጡት በሙሉ ከመግረፊያው ክፍል እንዲቆዩ ተነገራቸው። ሦስቱ ሴቶች አካባቢውን ሲመለከቱት አዩዩ ሆኑ። በተለይ ባለመኪናዋ በቅርብ ከአሜሪካን አገር የማስተርስ ዲግሪዋን በአካውንቲግ ተቀብላ የመጣች ሲሆን አረማመዷ ራሱ ለየት በማለቱ ከውጭ አገር የቆየች መሆኗን ለመገመት አያስቸግርም።ሰውነቷ በሃገራችን የፀሐይ ሙቀት ገና አልጠቋቀረም፤የለበሰችው ጉርድ ቀሚስ ሸሚዝና የደረበችው ከፋይ ኮት ያደረገችው ቡናማ ሹል ጫማ ያየ እሷን ቀጥታ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ጣቢያ በታክሲ ይዘው ያመጧት ይመስላል።

ፈለቀም ከፋሽሽታዊ ተግባሩ ሌላ መልክ መልክም ነው እጆቹ ከመለስለሳቸው የተነሣ ጣቶቹን የእንጀራው ጠርዝ የሚቆርጣቸው ይመስላል። እንደ አንዳንድ ግለሰቦች አጠራር የጨዋ ዘር እየተባሉ የሚጠሩትን ይመስላል። በጠንካራ ሠራተኛ ሕብረተሰብ ውስጥ ግን ለሰነፍና ለማይሰራ ያለፉበትን ተቀምጦ ለሚበላ ሰው ምሳሌነት ቢጠቀስ ደህና አድርጎ ይስማማል።

ለሁሉም ፈለቀ ከዕንቅልፉ ተቀስቅሶ ፊቱን በፎጣ እየጠራረገ ግራ ቀኙን እየተመለከተ ከመግረፊያው ክፍል መጣ።ፈለቀ «የቀይ ሽብር» ኮሚቴ ሲቋቋም ለሊቀመንበርነት የተመረጠውን መምህር ጌትነትን በሐሰት ሞት ካስወሰነበት ቀን ጀምሮ የፈለጋትን ሴት ተይዞ ስትመጣ ለሩካቢ ሥጋ ግንኙነት፤ ከአልጋ እንውጣ ብሎ በመብቱ ተጠቅሞ ቢያስገድዳት ሐይ የሚለው አይኖርም። ጌትነትም ፈለቀ ያደርግ የነበረውን ከሥነስርዓት ውጭ ተግባሩን በመንቀፉና ብሎም በማጋለጡ ከሜዳ አንዱን ወጣት አሲዞ ጌትነትን የኢሕአፖ አባል አስኝቶ የሞት ፍርድ ስለአስወሰነበት ቆንጆ ናቸው የሚባሉ ሴቶች ተይዘው ከመጡ ለፈለቀ ማቅረቡ ግዴታ ነበር።

ፈለቀም አካውንታቷን ሲመለከት በአካባቢው ያሉትን ገራፊዎች ሰብስቦ ከመኝታ ቤቱ ገብቶ፤ ከኮመዲናው ውስጥ ያለውን ውስኪ አያወጣ፤ከነጠርሙሱ እያደላቸው፤ ጉበዝ መለኪያ የለንም በማለት ለጤናችን ብሎ ለራሱ ተጉንጭቶ፤ለቀሩት ሲያስተላልፍ፤ እነርሱም በፊልም እንደአዩት እንደአሜሪካን አገር የከብት አረኞች እየተቀባበሉ ሲጠጡ፤ አታስቡ ሌላም አለ በማለት ያስቀመጠውን መጠጥ በሙሉ አውጥቶ ሲያድላቸው፤በነፍስ ወከፍ ሊያደርሳቸው ምንም አልቀረውም። «ከዚያንም ገብረመድህንና ፍሬው የት አሉ» በማለት ይጠይቃል።

የሴትዮቱን መኪና ለማምጣት እንደሄዱ ሰነገሩት፤እርሱም የአስቀመጠውን እስቴክ የዊንስትን ሲጃራ ከኮመዲናው ውስጥ እያወጣ «ዋዎ ! መሆን የለበትም፤ እንዲህን ያለ ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት እኔ መስማት አለብኝ» በማለት ቅሬታውን ይገልፃል። ለሁሉም ገብረመድህንና ፍሬውም መኪናዋን ከቦይ ውስጥ ቀርቅረዋት ይመጣሉ።

በመጨረሻም ይሰክራሉ። ሲሰክሩ መሣሪያ እንሰቶ መግደል ወይም አለንጋ ጎትቶ መግረፍ የተለመደ ስለሆነ አንደኛው ካድሬ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጓድ ፈለቀ «እነዚህን አናርኪስቶች የኢስታርሊንን ብትር» ብናቅምሣቸው ምን ይመስልሃል?» በማለት ይጠይቃል።

ፈለቀም «አሁን ሕዝባችን ተደክሟል ማን ከእነርሱ ጋር ሽቅብ ቁልቁል ይላል?» በማለት ልብሳቸውን ለብሰው ከመግረፊያው ክፍል እንዲወጡ እንዲያደርጉ ነገርአቸው፤ ለጊዜው የተዘጋጀ ሥፍራ ስለሌለ እውነቱ ከሚተኛበት ፍራሽ ተዘርግቶላቸው እንዲተኙ ሲደረግ፤መኝታው ለሰባት ሰው አይበቃም በሚል ሰም አከውታቷ ከፈለቀ መኝታ ቤት ስትወሰድ፤የዕለቱም ምርመራ በዚህን አበቃ።



## ፲፯

እውነቱም ከአብዮት ጠባቂዎች አስፈቅዶ ውኃ ለመጠጣት ግቢው ውስጥ ካለው ቧንቧ ሲሄድ፤እንደት ልጃገረድ ውኃ የምትቀዳ መስላ ወደጆሮው ጠጋ ብላ «አሁንም ለድርጅቱ ታማኝ ነህን?» በማለት ትጠይቀዋለች። እርሱም «ጥያቄሽ ከባድ ስለሆነ ልመልሰው አልችልም» በማለት መልሰላት ውኃውን መጠጣት ሲቀጥል፤ እስታከ ምግብ መውሰድ አለመውሰዱን ትጠይቀዋለች። እስር ቤቱ ከመጣ ጀምር ምግብ እንዳልተመገበ ሲነግራት፤ ከሴቶች መኝታ ቤት በሩጫ ሄዳ ተደርድረው ከነበሩት ምግቦች አንዱን ሣህን አንስታ አብዮት ጠባቂውን አስፈቅዳ አምጥታ ስትሰጠው፤በተጨማሪም ጠቆሞ ያመጣውን ገለሰብ ጠይቆ ከብዙሃኑ እስረኞች እንዲቀላቅለው እንዲያደርግለት ሐሣብ ታከፍለዋለች። ራቧ እንድትጠራለት በነገራት መሠረት ኃይሌ ተጠርቶ ይመጣል። እውነቱም ከበረዳው በሲሚንቶ ላይ ተቀምጧል። ኃይሌም ኩስተር ብሎ «ለምን ፈለከኝ» በማለት ይጠይቀዋል።

እውነቱም እንደበቱን ለሰለሰ አድርጎ ኃይሌ በማለት ይጀምራል፤ «በእርግጥ የጊዜው ሁኔታ ዛሬ ቢያለያየንም ቀደም ሲል ለጥቂት ቀናትም ቢሆን ጓደኛሞች ነበርን፤ለአንድ ቀንም ቢሆን ያስተናገድሁህ ይመስለኛል፤ሆኖም ግን ያንን ውለታዩን ከዚህ በተሻለ መንገድ እንድትከፍለኝ በማሰብ አይደለም። ሰዎች በተፈጥሮ ከአካባቢያቸውና ከቤተሰባቸው ተምረው የሚያደርጓቸው ብዙ ደጋግ ተግባሮች ይኖራሉ። አንተም ከዚህን ሥቃይ ስፍራ ከአስረከብከኝ ቀን ጀምር ዘር ብለህ አላየህኝም። ዛሬ በዚህን አካባቢ እንደአንተ የምታጽናናኝና ስንቅ የምታቀብለኝ እናት የለችኝም፤ሌላው ቀርቶ የተገረፉት በሙሉ የመጀመሪያ እርዳታዎችን ከታሰሩት ጓደኞቻቸው ሲያገኙ እኔ ግን ዕድሉ ተነፍጎኛል። ለሁሉም ከዚህን አካበቢ የማውቀው ከአንተ ሌላ ሰው ስለሌለ ችግሬን ልገለጽልህ ብዬ ነው። ደግሞም ለሚቀጥለው ገርፍ ሰውነቴ እንዲቋቋም ቢያንስ በቀን አንዴ ምግብ እንዳገኝ ብታደርግልኝ መልካም ይመስለኛል ሲለው፤» ኃይሌም መሬት መሬቱን እየተመለከተ «እንደሚመስለኝ ከነገ ዛሬ መመታትህ ስለማይቀር የመጀመሪያ እርዳታውም ሆነ ምግብ መውሰዱ አስፈላጊነቱ አይታየኝም» ብሎ ተኮሳትሮ ከአጠገቡ ሄደ።

እስረኛዋም ኃይሌና እውነቱ ሲነጋገሩ ከሩቅ ቆማ ትመለከት ኖር እንደወትሮው ውኃ ለመጠጣት ሲሄድ ጠብቃ ምን እንደተባባሉ ጠይቃዋ የተባባሉትን በሙሉ ነገሯት፤ ሁኔታው አሳዝኗት በየጊዜው ጠባቂውን በማስፈቀድ ምግብ ስታቀብለው፤ አንዳንዴም እየተሸሸገች በመምጣት የማጽናኛ ቃላቶቿን ጣል አድርጋ ትሄዳለች። እንደአጋጣሚ ከአጠገቡ ቆማ ስታዋራው አንደኛው ገራፊ አይቷት ኖሮ ጠርቶ እንደተለመደው በጥፊና በእርግጫ መትቷት፣ ማንም ሰው ወደእርሱ

እንዳይቀርብ ለጠባቂው ማስጠንቀቂያውን ሰጥቶ ቢሄማም፤ ምግብ ማቀረቢ አላቋረጠችም እብዮት ጠባቂውም ምግብ ይዛ ስትመጣ ለመቅረብ አልከለከላትም።

እንደወትሮ ከመጠጥ መልስ እኩለ ለሊት ላይ ድብደባው ሲቀጥል፤ ለስድስትና ለሰባት ጊዜ ለግርፍ የቀረቡ ሲገኙባቸው፤እለንጋው ያላረፈበት አንድም የሰውነት ክፍል የሌላቸው ነበሩ። እውነቱም ቀን ከሴት እስረኛዋ ሲነጋገር ታይቶ ስለነበር የመጀመሪያው ተገራፊ ሆኖ ቀረበ።ያው እንደተለመደው ተሰቀለ ግርፉ ቀጠለ። ሲደክመው አይተው ከመስቀያው አውርደውት ሌሎችን መደብደብ ላይ ሳሉ፤እንደኛው ገራፊ የተገረፈውን ወጣት ደም እየተጀረጀረ እያየ ሲጀራውን እያይዘ በእሣቱ ሲያቃጥለው፤ ወጣቱም የሙት ሙቱን እንተ የ«መቶ ብር ተቀጣሪ የፋሽሽት እህያ ነህ» ሲለው ወዲያውኑ ሊመታ አውጥተውት ይዘውት ሄዱ። ይህ እንደኛው የመገላገያ ዜዴ ነበር።

በዚያን ዓይነት በመግረፍ ላይ ሳሉ፤ትልቅ ጥቆማ መጣ የኢሕአፖ የትጥቅ ክፍል ሰው ተገኘ ተብሎ ሽር ጉዱ ሆነ። ለማውጣጣት ይደብድቡ ያሰቃዩ እንጂ ቁርጠኛው ጥቆማ ሲመጣ ሄደው ግለሰቡን ለማምጣት ሆዳቸውን ባር ባር ይለዋል። በተለይ የትጥቅ ሰው ባይጠቁሙባቸው ፍቃዳቸው ሲሆን፤ ከኢሕአፖ የተገነጠሉት ክፍሎች ቀስ በቀስ እያስተማሩአቸው እንጂ ቀደም ሲል የኢሕአፖን አባላት እንደልዩ ፍጥሮች አድርገው ስለሚመለከቷቸው፤ ከእጃቸውም ሲገቡላቸው እንደማርያም ጠላት የሚረባረቡባቸው፤ ከፍረናትም ጭምር ነበር።ለሁሉም ለግርፍ የሰቀሏቸውን እንደአጠለጠሏቸው የተጠቆመበትን ግለሰብ ለማምጣት ከከፍተኛ ሃያ አንድ ከለገሃር አካባቢ ከሚገኘው የቀበሌ እስር ቤት ታስሮ የሚገኘውን ወጣት ለማምጣት ተያይዘው ሄዱ።

የተጠቆመበት ኪሮስ ከአዲስ አበባ ለመውጣት የጓደኛውን እናት ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቷአቸው ከቤት ወጥቶ ሲሄድ ቀበሌዎች በአደረጉት ጠቅላላ አፈሳ ይያዝና ከቀበሌ እስር ቤት ሲጨመር፤ በአካባቢው የሚያውቀው ስለሌለ ትኩረት ያደረገበትም አልነበረም። ሆኖም የጓደኛው እናት ሲያዝ አይተው ስለነበረ፤በከፍተኛ ሃያ እስር ላይ ለነበረው ልጃቸው ይነግሩታል። እናት ከፍቅራቸው እንፃር ለልጃቸው ቢነግሩትም በጠበቁት መንገድ አልሆነም። ልጃቸው ጓደኛውን ጠቆመው።

ገራፊዎቹም ከተባለው እስር ቤት ሄደው ኪሮስን ቢጠይቁ ስሙን ለውጦ ስለነበር ሊያገኙት አልቻሉም። አጥተውት ተምልሰው ጠቋሚውን አታለልከን በማለት ድብደባቸውን ሲያጠረክሩበት፣ ወስደ መራቸው። ኪሮስም በነጋታው ከሚለቀቁት ሰዎች ጋር ተመድቦ



ተቀምጦ ፍችውን ሲጠባበቅ ባለ የድርጅት ጓደኛው እጁን ይዞ አስረከበው።

ኪሮስ ተይዞ መጣ። መቸም አይያዝም በማለት ብዙዎቹ በትጥቁ ክፍል ውስጥ እንደሚሠራ ጠቁመውት ስለነበር እርሱም መመታቱን በፍጹም አልተጠራጠረም። ገና ከበሩ ሲገባ የጠየቀው ጥያቄ ቢኖር «ሕዝባችንን ለፋሽሽቶች ድብደባ ያበረከከው ምንድን ነው?»የሚል ነበር።« ጉበዝ እንደ ጀብደኝነት ካልወሰድነው በስተቀር ይህ እንደሚመጣ አምንን አልነበረምን? የገባንበት የጥንቶቹ ጓዶች የዛሬዎቹ ጠቋሚዎች ምንድን ነው መፈክራቸሁ? ደርግም የራሱ አለው መኢሶንም እንደዚያው የእንናት ርዕዮተ ዓለም ምን ይሆን? ዛሬ እኛን ጓደኞቻችሁን አሣልፋችሁ ስትሰጡ የተመለከቷችሁ አምነው የሚቀበሏችሁ ይመስለችኋልን? ሆኖም ሁላችንም ከመሞት አንድንም። ይህንን ቀድመን ተናግረነዋል። የእናንተ ግን ድርብ እጥፍ ይሆናል። በሕብረተሰባችን ከሃዲነት ሥፍራ እንደሌለው ሁላችንም ይህንን ጠንቀቀን ከወላጆቻችን ተምረናል። ወደገራፊዎቹ ዞር በማለት የአንድ ሃገር ሕዝብ ከመሆናችን ሌላ አብረን ያደግን ጓደኞሞች ነን። እንደምታውቁት የደርግን ደጋፊዎች ገድለሃል ተብዬ ተጠቁሜአለሁ ሁሉንም በአለፈነት እቀበለዋለሁ።ሆኖም ግን ሰው መግደሉ የአረመኔ ሥራ በመሆኑ ሕብረተሰባችንም እንደማይቀበለው እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ እናምንበታለን። ይህ ሆኖ ከደርግ በኩል ሆነው እንዳንደራጅ የታየንን እንዳንገልጽ ጥሩትም ሲፈጸም እንዳንቃወም፤በቀበሌያችንም ሆነ በማንኛውም ሥፍራ እንዳንዘዋወር መውጫ መግቢያ የነሱንን ግለሰቦች ተውን በማለተ በሚቀርቢቸው ግለሰቦችም ሆነ በአድራሻቸው በመላክ በልመና ከተማጸናቸው በኋላ፤ ሰው ደጋግመው ሲያሲዙና ሲያስገድሉ እኛም የተቻለንን አድርገናል። ይህንንም ሁላችሁም የምታውቁት ነው።አሁንም ቢሆን ሰው በመግደል አላምንም፤ግን ሊገለኝ የመጣውን ለመከላከል የተቻለኝን ከማድረግ አልቆጠብም። በአንድ ሃገር ሕዝብነታችን ተከባብረን ለጥሩ ተግባር ጊዜያችንና ሞራላችንን ብናውለው እንጂ በአጉል ውሸትና የንዋይ ፍቅር ራሳችንን እየጋረድን የግል ጥቅማችንን መጥፎ ባሕሪዎቻችን ተጋልጠው እንዳይወጡ ሕዝቡም የታየውን እንዳይናገርም ሆነ እሰበ እንዳይሰራ አፍኖ ለሃገር የሰሩ ለመምሰል እርስ በርስ ቃታ መሳሳቡን አሁንም ደጋግሜ የማወግዘው ነው።የእንናት መሪዎች አለን የሚሉትን ወኔ እኛም ውስጥ አለ።እኛም ብንሆን ከሌላ አልመጣንም።ትናንትና ከዚያም በስቲያ ከወራሪ በመከላከል ለዘመናት አኩሪ ታሪክ የአወረሱን ጅግኖች ልጆች ነን።ዛሬ በሃገራችን ቀደም ሕዝባችንን የጨረሰው ዓይነት ግራዚያኒ ቢመጣ ጸጥ ለጥ ብላችሁ ተገዙ የሚለውን መረሆ ለማስተማር የቆማችሁ ትመስላላችሁ። መጭውንም ትውልድ በዚህን ዓይነት አስተሳሰባችሁ ለመተከት የተዘጋጃችሁ ከሆነ እኔ በበኩሌ አልቀበለውም።እንዴትስ እንደኛው ሌላውን አዋርደና አቆሽ መብቱን ገፎ ሊገዛው ሲሞክር ሌላኛው ሊበረከክ ይችላል? ይህም ወገንን

መናቅ ታሪክን ማጉደፍ ስለሆነ ይህንንም ሁኔታ ሕሊናዬ ሊቀበለው ስላልቻለ በግል መሣሪያ እንዲነሣ ያስገደደኝ ይህ ነበር።»

ማታው ኑ ኪሮስ፣ ሌላ ጓደኛውንና መምህሩን ጌትነትን ጪምረው ሊሊቱን ከፍተኛ ሁለት ተወሰዱ። ምክኒያቱም ፈለቀ የሁለቱም ከፍተኞች ክድሬ ስለሆነ ነበር። ጌትነትን አስቀርተው ሁለቱን ጓደኞሞች ከአንድ ሳምንት በኋላ ይመቷቸዋል። እስከሚመቱበት ቀን ድረስ ወይ! «ሀናለ» በሚል ርዕስ መዝሙር ደርሰው ይዘምሩ እንደነበር በአከባቢያቸው የነበሩ ይናገራሉ።



## ፲፰

እውነቱም ከብዙሃኑ እስረኞች እንዲቀላቀል ይደረገል። ከእስረኞቹም መልካም አቀባበል ተደረገለት። ሰው ጠቁሞ ባለማምጣቱ ከብዙዎቹ የሞራል ድጋፍ ተሰጠው። መኝታው ግን በፈረቃ ነበር። ሆኖም በግርፉ በጣም ለተጎዱት በእስረኞቹ ልዩ መከባከቦች ይደርጉለቸዋል። ለመኝታ ግን ምንም አይነት ምንጣፍ አይፈቀድም። አንሶላን ብቻ ዘርግቶ ይተኛል።ጠዋት ሁሉም የወገብ በሽተኛ ሲሆን፤በግቢው ውስጥ እውድማ ከሚያክለው ሜዳ ላይ ሁሉም እርስ በርሱ ሲተሻሹ፤ የብዙዎቹ ሰውነት ሲሸት፤ በግቢው ውስጥ ልዩ ጠረን ሲፈጠር፤ ሆኖም ሁሉም ቁስለኞች፤በመሆናቸው ሽታው ስሜት አይሰጣቸውም።

እርስ በርስ እርዳታዎችን ከተሰጣጡ በኋላ ከወለጆቻቸው የመጡላቸውን ምግቦች ቡድን በቡድን ተከፍለው ይመገባሉ። እስራቱ ምግብ ችሎ በመሆኑ የሌላቸው ክፍሎች ካላቸው ተጠግተው ይመገባሉ።እስረኛው ምንም የግል የሆነ ነገር የለውም። ምግብ ለትክልት ሲጃራው ሲመጣ ለተመረጡት ሃላፊዎች ይሰጣል። እነርሱም እስረኛው በሚደረሰው እኳኋን ያደለድሉታል።ሥጋና ቅባት ያለው ምግብ ከእጥሩ ደጃፍ አያልፍም። ከምግብ ጋር አንዳንድ መልክቶች ወደ እስርኛው ይገባሉ በማለት የሚቆጣጠሩት ክፍሎች፤ ከወረቀቱ ይልቅ ትኩረታቸው ከምግቡ ላይ ሲሆን፤ በተለይ የዶሮ ወጥ፣ክትፎ፣ የበግ ቅልጥም፣የዝልዝል ወጥና ዕንቁላል ተመርጠው ከገራፊዎቹ ክፍሎች ሲወሰዱ ምግቡ የመጣባቸው ሰሃኖች የአደሃሪያን ሰሃኖች ተብሎ ይመለስላቸዋል። ወላጅም የተገረፉት ልጆቻቸው ያገገሙላቸው እየመሰላቸው፤ ራሳቸውን እየበደሉ ቅርሣቸውን እየሸጡ ያመጡት የነበረው ምግብ ፈጽሞ ለልጆቻቸው አይደርስም ነበር። ይህን በመገንዘብ ከላይ የሽሮ ወጥ በማድረግ ለማሣሣት ቢሞክሩም አልሆነም። በቴርሙስ በፈሣሽ መልክ ለማቅረብም ሞከሩ እስከመቼ ሊሆን አልቻለም። እስረኛው በላም አልበላም ጉዳዩ አልነበረም። ትልቁ ችግር ውጥረቱ ነበር። በአዲስ አበባ ከሚገኙት ቀበሌዎች በሙሉ ግንኙነት አለን ስለሚሉ ከሌላው ቀበሌ እንኳን ጥቆማዎች ቢመጡባችሁ ትገደላላችሁ በማለት ሲያስጨንቋቸው፤ ምርመራውም አንድ ወጥ ባለመሆኑ እያንዳንዱ ገራፊና ክድሬ የራሱ የሆነ የማወጣጫ መንገድ ሲኖረው፤ የመኢሶን ፣ የወዝ ሊግ፣ የሰደድ አባሎችም የራሣቸው የሆኑ መፈክሮችም የአጠያየቅ ዘዴዎች ነበሯቸው። የሁለቱ ድርጅቶች ማለትም የመኢሶንና የወዝ ሊጎች የሰደድ አባሎችን ስለሚፈሯቸው እውነተኛ አብዮተኛነታቸውን ለማስመስከር በኢሕአፖ ስም ተይዘው የሚመጡትን ግለሰቦች የማያደርጓቸው ነገር የለም። ሰደዶች ሲፈልጋቸው እዚያው እስረኛው ፊት መሣሪያቸውን ተቀብለው ከኢሕአፖ እስረኞች ሲቀላቅሏቸው እነርሱም እንዲት አለንጋ ከሰውነታቸው ላይ እንድታርፍ

በለማይፈልጉ ከሰደድ አባሎች ጋር ያነበራቸው ግንኙነት የጌታና የሎሌን ያህል ነበር።

ከሰዓት በኋላ መፈክር በብዛት እንዲፈከር ከተጠየቀ ሰው እንደሚመታ ይገመታል። ከድሬዎቹም ወደእስረኛው ጫታቸውን ከጉጫቸው ሞልተው ወደአብዮቱ ሰፈር መመለሳቸሁን ለማወቅ እንፈልጋለንና መፈክር አሰሙ ይባላል። እያዳንዱ እስረኛ እጁን እያወጣ ከእስረኛው ፊት ቆሞ መፈክር ያስፈክራል። አንዱ ወጣት ተነስቶ «ደክተር አበበ ዓለሙ የአዲስ አበባን ከተማ ከኢሕአፖ ያነፃታል ያነፃታል» ብሎ ሲቀመጥ ፤ ሌለኛው ተነስቶ «ደክተር አበበ ዓለሙ ለአዲስ አበባ ከተማችን ብዙ መጸዳጃ ቤቶች ያቋቁማሉ ያቋቁማሉ»፤ ብሎ ሊቀመጥ ሲል ይህ የኢሕአፖ መፈክር ነው በማለት እያዳፉት ሊገርፉት ይዘውት ይሄዳሉ። ከዚያን ቆሞ የነበረው አንደኛው ከድሬ «ጓዱ አብዮቱን ማፋፋማቸውን ትተው ሽንት ቤት እንዲያስቆፍሩ ይሻል።ይህ ዋንኛው ኢሕአፖ ነው» በማለት አስተያየቱን ይሰጣል።

የወጣቱ መፈክር እንኳን በእስር ቤቱ ያለውን የሽንት ቤት ችግር ማጸባረቁ ነበር።አንዳንድ ቀን ወሳጅን ለማሸበር በጣም ወንጀለኛ ናቸው የሚሏቸውን በመሣሪያ እጅበዋቸው ከቀበሌው አጥር ጀርባ አዳሪ ይዘዋቸው ስለሚወጡ እግረኛው በአጠገባቸው ሲያልፍ እያፈሩ ሣይወጡ የሚመለሱም ነበሩ። ወጣቱም ይህ ሁኔታ ደርሰበት ስለነበር ብሶቱን መግለጹ።

ከመፈከሩ በኋላ በጊዜ እራታችሁን በልታችሁ ከመኝታችሁ ላይ ተገኙ የሚለው መልክት ተላልፎ፤ ከድሬዎችና አብዮት ጠባቂዎች ሽቅብ ቁልቁል ማለት ሲጀምሩ ግድያ እንደሚኖር ያኔ ግልጽ ይሆናል።በተለይ ገብረመድህን ፍሬውና ማስረሽ ከሴቶች መኝታ ቤት ጀምረው፤እንደ አሰሩን እናርኪሰት ዛሬ ማታ ልናደብን ነው በማለት የእህቶችን ሆድ ለማባባት ከፎከሩ ግድያ መኖሩ ቁርጥ ይሆናል።

ለሁሉም ዝግጅታቸውን ሲያበቁ በዕለቱ የተወሰነባቸው ወጣቶች ስም ይጠራል። ሁለቸውም «ኢሕአፖ ያቸንፋል!» የሚለውን መፈክር አሰምተው ሲወጡ፤ ከእስረኛው ዝንድ ፍጹም ጸጥታ ይሰፍናል። ሊሊቱን ማንም አይተኛም። እልፎ እልፎ የመሣሪያ ጩኸት ይሰማል።አከባቢያቸውን የሚያውቁት ጓደኞቻቸውን ስም በመጥራት ይህ እገሌ ነው በማለት በኢሕአፖ ውስጥ ይሰሩበት የነበረው ክፍለ የአበረከቱትን አስተዋፅኦ በመጥቀስ ሲናገሩ፤ ለሚያውቋቸው ሁሉ እንደዚያው ይቀጥላል። ለሦስት ለአራት ቀን በእስር ቤቱ ፍጹም ጸጥታ ይሆናል።ምግብ አይበላም። ሬሣ ተጥሎ ያለዩት ወላጆች የእስር ቤቱን አከባቢ ይሞሉታል። እንዲህን ያለ ግድያ ሲፈጸም ከወላጅም ሆነ ከእስረኛው ሕዝብ የአእምሮ ቀውስ



ይፈጠራል።ለግሪሣሰት ለጥቂት ቀናት ግድያ ይቆማል።ሆኖም ግን በየዕለቱ ይመታሉ በማለት ለማስፈራራት የሚቀጥሉትን ተረኞች የፍጥኝ በማሰር «ቀይ ሽብር ይፋፋም»የሚለውን መፈክር ለጥፈውባቸው በግቢው ውስጥ ሲያዞሯቸው የእስረኛው ቁጥር ይጨምራል።ወላጆም ዓይኔ እያየ ከፊቴ ከሚወሰዷቸው እያሉ እንቷቸው በማለት ለቀበሌ እምጥተው ሲያስረኩባቸው፤ሕፃናቱም ራሳቸውን እንዲያጋልጡ ሲጠየቁ በትምህርት ቤታቸው አከባቢ ወረቀት ተበትኖ ማየታቸውን ይናገራሉ።

አንድ እናት ሴት ልጃቸው ራሷን እንድታጋልጥ በማለት ከቀበሌ ይዘዋት መጥተው፤ ራሷን እንድታገልጥ ስትጠየቅ ሐረር ለቀሉቢ ገብሬኤል ስለት ከእናቷ ጋር በሄደችበት ወቅት ከሂርና ከተማ ወጣ ብሎ በሐረር መስመር ከአንድ ትልቅ እለት ድንጋይ ላይ «ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት የዮሐንስ አድማሱ መፈክር» የሚል እንብቤአለሁ በማለት ራሷን ታጋልጣለች። ለእናት ልጃቸው ከፍተኛ የኢሕአፖ አባል ነች ተብለው ሲነገራቸው ደንግጠው እያለቀሱ ልጃቸውን አስረክበው ወደቤታቸው ሲመለሱ፤ሁኔታውን ለማጣራት ከሐረር ለመሄድ ዝግጅቱ ሲቀጥል፤ በእርግጥም አንድ ፍንጭ ይገኛል ተብሎ ሳይሆን የአንደኛው አብዮት ጠባቂ ልጅ በአንደኛው ጓደኛው ተጠቅሞ ኖሮ እርሱም ታጠቅ ጦር ሠፈር ስልጥኖ ምሥራቅ ጦር ግንባር ከራማራ ላይ ሲዋጋ ተመቶ ጀጎል(ሐረር) ራስ መኰንን ሆስፒታል መተኛቱን ስለሚያውቁ ከተቻለ ለማምጣት ሲሆን የልጅቱም ጥቆማ ጥሩ አጋጣሚ ሆናቸው።

የወላጅ ልጆችን በፍቃደኝነት ማምጣት የእስረኛውን ቁጥር በይበልጥ ስለሚጨምር የመኝታና የሽንት ቤቱ ችግር ከቀድሞው በበለጠ ሆኖ፤ ተራዋን በመጠበቅ የረፈደባት ሴት እስረኛ ወደጓደኛዋ ዞር ብላ «የእነማዬ ትምህርት ዋጋ እጣ» በማለት ታጫውታታለች። እንዴት በማለት ስትጠይቅ ፤ «የሴት ልጅ ወርቃማው ሕጓ በቀን ቢያንስ ሦስቴ ከውኃ መገናኘት ሲሆን የማለዳው የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል፤» በማለት ዘውትር እየደጋገምች ትለዋለች። ጓደኛዋም መልሳ «የሁለችንም እናቶች አንድ ዓይነት መመሪያ አላቸው እንደነሱማ ሐሣብ ሥርዓትን ማስተማራቸው ነበር። ግን እልሆነም እንኳንስ በቀን ሦስቴ ይቅርና በወርም ሰውነታችን ውኃ አይነካውም። ያለንበትን አከባቢ ሰው እንደሚኖርበት አድርገሽ አትውሰጂው፤ አንዳንዴ ሣስበው ስለባሪያ ንግድ በፊልም ያየሁትንና በመጽሐፍ ያነበብኩትን ያስታውሰኛል።

የሃገራችንን መሪዎች እንደባሪያ ፈንጋይ ፤ ዋናውን ከድሬ መርከበኛው ፤ አብዮት ጠባቂዎቹንና ገራፊዎቹን በሪያዎቹን በመርከቡ ላይ እንደሚቆጣጠሩት ግለሰቦች ውሰጃቸው እኛ ግን የተሸጥን ባሮች ነን፤ እስር ቤቱ መርከባችን መሆኑ ነው። ደግሞ

እንዳንደቻችንን እየመረጡ ከመኝታ ቤታቸው የሚውሰዱንን ሁኔታ ከእየሁት ፊልም ጋር ሳወዳድረው ከንዴት ብዘት ያስለቅሰኛል። ሰውም በውጭ የሚፈጽመው የውስጥ ነጸብራቅ ነው።ይህ ባይሆን ኖሮ ይህን ያህል ሕዝብ ወንድ ሴት ፆታ ሳይለዩ በአንድነት እስሮ በአንድ ሽንት ቤት ያውም ውኃ በሌለው ተጠቀሙ ማለት እንኳንስ በሃገር ሕዝብ ላይ ይቅርና በምርከ በጦር ላይ ለተያዘ ሕዝብ ይህ ድርጊት አይፈጸምም።»

በአጠቃላይ የቀበሌው እስር ቤት እንደሕፃናት መዋያ ተወሰደ፤ከመካከላቸው እየመረጡ ሲገሉ በቀሪዎቹ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን የአእምሮ ቀውስ አለመመልከታቸው ግልጽ ሲሆን፤ ወላጆቻችንም ቢሆን በባሕላችን ደስታንም ሆነ ሐዘንን ከጎረቤት ወይም ከአካባቢ ሕዝብ ጋር መካፈልን የለመድን በመሆኑ፤ የአንደኛው ቤተሰብ ልጅ ታስሮ የሌለኛው ቤተሰብ ልጅ ከቤት መዋሉን አንፈልገውም። ለዚህም ነበር አንዳንዶቹ እንቷቸው በማለት አምጥተው የሚያስረክቧቸው። ከነበርው መንግሥት ተባባሪ ናችሁ እንባላለን ፍራቻ ነበር።ሌላው ቀርቶ በደቡብ ብዙ ንፍስ በማጥፋት የታወቀው የደርግ አባል የአሊ ሙሣ ልጅ ከሰፈር አብሮ የሚውላቸው ጓደኞቹ እናትየዋ ከቀበሌ እስር ቤት ከጓደኞቹ እንዲውል አድርገውት ነበር።



## ፲፱

ዕለቱ እሁድ ከሰዓት በኋላ ወራቱ የካቲት ፸ ዓመተ ምህረት ነበር። ወላጅ ጓደኞች ከየአቅጣጫው ምግብ የመለወጫ ልብሶችን ሲጃራ ገንዘብ አትክልት ይዘው ከቀበሌው አጥር በር ላይ ተኮልኩለው፤እስረኞቹም የጠያቂዎቻቸውን መልዕክት በመጠባበቅ ላይ ሳሉ፤ በበሩ ላይ የተመደቡት አብዮት ጠባቂዎች ጠያቂዎችን እያገፋተሩ ከአጥሩ በአሸገር እንዲቆሙ ሲያደርጉ፤ «የቀዩ ሽብር» የምርመራው መሪ የሆነው ገብረመድህንና ረዳቶቹ የታጠቁ አብዮት ጠባቂዎች ጭምር መሣሪያቸውን ወድረው ወደእስረኛው በመጣደፍ ሲመጡ እስረኞቹም ምን ነገር ተይዘ ይሆን በማለት ተደናግጠው በእንክሮ የሚሆነውን ሲጠባበቁ፤ ገብረመድህን ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ የሃያ ስድስት ወንዶችንና አራት ሴቶችን ስም ጠርቶ በግቢው ውስጥ ከነበረው ጥምልል ሽቦ እየተቆረጠ እጅ እጆቻቸውን አቆራንተዋቸው፤ በጀርባቸው ላይ «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለውን መፈክር ተለጠፎባቸው፤ በታጠቁ አብዮት ጠባቂዎች ታጅበው በቀበሌው ዋንኛው በር በስተደቡብ በኩል ይዘዋቸው ሲወጡ ጠያቂው ሕዝብ ከእስፋልቱ በአሸገር ቆሞ፤ሁኔታውን ለመመልከት የሰቀጠጣቸው ወላጆች ፊቶቸውን በነጠላ ሸፍነው፣ጓደኞች እንባቸውን አቅረው፣ በትኩረት ሲመለከቱ፤አባቶች በያዙት ከዘራ የቆሙበትን መሬት ሲከረኩሩ፤የተቆራኙት ወጣቶች የጠያቂዎቻቸውን ፊት ላለማየት ከፊት ፊታቸው የሚሄዱትን ጠባቂዎች በመመልከት ወደፊት ሲያመሩ፤የአንደኛው እስረኛ እናት በዕለቱ ከሲዳሞ ክፍለሃገር ድረስ ሊጠይቁት መጥተው ከጠያቂው ሕዝብ መካከል ኖረው ልጃቸውን ከሌላው ጓደኛው ጋር ተቆራኝቶ በጀርባው ላይ «ቀይ ሽብር ይፋፋም» መፈክር ተለጥፎበት ሲመለከቱ እዬዬአቸውን አሰምተው፤ ጮክ ብለው «ናፍቄህ ብመጣ ላገኝህ አልቻልኩም። እርሜን አወጣለሁ፤ ደህና ሁን፤ አባትህ ከዘመቻ በደህና ተመልሷል» በማለት የተሰማቸውን ሲገልጹ ወጣቱም ወደኋላው መለስ ብሎ እናቱን ለማየት ስላልቻለ ወደፊቱ ያመራል። እርሱም በሥራ ብዛት ምክንት ለሁለት ዓመታት እንዳላያቸው ይናገራል።

በቀኑ ወጣቶቹ የተወሰዱበት ቀበሌ እርባ ስምንት ጥይት ቤት እየተባለ ከሚጠራው ሲሆን የዚያው ከፍተኛ የአብዮት ጠባቂዎች ሊቀመንበር የቀበሌው ተመራጭ በመሆኑ ጥብቅ ጥበቃዎችን እንዲያደርግና በቅርብ እንዲቆጣጠራቸው ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር። ገብረመድህንም ለጠባቂዎቹ ከስምንት መቶ እስረኞች ውስጥ ውስጥ በከፍተኛ የወንጀል ሥራቸው ተመርጠው ለጥብቅ ጥበቃ የመጡ መሆናቸውን ጠቁሞ ፤ በተቻላቸው መጠን ቁጥጥራቸውን እንዲያደርጉ መመሪያውን ሰጥቶ ሲሄድ፤ጠባቂዎቹም የተሰጣቸው ሃላፊነት ከፍተኛ መሆኑን እምነውበት ለጥበቃው ያመቻቸው ዘንድ

ሁለት ሜትር በሁለት ሜትር በሆነች ክፍል ውስጥ ሃያ ስድስቱን ወንደቹ እንዲተኙ ሲያደርጉ አራቱ ልጃገረዶች ግን ለዘበኛ በተሰራች አንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ እንዲቆዩ ተደረገ። በቀበሌው መመሪያ የወላጅን ፊት ማየት አይፈቀድም። በሃያ አራት ሰዓት ሁለቴ ሽንት ቤት መኬድ ሲኖርበት፤ሽንት ቤቱም ከቀበሌው አጥር ውጭ በመሆኑ አንድ ወጣት ብቻውን በጠባቂዎች ታጅቦ ስለሚወሰድ፤ወላጅም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ልጆቻቸውን በሕይወት መኖር አለመኖራ ለማረጋገጥ ማልደው በመምጣት፤ ከአጥር ሥር ተለጥፈው ለእዳሪ ሲያወጧቸው ማደራቸውን ያረጋግጣሉ።

የአንደኛው እስረኛ እህት ከወሎ ክፍለሃገር ድረስ ልትጠይቀው መጥታ ያመጣችውን ምግብ ተቀብለዋት ግን ልታየው እንደማትችል ተነግሯት የተነገረው ወንድሟ አንድ ቀን ከቀበሌው አካባቢ እንደምትመጣ በመገመት በየዕለቱ ለሽንት ሲያወጡት ግራ ቀኙን ሲመለከት ከርሞ፤እንደአሰበውም አልቀረምና ሕፃኗን በጀርባዋ አዝላ ከአጥር ተለጥፋ ወንድሟን ለማየት ስትጠባበቅ፤በዝናቡ እሷም ሕፃኗም ርሰው በብርዱ ሲሰፈሰፉ በዚያኑም ላይ የሕፃኗ ሰውነት አብዛኛው በልብስ ስለአልተሸፈነ እንዳለ ሰውነቷ ለዝናቡ የተጋለጦ ወንድም ሲመለከት፤ እህትም ወንድም በመሣሪያ ታጅቦ ወደሽንት ቤቱ ሲወሰድ ተመልክታ፤ያዘለቻትን ሕፃን ከጀርባዋ አውርዳ ከቆመችበት ሥፍራ ተቀምጣ ጡቷን አጉርሰት እንባዋን ስታወርደው ፤ እርሱም ከሽንት ቤት ሲመለስ እህቱ ምጽዋተኛ መስላ ከቀበሌው አጥር ስር ተለጥፋ አይቷት ከክፍሉ ሲመለስ ከፊቱ ሐዘን ፀጸት ተስፍ መቁረጥ መነበቡን ያጤኑት ጓደኞቹ ያጋጠመውን ችግር ቢጠይቁት፤ እህቱ ከወሎ ክፍለሃገር ድረስ ልትጠይቀው መጥታ ልታገኘኘው ባለመቻሏ አጋጣሚውን በመጠቀም እርሱን ለማየት ብቻ እሷም ሕፃኗም ከውጪ በዝናብ እንደሚርሱ ነግሮአቸው ጓደኞቹም በተራአቸው ወጥተው ሲመለሱ ሁኔታዋን አጣርተው እንዲነግሩት በጠየቃቸው መሠረት ከእርሱ በኋላ ከሽንት ቤቱ የሄዱት በሙሉ ያደታል።

የዚህን ወጣት ቤተሰብ በምሳሌነት ልጥቀሰው እንጂ ከየክፍለሃገሩ ተበድረውና ተለቅተው ልጃቸውን ወይም ወንድማቸውን ይሁን እህታቸው ታሰረውባቸው ቀርበው ሳይነጋገሩ በአዲስ አበባ ከተማ ማረፊያ አጥተው ተጉላልተው የሚመለሱ ወላጆች ብዙዎች ነበሩ። እዚህን ላይ እንደጠቀስሁት ይህን ዓይነት አበሣና መከራ የሚደርሥባቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸው የታሰሩባቸው ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም። በእናት ሃገር ስም በየጦር ግንባሩ የተሰለፉት ቤተሰቦችም ቢሆኑ የዚሁኑ ዓይነት ግፍ ደርሶባቸዋል። አንድ ቀን እውነቱ ከመከላከያ ሚንስተር በላይ ከሚገኘው ከአባሳደር ትያትር ዝቅ ብሎ ካለው የሦስት ቁጥር አውቶቡስ ማቆሚያ፤ ስድስት ኪሎ ለመሄድ ሦስት ቁጥር አውቶቡስን ሲጠባበቅ፤አንዲት እናት ጦር ግንባር የሞተ ልጃቸውን አበል እንዲያጉኙ ለማድረግ ከ ጉንደር ክፍለሃገር ድረስ



መጥተው በየቀኑ በየምክኒያቱ እንደሚያጉላሏቸው ነገረውት እንደውም ማደሪያ ከማጣታቸው የተነሣ ከመቃብር ቤት እንደሚያድሩ ጠቁመው «ወይ! እግዚአብሔር ምን ዓይነት ዘመን አመጣብን ከሃገሬ የወጣሁኝ ቀን ምነው እግሬን በቆረጠው» በማለት ቀና ብለው በአካባቢው የነበረውን ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ተሰፋዩ ደበሣይ ሞተበትየሚባለውን ተመልክተው፤ «ልጄ ከዚህን ውስጥ የሚኖሩት እግዚአብሔርን ያውቁት ይሆን?» ብለው ሲጠይቁት፤ «እናቴ እነዚያ እሰን የሚያጉላሉት ዓይነቶች ይሆናሉ» ብሎ አውቶቡሷ ስለመጣችልት በኪሹ ያለችውን ሁለት ብር አውጥቶ ሰጥቷቸው ተሳፈረ።

## ፳

በቀበሌ ውስጥ ተመድበው የሚሠሩት ሠራተኞች በሙሉ መጥፎች ጨካኞች ናቸው ማለት አይቻልም። አንዳንዶቹ አብዮት ጠባቂዎች የተሰጣቸውን የበላይ ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ በሥራ ለመተርጎም ሒልናቸው ስላልተቀበለ እልፎ እልፎ እስረኞቹ ከክፍላቸው ወጥተው ንፋስ እንዲቀበሉ ከመፍቀድ አልፈው ተርፈው ከሚያገኙት ገንዘብ ሲጃራ ሆነ ምግብ ገዝተው ለእስረኛው የሚያቀርቡም ነበሩ። በዚያን አጋጣሚ ጠባቂዎቹ የእስረኞቹን ምንነትና ጸባያቸውን በውል ለማወቅና ብሎም ቀደም ሲል ይቀርብባቸው የነበረውን የማጥላላት ዘመቻ ከሚያዩት ሐቅ ጋር አዛምደው ሲመለከቱት በመጥኑም ቢሆን የነበራቸውን የቀድሞ አስተሳሰባቸውን በመሪያዎቻቸው የተነገራቸውን ደግመው ደጋግመው እንዲያጤኑት ሳይረዳቸው አልቀረም። ያ ሆነና ማንነታቸውን ሲረዱት ከታሰሩበት ክፍል ወጥተው በግቢው ውስጥ ጉድጓድ እንዲቆፍሩ ሲፈቀድላቸው፤ለወጣቶቹም ቢሆን የውጭውን ብረሃን ለማየት ጥሩ አጋጣሚ በማግኘታቸው፤ ሁኔታው ለወጣቶቹ ሰውነታቸውን እንዲያጠናክሩና ጤናማ ሆነው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ግርፍ ጥንከሬ እንደሚሠጣቸው ስለገመቱት ድርጊቱን በፍቃድኝነት በደስታ ሲቀበሉት፤ በሌላ አኳያ፤ ከወንዶቹ ተነጥለው የታሰሩትም ሴቶች አብረው ዶማና አካፋ ይዘው እንዲቆፍሩ በመደረጉ በአንድነት ሐሣብ ለሐሣብ ለመለዋወጥ አረዳቸው። ወራቱ መጋቢት የሴቶች በዓለ የሚከበርበት ቀን በመቃረቡና ሴቶችም በእስር ቤቱ ውስጥ ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው ወንዶችም በሐሣብም ሆነ በተግባር እንዲተባበሯቸው መጠይቅ አቅርበው፤ አጋጣሚውን ተጠቅመው በዓሉን የሚመለከት ድርሰት በትያትር መልክ ተዘጋጅቶ፤ በጥሩ ሁኔታ ከተቀነባበረ በኋላ፤ ተዋናኝ ጉድጓድ እየቆፈሩ ልምምዳቸውን አድርገው ሲያበቁ፤ የሴቶች ማሕበር ሊቀመንበር ጥሩ ሰላምተኛቸው ስለነበረች፤ ለቀበሌው ኋሪዎች የሴቶችን በዓል አስመልክቶ ትያትር ለማሳየት ማቀዳቸውን ሲገልጹላት ያለምንም መጠራጠር በደስታ ተቀብላቸው፤ጽሑፉም ለሰንሱር ቀርበ የሚያነሱትን አንስተው ለእነርሱ ዓላማ ይጠቅማል የሚሉትን እንዲያሣዩ ስለተፈቀደ፤ ወጣቶቹም ጽንሰ ሐሣቡን ሣይለውጡ በቀበሌው አዳራሽ ትያትሩን አሣዩ። የትያትሩ ተማልካቾች በሙሉ እናቶች በመሆናቸው በጣም ሲደሰቱ ግን ወጣቶቹን ታስረው ማየታቸውን አልፈለጉትም።እናቶችና ወጣቶቹ ከማንኛውም ሕብረተሰብ ክፍል በበለጠ ስለሚተዋወቁ፤ ስለወጣቶቹ የፈለገው መጥፎ ነገር ቢነገር ከልባቸው አይደርስም። በብዙ በታዎች አብረው ውለዋል፤ በሰላማዊ ሰልፉ በቤተሰብ ሸንጐው በዲሞክራሲ ግንባሩ ወዘተ አብረው ተከፍለዋል። እንደውም አንዳንዶቹ በግልጽ ተነስተው «በእውነቱ እነዚህን ልጆች ከምራቸው ሊገድሏቸው ነውን?» በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡ፤ «ይህ ከሆነማ ወጣቶቹ ሣይሆኑ ጥፋቶኞቹ ያለው



መንግሥት መሆኑን እንጠራጠርም» እስከማለት ሲደረሱ።የሴቶችም ሊቀመንበር ከበዓሉ ሥነሥርዓት በኋላ ተነስታ፤ «እነዚህ ወጣቶች ወደ አብዮቱ መስመር የተመለሱ ሲሆን ሆኖም ግን ከእነርሱ ተሽሎ የሚያነቃቸው በቀበሌአችን ስለሌለ ወደሪሺያ ቢሉኳቸው መልከም ነበር» ብላ ተናግራ፤።«እኛ ድርብ ጭቁኖች በትግላችን እናሸንፋለን እናሸንፋለን» በማለት የዕለቱ የሴቶች በዓል ተፈጸመ።

ወጣቶቹ በመጥኑም ቢሆን ዓላማቸውን ስለአስተዋወቁ በጣም በመደሰታቸው፤ ከወጣቶቹ አንዱ ሁኔታውን እንዲህ ያቀርበዋል። «ዘንድሮ እንደሴቶች ቀራጥነት በተለይ እንደእናቶች ቢሆን ኖር ይህ ሁሉ ጭፍጨፋ ባልተፈጸመ ነበር። በዚህን ከፍተኛ ውስጥ አንድም የሴት ገራፊ ከድሬ አላየንም።ሴቶች በተግባር እየተቷከሱ ሞተው እንደሆን እንጂ ተጠቁሞባቸው የመጡ በጣም ጥቂቶች ሲሆኑ፤ ሴት ሴትን ተጠቋቅመው የመጡ በጣት ይቆጠራሉ። ከዕለቱ ሁኔታ እንደታየው እውነትን ለመናገር በፍጽም ወደኋላ አላሉም። ያለፈውም ሆነ የአሁኑ ሥርዓት ሴቶችን ዝቅ አድርጉ ባያቀርባቸውና የወንዱን ግማሽ ያህሉ እንኳን ተምረው ቢሆን ይህ ያየነው ግፍ ሁሉ ላይፈጸም ይችል ይሆናል።»

ትዕይንቱ በመጠኑም የወንዶችን የማንእህሎኛነትን ጸባይ ይገልጻል።ያንንም ለማስወገድ ወንዶችና ሴቶች በጋራ ሊያደረጉት የሚገባቸውን ተግባር ጠቀሞ በጊዜው የነበረውን ተስፈንጣሪ ተግባር ሲቃወም፤ በቤተሰቦች መካከል ያለውን ያለመግባባት በጋራ ውይይት አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ በሚል ጽንሰ ሐሣብ የሚፈታ እንጂ በፕሮፖጋንዳና በሌላ የውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነት የሚገኝ መፍትሔ ያለመሆኑ ይገልፃል።

## ፳፬

ወጣቶቹ ትዕይቱን በሣዩ በአራተኛው ቀን ቀደም ከዚያን ቀበሌ አስረክበዋቸው የነበሩት፤ ገብረመድህን፣ ፍሬው፣ ማስረሸና እንዲሁም ከየፋፍሪካው የተመለመሉ የአብዮት ጠባቂዎች ሆነው ከቀበሌው ሲመጡ፤ ከገብረመድህን በስተቀር ሁሉሳቸው ከሳሽከብ ጠብመንጃ ታጥቀዋል። ገብረመድህን ግን የወታደር ኬፑን ከእናቱ ደፍቶ ጣቱን ከሽጉጡ ቃታ ውስጥ ጨምሮ አንድ አስሩን እናርኪስት በዛሬው ማታ እደፋቸዋለሁ፤ በማለት ፉከራውን ከሴቶቹ መኝታቤት ከአሰማ በኋላ ወጣቶቹም ከክፍሏ ወጥተው ከቀበሌው ጽሕፈት ቤት ጃርባ እንዲቀመጡ ተነገሯቸው ፤ አንድ በአንድ እየተጠሩ ከጽሕፍት ቤቱ በመግባት፤ በዕለቱም እንዲመቱ የተወሰነባቸው ወጣቶች በፎርም መልክ በተዘጋጀው ወረቀት ላይ እንዲፈርሙ ሲደረግ ምርመራቸው አልተጠናቀቀም የሚሏቸውን ምልክት በማድረግ ሲያልፏቸው፤ ፎርሙ ሙሉ ስማቸውንና በማስቃየት ከአገኙት ማስረጃ በኢሕአፖ ድርጅት በምን ክፍል ውስጥ ይሠሩ እንደነበር የሚያመለክት ሲሆን፤ በዚህን ዓይነት በዕለቱ የሚመቱትን መርጠው ከወጡ በኋላ ተመልሰን እንመጣለን በማለት ወጥተው ሲሄዱ፤እስረኞቹ በሙሉ ሴቶችን ጨምሮ በወንደቹ መኝታ ቤት እንዲቆዩ ሲደረግ፤በጊዜው ማን ተመቶ ማን እንደሚቀር ለይቶ ለማወቅ አልተቻለም ነበር። በክፍሉ ውስጥ ፍጹም ፀጥታ ነገሠ። ለሁሉም የምግብ ሰዓታቸውን ለማክበር የዕለቱ ተረኞች የመጣውን ምግብ በሦስት ገበታ ላይ ሠርተው ቢያቀርቡም፤ማናቸውም እንደቱን ጉርሻ ወደ ሆዳቸው መዋጥ ስላልቻሉ፤ ገበታው ተነስቶ፤የመጣው ብርቱካንና ሙዝ እንደየፍላጎታቸው ቢታደል፤ከአንዱ እስረኛ ከቸሩ በስተቀር አትክልቱንም ቢሆን የቀመሰ አልነበረም። ቸሩም እንዲቷን ብርቱካን ልጦ ዘለላዎቹን እየመጠጠ እውነቱ ከተቀመጠበት ሥፍራ ሄደ «ስንቅ ይሆነናል» በማለት ከላጠው ብርትኳን አከፍሎት ፤ እውነቱም የሲቃ ፈገግታ ፈገግ ብሎ የሰጠውን ብርቱካን እየመጠጠ ቸሩ ተጠርቶ በተዘጋጀው ፎርም ላይ ሲፈርም ስሻለየው የሱ መመታት አጠራጣሪ መሆኑን ሲገልጽለት፤እርሱ ግን በዕለቱ በተዘጋጀው ፎርም ላይ ባይፈርምም እንደሚገደል ቀደም ብሎ የተረዳው መሆኑን ጠቅሞ ያሲያዘችው የሴት ጓደኛው የብዙ ጊዜ ግንኙነት ስለነበራቸው ምንም ነገር ሣይቀራት ስለሱ የተናገረች ስለሆነና በተናገረችው መሠረት ከአውራሪስ ቡና ቤት ሄደው ስለአገኙት ቸሩን እጅ ከፍጅ እንደያዙት ስለሆነ መመርመሩም አላስፈለጋቸውም። የሱም ቃለ መጠይቁ የተጠናቀቀው እዚያኑ ፒያሣ ከፍተኛ ሁለት ሲሆን ከፍተኛ ሃያ ያመጡት ፈለቀ የሁለቱም ከፍተኛች ካድሬ በመሆኑ ነበር። ቸሩ ከታሰሩት ወጣቶች በዕድሜም ሆነ በአስተሳሰቡ በሰል ያለ ሲሆን በብሔራዊ ዮኒቨርሲቲ ውስጥ በተደረጉት የተማሪዎች ስብሰባ በዋና የሐፊነት እንደመራ ሲነገር፤ከመያዙም በፊት የአሰፋው ወሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ሰለ ወላጆቹን በቅርብ ሆኖ ለመርዳት



ከወሎ ክፍለሃገር በሚቀጥለው ቀን ለሚሄድ መዘጋጀቱን ለሴት ጓደኛው ነግሮት ስለነበር ለመሰነባበት ከቡና ቤቱ ሲጠብቃት ባላአሰበው መንገድ ጠቁማ ያሲያዘችው ስለነበር ብዙም ማስረጃ አልፈለጉበትም።

እስረኞቹም ገዳዮቹ ከአሁን አሁን ይመጣሉ በማለት ቢጠብቁም፤ የሄዱት ራሳቸውን በመጠጥ አስክሮ ለመምጣት ስለነበር፤ በእርግጥም የሚመጡበት ሰዓት አይታወቅም። የሰዓት እላፊው አዋጅ ስለማይመለከታቸው በር አዘግተው የመጠጣቱም መብት ስለነበራቸው ያው ወሰኙ መስከራቸው በመሆኑር፤ ወጣቶቹም በዚያን መብራት በሌለው ክፍላቸው ውስጥ ተቀምጠው ሞታቸውን መጠባበቅ ሆነ።

ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት አካባቢ መምጣታቸውን የሚያበስር ከበራፍ ጥይት ሲተኮስ፤ወጣቶቹም ማነህ ከማነህ ሳይለዩ ጫመዎቻቸውን ማጥለቅ ጃኬቶቻቸውን ለብሰው ተዘጋጅተው ሳለ፤በሩ ተከቶ አንድ በአንድ እያወጧቸው መብራት ካለበት ክፍል አመሣክረው፤ ከሟቾቹ መካከል ደህና ኮትና ጃኬት ያላቸውን አስወልቀው፤ በሸሚዝ ሲያስቀራቸው፤ቸሩን የለበሰውን ኮት ሲያስወልቁት ሣቅ ብሎ «ለሃገሬ ሕዝብ ከዚህ የተሻለ ነገር ትቼለት የምሄደው ይኖረኝ ይሆን?» በማለት ሲጠይቅ፤የቀድሞው የ«ቀይ ሽብሩ» ሊቀመንበር ጌትነት የፍጥኝ ታስሮ ከውጭ ቆሟል። ዘጠኝ ወጣቶች ተመርጠው ሲወጡ በጠቅላለው አስር ሰዎች ተይዘው ሄዱ። ግድያው ከዚያው ከቀበሌው በራፍ የግል አድራሽ በሌለው በችሩ ሲጀምር፤ ብዙ ሣይርቁ ከእህቱ ጋ ደብረዘይት ተጠቁሞበት የመጣውን ጌታቸውን በሁለተኛ ደረጃ ከዚያኑ አካባቢ መቱት። የቀሩትን በየወላጆቻቸው በራፍ ገለው ሲጥሏቸው ፤ እንደኛውን ወጣት ግን ከሦስቱ ከፍተኞች ማለትም ከከፍተኛ ሃያ አስራ ዘጠኝና አስራ ስምንት መጋጠሚያዎች መትተው ይጥሉታል።

በማግሥቱ ገብረመድህን ሌሎቹን ካድሬዎች አስከትሎ በይደር የቀሩትን ሰባት ወጣቶችና የሟቾችን ልብሶች ይዘው ከመግረፊያው ክፍል አስገብተዋቸው እንደቀድመው ጥያቄ በኢሕአፖ ውስጥ በምን ክፍል ውስጥ እንደሚሰሩ ለማውጣጣት በቀድሞ ግርፍ ላይ በዚያን በኤሌትሪክ ሽቦ ጀርባቸውን ተራ በተራ እያስገቡ ሲቀረድዱት፤ከደርግ ጽሕፈት ቤት «የቀዩ ሽብር» ኮሚቴ ይፈለጋል የሚለው መልዕክት ስለተላለፈ ሁላቸውም በጥሪው መሠረት ግርፋን አቁመው ከተጠሩበት መሥሪያ ቤት ደርሰው የተፈለጉበትን ሲጠይቁ፤ ዋናው የተፈለጉበት ምክንያት ባለፈው ቀን ከመቷቸው ወጣቶች መካከል ከሦስቱ ቀበሌዎች መጋጠሚያ የተጣለው ወጣት አስከሬን የማን ቀበሌ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፤ የዚያነው የእርሱ ነው በማለት ሣይነሳ እርፍደ፤ አላፊ አግዳሚው የውጭ አገር ሰዎች ሳይቀሩ ተመልክተውት፤ ሁኔታውም በሪፖርት መልክ ከደርግ ጽሕፈት ቤት

በመድረሱ የራሳቸው ሰው መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ እንደነበር ይነገራቸዋል። ለግርፍ የተወሰዱትም ወጣቶች ከወላጅ ምግብ እንዳይደርሳቸው ተከልክለው ገራፊዎቹ እስከሚመለሱ ከመገረፊያው ቤት ተዘግቶባቸው ዋሉ።

ያም ሆነ ይህ «የቀይ ሽብሩ» ከሚቴዎችም ጃንበሯ ዘቅዘቅ ስትል ከሰብሰበው መጥተው፤ ተዘግቶባቸው የዋሉትን ወጣቶች ለሽንት ማውጣት ስለነበረባቸው በመሣሪያ አጅበው ከከፍተኛው ጽሕፈት ቤት አጥር ውጭ ከሚገኘው ሜዳ ላይ ለአዳሪ ሲያወጧቸው፤ቀኑን በሙሉ ተሰፋ ባለመቁረጥ ፊታቸውን ለማየት ከዚያን የዋሉት ወላጆችም ያንን አጋጣሚ በመጠቀም ለማየት ባለፈት ቀን እንደአዩት የነሱንም ልጆች ገለው አምጥተው ከበራፍ ይጥሉብናልን በመፍራት በራቸውን እየዘጉ ከዘመድ ዘንድ በመሄድ የተጠለሉም ነበሩ። በዚያን ዓመት አበከሽን ጃንበር አትጥለቂቢኝ የሚያሰኝ ነበር።በወቅቱ ቀኑ ደገዝገዝ ሲል የሚፈለግ ሰው ይኑርም አይኑርም ቀበሌዎች እንደሃገር ቤቱ ሽፍታ በር እያስከፈቱ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ ቤቶችን የሚፈትሹበት ሰዓት ሲሆን፤ልጆች ላላቸው ቤተሰቦች ታሰሩም አልታሰሩም ምንም ለውጥ አልነበረውም። ምንጊዜም መጥተው ስለሚወስዷቸው ከመጪነቱና ከመሸበሩ እንብዘም አልዳኑም።በቁጥጥር ላይ ያሉትም ቢሆኑ ከድሬዎች ሜታቸውን ቀመው ባላዩ መጠጥ ከጠጡ በኋላ ማብረጃቸው በእስር ላይ የሚገኙትን መደብደብና ማሰቃየት ነበር።

በዕለቱም ስብሰባ ላይ ውለው የመጡት «የቀይ ሽብሩ» ከሚቴ አባሎች በቁጥጥራቸው ሥር የሚገኙትን ወጣቶች ለመግረፍና ለማሰቃየት አልታከታቸውም። ሰባቱን ወጣቶች በድብ ሲያሰቃዩቸው አምሽተው፤ በመጨረሽም የፍጥኝ እጆቻቸውን አስረው «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለውን መፈክር በመለጠፍ ለብዙሃኑ እስረኞች ያደረጓቸውን ለማሣየት ሰወሰዷቸው በውስጥ ሱሪያቸው ብቻ ሲሆኑ የተገረፈው አካላቸው ፍጹም ከሰል መስሏል፤ ከአንዳንዶቹ ቁስል ደሙ ሲወርድ መቆምም አቅቶአቸዋል። እንደአጋጣሚ የአንደኛው ወጣት ሁለት እህቶቹ ከሴት እስረኞች ውስጥ ኖረው ወንድማቸውን በፍጹም ሊለዩት አልቻሉም። በሌላ ጓደኛቸው እርሱ መሆኑ ሲነገራቸው ራሳቸውን ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ሁኔታ እሪ ብለው ሲጮኹ ምላሹ ግን ጥፊና እርግጫ ነበር።ከዚያንም ስድስት መቶ እስረኞች ወደሚሆኑት ወሰደዋቸው፤ «እኛን ያየ ይቀጣ ብላችሁ ተናገሩ» በማለት ሲጋበዟቸው፤ ማንም አልተናገረም ሁላቸውም ጸጥ ሲሉ፤ገብረመድህን ከእውነቱ ዘንድ ቆሞ ስለነበር በያዘው ሽጉጥ አፈሙዝ ተናገር ነው የምልህ በማለት እናቱን ሲበረቅሰው፤ ደሙ ከእናቱ መኸርኸር ሲጀምር የወታደር ኬፑን ከራሱ ይጭንበታል። የሚያደርጉት ነገር በሙሉ ቀልድና ጫወታ ይመስላል።



## ፳፱

«ቀይ ሽብር ይፋፋም» ተሸሽሎ «ቀይ ሽብር በአብዮታዊ ዲስፒሊን ይፋፋም» በሚል መፈክር ተለወጠ።ቀድሞ የነበረው ውጥረት በመጠኑም ቢሆን ለቀቅ ያለ ቢመስልም ግን የእያንዳንዱ ቀበሌ ሠራተኛ ሌላውን ጎድቶ የራሱን ጥቅም የማስጠበቁ ሁኔታ አልተለወጠም። የ«ቀይ ሽብር» መፈክር የወጣው የኢሕአፖን ደጋፊዎች ለማጥፋት ቢሆንም፤ሊያጠቁት የፈለጉትን ግለሰብ የኢሕአፖን ስም እየለጠፉበት ማስፈራራቱና ገንዘብ መቀበሉ አሸፈረኝም ካለ ከቀበሌ አምጥቶ መግረፉ የየዕለቱ የቀበሌ ሥራ ሲሆን፤ ቡና ቤት ገብቶ በነፃ መጠጣት፤ የፈለጓት ሴት ከአልጋ ይዞ መውጣት ገና አቅመ አዳም ያልደረሱ ሕፃናትን በሩካቤ ሥጋ መገናኘት ይህ አልፎ አልፎ የሕዝብ ቁጣ ለማብረድም በሬዲዮ ይነገራል በጋዜጣም ታትሞ ይወጣል። በጊዜው ግን የኢሕአፖ አባል ተብዬ እታሰራለሁኝ ወይም እገደላለሁ በመፍራት ትክክለኛ ሐሣቦችን ማቅረብ ሆነ ስህተት የሆኑትን መቃወም አልተቻለም። እንዳንዱ ይግረፍ ይግደል እንጂ በውስጡ በራሱ በደረሰበት ችግር የደረገ መንግሥት ተቃዋሚ ሊሆን ሲችል፤ በሌላ አኳያ ለመሠረታዊ ለውጥ ደርግን የሚቃወሙት ክፍሎ ይገላል ያስራል፤ ሁኔታው በጣም የተዘበረቀ ስለነበር እውነተኛውን ከአጭበርባሪው መለየት ያስቸገረበት ወቅት ነበር። በኢሕአፖ ላይ ግን ሁላቸውም አንድነት አላቸው። ምክንያቱም ብዙ ኢሕአፖን ማውገዝና ደጋፊዎችን ማጥፋትን እንደሽፋን መጠቀማቸው ግልጽ ሲሆን፤ያንንም የኢሕአፖን ደጋፊዎች አጠፋን ካሉ በኋላ ምን ሠሩ የሚለውን ጥያቄ በማቅረብ መልሱን ለማግኘት ቢሞከር በእውነትም ይደረጉ የነበሩት ነገሩች በሙሉ የሕዝብን እድገት ለማፋጠንና ጠንካራ ሃገር ለመገንባት እንዳልሆኑ ብዙም የሚያጠያይቅ አልነበረም።

የቀበሌ ተመራጮች ቀድሞ ይፈሩት የነበረው የኢሕአፖ ጥይት እንደማይመጣባቸው ሲረዱት በአካባቢው ሕዝብ መመረጣቸውን ዘንግተው ፍጹም እምባገነኖች በመናቸው፤በየምሽቱ በየመንገዱ የሚያገኙትን የሚያገኟትን ከቀበሌው እያመጡ መግረፍ ሥራቸው ሆነ። አንድ ቀን በቀበሌ አርባ ስምንት ውስጥ በሚገኝ መጠጥ ቤት ሁለት ግለሰቦች መጠጥ ቀርበላቸው ክፍያ ላይ ከአቅራቢዎች ጋር አለመግባባት ተፈጥረው ፤ባሌቤቷ ስልኳን አንስታ ከቀበሌ ስትደውል፤ባአጋጣሚ ዋናው የከፍተኛው አብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር ከዚያው ከቀበሌ ኖሮ አብዮት ጠባቂዎችን አስከትሎ ከላሽኮፑን ታጥቆ በመሄድ የተባሉትን ግለሰቦች ይዘዋቸው እነርሱም ያልተግባቡበትን ምክንያት ገልጸው ከዚህን ችግር ሁሉ ከመድረሳቸው በፊት ለመክፈል ፍቃደኛ ሆነው መቅረባቸውን ይገልፃሉ። በእርግጥ የተፈጠረው አለመግባባት እስከዚህም ከብደት የሚሰጠው ሳይሆን ክብደት እንዲኖረው ያደረገው በወቅቱ ትልቁ ለመኖር የሚሠራው ሥራ ሰውን

ማሰሪ መግረፉ ግለሰብም ነፃ ነኝ ለማለትና ታማኝነትን ለመግለጽ ሌላውን እንደወንጀለኛ ማቅረብ እንደፈሊጥ በመወሰዱና በሌላ በኩል ደግሞ የቡና ቤቱ ባለቤት የሊቀመንበሩ ቁባት ስለነበረች አለሁልሽ ለማለት ይመስላል ሠራዊቱን አስከትሎ ያለአንዳች ምርምር የሄደው። ከሳሽም ቃሏን በመስጠት ላይ ሳለች ሁለቱን ሰዎች በርግጫና በጥፊ ከዚያ ኑ ከቢሮ ድብደባውን አድርጎ፤ በአከባቢው ያሉትንም የአብዮት ጠባቂዎች እውነቱን እንዲያወጡ እንዲያደርጧቸው ትዕዛዙን ሰጥቶ ከከሳሽ ጋር ተያይዘው ሄዱ።

አብዮት ጠባቂዎችም ቀኑ ጨለምለም ሲል ሁለቱን በመጠጥ ምክንያት የተያዙትንና አንድ በቀበሌው ውስጥ የምትኖር እህቱን ለመጠየቅ ከትግራይ ክፍለሃገር መጥቶ እህቱም እንግዳችሁን ከቀበሌ አስመዝግቡ ተብሎ በወጣው አዋጅ መሠረት ልታስመዘግበው ወስዳው ያስቀሩትን ጥምር ድብደባቸውን ሲፈጽሙባቸው፤ በአካፋዩ ታስረው የነበሩትም ወጣቶች የሚከሄደውን ድርጊት በሙሉ ይከታተሉታል። በጊዜው ሰውን መግደል ማስቃየት ሹመትና ንብረት የሚያስገኝ መሆኑን በየተራቸው በከፍተኛው ቀበሌ ጽሕፈት ቤት ዘብ ሲቆሙ ያዩት ስለሆነ እነርሱም በበኩላቸው በመብታቸው ለመጠቀም ሰዎችንም ሙሉ ወንጀለኛ አድርጎ ለማቅረብ ድብደባቸውን ሲያደርጉ፤ የነዚህ የአሰቃያየት ዘዴ ደግሞ ፍጹም የተለየ ነበር። በቤቱ ውስጥ የተዘረጉትን የኤሌትሪክ ሽቦች በመፍታት የኤሌክትሪኩ ኃይል በሰውነታቸው ውስጥ እንዲያልፍ ሲደርጉት፤ በዚህን ጊዜ ግለሰቦቹ ራሳቸውን ሊቆጣጠሩት በማይችሉት መንገድ ሲጮኹ፤እንደራሩላቸው በእግዚአብሔር ስም ሲማጸኗቸው፤ እነርሱ ግን ፍጹም ርህራሄን ለማሣየት ተስኖአቸው ሲያገኟቸው፤ «በኪሳችን ያለው ገንዘብ ከተነገረብን ስለሚበልጥ እባካችሁን ወገኖች አታሰቃዩን» በማለት በልመና መልክ ተማጠኗቸው። ከትግራይ ክፍለሃገር የመጣውንም ለወንበዴዎች ገንዘብ ልትሰበስብ ነውና የመጣህው በአዲስ አበባ የምታውቃቸው ግለሰቦች ካሉ ተናገር ባሉት መሠረት፤ አንድ ባለጋራዥ ቤት የትግራይ ሰው ጠቁሞ ሲያስመጣ፤ ሸልስሸገን የቤት መኪና ስለነበራቸው ወደያውኑ ቁልፉን ተቀብለው ግለሰቡን ከቀበሌው እስር ቤት ከወጣቶቹ ቀጥሎ ካለው ክፍል አስገብተው ቆለፈውባቸው፤ በመጠጥ ምክንያት የተያዙትን ግን ማሰቃየታቸውን ሲያደርጉ፤እንደኛው ከኤሌትሪኩ ሾክ የተነሣ «ውኃ ውኃ የሰው ያለህ ወገኖቼ ሞትኩ» ቢላቸውም አባሩበት እንጂ አራሩም።«ቀበሌ ዘመዴ ቀበሌ ወዳጄ ቢላቸውም» ምንም ከአንደኛው መኪና ስለአገኙ ከነዚህ ደግሞ ምን እንደሚፈልጉ እምላክ ይወቀው። በመጨረሻም የአንደኛው ድምጹ እየሰለለና እየደከመ መምጣቱን፤ ያዳምጡ የነበሩትም ወጣቶች በመሞቱ ደምድመው «ሃገራችን ይህን መሰል ሕዝቦች» አሏት በማለት ተቆጭተው ጉናቸውን ጋደም አደረጉ።



## ፳፫

በጥበቃ ሥር የሚገኙትም ወጣቶች እንደወትሮአቸው ጉድጓድ ለመቆፈር አካፋና ደማ ለማውጣት ከእንዲት የቀበሌው ዕቃ ግምጃ ቤት ሲገቡ የሰው አስከሬን በባና ብርድልብስ ተጠቅልሎ ተጋድሟል።ከወጣቶቹ አንዱ በባናው ብርድልብስ የተጠቀለለውን አስከሬን ሲመለከተው ከሽልል ብሎ ደርቋል። እርሱም የማታውን ሰው እንደገደሉትና በባና ብርድልብስ ጠቅልልው ከዕቃው ግምጃ ቤት ማኖራቸውን ለጓደኞቹ ሲነግራቸው እውነትነቱን ለማረጋገጥ ተራ በተራ እየገቡ እየተመለከቱ ሲወጡ ጠባቂው አይቶ ኖሮ በዕለቱ በራሱ ሥልጣን ከጉድጓዱ ቁፈራ ነፃ እንደአደረጋቸው ነግሯራው፤ በእስር ቤት ፍጹም የተከለከለውን አስካሪ መጠጥም እንዲጠጡ ያቀርብላቸዋል። ወጣቶቹም አንፈልግም በማለት መጠጡን ይመልሱሉ። አንደኛውም ወጣት «እንደዚህን የምንደለል ቢሆን ኖሮ መች ከዚህን እንደርስ ነበር» በማለት የተሰማውን ይገልፃል።

ማታውን ጭለማን ተገን በማድረግ የዚያን ምስኪን ወገን አስከሬን በቃሬዛ ተሸክመው ከቀበሌ አርባ ስምንት በአሻገር ማለትም በስተጀንበር መግቢያ ካለው ረግራጋማ ሥፍራ ምሰው ቀብረውት፤ ሁለቱን ግለሰቦች ግን ምስጢር እንዳያወጡ በየአድራሻቸው የቀበሌ መታወቂያ ሰጥተዋቸው ከአውቶቡስ ተራ ድረስ ሄደው ሲያሰፉሯቸው፤ከትግራይም የመጣው ወደክፍለሃገሩ ሲሄድ፤ከሰደም የመጣው ጓደኛውን አጥቶ ወደጨበና ጉራጌው አውራጃ ይሰዱታል። እውነቱም ከሰደ የመጣውን ሰው ከመሄዱ በፊት ጠጋ ብሎ «ለመሆኑ የአንድ መለኪያ መጠጥ ዋጋ መክፈል አቅቷችሁ ነው ከዚህ ሁሉ የደረሰችሁት» በማለት ቢጠይቀው ተከዝ ብሎ «እውነቱን ተናገር ካልከኝ እንደውም የእኛ አልፎባቸው እንደሆን እንጂ ፍጹም ይህ የተባለው ነገር ሐሰት ነው» ፤ በማለት ትንሽ ከአሰበ በኋላ «እኔንም በገደሉኝ ኖሮ ይበጀኛል ፤ ለቤተሰቡ ምን ብዬ እናገራለሁ? የቀን ሥራ ሠርቶ ለቤተሰቡ ገንዘብ ይዤ እመጣለሁ ብሎ የተናገረና እነርሱም በናፍቆት የሚጠብቁትን ሰው ሞተ ብዬ ስላቸው ምን እንደሚሰማቸው አላውቅም። መቃብሩን እሣየን ቢሉኝ የት ብዬ እሣያቸዋለሁ?» ልጆች አሉትን ብሎ ሲጠይቀው «ሦስት ልጆች አሉት። ሚስቱን አራስ ቤት ትቷት የተዘራው ሰብል እስከሚደርስ ከመቀመጥ ብለን ለልጆች ልብስና ቀለብ ብናተርፍ በማለት ነበር የቀን ሥራ ለመሥራት ከከተማ የመጣነው። አልሆነም» በማለት እየተገሰመጠ ከእጠገቡ ሄደ።

ሁኔታውን ተጀምሮ እስኪያልቅ ይከታተሉት የነበሩት ወጣቶች በምን መንገድ ደርጊቱን ማጋለጥ እንደሚቻል ከመከሩ በኋላ የሴቶች ማሕበር ሊቀመንበር ከቢሮዋ ስትመጣ በሷ በኩል ድርጊቱን ለመንገር በተስማሙት መሠረት፤ከቀበሌው ስትመጣ ጠቅላላ

የተደረገውን ድርጊት ሲገልጹላት በአስቸኳይ ለባለቤቷ ነገረው፤እርሱም ለሚያውቃቸው ባለሥልጣኖች ሁኔታውን አቀርበት፤ በአስቸኳይ ለከፍተኛው ቀበሌ የተባለው ድርጊት ተጣርቶ እንዲቀርብ በትዕዛዝ መልክ ሲጠየቅ፤ ሁኔታውን ለማጣራት የከፍተኛው ቀበሌ ሊቀመንበር ከነአብዮት ጠባቂዎቹ ለጥያቄ ከከፍተኛው ጽሕፈት ቤት አቀርበው ሲመረምሯቸው ብዙም ሣይደበደቡ አስከሬ ኑንን የቀበሩበትን ሥፍራ መርተው ያሣያሉ። መርተው ሲያሣዩ አስከሬ ኑ ተቆፍሮ ሲወጣ በተሌቭዥን ተነስቶ ለአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብ ይታያል። በኢትዮጵያ ሬዲዮ ይተላለፋል ፤ በአዲስ ዘመን ጋዜጣም ታትሞ ይወጣል። የዚህን ዓይነት ግድያዎች በየቀበሌዎቹ ቢፈጸሙም፤ የኢሕአፖ አባሎች እየተባሉ «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለው መፈክር ተለጥፎባቸው ይጣላሉ። የከፍተኛው ካድሬ ፈለቀም ለሊቀምንበሩ ተሰምቶት ምነው ለእኔ ነግሮኝ ቢሆን ኖሮ አንድ እስሩን ከነዚህ ውስጥ ገድለን አብረን እንጥለው ነበር በማለት በድፍረት ተናግሮታል። ያም ሴራ የወጣቶቹ መሆኑን አምኖ እንገናኛለን በማለት ፉከራውን አሰምቶ ሄደ።



## ፳፬

የቀበሌ አርባ ስምንት ሊቀመንበርና አብዮት ጠባቂዎች በፈጸሙት የግድያ ወንጀል ከእስር ቤት ሲገቡ በቀበሌውም ለጥብቅ ጥበቃ የታወሰዱት እስረኞች በዚያ ኑ ከፍተኛ ቀበሌ ሰላሳ ሁለት ይወሰዳሉ።የአዲሱ ቀበሌ አብዮት ጠባቂዎችም በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ጥበቃቸውን በጣሙን አከረሩት። ለጥበቃው ያመቻቸው ዘንድ አስራ ዘጠኙንም የቀድሞው ባለንብረት ጋራዥ ከነበረ አለት ድንጋይ ከተነጠፈበት ወለል ላይ እንዲተኙ ተደረገ። አስራ ስምንቱ ወንዶችና አንዲቱ ልጃገረድ በተመደበላቸው ሥፍራ እስላቸውን እንጥፈው ተኙ። ወላጅን በፍጹም ማየት አይቻልም። ሽንት ቤቱም ከግቢው ውስጥ ስለነበር ወላጆች ከቀበሌ አርባ ስምንት ይጠቀሙበት የነበረውን የልጆቻቸውን ማየት ዕድል ሊያገኙት አልቻሉም። በቀበሌው ውስጥ ከሰባት እስከ አስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ለንቃት ተብለው ከዚያን ታስረው ይገኛሉ። ከእስራ ዘጠኙ እስረኞች ወንድምና እህቶች ከውስጣቸው ያላቸው ነበሩ ግን ቀርበው ለመነጋገር አልተፈቀደላቸውም። በሩቅ ዓይን ለዓይን እየተያዩ እንባቸውን ያፈሣሉ።

ቀበሌዎች በአገራረፍ ዘዴአቸው የተለያዩ ቢሆኑም በብዙ ተግባራቸው ይመሣሰላሉ። ለምሳሌ ከለውጡ በፊት ጸበኛቸው የሆነን ግለሰብ ምክንያት ፈጥሮ በማሰሩ፤ በቀበሌው ውስጥ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩትን ነጋዴዎች የዳቦ ቤቶች የመጠጥ ቤቶች ባለቤቶች ከቀበሌ አምጥተው በማስፈራራትና ገንዘብ በመቀበሉ ድርጊት ላይ አንድ ናቸው። ያም ሆነና ለጥበቃ የተወሰዱት አስራ ዘጠኙ ወጣቶች የቀበሌው ሹማምንት በፈጸሙት ወንጀል ምክንያት ወደ ቀበሌ ሃያ ዘጠኝ ተዘወሩ።

የቀበሌው ሹማምንትም እንደቀድሞ ሥራቸው በቀበሌው የስኳር እጥረት ተፈጥሯል በሚል ስም አንዱን ባለዳቦ ቤት ባለቤት ደብድበው ቤት ሲፈትሹ፤ ለዳቦ ማጣፈጫ የገዛውን ሁለት ኩንታል ስኳር ሲያገኙ፤ በራሱ መኪና ጭነው ከቀበሌ አምጥተው፤ እርሱንም ደብድበውት ከሌሎቹ እስረኞች ቀላቅለውት ሲሄዱ፤ ወጣቶቹም ከዚያን ያደረሰው የሁለቱ ኩንታል ጉዳይ መሆኑን ሲጠይቁት፤ ስኳሩን ከቀበሌው መግዛቱን ተናግሮ የተደበደበበት ምክንያት ግን እርሱና የቀበሌው ሊቀመንበር ቀድመ አብዮት ጸብ እንደነበራቸው ጠቁሞ ሁኔታው ብቀላ መሆኑን ይነግራቸዋል። ይህ በዚህ እንዳለ የተደብዳቢው እናት ለዘመዳቸው ለሆነ ከሌኔል የደረሰባቸውን ጥቃትና የንብረታቸውን በቀበሌ መዘረፍ ተናግረው ኖር ከሌኔሉም ከደርግ ጽሕፈት ቤት ነው በማለት የወሰዱትን ስኳርና የአሰሩትን ግለሰብ በአስቸኳይ ፈተው እንዲለቁ በስልክ ትዕዛዙን ሲያስተላልፍ፤ በእርግጥ ከደርግ ጽሕፈት ቤት መሆን አለመሆኑን

ለማጣራትም ጊዜ አልወሰዱም። ወዲያኑ ግለሰቡን በወሰሰ ተሸከመው የወሰዱትንም ሰኪር በመኪናው ጭነው እሰናብተዋቸው፤ ሃገር ሰላም ነው ብለው ባለትንንሽ ኪወስክ ቤቶችን እያስፈራሩ ገንዘብ ሲቀበሉ፤ በቀድሞው ወንጀላቸው ሁላቸውም ተይዘው ከከርቸሌ ተጨመሩ። በቀበሌው ጥበቃ ሥር የነበሩትም ወጣቶች በዚያኑ ከፍተኛ ቀበሌ ሃያ ዘጠኝ ተዛወሩ።

አዲሱ ቀበሌ በመጠኑም ቢሆን ከቀድሞቹ ቀበሌዎች በጥበቃው ላላ ያለ ነበር።ወላጅንም ሆነ ጓደኞችን ለተወሰነ ሰዓት ማነጋገር መቻሉና የእስሩም መላላት ያለምክንያት አልነበረም። በጊዜው በከፍተኛው ቀበሌ ውስጥ በ«ቀዩ ሽብር» ውስጥ ተመርጠው የነበሩት ግለሰቦች በራሳቸው አነሳሽነት በፈጠሩት ወንጀል እየተያዙ ከእስር ቤት በመታጎራቸውና፤አርባ አናርኪስቶችን አጋድሜአለሁ በማለት ይፎክር የነበረው ገብረመድህን ከረዳቶቹ ጭምር ከከርቼሌ በወረዱ፤ በወቅቱ የኢሕአፖን ደጋፊዎች ለማጥፋት መንግሥት የሸማቸው ግለሰቦች የሠሩት ወንጀል ከፍተኛ በመሆኑ፤ የሕዝብ ቁጣ ለማብረድ ከተጠቀሙባቸው በኋላ በሸረቡት ገመድ እንዲገቡ ሲደረግ፤ መንግሥትም ገብረመድህን ፍሬው ማስረሸንና ፈለቀን ለመሰሉ ግለሰቦች የግድያ ፍቃድ ሲሰጥ መጨረሻውም ይህ እንደሚሆን ያውቀዋል። በመጨረሻም እነርሱን ብቻ ጥፋተኛ በሎ ለማቅረብ ሆን ተብሎ የታቀደ በመሆኑ ድርጊቱ ብዙም የሚያጠራጥር አልነበረም።

በአጠቃላይ ይደረጉ የነበሩት እስሮችና ግድያዎች ቆመዋል ማለት አይደለም። ከከርቼሌ ከፖሊስ ጣቢያዎች ከቀሩት ከፍተኞችም ሰዎች እየተመረጡ የመታሉ።፤ውሎ አድሮ ሁላቸውም ተራቸውን ጠብቀው ከእስር ቤት ሲገቡ፤ መንግሥት ያቋቋመውም «የቀይ ሽብር» ከሚቴ በአዋጅ ፈረሰ ባይባልም እንደው ሹማምንቱን ከእስር ቤት በመጨመር ተበተነ።



## ፳፫

የአራተኛው የአብዮት በዓልም ሰመቃረቡ በዙው ዝግጅትም ለዚያን ሆነ። በተጨማሪም የሶማሊያን ወረራ ለመከላከል ለመሣሪያ መግዣ የወጣውን ገንዘብ ለመመለስ «የእናት ሃገር ጥሪ» በሚል የገንዘብ ስብሰባ ዝግጅት በየከፍተኛው ዕለተጀመረ በዙም የቀበሌ ሥራ ወደዚያን አተከረ።በእስር ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ጉዳይ ከቁምነገር የወሰደው አልነበረም። ወጣቶቹም ቀድሞ አውጥተው ይመቱናል የሚለው ሐሣባቸው እየተለወጠ ሲመጣ፤ የት እንዳሉ ለማያውቁ ጓደኞቸውና ዘመዳቸው መልክት ሲላኩ፤ አንዳንድ ወላጅም በሞታቸው አምነው እርማቸውን ከአወጡ በኋላ የተገናኙ ነበሩ። በጊዜው አንድ ሰው በቁጥጥር ሥር ከዋለ መገደሉ እርግጠኛ ቢሆንም የጥቂቶች በሺ ከሚቆጠሩት ውስጥ በሕይወት መትረፍ ከአንድ ማሰሩ የአተር ንፍሮ ውስጥ አንድና ሁለት ጥሬ የአተር ፍሬ የማግኘት ያህል ነው።የሰው ልጅ ተገድሎ በአደባባይ በሚጣልበት ሃገር አንድ ሰው በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ በሕይወት ይኖራል ብሎ መገመትም ሞኝነት ይሆናል። አንድ ለሕዝቡ በየጊዜው የሚዋሽ መንግሥት እንኳንም ጥፋቱና በደሉ በገሃድ ወጥተው ይቀርና መልካም ቢሰራ እምኖ የሚቀበለው አይኖርም። ያም ሆነ ይህ ከቀን ወደቀን በቀበሌው ውስጥ በተፈጠሩት ወንጀሎች ለሞት ቀረበው የነበሩ ወጣቶች በአጋጣሚ በዚህን ቀበሌ ሊድኑ ችለዋል።

ለምሳሌ እውነቱ ለመገደል ከተወሰነባቸው ወጣቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በማነህ ማነህ የሞት ተራውን ሲጠብቅ ጊዜው በመራዘሙ እስከዚህን ሊቆይ ችሏል። ከቤሔራዊ ዮኒቨርሲቲም እንደተያዘ ሞታል ተብሎ ተወርቶ ስለነበር ይኖራል ብሎ የገመተ አልነበረም። እርሱም ታስረው ከተፈቱት ጠያቂ ጓደኞቹ ጋር ከበር ቆሞ ሲነጋገር ከዚያን ቀበሌ ከነበረበት ክፍለሃገር ዘምታ የነበረች ልጃገረድ ስሙን በመጥራት እናግራው፤ ሰላምታ ተለዋውጠው ጓደኞቹም በየጊዜው እንደሚያነሱትና በመሞቱም አምነው ለወላጆቹ ሣይቀር ማርዳታቸውን ተናገራ፤ የመጣችበትን የቀበሌ ሥራዋን ትታ ከአከባቢው አትክልት ገዝታ ከመጣችለት በኋላ በሕይወት መኖሩን በአከባቢው ለሚኖሩ ጓደኞቹ ለመንገር ትሄዳለች። እውነቱም ለዓመት አንድ ጠያቂ መጥቶ ያላየው ጠያቂ በማግኘቱ፤ለእስር ቤት ጓደኞቹ አዲስ ዜና ለእርሱም ትልቅ የአእምሮ እረፍት ለወላጆቹም ለጓደኞቹም ትልቅ ደስታ።

በቀበሌው ውስጥ ታስረው የነበሩት ወጣቶች ከከፍተኛው ውስጥ ከሚገኙት ቀበሌዎች ቢሆኑም ቅሉ የጥቂቶቹ ወላጆች ኗሪነታቸው ክፍለሃገር በመሆኑ፤ እነርሱም በወሬ እንደተነገራቸው ሞተዋል የሚል ስለነበር፤ እርማቸውን አውጥተው ከተቀመጡ በኋላ በመገናኘታቸው ደስታቸው ከመጥን አልፎ እያስደሰታቸው ያለቀሱም

ነበሩ። ከቀሪዎቹ ውስጥ ተነጥለው የተመቱባቸውም ቢሆኑ እየመጡ «እንኳንም አተረፋችሁ» በማለት የተሰማቸውን ደስታ ሲገልጹ፤እንዳንዶች ጨርሰው የልጆቻቸውን ሞት እምነው ያልተቀበሉም ነበሩ። ለምሳሌ የአንድ «በቀዩ ሽብር» የተመታ ወጣት እናት ዘውትር እሁድ በዚያን ኑሮ ውድነት አረቄ አውጥተው በገኙት ገንዘብ በሰልፍ ዳቦ እየገዙ መጥተው ወጣቶቹን ሲጠይቁ፤ ወጣቶቹም ድርጊታቸው የአእምሮ እረፍት ስለነሣቸው ተሰብስበው ቀርበው ዳግመኛ ምንም ነገር ይዘው እንዳይመጡ የሚጠይቋቸውም ከሆነ በደ እጃቸውን መጥተው እንዲጠይቋቸው ሲነግሯቸው፤ እሳቸውም መልሰው «ልጄ አሁንም ከእናንተ መካከል ያለ እየመሰለኝ ነው፤ ልጆቼ የልጅን ነገር አድጋችሁ ወልዳችሁ እዩት። ፍቅሩ እንዴት እንደሚያደርግ ታዩታላችሁ። መቼም ልጄ ላይ ሞት የወሰኑት ሰዎች ወገኖች እንዳልሆኑ አልጠራጠርም። ምን ያደርጋል ጥቁርና ነጭ ሆኜ ካትከለ ፍቂ ያሣደኩትን አንድ ልጄን እንዲህ ለሚያልፍ ቀን አጣሁት» በማለት እንባቸውን ሲያፈሱት ወጣቶቹም ተነስተው እየተከዙ ወደክፍላቸው ይገባሉ።

ቀኑ እየገፋ ሲሄድ ወላጅን የተፈለገውን ያህል ማነጋገር ሲፈቀድ፤ እናቶችም ለቀበሌ ሥራቸው ሲመጡ ትንንሽቹን ልጆቻቸውን ከታሰሩት ታላላቆቻቸው ጋር እንዲውሉና ናፍቆታቸውን እንዲወጡ በማለት ከእስር ቤቱ እየተዋቸው ስለሚሄዱ፤ እንደአጋጣሚ የመንግሥቱ አባት ቀበሌአቸው ከዚያን ዋሮ ከጓደኞቻቸው ጋር ከቀበሌው ጽሕፈት ቤት በራፍ ቆመው ሲጫወቱ ፤ የቀበሌአቸው ወጣቶች ያውቋቸው ዋሮ «የመንግሥቱ አባት» በማለት ይጠቃቀሱባቸዋል። ይህንን የተመለከተች ሕፃን ከታሰረው ወንድሟ ጋር መጫወቷን አቋርጣ «አባባ» በማለት ሱሬአቸውን ትጎትታለች «እሳቸውም የማነሽ? ቆንጆ» በማለት ብድግ አድርገው አቅፈው ከሣሟት በኋላ አባቷን ጠይቀዋት፤ እሷም የአባቷን ስም ከነገረቻቸው በኋላ፤ የአውራ ጣቷን ከጉሟ ጨምራ «እርሶ የጋሼ መንግሥቱ አባት አይደሉም?» በማለት ስትጠይቃቸው፤ እሳቸውም አብረዋቸው ወደቆሙት ሰዎች ዞር በማለት ስቀው «ማን ነገረብኝ ብለው አዎን ነኝ» በማለት ሲመልሱላት፤ እሷም በመቀጠል «ለምን ወንድሜን እንዲፈታው አይነግሩትም» ስትላቸው፤ «እነርሱ ያመጡብን መዓት ነው ይበላቸው» በማለት ያሰናብቷታል።



## ፳፮

ኢሕአፖም ተደመሰሰ ተባለ «የቀዩ ሽብር ይፋፋም»መፈከሩ ተቀይሮ፤ በምትኩ ኢማሌድህ (ኢትዮጵያ ማርኪሲስት ሌኒኒስት ድርጅት ህብረት) ይጥንከር በሚል መፈከር ተለወጠ። ኢማሌድህ የሠራተኛው ፖርቲ አዋለጅ ናት፤ ኢማሌድህ የሠራተኛው ፖርቲ ጥስስ ናት፤ ኢማሌድህ ህብረት ናት ተባለ፤ እያደር አብዮቱ ልዩ ዓይነት ሃይማኖት እየሆነ ሲመጣ፤ ስለሤዎች አንድም ሦስትም ሆነው፤ አብ ወልድም መፈስ ቁዱስም ሠራዊም ነው። ኢማሌድህ አዋለጅም ጥንስስም ህብረትም ናት። የአንደኛውን መፈክር ለማጠናከር ሌላ መፈክር ማውጣቱ የተለመደ ሲሆን፤ ኢማሌድን ለማጠናከር፤ አረጓዴው ዘመቻ ግቡን ይመታል በማለት አብረው ተፈከሩ።መፈክሮችን በተግባር ለመተርጎምና ግለሰቦች ከፍራቻ አንፃር ተገተው እንዲሠሩ እየተባለ አስቀድሞ ግድያዎች በየጊዜው የተሞከረ ስለነበር በዚያን ስም ሌላ ግድያ መደረጉ፤ ሁኔታውን የአስራ ስምንተኛውንና አስራ ዘጠነኛውን መቶ ዓመታት የባሪያ ፈንጋዮች ሥራ አስመሰለው። ለምሳሌ ከአፍሪካ አህጉር ተጭነው የሚሄዱት ባሮች በመርከብ ላይ አመጽ እንዳያከሂዱ አስቀድመው አንድ አስሩን ገድለው በባሕር ውስጥ እንደሚጥሏቸውና የቀሩትምንም በእግር ሙቅና በእጅ ካቴና ያስሯቸው እንደነበር ሳይሸሽጉ በፊልም ሲያሣዩን፤ እኛ ግን በሃየኛው ክፍለዘመን በወገን ከዚያን ላቅ ባሉ አረመኔአዊ ተግባር ሲፈጸም እናያለን። ከመፈክር ተታከው የሚፈጸሙት ግድያዎች ያጤኑ ወጣት «እንኳንስ አቅመ አዳም ደርሼ ራሴን በማስተዳድርበት ጊዜ ይቅርና የሰባት ዓምት ሕፃን ሆኜ ካልመሰለኝ የእናቴን ትዕዛዝ እንኳን አልቀበለም። የእኛ መሪዎች ግን በአስፈራርቾ ሕዝቡን ያለፍላጎቱ ሊያሰሩት መሞከራቸው፤ ራስ ብቻ ለሃገር አሣቢ አድርጎ ማቅረብን ስለሚያመለክት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።»

ስለሆነም በኢማሌድህ ሠርገው የገቡ ፀረ- አብዮተኞች ይመነጠራሉ በሚል ስም አዲስ ግድያዎች ሲፈጸሙ፤ በአንደኛው ድርጅት ባልድን በሌላው አድናለሁ በማለት የሁለቱንም ድርጅቶች ትኬቶችን የገዙ ግለሰቦችን መግደል ማሰር ተጀመረ። በዚህንም ብዙ የተጎዱት ቀደም ሲል በወዝ ሊግ ውስጥ ተመልምለው ሲሰሩ ቆይተው ድርጅታቸው ሲበተንና መሪዎቹ ሲከበልሉ ወደ ወታደሩ ድርጅት ሰደድ የተመለመሉት ስለነበሩ፤ ሁኔታው ሁለት ዛፍ ትከል አንዱ ሲሰበር በሌላው ተጠልጠልን ሆኖ ሳለ ግን ባለመስራቱ በጣም አደገኛ ናቸው የሚሏቸውን አውጥተው ሲመቷቸው የቀሩትን ቀደም እጆቻቸውን ጡታቸውን ከቆረጧቸው ወገኖቻቸው ጋር ከእስር ቤት ጨመሯቸው።

«አብ ሲነካ ወልድ ይነካ» ነውና ታሪኩ የጓደኞች መታሰርና

መገደል የተመለከቱ የቀበሌ ተመራጮች በእናት ሃገር ስም የሰበሰቡት ገንዘብ እየያዙ በየአቅጣጫው ሃገሪቱን እየለቀቁ ወጡ። ሃገሪቱን በረሃብና በችግር ላይ ጥለዋት በእርግጥም ይቆጨሳትና በተግባር ሊሰሩላት የተዘጋጁትን ልጆቿን ገድለውና ከእስር ቤት ጨምረው ውስ አድራ እንኳን እንዳተንሰራራ አባት መሸመቻውን እናት የቡና መግዣዋን ከመቀነቷ ፈታ የሰጠቻቸውን ገንዘብ ይዘው በበዕድ ሃገር ተደላድለው ለመኖር ሃገሪቱን በየአቅጣጫው እየተዋት ከበለሉ።

የቀበሌ ሃያ ዘጠኝ ተመራጮችም ከራ ማራ ለአረም ሥራ በማለት የሰበሰቡትን ገንዘብ ይዘው ከሃገር ወጡ። ይህን እንደምሳሌ ልጥቀሰው እንጂ በአጠቃላይ ከሕዝብ የተሰበሰበው መዋጮች በትክክል ለተፈለገው ቦታ ደርሰዋልን? በእርግጥ በጊዜው ይሰጡ የነበሩት ምክንያቶች ገንዘቡ የሚውለው ለመሣሪያ መግዣ ስለሆነ ቢወሰድም ትክክል ነው በማለት ራሳቸውን ንጹህ ለማድረግ የሚሞክሩም ነበሩ። ይህ ግን ልባስ እንጂ በእውነትም ተቀርቃሪነትን የሚያሣይ አይሆንም። አሁንም ያንን ገንዘብ አጥፍ ድርብ አድርጎ የሚከፍለው ያው ሕዝቡ በመሆኑ ከዚህን ዓይነት ጉዳት ላይ እንዳይደርስ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ለመለወጥም ሆነ እነርሱን መከታ አድርገው የሚያሰቃዩትን ለማስወገድ የሚያደርገውን ቅዋሜ አፍኖና አዳፍኖ ልጆቹን ገድሎ የቀሩትን ከእስር ቤት ጨምሮ ሃገሪቱን በመሣሪያ ዋጋ በወልደ አግድ አሲዞ ሃገር ትቶ መውጣት ፍጹም በማንም ሃገርና ዜጋ ያልተደረገና ይደረጋል ተብሎ የማይታሰብ ድርጊት በዚያች ሃገር ስለተደረገ መጨው ትውልድ አዳውን እየገፈገፈ እህ! ሲል ይኖራል።

የቀበሌ ሃያ ዘጠኝ ተመራጮችም ገንዘብ ይዘው በመጥፋታቸው በጥበቃ ላይ የነበሩት አስራ ዘጠኙ ወጣቶችና ብዙሃኑ ተፈተው ከቀሩት ሃያ ወጣቶችን ጨምሮ ቂራ አካበቢ ከሚገኘው ቀድሞ የምስራቅ ክፍል ፍርድ ቤት ሕንፃ ውስጥ ተዛወሩ። አዲስ ካድሬ ተመድቦ ሲመጣ የከፍተኛውም ጽሕፈት ቤት ከዚያን ሆነ።አዲሱ ካድሬም ከቀድሞቹ ካድሬዎች በአሰራሩ ለየት ያለ በመሆኑ፤ ወጣቶቹን ለከፉም ሆነ ለደግ ቀርቦ ማነጋገርን አይፈልግም።በወቅቱ የሌንን ካበርት (ካባ) ለባሾች አንዱ ሆኖ ደረጃን የመጠበቅም ነገር እማ፤ ለሁሉም በጊዜው የሌኒን ካፖርት ለባሾች የተዘፈነላቸው ዘፈን ቢኖር

ለብሣ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሣ
ተመለሺ ቢሏት ወየት ተመልሣ

በወቅቱ የአራተኛው ዓመት የአብዮት በዓል ዝግጅት የሚደረግበት ስለነበር የእስረኛው ጉዳይ እንደአገባጋቢነት በለመወሰዱ፤ እስረኞቹም አሁድና ቅዳሜ ያለገደብ ከጒደኛም ሆነ



ከወላጅ ጋር ያለገደብ እንዲውሉ፤ሲፈቀድላቸው፤ እውነቱም ከመታሰሩ በፊት በሐሣብ ተለያይተው የነበረውን ሁሴንን በሕይወት መኖሩን ሰምቶ ሊጠይቀው ከቀበሌ መጥቶ አስቀድሞ የጠየቀው ጥያቄ ቢኖር፤ «አሁንም በቀድሞው አስተሳሰብህ ነህን?» የሚል ሲሆን፤«እርሱም በቆጣ በመጀመሪያ እንኳንስ አተረፈህ አይበልጥምን?» በማለት ቅሬታውን ሲገልጽ፤ የጋራ ጓደኞቻቸው ነገር እንዳይከረር ሁሴንን ተቆጥተው እንዴት እንደተያዘና ማን እንዳሲያዘው ሲጠይቁት፤ እርሱም ሁኔታውን በዝርዝር ሲያስረዳቸው፤ ሁሴንም በቀድሞ ጓደኛው የደረሰበትን በጥሞና ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ እርሱም በበኩሉ በሕይወት ይኖራል የሚል ግምት በፍጹም በሐሣቡ እንደሌለ ገልጾ ግን በሕይወት በመገናኘታቸው ደስታው ከፍተኛ መሆኑን ጠቁሞ፤ «አብረን በስደት በአዲስ አበባ ከተማ መሆናችንን ወላጆችህ በማወቃቸው አድራሻህን እየደጋገሙ ሲጠይቁኝ ፤ እኔም የምሰጣቸው መልስ ስላልነበረኝ ከማናኛቸውም እኔንና አንተን ከሚያውቁን ግለሰቦች ግንኙነቴን ሰቋርጥ፤ በተጨማሪም፤ እንደአስያዝኩህ በመወራቱ፤ በወላጆቻችን መካከል ቅሬታ ሲፈጠር፤ የጋራ ጓደኞቻችን ለእውነቱ ያልሆነ ለማ በማለት በፈጹም አስወገዱኝ።እነርሱን በአየሁኝ ቁጥር ስለእኔ የሚያወሩ እየመሰለኝ የአእምሮ እረፍት ነሣኝ የሥራ ጊዜዬንም ጨርሶ ወሰደብኝ። ዛሬ እውነቱን በሕይወት በማግኘቴ ለእኔ ትልቅ የምስራች ነው» በማለት ሐሽና ሲጃራውን አውጥቶ ሲያጤስ እውነቱም ተመልክቶ ከጥርሶቹ ፈገግ ብሎ «ከዊንስተን ወደ ሐሽና እንኳን በደህና ተሸጋገራችሁ» በማለት ሲያሾፍበት፤ የጋራ ጓደኞቻቸው «እናተስ ምንድነው? የምታጤሱት» በማለት ሲጠይቁት «ናያሳና ጉሬዘ ነው ሲላቸው» ሁሴንም መልሶ «ናያላ ለሚሊሻ ስለሚሠራ ጥራቱ ቀንሷል» ሲል እውነቱም መልሶ «እናንተ ሐሽና የምታጤሱ ዘመናዊያን የምታስወሩት ወሬ ነው» በማለት ንግግራቸውን በቀልድ ዘግተው በሚቀጥለው ሰንበት መጥተው እንደሚጠይቁት ነግረውት ይለያያሉ።

## ፳፬

የአዲሱ እስር ቤት ጥበቃው የላላ ቢሆንም በቁጥጥር ሥር ለሚገኙት እስረኞችም ሆነ ለቤተሰቦች፤ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስመርር ወቅት ነበር። ቤተሰብ በእስር ላይ ለሚገኙት ልጆቻቸው ምግብ ለማቅረብ ሲሉ ያላቸውን ንብረት ሙጥጥ አድርገው ጨርሰው የሚተኙበትን አልጋ ሳይቀር መሸጣቸውን ሲነግሯቸውና እነርሱ ግን ተቀምጠው ወላጆች ጾም እያደሩ የሚያቀርቡላቸውን ምግብ መቀበሉን ሲያስቡት የማያስወግዱት ፀጸት ከመሆኑ ሌላ፤ ከሉበትም ሁኔታ የባሰና የሚያስመርር ሆኖ ያገኙታል። ቤተሰቦች ችግራቸውን ለልጆቻቸው በመንገራቸው የተቃለለላቸው ቢመስላቸው ልጆቹም ቢሆኑ ሌላው ችግሮቻቸው ነበሩ። ወጣቶቹም ያንን በመረዳት በቀን ሦስቴ ይቀርብላቸው የነበረውን ምግብ ወደ አንድ ዝቅ እንዲል ሲያደርጉ፤ ችግሩ በጣም የባሰባቸው ቤተሰቦች ግን አልፎ አልፎ እንዲያቀርቡላቸው በመንገር በመጠኑም ችግሩን ለማቃለል ጥረት ያደርጋሉ። ወጣቶቹም ቢሆኑ የሚቀርብላቸውን ምግብ ለብቻቸው ሳይሆን የሚመገቡት እግዚአብሔር ያውጣችሁ ለማለት የሚመጡት የአካባቢው አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ድርሻ አላቸው።ያም ሆኖ ይቀርቡ የነበሩት ምግቦች እንደው ልጁን ጾም አላሣድር በሚል ቅን አሣቢነት ያምጡት እንጂ ከእንጀት ጠብ የሚልም አልነበረም። ሌላው ችግር በወቅቱ እንደመደበኛ ምግብነት ይቀርብ የነበረውን በቆሎ ሕዝቡ ለእንጀራነት ተጠቅሙበት ስለማያውቁ በምጣዱ ላይ እየነከረባቸው አማራጭ ስለሌላቸው ብቻ የሽሮ ወጣቸውን አፍስሰውበት ያቀርቧሉ። ያንንም በቆሎ ከቀበሌ ለመግዛት ያለው ውጣ ውረድ አያድርስ ነበር። «የእናት ሃገር ጥሪ» ያልከፈሉ ወይም ለቀበሌዎች ጉቦ ያልሰጡ ጥቂት መሽመቻ ገንዘብ እንኳን ብትኖራቸው እንደያዟት ይሞታታል እንጂ እህሉን አያገኙም።ትልቁ አማራጭ እንግዲህ የነበረን ኩራትና ክብር አፈር አልብሶ አንዳንድ የውጪ ድርጅቶች እህል ያድላሉ ከሚባልበት አካባቢ ሄዶ መሰለፍ ብቻ ነበር።

በጊዜው ወላጆች ለልጆቻቸው ከሚያቀርቡት ምግብ ተነስቶ የሃገሪቱ ሕዝብ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ መገምገም ያስችላል።በመጀመሪያ ወጣቶቹ እንደታሰሩ የጤፉ እንጀራ ከሥጋ ወጥ ጋር ያለገደብ በትልልቅ ሣህኖች ይመጣባቸው የነበሩት ቤተሰቦች ያ ሁሉ ቀርቶ የተሰባበረ የበቆሎ እንጀራ የሽሮ ወጥ ፈሰባቸው ሲመጡ ሲታይ ለመራባቸው ምንም መነገርም የሚያስፈልገው አልነበረም።«በአንቀርት ላይ ጆሮ ደግፍ፤» እንደሚባለው፣ በዚያ ላይ የእናት ሃገር መዋጮ ግዴታም ነበር።የእስር ቤቱን ሁኔታ ያጤነው እውነቱ «ጾም በሚታደርበት ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ግለሰብ ረሃብተኛ ነው ይላል። ዛሬ ጠግቦ ቢያድር ነገ መራቡ ስለማይቀር አልተራብኩም ብሎ የሚያስዋሽ አይደለም። ከሃገራችን



አንደኛው ክፍለሃገር ቢራብና ቢቸገር የቀሩትም ክፍለሃገሮች ረሃብና ችግር ላይ መሆናቸውን የተረዳሁት በአካባቢያችን ያለውን ሁኔታ ካጤንሁ በኋላ ነው። ከእኛ ውስጥ የአንዳችን ቤተሰብ መቸገር ሁላችንን ይነካናል ወይም ይመለከተናል። እኛ በውስጡ ያለነውን ትተን ከሃገር ውጭ ያለውን ሌላውን ዓለም ሣይቀር የሚነካበት ሁኔታ አለው። የእኛ መኖር ከሌሎች ሕዝቦች መኖር ጋር ተደጋጋፊነት አለው። ያም ሆኖ ሳለ የእኔ ቤተሰብ አልተነካም፤ አልተራበም አሁንም ጮማው ይቆረጣል፣ ጠጁ ይጠጣል ተብሎ የሚያስፎክር አይደለም።ቀደም ሲል አንዳንድ ክፍለሃገራት ሲራቡ በአዲስ አበባ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ ቢጠየቅ አልተራብንም ይል ይሆናል። አሁንም በቤተመንግሥት ዘብ የሚቆሙት ወታደሮች ስለረሃብ ቢወራላቸው ምንአልባት ጆሮአቸውን አይነካው ይሆናል።እንግዲህን በየጊዜው ለሚነሱት ችግሮች በቅድሚያ እንደራሳችን ችግሮች ወስደን መንስኤአቸውን ፈልገን ለማጥፋት መረባረብችን ካላደረግንና የራሴን ጭብጦ እዤአለሁ ስለሌላው ምን አገባኝ ከተባለ ረሃብ እንደተስቦ በሽታ ነውና እየተጎተተ ከማንኛችንም ቤት ይገባል።ቀድሞም እንደታየው ሁሉም ከአለፈነቱ ለማምለጥ የተቸገሩት ክፍለሃገራት ይጠቁማል። ያንን ሁኔታ ወደኋላ መለስ ብዬ ስመለከተው አሁን ከማየው ጋር ሣገናዝበው አሣፋሪና አጉል ግብዝነት እንደሆነ አረዳለሁ።»

ወጣቶቹም የወላጆቻቸውን ችግር መስማት ያናደቸው ያበሳጫቸው እንጂ ቢወጡም እንኳን ተሯርጠው በነሱ ምክንያትና በእግዚዙ መጥፎነት የተጎዱትን ቤተሰባቸውን ሠርቶ ለመርዳት ተስፋቸው የመነመነ ስሆን፤ ቀደም ሲል ተፈተው ከወጡት እነደተረዱት ነፃ ናችሁ የሚል ማስረጃ ከቀበሌ ካላመጣችሁ በመባል ቀጣሪዎች ሲመልሷቸው፤ ሌላው ቀርቶ ወላጆቻቸው ታክስ ለሚከፍሉበት ትምህርት እንኳን መብቱ እንደተነፈጋቸው ሲናገሩ በወቅቱ ግን ያለ ቀበሌ መታወቂያና የትምህርት ደረጃ የሚቀጥር የግል ድርጅት ቢኖር ከመርከቶ የሚገኘው ጋሜ ብቻ በመሆኑ እርሱም ቀደም ሲል ከሃገሪቱ ከየትኛውም አቅጣጫ ለሥራ ፍለጋ አዲስ አበባ ለሚመጡ ሥራ ፈላጊ ለቡና ቤት፣ ለአልጋ አንጣፊነት ለግለሰብ ምግብ አብሣይነት የሚያስቀጥር ከአብዮቱ በኋላ ግን ላይ ለተጠቀሱት ሥራዎች ተማሪዎችን እያስቀጠረ ወደ ክፍለሃገር ያለ ምንም መታወቂያ የሚልክ የግል ድርጅት ቢኖር እርሱ ብቻ ነበር። ከእስር ቤትም የተለቀቁት ወጣቶች ዳግመኛ የኢሕአፖን ድርጅት መዋቅር ትዘረጋላችሁ ተብለን ወደእስር ቤት እንጨመራለንን በመፍራት በትንሽ ገንዘብ እየተቀጠሩ ወደ ክፍለሃገራት ሲሄዱ አንዳንድ እህቶችም አማራጭ በማጣት ለሃገር ጉብኝት የሚመጡትን የውጭ አገር ሰዎችን በማግባት ማንነታቸውን ሳያውቁና ወደፊት ምን እንደሚገጥማቸው ከማንም ሳያማክሩ ከአለው ውጥረትና እስራት ብቻ ለማምለጥ በጋብቻ መልክ ተፈራርመው ከሃገር ለመውጣት ብቻ እንደአማራጭ እንዲወስዱ ተገደዋል።

## ፳፰

በማንኛውም አቅጣጫዎች ሁኔታዎች እየተባበሉ እንጂ እየተቃለሉ አልመጡም። በቤተሰብ ላይ ሆነ በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ በገንዘብና በንብረት ማለቅ ባስከተለው ጉዳት አብዛኛው ሕዝብ በበሽታ ላይ ሲወድቅ እስከሞት ያደረሰቻውም ነበሩ።

ለምሳሌ የአንዲት እስረኛ አባትና እናቷ በአንድ ሰሞን ውስጥ ታመው ከሆስፒታል ገብተው፤የጤናው ምርመራ ሲደረግላቸው ሁለቱም የደም ማነስ በሽታ እንዳለባቸው ተገልጾ፤ በእስር ላይ ያለችው ልጃቸው በአብዮት ጠባቂዎች ታጅባ ከሆስፒታሉ በመሄድ የደሙን ልገሣ ለማድረግ ምርምራ ሲደረግላት፤ራሷ የሚያስፈልጋት ሆኖ የሄደችበት ጉዳይ ሣይሣካላት ቀርቶ ከእስር ቤቱ ተመልሣ ሌሎቹ እስረኛ ጓደኞቿ የደሙን ልገሣ ለወላጆቿ እንዲያደርጉላት በጠየቀችው መሠረት ፍቃደኛ መሆናቸውን ገልጸውላት፤ ከቀበሌው እስፈቅዳ ይዛቸው ለመሄድ በመዘጋጀት ላይ ሳለች እናቷ አረፉ፤ የሚለው መልክት ከሆስፒታል ደረሰት። እርሷም የእናቷን አስከሬን አፈር ለማልበስ እንደወጣችና በእዝን ላይ ተቀምጣ ሳለች አባቷ ማረፋቸውን የሚገልጽ መልክት ከሆስፒታሉ ሰለተላከ አስከሬኑን ከቤት ለማምጣት ከሆስፒታል ተኬደ።

የወጣቷ አባትና እናት በአንድ ቀን ልዩነት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩት ፤እሷም ብትሆን ለጊዜው የአባት እናቷን አስከሬን አፈር ለማልበስ ተፈቀደላት እንጂ አልተፈታችም።

ዕልስታቸው እስከሚወጣ የተሰጣት ፍቃድ በማብቃቱ፤ ታናሽ ወንድሟን ከዘመድ እንዲከርም አድርጋ ያንን ከስምንት ቤተሰብ በላይ ይኖርበት የነበረውን ቤት ከጓሮ ዘግታ፤ የቅርብ ዘመደቿ ጅማ ለሚገኙት እህቶቿ እርማቸውን እንዲያወጡ እንዲነገሯቸው እንዲያደርጉላት ለጎረቤቶቻቸው ነግራ ወደእስር ቤቱ ተመለሰች።

ከእስር ቤቱም ተመልሳ ለብዙ ጊዜ ጓደኞቿ ለነበሩት እጽናኞቿ፤ ስለ አባት እናቷ ሞት መንስኤ የሆኑትን ምክንያቶች በሚቀጥለው ሁኔታ ትነግራቸዋለች እማዬ ትላለች ወጣቷ «ታላቅ ወንድማችንን በጣም ትወደዋለች፤ እርሱም ቢሆን የእማዬ ነገር አይሆንለትም፤ዘውትር ማታ ከወንድም ጋሼ በስተቀር የቀረነው እባባን ከበን ከመኖሪያ ቤት ስናጫውተው ፤ እማዬና ወንድማችን ከማድ ቤት የራሣቸው የሆነ ጫወታ አላቸው። እንደወትሮ እማዬና ታላቅ ወንድማችን ከማድ ቤት ተቀምጠው እርሱም ለእማማ የባጡን የቆጡን ሲያወራላት እሷም በቁም ነገር ስታደምጠው፤ የመኖሪያ ቤታችን ተንኳኳቶ፤ ማንነታቸው ሲጠየቅ የቀበሌው ተመራጮች መሆናቸውን ሲናገሩ፤ አባባም እንድንከፍትላቸው በነገረን መሠረት በሩ ተከፈቶላቸው ከቤት ከገቡ በኋላ አንደኛው በእባባ ላይ ሽጉጡን ሲደግንበት፤ እባባም የተፈለገበትን ምክንያት ጠይቆ ለመውጣት በመዘጋጀት ላይ ሳለ «ያ እናርኪስት ልጅ የት አለ?» በማለት ሲጠይቁት መሣሪያ ከደገነበት ካድሬ ጋር «እኔስ ምንድ ነኝ?» በማለት ግብ ግብ ሲገጥሙ፤ ለሁሉም የመጡት ወንድም ጋሼን ለመያዝ ስለነበር፤ እርሱም ከማድ ቤት ተቀምጦ ስሙን ሲጠሩት ስለሰማ እማዬን ደህና ሁኚ ብሎ ጉንጮቿን ስሞ ከበር ወጥቶ ከሄደበት ቀን ጀምሮ እማማ እንደእለቀሰች ነበር። አይኖቿም እየደከሙ አቅምም እያነሣት ያለ እድሜዋ አረጀች። የወንድሜ ጉዳይ ሲፀጽታቸው ሁለት ልጆቻቸውን ቀበሌዎች መጥተው ሲወስዱን፤እባባንም ልጅህን እቅርብ በማለት ከእስር ቤት ሲጨምሩት፤ ወላጆቻችን ተደላድለው በሚቀመጡበት ወቅት በእኛ በልጆቻቸው ምክንያት በሥርዓቱ መጥፎነት ብስጭትና ንዴት በፈጠረው በሽታ እየታመሙ ለመሞት በቁ» በማለት የቤተሰቧን ችግር ታቀርበዋለች ።

ወጣቶቹም አልፎ አልፎ በወላጅ ተያዥነት እየተፈቀደላቸው ሲወጡ ቀደም ከተፈቱት ይነገራቸው የነበረውን በተግባር ሲመለከቱት ይብሱን ተስፋ የሚያስቆርጥ እንጂ የተሻለ አልነበረም። ከውጪው እስር ቤቱ የተሻለ መሆኑን ሲገልጹ ውጥረቱና እርስ በእርስ የነበረው መፈራራቱ እጅግ የከፋ ሲሆን በተግባር ጎልቶ የሚታይ ነገር ቢኖር፤ቀደም ሲል «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለው መፍክር ተለጥፎባቸው የነበሩት የኤሌትሪክ እንጨቶች «አረንጓዴው ዘመቻ ግቡን ይመታል።» የሚለው መፈክር ተለጥፎባቸው መታየቱ ነበር። መፈክሩንም በተግባር ለመተርጐም በሚል ስም አፈሳ መጀመራቸውና፤ ዘመቻውንም የተቃወሙ ክፍሎችን መግደሉና ማሰሩን ሲያጧጡፉት «ቀይ ሽብር» ሥራ ያስገኘላቸው ካድሬና አብዮት ጠባቂዎች በአዲስ ጉልበት የአረንጓዴውን ዘመቻ መፈክር በተግባር ለማዋል መሯሯጥ ሲያደርጉ ይታያሉ። የአረንጓዴው ዘመቻ ይበልጥ ትኩረታቸው፤ በሴታኛ አደሪ ላይ በመሆኑ ትዘምታላችሁ በማለት ቀበሌና ካድሬ ሕጋዊ ዘረፋቸውን ሲያደርጉባቸው፤ ለዓመታት ያጠራቀሙትን ንብረታቸውን በጌጥ መልክ ያስቀመጡን ገንዘባቸውን በርካሽ ዋጋ በገዲ ቀባ ሲያሸጧቸው፤ ከዘመቻው እናድናችኋለን በማለት የፍቶተ ሥጋ ግንኙነቱን ጉቦ መቀበሉን በወቅቱ ተያይዘውት ነበር። መንግሥት በአዋጅ ያወጣው ስለሆነ የመብት ጥያቄ ከሞት እንደሚያደርስ ስለሚታወቅ ማንም የቅዋሜ መልክ እንብዛም አላሣየም። በሕብረተሰቡ ውስጥ ከዕለት ወደዕለት ይፈጸሙ የነበሩት እስነዋሪና አሣፋሪ ተግባሮች እንደቀልድ በመወሰዳቸው፤ እንዳንድ ግብዞች ከሁኔታው ያልተጎዱ ክፍሎች በጊዜው በሕዝቡ ላይ

የሚፈጸሙትን ድረጊቶች እንደማፈዣና መሳቂያ ሲጠቀሙባቸው የሰማ ከእስር ቤቱ በወሰጅ ተያዥነት የወጣ ወጣት እንዲህ ያቀርበዋል።

እንድ ጠዉ ቢራ ያቀረበችለትን የቡና ቤት ሠራተኛ ዳሊዋን መታ አድርጎ «ጋሼ መንግሥቱ ይቀልዳል፤ ይህንን የመሰለ ሰውነት ከጊቢ በረሃ ሊልከው ነው በማለት ሲያሸፍ ጓደኞቹ የተከረከሩትን ያህል ይስቃሉ።በከተማችን ያለው ዜና ይህ ነው» በማለት ያጫውታቸዋል።

የወጣቱንም ዜና ከሚያዳምጡት እስረኞች አንደኛዋ ሴት የተሰማትን እንዲህ ታቀርበዋለች። «ለራሱ ነፃነት የሌለው ግብዝ ወንድ ሥርዓቱ ከጀመረ ጀምሮ ዝቅ ያደረጋትን እህቱን በበኩሉ ሊጫናት መሞከሩን ሁላችንም በየዕለት ኑሮአችን የምናየው ነው። አብዮት ከፈነዳበት ጀምሮ አንዳንድ ግብዞች ለውጡን እነርሱ እንዳመጡት በመገመት ራሣቸውን በማመፃደቅና አንድ እርምጃ ወደፊት የሄዱ መስሎአቸው አብረዋቸው በረሃ ለበረሃ ይጉላሉ የነበሩትን የልጆቻቸውን እናቶች በመፍታት የአሁኑን አጋጣሚ በመጠቀም ሚስት ማመረጥ መጀመራቸው፤ የደርግ አባል የሕዝብ ድርጅት ሠራተኛ የቀበሌ ተመራጭ እየተባለ ቅምጥ ማስቀመጥ ፤ ከድሬው የተመኛትን እህት የኢሕአፖ ስም እየለጠፈበት ያለፍላጎቷ አልጋ ይዟት መውጣት የወቅቱ ታሪካች ነው። «የነፃውን እርምጃ» ወቅትማ አይነሣ የኢሕአፖ አባላት ጠቅላላ ሴቶች ነበሩ ለማለት ያስደፍራል።«የቀይ ሽብሩንም» ቢሆን አብረን አይተነዋል። ቀሚሰችንን አስወልቀውን እየው ዳሌዋ እግሮቿ ትንሽ በይጣመሙ ፀጉሯ በይከረድድ እያሉ እንደበሪያ ፈንጋይ ሲሰፍሩን ሲለኩን ያያችሁት ነው።የሃገራችን መሪዎች የሚከሄደውን ግፍ ያውቁታል ሥልጣናቸውን ስለማይነካባቸውና በተዘዋዋሪ የድርጊቱ ተካፋዮች በመሆናቸው ዝም ብለው ያዩታል። ለምሳሌ የከፍተኛ ሰባት ሊቀመንበር የነበረው እስር አለቃ የአስራ ሁለት ዓመት ወጣት ክብረ ድንግልናዋን በመድፈሩ ሕዝብ ተቆጥቶ ሲነሳባቸው መግደላቸው ለሕዝቡ ተቆርቁረው ሣይሆን ቅዋሚውን ለማቀዝቀዝ ሆን ተብሎ የተደረገ ዘዴ መሆኑን ማንም ያውቀዋል።እኔም በግል በሴትነቴ ያየሁት ሲሆን እናተም በበኩላችሁ የታዘባችሁት ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በአሁኑም ጊዜ በዘመቻው ስም አማከኝቶ የሴተኛ አዳሪን ንብረት ማሸጥና አገባሻለሁ ብሎ ማታለል የሚያስደንቅ አይደለም። በየምሽቱ ከቡና ቤቶች ደጃፍ ቆሞ ለተመለከተ ለሦስት ለአራት የኩዩባ ወታደሮች እህቶችን አባት እናት በገዙት የጂፕ መኪና ላይ ሲጭኗቸው ሣናይ አልቀረንም። ምን ዋጋ አለው «ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አያነሣውም»ይባላል።



## ፳፱

በአዲስ አበባ ቀበሌዎች ጥበቃ ሥር የሚገኙትን እስረኞችን ሁኔታ እንዲመረምርና ወሰኔ ተሰቶባቸው ወደ ከርቼሌ ከትልቁ የሃገራችን እስር ቤት እንዲወርዱ ለማድረግ፤ከሃያ አምስቱ ከፍተኞች ተጢምቆ የወጣ አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቋመ። ኮሚቴውንም በሊቀመንበርነት እንዲመራ የተመረጠው የከፍተኛ አስራ አምስት ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ በሣዝኖ ባይሳ ሲሆን፤ አባላቱም ቀድሞውንም በጭካኔአቸው የታወቁ ስለነበር ብዙም የሚያስደስት ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ የገመተ አልነበረም። እንደ በሣዝነው ካለ የዮኒቨርሲቲ መምህር ለብዙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለሆኑ የሚያቀርበውን ጥያቄ መመለሱ ከባድ ይሆናል ብለው ወጣቶቹ በማሰብ ድንጋጤ ላይ ሣይወድቁ አልቀሩም። አንዳንደቹም «ምንእልባት ስለሃገሩ ወጣቶች ተሰምቶት በትልቅ ደረጃ ጥናት ያካሄድ ይሆናል» በማለት ትልቅ በታም የሰጡት ነበሩ። በቅርብ የሚያውቁት ደግሞ «የዚህን አይነት ሰው ቢሆን ኖሮ በከፍተኛው ያንን ያህል ወጣት አያስመታም ነበር» በማለት የምሁሩነቱን ደረጃ ዝቅ አድርገው ለመመልከት የሞከሩም ነበሩ። «ሆም እርሱ ሊመረምረን እንደመጣው ሁሉ እኛም የምሁሩነቱን ደረጃ እንመረምረዋለን» በማለት ተራ በተራ ለአዲሱ ጥያቄ ቀረቡ።

እንደነገብረመድህን መለዮ አያድርጉ ሽጉጣቸውን በጠረጴዛ ላይ አያስቀምጡ እንጂ ሁኔታቸው አንድ ነበር። አንድ ወጣት ተጠይቆ ከወጣ በኋላ ሁኔታው አስገርሞት የማንንም ስም ሣይጠቅስ «ሕዝብ የትምህርት ታክስ የሚከፍለው ይህንን መሰል ምሁራን ለማፍራት ከሆነ ጥፋት ነው። ለካንስ ምሁሩ የፖለቲካን ሥራ ለመሥራት የሚሯሯጠው በተማረበት መስክ ውጤት ማስገኘት ሣይሆንለት ሲቀር ነው። ትምህርት የተደፈኑትንና የተሸሸጉትን ለሰው ልጆች አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ፈልጎ ማውጫ መሣሪያ መሆኑ ታምኖበት ሁላችንም ከሰባት ዓመት ዕድሜአችን ጀምሮ ያለውን ጊዜያችንን አጥፍተንበታል፤ሆኖም በበኩሌ ስመለከተው ውጤቱ አልታየኝም። አንዳንድ ግለሰቦችን ከሚሰሩት ሥራ ስመለከት መግለጫው አባባል እንጂ ሐቅነቱ ያጠራጥረኛል። ወይም ትምህሩትን ስህተት በሆነ መንገድ ተወስደ ይሆን በማለት ጥርጣሬ ውስጥ ጢምሮኛል። በጣም ጥቂቶችን ሳስታውስ ደግሞ እእምሮዬ ይጽናናል።»

መርማሪው ኮሚቴ በቀበሌ ቁጥጥር ሥር የነበሩትን ወጣቶች ከቀበሌ ቀበሌ ያዘሯቸው ከነበሩት ውስጥ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በመፍረድ ከከርቸሌ እንዲወርዱ ወሰነው፤ይህ በዚህ እንዳለ ወጣቶቹ

ከቀድሞ በበለጠ ሰውነታቸው እየከሳ የጥፍሮቹ እግሮቻቸው እያበጡ፤ የምግብ ፍላጎታቸው እየቀነሰ፤ አልፎ አልፎ እያሰላቸው ደም መትፋት ስለጀመሩ ፤ ወለጆች ወጥተው እንዲታከሙላቸው በማለት መጠይቅ አቀርበው፤ በአብዮት ጠባቂዎች እየታጀቡ ከሰንበ ነቀርሣ ሲወሰዱ ፤ ያንን አጋጣሚ በመጠቀም እውነቱ ከጥበቃ ያመልጣል።





እውነቱ በወቅቱ ከዘመድ ወይም ቀድሞ ከሚያውቃቸው ጓደኞቹ ዘንድ ለመሄድ አልፈለገም። ከዘመድ ዘንድ ቢሄድ ወደእስር ቤት እንዲመለስ አድርገውት ይቅርታ እንጠይቅልሃለን እንደሚሉት ያውቀዋል።ይህ ደግሞ ቀደም ሲል አንዳንድ ወላጆች ሞክረውት ሊያመልጡ የሚችሉትን ልጆቻቸውን ከእስር ቤት እንዲመለሱ አድርገው ያለርህራሄ ገለዋቸው ከደጃፍ ሲጥሉላቸው እንደነበር እስር ቤት በነበረበት ወቅት ተመልክቶታል። በጓደኛም በኩል ያለው እምነት በጣም ቀንሷል። ኢሕአፖ ጠፋ እየተባለ በሚወራበትና «ቀዩ ሽብር» ሕዝቡን ፍራት ላይ ከጣለው በኋላ ከጓደኛ ዘንድ ሄዶ ገንዘብ መጠየቅ እንደው ጊዜን ማጥፋት እንደሆነ ተረድቶታል።የቀድሞ የልብ ጓደኞቹ ጌትነት፣ ታደሰና ሙሉጌታ መመታታቸውን ከእስር ቤት በነበረበት ወቅት ሰምቶታል። ጌቱ በከፍተኛ አራት አርጌው አይሮፕላን ጣቢያ ከለው ቀበሌ ውስጥ በድብደባ ሞቶ«ቀይ ሽብር» ተለጥፎበት ከክፍለሃገር አውቶቡስ ጣቢያ መጣሉን ፤ ሙሉጌታ ተይዞ ከቀበሌ ሲወሰድ ለማምለጥ ሞክሯል በመባል መገደሉን፤ ታደሰም ከጓደኞቹ ቤት ተጠልሎ ሣለ በጥቆማ በአፋኝ ጓዶች ተይዞ ከከፍተኛ ሃያ አምስት ተወስዶ በአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ከአጎል በታ ተመቶ ስለሞተ መቀጣጫ ተብሎ «ቀይ ሽብር ይፋፋም» የሚለው መፈክር ተለጥፎበት ከሣችስ ከእርሸ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ደጃፍ ላይ መጣሉን ተነግሮታል።

ሆኖም ታደስን ለማያውቁት የቀቤ ባለሥልጣኖች ወይም የነበረው መንግሥት ተወካዮች እንደመቀጣጫ ያቀርቡት እንጂ አብረውት ይሠሩ ለነበሩት የእርሻ ሚኒስትር ሠራተኞች ለጎጃም ለባሌና ለሲዳሞ ገበሬዎች ጥሩ ምሳሌ ነበር። ከአብዮት በፊትም ሆነ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደአሜሪካን አገር እንዲሄድ በተደጋጋሚ ቢጠየቅ የነበረው ዕውቀት ከሃገሩ ገበሬ ጋር ለመሥራት በቂው መሆኑን ጠቅሶ የተሰጠውን ዕድል ሣይቀበለው ቀርቶአል።ከሃገሪቱ አስተዳደር መለወጥ በኋላም ቢሆን ከነበረው ግድያና እስራት አንፃር ብዙ የተማረው ክፍል ሃገር ለቆ ለመውጣት በሚሯሯጥበት ወቅት ከሶቪየት ሕብረት ዕድሉ ቢሰጠውም ቀደም ሲል የሰጠውን ምክንያት በማቅርብ ሳይቀበለው ቀርቷል። የመሥሪያ ቤቱም ባለሥልጣኖች ባለው ችሎታ በመተማመን በጊዜው ለእርሻ ሥራ ባለሞያዎች ይሰጡ ለነበሩት ሴሚናሮች እየተጋበዘ ያጠናቀራቸውን ጥናቶች በማቅረብ ብዙ አስተዋእፅዎችን ያበረከተ ሲሆን በወቅቱ ተፈጥረው የነበሩት የፖለቲካ መስመር ልዩነቶች ሰፍተው ተገልጋዩን ሕዝብ እንዳይጎዱት በማለት በደብረዘይትና በአዋሳ በተደረጉት ሴሚናሩች ተገኝቶ ትልቅ

እስተዋእፅ ያበረከተ ባለሞያ እንጂ እንደተነገረበት ወንጀለኛ አልነበረም።

እርሱም ለገበሬው መደረግ ያለበትን ገበሬውም ምርቱን ለማሳደግ ኑሮውን ለዘለቄታው ለማሻሻል መከተል የሚኖርበትን በማስተማርና በመማር ላይ ሳለ በጊዜው በተመሠረቱት የፖለቲካ ቡዱኖች እርሱንም የቡድናቸው አባል እንዲሆን ሣይጠይቁት አልቀሩም። የሱም ግዴታው በተማረው የግብርና ሥራ የሚጠበቅበትን የሥራ ክፍፍል ማከናወን እንጂ ሕዝብ ባልመረጣቸውና መሥራት ያለመሥራታቸውን ከማያውቃቸው ጋር ተሰልፎ ከሥልጣን ወጥቶ ለመቀመጥ ያለመፈለጉን ይገልፃል። «በተጨማሪም በተቀደሚ በተግባር ሣልፈተንና መሥራት ያለመሥራቴን በተገልጋዩ ግብር ከፋዩ ሕዝብ ሣይገመገመኝ የዚህ ድርጅት አባል ነኝ ተቀበሉኝ ማለቱ በይበልጥ በሕዝብ ውስጥ ጥርጣሬን ከመፍጠሩ ሌላ የሚያመጣው ውጤት የለውም። ይህም ስለሆነ በገበሬው ውስጥ ጥርጣሬዎች ተፈጥረው እርስ በርሱ በሐሣብ ተለያይቶ የመሥራት ፍላጐቱ እንዲመክን አልፈልግም። ሕዝቡ በፈለገው መንገድ ሊያሰራኝ ከመረጠኝ ግን እሌ አልልም።» ይህን መሰል ሐሣብ በመሰንዘሩ እናርኪስት ነው በማለት የስም ማጥፋት ዘመቻ በማድረግ ከሚያገለግለው ገበሬም ጋር ተጨባጭነት የሌላቸውን ምክንያቶች በማቅረብ ሲያጣሉት፤ እርሱም በዚያን አይነት ለዘለቄታው መሥራት ስላልቻለ በአካባቢው የነበሩትን ድክመቶች ከሰበሰበው ማስረጃ ጋር ለክፍለሃገሩ አስተዳደር በማቅረብ ሥራውን ለቆ ከአዲስ አበባ ከጓደኞቹ ተጠልሎ ሳለ የኢሕአፖ አባል ተብሎ በመያዝ ተገደለ።

ለእውነቱ የጓደኞቹ በየምክንያቱ መሞት ለሱም የሚሄድበትን አቅጣጫ ሳያጠብብት አልቀረም።በአዲስ አበባ ለዘለቄታው መቆየቱ አልታየውም። ከከተማው ለመውጣትና ኬላዎችን ለማለፍ መታወቂያ ያስፈልጋል። ያ ደገሞ የለውም።ያለው አንድ ዕድል ብቻ ነበር። ይሄውም ከዮኒቨርሲቲ ሄደ የመኝታ ቤት ጓደኛውን ማግኘት ብቻ ሲሆን ጓደኛው ከእስር ቤቱ መጥቶ ይጠይቀው ስለነበር፤ የእህቱን የመሥሪያ ቤት ስልክ ተጠቅሞ ደውሎለት፤እሷም በያዘችላቸው ቀጠሮ መሠረት ከዮኒቨርሲቲው ደጃፍ ማለተም ከስድስት ኪሎ ሲገናኙ፤ጓደኛውም ሊያምን አልቻለም።ለሁሉም ዳግም ተገናኘን በማለት እየተጫወቱ ቁርሣቸውን ለመመገብ ወደዮኒቨርሲቲው የምግብ አዳራሽ ገቡ።

ጓደኛውም ድርሻውን ምግብ ይዞ መጥቶ እየተመገቡ በአካባቢው ስለተደረጉት መሻሻሎች እየጫወተው፤ በማሸፍ «በዮኒቨርሲታችን የተለወጠ ነገር ቢኖር ከበቆሎ ዳቦ ወደ ስንዴ



ቅንጩ ተሸጋግረናል፤ ተማሪ ከዚህ ሌላ ምን ይፈልጋል።«ነጭ ኑግ ጥቁር ወተት» ካልሆነ በስተቀር።»

እውነቱም ሣቅ ብሎ «እኛስ የበቆሎው ዳቦ አርብናል።» ጓደኛውም መልሰ «እድሜ ለፐሬዘዳቱ ለጁሪ ሙሐመድ ምግብ ቤታችንን ጎብኝቶ ይህንን ችሮታ አድርጎልናል።»

እውነቱም በመቀጠል እንደእኔስ «ያንኑ የሃገራችንን የበቆሎ ዳቦ ብትመገቡ እመርጣለሁ።» ጓደኛውም በመቻከል፤« ቅንጩውስ ከየት የመጣ ነው የሃገራችን አይደለም?» ሲለው «ከአሜሪካን መንግሥት በእርዳታ የተሰጠ ነው» ብሎ ይመልስለታል።«ማስረጃ ቢያስፈልግህ ከምግብ ቤቱ መጋዘን ገብተህ የመጣበትን ከረጥት ላይ የተፃፈውን ብታነበው ከአሜሪካ መንግሥት በእርዳታ የተሰጠ ሊሸጥ ሊለወጥ አይችልም የሚለውን ጹሑፍ ታነባለህ።» ጓደኛውም ትክዘ ብሎ «ለመሆኑ ከሃገራችን ስንዴ እንዴት ልትለየው ቻልክ?» በማለት ሲጠይቅ፤ እርሱም የሚገብበትን ማንኪያ አስቀምጦ ወደኋላው ለጠጥ ብሎ ተቀምጦ «ይህንን ሣይ የመጀመሪያዩ አይደለም።እስታውሳለሁ በ፲፱፻፶፰ ዓመተ ምህረት ከወዳጅ አገር በእርዳታ የተሰጠ ተብሎ ማኛ ጤፍ ስንዴ እጂ ወዘተ ለሚያመርተው ገበሬ በነፃ ሲታደለው፤ ያም ሣይበቃ ቀርቶ፤ የመንዝን ገበሬ መሬትህ ተበልቷል ተብሎ ያንን የእርዳታ ስንዴና እልቤን ጠብመንጃ እሲዘውት ወርቃ ከሚባል ደናማ አካባቢ ከባሌ ክፍለሃገር አስፈሩት። በነገራችን ላይ ከዚያን አካባቢ ብተሄድ ሰዎቹም የሉም ደኑም ተመንጥሮ ምድረበዳ ሆኗል።» ጓደኛውም መልሰ «ሰዎቹን ምን ነካቸው?» «ወባ ጨረሳቸው።» «በዚያን ዘመን የሃገራችን ሕዝብ ተርቧልን?» ብሎ ሲጠይቅ፤ «ፈጽሞ አልተራበም። ባይገርምህ የመቶ ኪሎ ማኛ ጤፍ ዋጋ ቢበዛ አስራ አምስት ብር ብቻ ነበር። ይህ በአዲስ አበባችን የነበረው ዋጋ ነው ። ከክፍለሃገራት ግን መቶ ኪሎው እስከ አስር ብር ሲሸጥ፤ እጃውንና ገብሱን ለጋማ ከብት መኖነት የሚጠቀሙ ገበሬዎችም ነበሩ።ስንዴውንም ቢሆን ሕዝባችን ለእህል አረቄነት ይጠቀምበት እንደሆን እንጂ ለምግብነት ብዙም ተፈላጊነት አልነበረውም።»

እውነቱም ተክዝ ብሎ «በወቅቱ የእርዳታው ስንዴ እንዴት በነፃ ወደሃገራችን ሊገባ የቻለ ይመስልሃል?» ጓደኛውም የሚመገብበትን ማንኪያ አስቀምጦ ከተዝናና በኋላ «እንደሚመስለኝ የሰጪው ሃገር ገበሬዎች በሃገራቸው በተፈጠረው ትርፍርፍ ምርት ተስፋ እንዳይቆርጡና የመሥራት ፍላጎታቸው እንዳይመክን በዱጎማ መልክ መንግሥታቸው ገዝቷቸው ለእኛ ገበሬዎች ግን በችርታ መልክ የተሰጠ መሆኑ እሣምኖኛል።

እውነቱም በመዝናናት «የማነው ጥፋቱ?» «የአስተዳደሩ

መሆንን አልጠራጠርም።» «በጣም ልክ ነህ፤ «ጥሩ መሪ ለሕዝቡ ዓሣ ማስረግን ሲያስተምር መጥፎ መሪ ግን ሌላው በሣረገው ዓሣ ተማምኖ እንዲኖር ያደርጋል ይባላል።» ትክክለኛ የሆነና በማስረጃ የተደገፈ ትንታኔ አቅርበን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሕዝባችን የመሥራት ፍላጎት እየጫጫና፣ እየቀነጨረ፣ እየቀነሰ እንዲመጣ ተደርጎል በማለት የምንጠቅሰው ማስረጃ ባይኖረንም፤ ባጠቃላይ ግን ይህን መሰል ድርጊቶች ግለሰብንም ሆነ ሕዝብን በራስ መተማመንን እንደሚያሳጡት ከምናየው መገምገም እንችላለን። ቀደም ሲልም ተለምነን ውሰዱልኝ እንባል የነበረውን ስንዴ ይሄው ዘንድሮ የታናናሽ ቻችንና የአዛውንቶቻችንን እስከሬን እየሣየን መግቡን ከማለት ደረጃ ደርሰናል።»

«ጓደኛውም ትንሽ ካአሰበ በኋላ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በምማርበት ዘመን ከአንድ ሐብታም ድርጅት የተሰከለችሁ ነው እየተባልን በሰልፍ ሣሙናና ደብተር የዱቄት ወተት ሲታደለን፤ ቱኩሱን የሰማችንን ወተት ከነአረፋው ከመጠጣት ይልቅ በወቅቱ ስኳር የተጨመረበትን አሬራ ያስመረጠኝን ምክንያት አሁን ትዝ ሲለኝ አልገባኝም።»

እውነቱም በመሣቅ «ከሃገርህ የበቀሎ ዳበ የውጭ ሃገሩን ቀጮ ያስመረጠህን ምክንያት አውቀህዋልን?» ጓደኛውም በመቆናጠርና በመበሳጨት «እኔና አንተ ብቻ ነን? ለሃገር ተቆርቋሪ? ይህንን ለማድረግ ውሳኔ ለመስጠት መብት የነበራቸው እንዴትስ ሊታያቸው አልቻለም?»

እውነቱም ሣቅ በማለት ጓደኛውን በማጽናናት «የሚታያቸው የማይታያቸው ሊኖሩም ሳይኖሩም ሲችሉ፤ የሚታያቸው ክፍሎች ጥቅማቸው እስከ ተጠበቀ ድረስና የሚያዝናናቸው ከሆነ ግድ አይኖራቸውም በሕዝብ ስላልተመረጡ ከያዙት ሥልጣን ያወርዱኛል ብለው እስጉም፤ ያው እንደምታየው ከክቡ እስከሚገቡበት ያሻቸውን ያደርጋሉ ማለት ነው።እኔና አንተም ብንሆን በዚህን በትምህርት ቤት እስከአለን ድረሰ መጥፎ ሰሪውን እንከንናለን እንጅ በተግባር ስንሰለፍ በትክክል እንሠራለን የሚለውን ለመናገር ወቅቱን መጠበቅ አለብን። ቀደም እንደተናገርከው ደብተርና ወተት የሰጠህ ድርጅት ማርሲዲስ ወይም ቢኤም ደብሊዩ ቢሰጥህ አልፈልግም ትለለህ? አልፈልግም ለማለት ያለህን ቆራጥንት አላውቅም።» ጓደኛውም የሚመገብበትን ማንኪያና ሣህን ከፊቱ «በንዴት ከገፋ በኋላ ለሃገራችን ምን የሚበጃት ይመስልሃል?» በማለት ይጠይቃል። እውነቱም «አንተ የሕብረተሰቡ ቁጮ የሆንከው ክፍል ነገረኝ እንጂ እኔማ ግራ የገባው ግራ ሆኛለሁ።» ጓደኛውም «የእኛን ሁኔታማ የምታየው ነው፤የሃገራቱን



ምሁራን ከሚወጡበት ተቋም ውስጥ የእርዳታ ስንዴ እየቀረበልን ስለአጠቃላይ ሕዝቡ ምን የተሻለ ነገር እንዳለ ምን እንድነግርህ ትፈልጋለህ? ከአካባቤዬ ጀምሬ ያለውን ብገልጽልህ ማናችንም የሆነ መንገድ ፈልገን ከሃገር ለመውጣት የተዘጋጀን ነን። ምሁራንን የሰላም ጓዶች በሳቸው አንድ ዓመት ከዚህን ያየህው መምህር በሚቀጥለው ዓመት አታየውም። ሌላው ቀርቶ ያለውን መንግሥት ደጋፊዎች ብዙ ነገሮችን ከአጠፉም ሆነ ካለሙ በኋላ እንዴ ከሃገር ከወጡ አይመለሱም።በዚሁም ላይ የቅጦት ዕቃዎችን ይዘን ካልገባን በማለት ከውጭ የሚቀሩም አሉ።ከላይ የሚሰጠው ምክንያት ግን የፖለቲካው መጥፎነት ይሆናል። አንዳንዱም በሌላ አቅጣጫ ስትመለከተው በሰዎችም በአጠቃላይ መፍረዱ ያስቸግራል። የአስራ ሁለተኛን ክፍል ያለአጠናቀቀ የክፍለሃገር የፖለቲካ ኮሚሰር የወር ደመወዝ እስከ አንድ ሺ ብር ይደርሣል። በዚሁም ላይ ባለቤቱ አዲስ አበባ ተቀምጣ ከሐረር ወደ ጅቡቲ ጫት ከሚልከው ድርጅት አበል ሆና ከሁለት ሺ ብር በላይ አበል ትቀበላለች። የጸጥታ ሠራተኛ ሸንበል ለልጆቹ ልደት ሁለት ሦስት የሐረር ሠንጋ አስጥሎ ውስኪ በደበጃን ሲያቀርብ ስትመለከትና ከአዲስ አበባ ከተማ ትንሽ ወጣ ስትል ሕዝቡ የሚጠጣውና የሚበላው አጥቶ ሕፃን የእናቷን ጡት ታቅፋ ስትሞት በምተይበት አካባቢ እንዴትስ መኖር ያስመኛል?»

እውነቱም ተከዝ ብሎ «እኛም እስር ቤት ያለነው ተርበናል፤ አንድ ሰው ከሦስት የምግብ ጊዜ ወደአንድ ዝቅ ካለ እንደተራበ ነው።»

ጓደኛውም የራሱን አስተያየት ከሰጠ በኋላ ከእውነቱ አስተያየት ሲጠይቅ፤ እውነቱም መልሰ «ያለውን የአስተዳደር መጥፎነት የግለሰቦችን ሥርዓቱን በመጠቀም የራሣቸውን የስግብግብነት ባሕሪ ሲያጸባርቁ ሲታይ ብዙ ደከመው ሃገሪቱን ከዚህ ያደረሷት አባትና እናቶቻችንም ከሃገር ለመውጣት ሳይደዳቸው አልቀረም። በሕዝብ ገንዘብ ተቀጥሮ መልሶ መዝረፉ ምንጩን ማድረቅ ስለሆነ ችግሩ ጊዜውን ጠብቆ ሁሉም ይደርሰዋል። ሆኖም ግን ለሚደረገው ጠቅላላ ጥፋት ሃገር ትቶ መውጣቱ መፍትሔ ይሆናል ብዬ ለማመን ያስቸግረኛል። ከዚህ ሃገር ቤት የሚሠራው ጥፋት በውጭም አገር ብንሄድም ራሳችንን መጉዳቱ አይቀርም። ይህቺ ሃገር ይዘታችን ናት በይዘታችን ላይ ጠንክረን ሠርተን እንደማንኛውም ዓለም ሕብረትሰብ መኖር ካልቻልን በሰው ሃገር ሄደን በግል ጥረታችን ያሉትን ውድድሮች ብናሸንፍ እንኳን የተወለድንበት ሃገር ሁኔታ ይሰበናል። ሌላው ደግሞ የምሁራኑ ሃገር ትቶ መውጣት ሁኔታ ጠቅሰህዋል። ጥፍቱ ግለሰቦች ላይ ሳይሆን ከሥርዓተ

ትምህረቱ መዋቅር ላይ ነው። በሃገራችን የሚሰጥው ትምህርት በሌላ ሃገር ሥርዓተ ትምህርት ላይ የተሞረከዘ በመሆኑ፤ እንግዲህን ሥርዓተ ትምህርቱንና አስተዳደርን ገንጥለን የምናየው ነገር አይደለም። የእኛም ከቀድሞ ጀምሮ አስተዳደራችን ሌላ በትምህርት ቤት የምንማረው ሌላ ያም በመሆኑ በትምህርት ቤት የተማርነውን በተግባር ለምን አልተፈጸመም በማለት ይመስለኛል ብዙውንም ዘመን ከትምህርት ቤት አከባቢ በአስተዳደር ላይ ቅዋሚ ሰናነሣ የቶየነው።

አሁንም ምሁራን በሃገር ሕዝብ ገንዘብ ለውጭ ሃገር ድረጅቶች ሥራ የሰለጠኑ ስለሆነ መከነኑ አግባብ ነው ባይባልም እንደአንድ ሃገር ዜጋ ግዴታ ግን ሙሉ በሙሉ ልክ ነው ማለቱ ያስቸግራል።የሥርዓተ ትምህርቱንም ሆነ የአስተዳደሩን መዋቅር የሚስማማበትን ዘዴ በተቻለ መንገድ ለሕዝብ ማቅረብ እንጂ ትቶ መውጣቱን እንደመፍትሔ መቁጠሩ እብዘም ለተተኪው ትውልድ አያሰምንም። የዮኒቨርሲቲው ምሁር የከድሬውን ደመወዝ መመልከት አይኖርበትም።ማየት ያለበት በባዶ እግሩ እየሄደ ግብር ከፍሎ ያስተማረውን ሕዝብ መሆን ይኖርበታል። ያንን ሕዝብ የመርዳት ያህል ደስታ የትም አይገኝም።ምሁሩ ምሰሌ ሆኖ ወጣቱን በጥበብ ከልገራው ፈሩ ሁሌ የተበላሸ ሆኖ ይቀራል። እንደሕንዱ መሪ እንደጋንዲ በእጆቹ አጠንጥኖ የሠራውን ልብስ ለብሶ የሚያሣየን መሪ ከሽን እኛም እንደዚያ ለመሥራት መጣር ሊኖርብን ነው። በመሠረቱ ንዋይ ከአንድ ሃገር ባህልና ወግ ጋር ጎን ለጉን እንደመደራደሪያ ሐሣብ ሆኖ መቅረብ ያለበት ነገር አይደለም። ንዋይ ይመጣል ይሄዳል ግን የወገን ባህልና ወግ እንዴ መስመሩን ከሳተ ኑሮ መደናበር ይሆናል። ተራ ወታደሩ ፒጆት ይነዳል እኔ ግን በእግሬ እሄዳለሁ የሚለውን እንተወው ወቅታዊ ነው።»

ከምግብ ቤቱ ውይይታቸውን አብቅተው እውነቱ የመጣበትን መታወቂያውን ለመውሰድ ከጓደኛው መኝታ ቤት ተያይዘው በመሄድ ላይ ሳሉ፤ ጓደኛውም ለእውነቱ በተያዘበት ወቅት ያለፈባቸውን አካባቢ እያመለከተው ስለአለፈው አሰቃቂ ሁኔታ እያወሩ ከመኝታ ቤቱ ሕንፃ ሲደርሱ፤አካባቢው በጣም ቆሽሿል።እንደንድ በራቸው የተከፈቱ ከፍሎችን ሲመለከት ፍራሹ ከወለሉ ተዘርግቷዋል።የጫቱ ገራባ ክፍሉን ሞልቶታል፤ከረደሩ ይሸታል። እውነቱም ለምን ይህ ሊሆን እንደቻለ ጓደኛውን ይጠይቀዋል። ሣቅ ብሎ «ዮኒቨርሲታችን ሁለተኛው ታጠቅ ጦር ሠፈር ሆኗል። ለሁሉም ምድር ቤቱ እንኳን ለሰማሊያ ስደተኞች የተለቀቀ ስለሆነ ሌት ተቀን ጫት ይቅሙበታል። የሚያጸዳውም የለም። እንድን ነገር የምትከባከበው የደከምክበት ሲሆንና የራሴም የወገንም ብለህ ስታሰብ ነው።» ከጓደኛው ክፍል



ሲገባ ምንም ከምድር ቤቱ የተለየ አልነበረም።የጫቱ ገራባ ቁልል ክፍሉን ሞልቶታል፤የሲጃራው ሺታ ልብ ድከም ያሲዛል፤ለሚርቃና ጨብሲ የተገዛው የሺኖ ጠርሙስ ክፍሉን አጣቧታል። እውነቱም ሁኔታውን ተመልክቶ «ሕዝባችን በአጠቃላይ ተመርዟል ማለት ይቻላል።»

ጓደኛውም መልሰ «ዘንድሮ ጫትና መጠጥ የንዴት ማብረጃ ሆነው ተገኝተዋል፤እነርሱን ስትወስድ ሐሣብህ በሙሉ ክፍል ይልልሃል፤ግን በየዕለቱ በሚሠሩት ሥራ እያየ ሲበሳጭ ይኖራል? መፈከራችን እኛ ምን አገባን ሆኖአል። ዘንድሮ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ለግብር ይውጣ ሲሆን፤ እንተ ሺኖ በመጠጣታችን ትከንን ይሆናል። በየመሥሪያ ቤቱ መጠጥ እንደጽሕፈት መሣሪያ በጀት ተመድቦለታል። መሪዎቻችን ለእመኑበት ሕዝቡ ያለዳበ እንዲሥራ ይሸሉ፤ እነርሱ ግን ጮማ እየቆረጡ በውስኪና በሻንባይ ይራጫሉ።»

«በዚህን ዓይነት ሃገር ይገነባል ብለህ ታምናለህን?» ብሎ ሲጠይቀው፤ «ከምንም እንደማያደርስን እውቀዋለሁ እኛም ተማሪዎች የምናደርገው ትክክል ነው ማለቴ አይደለም። ግን ተጽኖ የማይደረግብህ ተመሰስለህ ስትገኝ ብቻ ነው። እኛም ትክክል አለመሆኑን እምነን እናደርገዋለን። ዛሬ እንኳን ይህንን ያህል ስለሃገር ጉዳይ እንስቼ የተወያየሁት እንተን ስለአገኘሁ እንጂ ማንን ታምናለህ? ዮኒቨርሲታችን የከድሬ መናህሪያ ሆኖል። ፈተናውን አልፈው ባይገቡም ሽጉጣቸውንና ከርዳቸውን በማሣየት ገብተዋል። እንግዲህ አንዳንድ ደከማች እንተ የተናገርከውን ይዘው ቀርበው አበሳቸውን ያሣድጋሉ።በአሁኑ ጊዜ የሳይንስ ምርምር ቀርቷል። ሰዎችን ማሲያዝና ማሳሰር እንደልማት ተቆጥሯል።ማን ባጠመዴት ወጥመድ ውስጥ ይገባላቸዋል? እኛ ምን አገባን እያልን እንኖራለን።»

«እናንተ የተማራችሁትና ያወቃችሁት ክፍሎች ትክክል ያልሆነውን አይደለም ማለት ካልቻላችሁ ማን እንዲለው ትፈልጋለህ?»

«ማንው የተማረ ሁሉ ትክክል ያልሆነውን ነገር አይደለም ብሎ ይቃወማል ያለው? ጊዜ መስተዋት ነው ሁሉንም አይተናል። ለዚህ ሁሉ ጥፋት የተማረው መሆኑን አሁንም የተገለጸልህ አይመስለኝም። አንተ አሁንም ትኩስ ነህ።»

እውነቱም እኔስ የታየኝን ከማድረግና ከመናገር ወደኋላ አልለም።ጥሩ የሚሠራውን ማመስገንና ማድነቅ የሚያበላሸውን መንቀፍ ግዴታችን ሳይሆን አይቀርም።» ጓደኛውም መልሰ «እተሞኝ ሰሚ ካለው ያለፈው ይበቃል።»

ለሁሉም የሚበጀውን ያምጣ ተባብለው የመጣበትን መታወቂያውንና ሸንጣውን ወስዶ ጓደኛውም በኪሱ ያለውን ገንዘብ ሰጥቶት ምንም ሳይጠይቀው እርሱም ሳይነግረው ደህና ሁን ተባብለው ከስድስት ኪሎ ዮኒቨርሲቲ ደጃፍ ላይ ተለያዩ።



## ዳግም ወደገጠር

እውነቱም ከጓደኞቹ ጋር በተገባቡት ቃል ኪዳን መሠረት ለየወላጆቻቸው በየአድራሻቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን የሚገልጽ ደብደቤ ሰዶላቸው እርሱም አዲስ አበባን ለቆ ለመውጣት ትኬቱን ለመግዛት ከአውቶቡስ ጣቢያ ሄደ፤ ትኬቱን ገዝቶ አውቶቡሱ አዲስን ለቆ እስከሚወጣበት ድረስ ሁሌ ከጓደኞቹ ጋር ቁርስ ከሚያደርግበት ሻይ ቤት ገብቶ ዳቦ በሻይ አዞ ለመመገብ ቢሞክር ፈጽም ከጉሮሮው ሊወርድለት ስላልቻለ መመገቡን ትቶ፤ አገጩን በእጁ ደግፎ ስለአለፉት ጓደኞቹ ሲያስብ ገጽታቸው ወደአእምሮው ሲመጣ ዐይኖቹ እንባን ሲያቀሩ ተመጋቢው ሕዝብ አየኝ አላየኝ በማለት ሂሣቡን ከፍሎ ጉዞውን ለመጀመር ወደ አውቶቡስ ጣቢያው ይሄዳል።

እርሱም የገዛውን የሐዘን ከፍያውን በአናቱ ደፍቶ በሁለት መንገደኞች መከከል ተቀምጦ ጉዞውን ሲያደርግ አውቶቡሱ የአዲስ አበባን ከተማ አቋርጦ ሲጓዝ እርሱና ጓደኞቹ በአለፉት ጊዜያት ይመላለሱባቸው የነበሩት መንገዶች እየተመለከተ የመንገዶቹንም በታንክ መታረስ እያሣዘነው ሲያስብ ሲያሰላስል፤ ሣያስበው ከቃሊቲ ብስኩት ፋብሪካ አካባቢ ቆመው ይቆጣጠሩ የነበሩት ዘበኖች አውቶቡሱን ሲያስቆሙ በጉዞ ላይ መሆኑን ያስታውሳል።ቃሊቲ ወደ ደቡብ ክፍለሃገራት ለሚወጡም ሆነ ከደቡብ ክፍለሃገራት ወደአዲስ አበባ ለሚገቡ ተሸከርካሪዎች መፈተሻ ኬላ ስለነበረች ሁሉም ተጓዥ አውቶቡሱን ለቆ እንዲወጣ ተነገርት፤ የታጠቁ ግለሰቦች ከአውቶቡሱ ውስጥ በመግባት ከተመለከቱ በኋላ ተሳፋሪው መታወቂያውን እያሣየ እንዲገባ ተቀዶ ጉዞ ሆነ። ይህ የመጀመሪያው ፍተሻ ሲሆን አውቶቡሱ አቋርጦ በሚጓዛቸው ከተማዎች በሙሉ ተማሳሰይ ድርጊት ሲፈጸም ፤ በተለይ ከከፍለሃገር ወደአዲስ አበባ ከተማ ለሚገቡ ተሸከርካሪዎች ቁጥጥሩ በጣም የከፍ ሲሆን ለቀው ለሚወጡ እንብዛም የጠበቀ አልነበረም።

ያም ሆነ ይህ ከአንድ ቀን ተኩል ጉዞ በኋላ ከገጠር ከሚኖሩ አጉቱ ቤት ሲደርስ፤ጆንበር ጠልቃለች ጎረቤት ላሞቹን አልቦ አጥሮቹን ዘግቷል። በአካበቢው የሚያልፈውን ሰው ለመለየት ያስቸግራል።እርሱም ጭለማን ተገን አድርጎ ማንም ሳያየው የአጎቱን ከተበሪ ከፍቶ ሲገባ፤ አጎት ተፈራ በብረኩበ ላይ ተቀምጠው የምሽት ፀሎታቸውን ሲደርሱ ሳለማቋረጥ በእጃቸው ወደቤት ዘልቆ እንዲገባ አመለከተውት እርሱም እንደምን ከረማችሁ በማለት ዘልቆ ከቤት ሲገባ ወይዘሮ ልከየለሽ የአጎት ተፈራ ባለቤት እሱነው አይደለም በማለት

የናፍቆታቸውን እቅፈው ስመውት፤ ዓይናቸውን ባለማመን የሚበራውን ፊኖስ ከፍ አድርገው እተኩረው ተመልከተው፤ የሰውነቱ መጎሣቆል የመልኩን መለወጥ ኢጢነው፤ «ወይ! ልጄ» በማለት እንበቸውን ሲያፈሱ፤ እ ኅትዩውም ፀሎታቸውን አድርሰው በተራቸው ደህንነቱ እየጠየቁ፤ቀደም ሲል አዲስ አበበ ሄደው ከጠየቁት ዘመደቻቸው እንደተረዱት ግድያ ወይም የዘመን እስራት እንደሚኖር የጠቆሙ ሲሆን በዚህን አጭር ጊዜ ውስጥ መጥቶ ሲያዩት ታምር ሆኖባቸው፤ ዕለቱም የከቲት ፲ ፪ ስለነበር «በዕለተ ቀኑ የማምንበት ቅዱስ ሚካኤል ታምር አሣየን» በማለት የሚካኤልን ታምር ሰሪነት ሲያወድሱ ፤ ወይዘሮ ልኬየለሽም ስለታቸው በመድረሱ የቤተሰብ ደስታ ሲሆን፤ ያለፈው ሁሉ ተረሰ። የመጣበት ሃገር እሩቅ መሆኑ ተጠቁሞ እራት በእስቸኳይ እንዲቀርብ ተጠይቆ፤ ያ ወፍራም ከገብስና ከጤፍ የተጋገረ እንጀራ የከክ ወጥ፣ ጎመንና አይብ ተደር ጉበት ቀረበ። «ለቅዱስ ሚካኤል ዝክርት ከደፋሁት ፃዲቅ ፤በእስራ ከጠመኩት ጸበል የደረስክበት» በማለት በአበሬ አቅረው በብርጭቆ እየቀዱ ለእርሱና ለአቶ ተፈራ ጠሳውን ሲያሲዟቸው፤ አቶ ተፈራም ምግባቸውን እየተመገቡ የኑሮአቸውን ማዘቅዘቅ ለእውነቱ ያጫውቱታል። «ለወትሮው ልክየለሽ እራት አምስት ጋን ጠሳ ጠምቃ በሰፊው ደግሣ ትዘክረው የነበረው ሚካኤልን ዛሬ በእስራ ጠሳ ትዘክረው ተገደደች።» ወይዘሮ ልክየለሽም መልሰው «እግዚአብሔር ከሃገራችን ቁጣውን አንስቶ ሰላምና ፍቅርን እንዲሰፍን ከደረገ በሰፊው የማንደግስበት ምንም ምክንያት የለም። እምነታችን እንጂ መብዛትና ማነሱም አይደለም። ይህችኑ ባደረግናት ዝክርት ሰምቶን የሸነውን አድርጎልናል። ለሁሉም ቅን ሐሣብ በልብ ካለ የማይሆን ነገር የለም።»

ማዕድ ከተነሣ በኋላ «እግርህን ለማጠብ ስለት ገብቻለሁ» በማለት በጣሳ ውኃና መታጠቢያ ገበቴአቸውን ይዘው ሲቀርቡ፤እውነቱ ከጠበቀው በላይ ሆኖበት አልታጠብም በማለት ከመቀመጫው ሲነሣ፤ አቶ ተፈራም በቁጣ መቼም «የዛሬ ልጆች ፍሬሐ እግዚአብሔር የላችሁም፤ እግሮችህን ማጠብ አትችልም በማለት አይደለም፤ግን ስለቷ ስለደረሰላት ቃል ኪዳኗን መጠበቋ ነው።» ከዚያንም እግሮቹ ታጥበውለት በቅቤ ታሽተውለት ከመደብ አጎዘው ተነጥፎለት የክት ጋቢያቸውን ከስንዱቅ አውጥተው አልብሰውት ስለአመጣጡ ሣያነጋግሩት ተኛ።

የእውነቱ ለቤተሰቡ ከሞት አምልጦ መምጣቱ ቢያስደስታቸውም የአመጣጡን ሁኔታ ገና ባለማወቃቸው ባልና ሚስት ነገሩን በውል ከሱ እስከሚሰሙት ድረስ ወይዘሮ ልክየለሽም የጠዋት ቡናቸውን ዘግየት እንዲያደርጉ አቶ ተፈራም ከቡና ማሳቸው ውስጥ



ይዘውት ሄደው የአመጣጡን ሁኔታ እንዲያጣሩ ተስማምተው ተኙ።

ለቀድሞ የጎረቤት ቀስቃሽ የነበረው የወይዘሮ ልክየለሽ የቡና ወቀጣ ባለመሰማቱ በጤና አይደሉም በማለት ጐረቤት በሣት መጫር ስም እያመሃኙ ከቤታቸው ይመጡ ጀመር። ያንን የተመለከተ አንድ የጐረቤት ኗሪ «ቀደም ሲል ዋናው ሠራተኛ አቶ ተፈራ ብቻ መስለውኝ ባለ በዚህን ቀን ግን ዋናው ቅንብርብር ከማጀት መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ» በማለት የወይዘሮ ልክየለሽን ሠራተኛነት ያደንቃል።።

አቶ ተፈራም ከቡናው ጎጆአቸው ውስጥ ይዘውት ከሄዱ በኋላ የአመጣጡን ሁኔታ እንዲነግራቸው ሲጠይቁት፤ ሳይለቀቅ አምልጦ መምጣቱን ሲነግራቸው፤በአካባቢው ይደረጉ ከነበሩተ ኢሰባዊ ተግባሮች አንፃር በነበረው መንግሥት ላይ ትልቅ ጥላቻን ስለነበራቸው አምልጦ በመምጣቱ አድንቀውት ቀድምውንም ወደከተማ ከመሄድ ወደሳቸው ዘንድ ቢመጣ ኖሮ ከዚያን ሁሉ አደጋ ውስጥ እንደማይደርስ ተናግረው የወደፊት ዕቅዳቸውን ይገልጹለታል። የአካባቢው ሕዝብ የሚወደውንና የሚጠላውን ነገሮች አስቀድሞ እንዲያውቀው በማለት ስለሕዝቡ ማብራሪያ ያቀርቡለታል። የሃገር ቤቱ ሕዝብ ኑሮን ለማሸነፍ ሸቅብ ቁልቁል የሚሯሯጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ «ቀደም ሲልም በከተማ ይደረግ የነበረውን እስራትና ግድያ አስደንግጦት ከዱር መሸጎ የኖረ ሕዝብ ሲሆን፤እንደምታውቀው ሕዝብ የሚኖርበትን አካባቢ ትቶ ሲሰደድ ንብረቱ በማነህ ማነህ ባከኖ ስለሚያልቅ በመጨረሻም በችግርና በረሃብ ላይ መውደቁ፤ የማይቀር ነው። ከከተማ ግንኙነት ተቋርጦ፤ መንግሥትም የሠርጎ ገቦች ተባባሪ ናችሁ በማለት ተኩስ ሲከፍትባቸው፤ ንብረታቸውን እሣት ሲለቅበት የደረሰ ሰብላቸውን ለአውሬ እየለቀቁ፤ ወደ ዱር ተሰደው የኖሩ ሕዝቦች ናቸው። በተሰደዱበትም ተደላድለው፤ የልማት ሥራቸውን እንዳይሠሩ ከዛሬ ነገ መጥተው ያጠፉናል በማለት ሲባዝኑ፤ከሰማሊያም ታጥቀው የመጡትም ቢሆኑ ቀደም የተነሱበትን ዓላማ ዘንግተውት መሣሪያ ያስታጠቃቸውን መንግሥት ጥቅም በማስጠበቃቸው፤እነርሱንም ቢሆን እምኖ ለመቀበል ሕዝቡ አልፈለገም። አልፈው ተርፈው ቀለባቸውን ከማምረት እንደመደበኛ ወታደር መሣሪያ ተሸክመው ሸቅበ ቁልቁል ማለታቸውን ስለአበዙና እጆቻቸውን አለሰልሰው ቀለብ ከሕዝቡ ስለሚጠይቁ እነርሱም ሌላው ሸክም በመሆናቸው፤ ከዚህም የተነሣ በመጨረሻ ሕዝቡ ራሱ በረሃብ ላይ ስለወደቀ፤እሮጊት ሽማግሌ ሕፃናት በምግብ እጦት እንደቅጠል ሲረግፉ፤ አማራጭ ሲጠፋ በኑርንበት አካባቢ በጥይትም ይሁን በረሃብ ሕይወታችን ትለፍ በማለት ወስነው የሚኖሩ ሕዝቦች ስለሆኑ ተንከል

ለማስብም ሆነ አንዱን ወገን አሣልፈው በመስጠት ተደስተው የሚኖሩ አይደሉም። ሁለቸውም ከጠዋት እስከ ማታ ከማሳቸው ውስጥ በሥራ ተጠምደው የሚውሉ ሲሆን በእርግጥ ከሌላ አካባቢ አምጥተው ከሰፈሯቸው ውስጥ የመለመሏቸው አብዮት ጠባቂዎች የሚሏቸው ብቻ ብረት ተሸክመው ያለሥራ የሚታደለቸውን የልመና ስንዴ ዱቄትና የታሸገ ቅቤ ለቀለብ እየተቀበሉ ሕዝቡን የሚያስጨንቁት ከልሆኑ በስተቀር ሌላው ሕዝብ ደህና ነው።

በአጠቃለይ ሕዝቡ በሁለት እሣት መከከል የነበረ ነው ለማለት የአቀረብሁት ሐሣብ ነው። ለሁሉም ተከለኞቹ ለይተው አውቀው ለበለዬቻቸው እንዳይጠቁሙህ የልብሶችህን አለባበስ ለውጠህ ይህን መሬት የሚጠርገውን ሱሬህን አሣጥረህ በማንኛውም መንገድ ከሕዝብ ተመሳስለህ ከእኔ ጋር የግብርና ሥራችንን እንጀምራለን። እናንተ ተማሪዎች የቱን ያህል ሠራተኞች እንደሆናችሁ በተግባር እንፈታተናለን። ሜዳውም ይሄው ፈረሱም ይሄው። የገበሬ ማሕበር ሊቀመንበሩም ቢሆን አብረን ከፉውን ደጉን ያየን ስለሆነ ስለአንተ ሁኔታ ማንኛውንም ጉዳይ አሜውተዋለሁ። ልኬየለሽም የምትሰጠውን አስተያየት ተቀብያት የሚበጀውን እናደርጋለን። እኔ ተፈራ ከንዴን ሳልተራስ ምንም ነገር አይደርስብህም።ለደርግም ቢሆን በእጄ የኖረውን መውዜሬን አላስረከብኩም።» ስለአካባቢው እየነገሩት ሳሉ ወይዘሮ ልክየለሽ በአገልግል እንጀራቸውን በጀበና ቡናቸውን ለጣት ወኃቸውን ይዘው ትፍረድንና አንዳርጋቸውን አስከትለው ወደጎጆዋ ይመጣሉ።

አቶ ተፈራም የባለቤታቸው ድካም ተሰምቶአቸው «እነርሱም ወደቀዬ ለመምጣት በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ገልጸውላቸው፤» ቀርሣቸውን እየተመገቡ ስለእውነቱ አመጣጥ ያጫውቷቸዋል። እሳቸውም ንግግሩን በጥሞና ከዳመጡ በኋላ፣የታያቸውን ሐሣብ ያቀርባሉ።ወይዘሮ ልኬለሽም ቢሆኑ እንደባለቤታቸው የፈሩት በዚያን ተመድበው ያሉትን የአብዮት ጠባቂዎቹ ከልሆኑ በስተቀር በሕዝቡ ላይ ትልቅ እምነት አላቸው።

የአቶ ተፈራ የወንድም ልጅ ከሸዋ መጣ በማለት በአካባቢው በሰፊው ተወራ። የደስታቸው ተካፋይ ለመሆን የአካባቢው ሕዝብ ያለውን እየያዘ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ከቤታቸው የአካባቢው ሕዝብ ይጎርፋል። ብዙው የአካባቢው ሕዝብ አርሞ ስለሆነ የባህል ምግባቸውን ቡራቶ፣ ሚጭሮ፣ ገንፎ ሃጺ ወዘተ እየያዙ በመምጣት ደስታቸውን ሲገልጹ፤ የወይዘሮ ልክየለሽ የቡና ጀበና ከጠዋት እስከ ማታ ከጉልቻው ተጠልጥሎ ሲውል፣ አቶ ተፈራም የከት ጋቢአቸውን



አጣፍተው ከቶዳ ወጥረው ከሰሩት ወንበር ተቀምጠው እንግዶችን እየስተናገዱ፤ በዚያ አጋጣሚ እውነቱም ከእነርሱ እንደሚቶይ ያጫውቷቸዋል።እውነቱም የሃገር ቤቱ ግኑኝነትና ፍቅር እንዳለ ሳይለወጥ መኖሩን በማድነቅ የተሰማውን ደስታ ሲገልጽ፤ እሳቸውም የሃገር ቤቱ ኑሮ ምንም ያልተበረዘና ሕዝቡም ከበህሉና ከወጉ ጋር መሆኑን ጠቅሰው፤ እንደአንዳንድ አሳዋቂ ለጊዜዊ ጥቅምና ሥልጣን ተሸነፎ፤የቶየ ባህሉንና ወጉን ለውጦ፤ አብሮ ኗሪውን፣ ሲታመም ጠያቂውን፣ ሲቸገር ደጓሚውን፣ ሲሞት ቀባሪውንና፣ ልጆቹና ልጆቻቸው፣ ነግ ጋብቻን መስርተው፣ ሕብረተሰብን ለመገንባት፣ ሃገርን ለማበልጸግ፣ በተዘጋጀ የወገን ሕዝብ ውስጥ ምንም እስነዋሪና ለቀሪው ለተተኪው ትውልድ፣ አሳፋሪ የሆኑ ተግባራትን ለመፈጸም፤ ፍጹም የተቶጠቡ ሕዝቦች በመሆናቸው፣ ፍቅራቸው ያው እንደጥንቱ ነው። እኛም በውስጡ ስለአለንበት ይህ የፍቅር ፀጋ ጎልቶ አይታየንም። ሆኖም እንደአንተ ወጥረቱንና የሰዎችን መከዳዳት ለአየ ኑሮው ጥሩ አካባቢው የተባረከ መሆኑን አድንቶ ሊናገር ይችላል።

## ፴፱

እንዱ ማምንት የአከባቢውን ሕዝብ በማስተናገድ በማለፉ፤የባከነውን የሥራ ጊዜ ለማጣጣት አቶ ተፈራና እውነቱ በማለዳ ተነስተው በትልልቅ ቅሳቸው የወተት ቡናቸውን ከገብስ ቆሎቸው ጋር ተመግበው ወደእረም ሥራቸው ተሠማርተው፤እውነቱም የአቶ ተፈራን ያክል ጠንክራ ሠራተኛ ባይሆንም ራሱን ከአጎቱ ለስማስነሰና ከሚሰነዙሩበት የቃለት ውረፋ ለማምለጥ በተቻለው ሁሉ ሲፍጨረጨር፤ እንዳንዴም ከድከም የተነሣ እግሮቹ ሲተሳሰሩ ምክንያቱ በእስር ቤት መቆየቱ እንጂ ብዙ ሠርቶ እንዳልሆነ ራሱን እያጽናና፤ አጉቱም በተማሪነቱ እየወረፉት ለወደፊት ጥሩ ገበሬ እንደሚሆን ሞራሉን እየገነቡለት እባቸውም በሥራቸው ላይ የሚወዳደራቸውና የሚያናግራቸው በማግኘታቸው ተደስተዋል።

ለሚሰሩት ሥራ ፕሮግራም እሳቸው ከሰዓት በፊት በበቆሎ ማሳቸው ውስጥ ሲሠሩ ቆይተው ምሳቸውን ተመግበው ቡናቸውን ጠጥተው ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ከቡናው ማሣቸው በመሄድ የቡና ኩትኳቶ ሰያደርጉ፤ ወይዘሮ ልኬየለሽም ቢሆኑ በበኩላቸው ምግብ ማብሰል ብቻ ሳይሆን የጓሮ አትክዕልቶችን ስለሚያለሙ፤ በጓሮአቸው የተከሉት ጉመን፤ ድንች፤ሽንኩርት ወዘተ ከቀለባቸው አልፎ የጪውወጪያቸውን እንደሸፈነላቸው፤ ዘውትር ተሰብስበው ስለእርሻ ሥራ ጡሩነት ሲያወሱ፤ ሳይጠቅሱት ቀርተው አያውቁም። አቶ ተፈራም ከእሳቸው ኩዳድ ማሣ ይልቅ «በተቀዳሚ የልከየለሽን ያህል የጓሮ አትክልት በደማ ማልማቱ ይመረጣል» ይላሉ። «አንድ መሬት አንድን ዘር መቀበል አለመቀበሉን በትንሹ ተሞክሮ ሳይታይ በጭፍን በሰፊው መሬት ላይ ቢዘራ በመጨረሻም መና ሆኖ ይቀራል፤ ኪሳራም ያስከትላል። አንድ የእናንተ ተማሪ እንደነገረኝ በዚች ትንሽ የጓሮ ማሣ ላይ የዘሩት የተለያየ ዘር እንደመግቢያ ሆኖት ትልቁን ኩዳድ መሬት አልምተው በሥራ ውጤትን አስገኝቶ ደስተኛ ገበሬ ለመሆን ይቻላል በማለት ምክሩን ለግሰኛል። የሱ ልጅ ቤተሰቦች በሙሉ ገበሬዎች እንደነበሩ ሰው አጫውቶኛል። እርሱም የእርሻ ትምህርት ቤት ገብቶ እንደተማረ ነገሮኛል። እኛ በተግባር የተሰለፍነው ይበልጥ እንደምናውቅ ያምናል ሆኖም አንዳንድ መሻሻል የሚኖርባቸውን ነገሮችም ሳይጠቁመኝ አልቀረም።» ቆይ በማለት ሰሙን ለማስታወስ ቢሞኩሩ ሳይታወሳቸው ቀርቶ፤ እንደአጋጣሚ ወራትን እንደሚያበቅሉት የእህል አዝዕርት ከፋፍሎ በሰጣቸው ቀን መቁጠሪያ ላይ ስሙን ከትበውት ኖሮ ከአስቀመጡበት ሥፍራ ወይዘሮ ልክየለሽ አውጥተው ሰጥተዋቸው፤ ስሙንም ለእውነቱ ሲያስነብቡት፤ የሚያውቀውን የታደሰ ስም በመሆኑ፤ ስለታደሰ አቶ ተፈራ



የሚናገሩትን እያደመጠ በቀን መቁጠሪያው ላይ በአከባቢው በዓመት ሦስቴ ሊመረትበት እንደሚቻል የገልጸውንና፤ በምን ወር ምን መዘራት እንደሚኖርበት ዝናብ በየትኛው ወር መጣል እንደሚጀምር የሚያሳይ መግለጫዎቹን በቀን መቁጠሪያው ላይ ማመልከቱን ያነባል። አቶ ተፈራም በመቀጠል «ይህ ነገር ትንሽና ቀላል ይመስላል ግን እርሱ በሰጠኝ መመሪያ ተጠቅሜ ብዙ አግኝቼበታለሁ።» ታታሪነቱን እየደጋገሙ ለእውነቱ ይነግሩታል። ወይዘሮ ልክየለሽም ቀጥለው «ያመጣላቸው የጉራጌ ጉመን ዘር እስከ ዛሬ ዘሩ አለ፤ የተተከለውም በየዓመቱ እያቆጠቆጠ እየቆረጥሁት በመሸጥ የጪዊን ወጪ ችሎልኛል።» አቶ ተፈራም በድጋሚ «እርሱ ልጅ እንደእናንተ እንደዘመኑ ተማሪዎች አይደለም። ለሥራ ከእኛ ዘንድ ሲመጣ እርፉን ተቀብሎን ሲያርስ እኔነኝ የሚል ገበሬ አይስተካከለውም፤ የአጭዳውንማ ነገር ተወው! በአንድ ጉዛ ላይ ተገኝቶ ጅገኛውን በአጨዳው ሲመራው ሕዝቡ ከተማረ የማይጠብቀው ስለሆነ ታምር ይሆንበታል ። ከዚያንማ በኋላ ስለግብርናው ሥር እርሱ ያለውን ለመቀበል ገበሬው ምንም አይጠራጠርም። ከዚያን በፊት ግን አንዳንድ ተማሪዎች መመሪያ ሊሰጡ ሲመጡ አስቀድመን የምንመለከተው እጃቸውን ነበር። የሚናገሩት ቃል እውነትነት ቢኖረውም እንኳን እምነነን ለመቀበል ያስቸግረናል። እኛ እጆቻችን መጅ እስከሚያወጡ ለፍተን ያልደረስንበትን ዘዴ ይህንን እሸት ቆርጦ የማያውቅ እጆቻቸውን ይዘው መጥተው እንዴትስ ሊያስተምሩን ይችላሉ በማለት እናሾፍባቸው ነበር።»

በእርግጥ እንደተናገሩት ታደሰ ገበሬውን ለማገልገል ታጥቆ የተነሣ ባለሞያ ሆኖም ሰለ ግን የከፍለሃገሩ የአስተዳደር ክፍልና የሕዝብ ድርጅት አባሎች የድርጅታችን አባል ካልሆንክ በማለት ስለአስቸገሩት ሥራውን ለቆ ወደአዲስ አበባ ይሄዳል። በተጨማሪም በመሬት አዋጁና በሕብረት ሥራ ስም ሕዝቡን በሃያ ጋሻ መሬት ክልል ውስጥ ይደረግ የነበረውን መሰባሰብም አጥብቆ ሲወግዘው ለዘያም ያቀረበው ምክንያት «እያንዳንዱ ገበሬ የያዘውን ይዞታ አልምቶ ውጤት ካላሣየ በምንስ መንገድ ታታሪውን ሠራተኛ ከልግምኛውና ደተኛው ገበሬ ለይቶ ለማወቅ ይቻላል? የሚያርስበት በሬ እንኳን ከሌለው ሁኔታው ተጠንቶ በብድር ስም ተገዝቶለት እንዲሰራ ተደርጎ፤ ሁኔታው ተሟልቶ መሥራት ካልቻለ ለሚሠራ መሰጠቱ እንደማይቀር ይነገረዋል።ከዚህም ሌላ የሚበጀውን የሠራተኛውን ገበሬ ሙሉ ተሣትፎና አስተያየት ይጠየቃል። ያለበለዚያ ግን የለምንም ጥናትና ሙከራ ሥራውን በተግባር ተሰልፈው ባለዩ ግለሰቦች በጠረጴዛ ዙሪያ የተነደፈውን መመሪያ ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋሉ ይከብዳል። የገበሬውንም የሥራ ፍላጐት ይገታል፤ያቀነጭራል።»

በማለት የሕብረት እርሻ ሥራው ሊያመጣ የሚችለውን ቀውስ ጠቀሜ መፍትሔውንም በማቅረቡ እንደሕዝብ ጠላት ተቆጠረ።

አቶ ተፈራም ንግግሩን አቋርጠው «የእነርሱን የሕብረት እርሻ ሥራ እየንሳቸው፤ ከእኛ የወሰዷቸውን አራሽ በሮች ከገበያ አውጥተው እየሸጡ ወይም አርደው እያቀራጩ ያልተገሩ ወይፈኖችን ያለገሪ አበት በሬ እየጠመዱ ለሕብረቱ እርሻ በመውጣት በሃያ ጋሻ መሬት ላይ የተመረተውን ምርት በጣሣ እየሰፈሩ ሲከፈሉ አይተናል። ሁኔታው «አድበስብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ዓይነት ነው። ለሕዝባችን መራብ አንደኛው ምክንያት መሆኑን አልጠራጠርም። እኛም በወቅቱ ይህ ነገር አይሆንም «የኑቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ሰንበሌጥ» አይነት ነውና አድምጡን ልምዳችንን እናካፍላችሁ ብንል ያን ጊዜው ያመጣውን ስድባቸውን አቅርቧዥ አወናበጅ በማለት ውርጅብኝ ሲያወርዱብን አፋችንን ያዝን፤ ጨርሶም ከሕብረት ሥራው እንዳንገባ ገደብ ተደረገብን ፤ እንደሁለተኛ ዜጋ ተቆጠርን። የሚያስደንቀው ለሥራ አስኪያጅነት የተመረጡት በገበሬው ውስጥ በስንፍናቸውና በልግመታቸው የታወቁት ግለሰቦች ስለሆኑ ገበሬውም በጂጊውና በደበው አብሮ ስለሚሰተፍ ማን ሰነፍ ማን ጎበዝ መሆኑን ስለሚተዋወቅ ታታሪዎቹ በመሪነት የተመረጡትን ሲመለከቱ ውጤቱ እንደማያምር በመገመት ራሳቸውን ገልል አደረጉ። ያም ሆነና ውጤቱ ሳያምር ቀረ።»

ታደሰ ስለሰፋፊ እርሻዎችም ያለውን አስተያየት በጊዜው ሲጠቁም፤ «ሰፋፊው እርሻ ከመውረሱ ይልቅ በሚያለሙት ግለሰቦች እጅ መቆየት ነበረበት። ምክንያቱም ለባለሰፋፊ እርሻዎች ተቀጥረው የሚሰሩት ሠራተኞች የራሣቸው መሬት ተሰጥቶአቸው ማልማት ሲጀምሩ ባለሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች የሠራተኛ እጥረት ስለሚፈጥርባቸው፤ ያም የከተማውን ሥራ አጥ ለመቀጠር ይገደዳሉ። መንግሥትም የትንንሽ እርሻ ባለቤቶችን በባለሞያና በግብር ቅነሣ ራሳቸውን እንዲያቋቁሙ ድጎማዎችን ሲያደርግ፤ የባለሰፋፊ እርሻ ባለቤቶችን ግን ለሚደረጉላቸው አገልግሎቶ በሙሉ እንዲከፍሉ በማድረግ፤የልማቱን ሚዛን መጠበቅ ያስችላል።»ብሎ ቢጠቅስ፤ ሊቀበሉት አልቻሉም።እንደውም ገበሬው የበሰለውን ኩዳድ መሬት እንዳይከፋፈል መንገዱን ዘግቶብችኋል በማለት ከገበሬው አጣልተውት ገበሬውም ቢሆን የዕለቱን ብቻ በመመልከት የበሰለውን መሬት ለማግኘት በመጓጓት ይወደውና ይከተለው የነበረው ገበሬ በሙሉ እንደጠላት ስለቆጠረው ሥራውን ለቀቀ።

አቶ ተፈራም በመቀጠል «ችግሩ የተቃወመን ሁሉ እጥፈ



የደገፈን በሙሉ አልሚ አድርጎ የመቀበሉ ጉዳይ ነው። በሕብረተሰባችን ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ነገር ቢኖር ትክክል ያለመሆኑ እየታወቀ መሪ ለማስደሰትና ላለማስቆጣት ወይም ካሉበት ሥልጣን ዝቅ ላለማለት ብቻ ልክ ኖዎት ባዮች መብዛታቸው ነው። ልማቱ ቶሞ ሕዝብ በሚሊዮን የሚቆጠር ተርቧል እየተባለ የልማቱን እድገት ሰማይ አድርሰው ያቀርቡታል።»

እውነቱም የአቶ ተፈራን ሐሣብ በመደገፍ «አንድ የታደሰ ምክትል ሆኖ ይሰራ የነበረን ግለሰብ አግኝቼው እንዴትስ እስከዛሬ በሥራ ሊቆይ እንደቻለ ስጠይቀው ከት ብሎ ስቆ የሞኝነቱ ጊዜ አልፏል። እነታደሰ እንደው በሞኝነት እነርሱም ራሳቸውን ጎድተው ቤተሰባቸውንም በችግር ላይ ጣሉት። ባለሥልጣን ነኝ ብሎ ሲመጣ ከእርሱ ጋር ምን ያከራክራል ክርክርና ማስረጃ ሞያውን በሚገባ ከሚያውቁና ከሚረዱ ጋር ነው። የደርግ አባል ሆነ ሊቀመንበር ስለእርሻ የሚያውቁት ጉዳይ የለም። ስለዚህ ነብስን ለማዳን ሠጠረኸ ሠርቶ ከአብዮቱ በፊት የለሙ አካባቢዎችን ዝቅ በማድረግ ከአብዮቱ በኋላ የለሙ አካባቢዎችን ከፍ አድርገህ ስታቀርብ እናመሰግናለን ጓድ አከሌ ተብለህ ምስጋናህን ትቀበላለህ። የደርግ አባሎች ለቴሌቭዥን ካሜራ መነሣትን ስለሚወዱ በአንድ ለሙከራ በተዘራ የበቆሎ ማሣ ውስጥ ፎቶ አስነስተህ አስተናግደህ ስትልካቸው ያ የተነሱት ፎቶ በቴሌቭዥን ሲታይ በሳምንቱ የአንድ ክፍል ሹምነት እንደተሰጠህ የሚያበስር ደብዳቤ ይደርስሃል። ኑሮው እንደዚህ ነው በማለት አጫውቶኛል።»«እኔም ሁኔታው አስገርሞኝ ይህ ነገር ውሸትነቱ ቢገለጸስ» ብዬ ብጠይቀው «ማነው በሥልጣን የተቀመጠ የማይዋሽ? ሁሉም ይወሻል። ሃምሣ ሰው የደርጉን አባል ንግግር አዳምጦት ሃምሳ ሺ ሕዝብ በስብሰባው ተገኘ ተብሎ በዜና ማሰራጫ ይተላለፋል። «ጭራ እናትን ይከተላል ተብሏልና» እኛም መሪዎቻችንን ብንከተል አያስነውርም» በማለት በቀልድ ጥያቄዬን መለሰልኝ።

በአጠቃላይ ልግመቱም ሆነ የነበረውን ማውደም በግብርናው መስክ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም በተወረሱ ድርጅቶች ጭምር ነው። የራሱን ንብረት በትክክል መምራት የማይችል ወይም የማይችሉ ግለሰቦች የሕዝብ ንብረት የሆኑትን ድርጅቶች ይመራሉ ማለቱ ያስቸግራል። በየአቅጣጫው ሥራውን ይመሩ የነበሩት ግለሰቦች የሰነፎቹ ገበሬዎች ዓይነቶች መሆናቸው አያጠራጥርም። በመንግሥት ተወረሱ የሚባሉትን ቡና ቤቶችን ብጠቅስ የከድሬ የአብዮት ጠባቂ የደርግ አባሎች መጨፈሪያ ናቸው። እንቦላቸው አይታጠብም ክፍሎቹ አይጸዱም አለቃና ምንዝሩ አይታወቅ፤ ተራው ሠራተኛ የፖለቲካው ድርጅት አባል ሊሆን ይችላል አሰሪውም የሥራ ክፍፍሉን መናገር

ይፈራል፤ እንደው ድርጅቱ እስከሚከስር በዘፈቀደ ይመራል። የሕዝብ ወይም የራሴ ንብረት ነው ቢበላሽ ከሥራ ውጭ እሆናለሁ ሃገሪቱ በምጣኔ ሐብቷ ትደቃለች ብሎ የሚያስብ የለም። አብዮት ሁሉንም ነገር ነው ዳቦ ነው ቢራ ነው መኪና ነው መሣሪያ ነው ስሙን የጠራ ሁሉ መና ከሰማይ ይወርድለታል ተብሎ ስለሚገመት ፀሎቱ በየጊዜው የሚወጡትን መፍክሮችን ማሰማት ሆኗል።

አቶ ተፈራም በመቀጠል «ማን አከፋና ደማ ያነሣል? የተሟላ ሰውነት ይዞ የእርዳታ ስንዴ ያስገባል።»

የቤተሰብ ውይይታቸውን ካበቁ በኋላ ወይዘሮ ልክየለሽ ስለታደሰ በሕይወት መኖር ሲጠይቁ፤እውነቱም ልንገራቸው አልንገራቸው በማለት ትንሽ ከአመነታ በኋለ፤ «ይህች ሃገራችን በእውነት የሚሰራላት ሰው ሊኖርባት አልቻለም፤» ሁለቱም በአንድ ቃል «ከሃገር ወጣ» በማለት ሲጠይቁት፤ እንገቱን ደፋ አድረጎ «ያ ወጣት ያለውን መንግሥት ሲቃወም መፍትሔውን እያቀረበ ነበር።»

አቶ ተፈራም «ምን ሆነ ነው የምልህ»በማለት በቁጣና በመቻከል ሲያፋጥጡት እርሱም መገደሉን ሲነግራቸው፤ ሁለቱም ምራቃቸውን ትፍ ብለው «ምን አይነት ዜና አመጣህብን» በማለት ወደመኝታቸው ይሄዳሉ።



## ፴፫

እንደወትሮአቸው ወይዘሮ ልክየለሽ በጠዋት ተነስተው ቡናቸውን አፍልተው ቁርስ አዘጋጅተው አቶ ተፈራና እውነቱን ወደ አረም ሥራቸው እንዲሄዱ በማስተናገድ ላይ ሳሉ የቀድሞ የኩል አራሻቸው የነበረው ባልቻ ከቤታቸው ይመጣል።

ባልቻ ከአካባቢው የገበሬ ማሕበር በፍቃደኝነት ተመልምሎ ታጠቅ ጦር ሰፈር ከሰለጠነ በኋላ ምስራቅ ጦር ግንባር ሲዋጋ ተመቶ ከሆስፒታል እርዳታዎች ተደርገውለት ሲሻለው በአምራች ግብር ኃይልነት ወደነበረበት አካባቢ ከተሰከ ዓመት አልፎታል። ግን ችሎ ያለማው ምንም ነገር አልነበረውም፤ስለዚህ ከአቶ ተፈራ ዘንድ የመጣው በድርቅ ለተጎዱት ወገኖች ተብሎ የመጣውን የስንዴ ዱቄትና የታሸጉ ምግቦች በራሽን መልክ እንዲሰጠው መጠይቅ አቀርቦ መቀበሉን በዕማኝነት የሚመለከትለት ከአካባቢው የሚያውቀው የሃገር ሽማግሌ ካለ እንዲያቀርብ በተጠየቀው መሠረት አቶ ተፈራ በታዛቢነት እንዲገኙለት ለመጠየቅ ነበር። አቶ ተፈራም ለጊዜው ለአረም ከማሳቸው ለመሄድ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው ፤ ግን ከሰዓት በኋላ ከአረም መልስ እንደሚገኙለት ተስማምተው፤ ከዚያንም ቡናቸውን እየጠጡ ስለጦርነት አስከፊነትና አደገኝነት ጠቅሰው፤ የእርሱንም በሕይወት መትረፉን ለእግዚአብሔር ምስጋናቸውን አቅርበው፤ግን መሬት ለአራሹ ተብሎ በታወጀበት ወቅት በሐሰት የማያርስባቸውን በሮችና የማያርሰውን መሬት የእኔ ነበር ብሎ በመውሰዱ ሲወቅሱት፤ «ደግሞም ልክ በጠላት ዘመን እንደተደረገው መሣሪያ ቀብሮአል ብዙ ገንዘብ አለው፤ አደሃሪ ነው በማለት መግቢያ መውጫ እንዲያሳጡኝ ያደረከበትን ምክንያት ለእኔም ሆነ ለልኬለሽ ሊከሰትልን አልቻለም፤ እውነት ለመናገር የመሬቱ መወሰድ እስከዚህም አልቆጨንም። ቀድሞውንም ቢሆን ሐንዱራ መሬቱ የእኛ ይሁን እንጂ የአመረትከውን እኩል እየተካፈልን ትወስድ ነበር። ማመዛዘን የነበረብህ ታርስባቸው የነበሩት በሮች የእኛ ሐብት ሲሆኑ መሬቱም እርስታችን ነበር።በእኛና በአንተ መካከል ለባለጋራነት የሚያደርሰን ምንም ነገር አልነበረም።ሌላው ቀርቶ ለልጅህ ማሰደጊያ ጥገት ላሟችንን ስጥተን፤የጉሉማ መሬት ከፍለን በሰላም የምንኖር ሰዎች እንጂ ለዚያን ሁሉ መቃቀሮች የሚያደርሰን ምክንያት አልነበረም። ይህ የእኔና የአንተ ግንኙነት ነው፤ የሌላውን አላውቅም። በእርግጥ አተኩረን ብንመለከተው መሬቱን የሌላ ሃገር ሰው መጥቶ አልወሰደውም ያው በወገን እጅ ነው። እርቆ ለአሰበው ከማይሰራው ተወስዶ ለሚሠራው መሰጠቱ የሚያስከፋ አይሆንም፤ ሆኖም ግን ከውጤቱ ሲታይ እንደታሰበው አልሆነም። ባልቻ ከሁሉም ድርጊታችሁ እኔንና ልኬለሽን በጣም አደርጉ ያሣዘነንና ያስቆጨን ነገር ቢኖር ያቺ ምንም የማታውቀው ሕፃን ልጃችሁን የእኛ ፍቅር ይዟት ከቤታችን ስትመጣ እንተም ሚስትህም እንዳትመጣ

ስታደርጎትና አልፎም ተርፎም በልምጭ እየደበደብከት ከበራፋችን ስትመልሰት ስናይ እጅግ በጣሙን ሐዘን ተሰማን ዓምላክን ምን ዓይነት ዘመን አመጣብን በማለት አማረርን።ባንወልዳትም ልጃችን ነበርች። ሌላው ቀርቶ በሃይማኖታችን የክርስትና ልጅ እንደውም ከወለዱት ልጅ ይበልጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃል ይባላል። እኔና ልኬለሽም ከዚያን ቀን ጀምሮ እንግዲህ ከሰው መኖር በቃን ብለን ወሰንን፤ ምን ያደርጋል ከሰው ተነጥሎ እስከ መቼ ይኖራል? ያ ሆነና ልቧ አላስችለው ብሏት ልከየለሽ ለጦርነቱ ተመልምለህ ስትሄድ ከቤትህ ድረስ መጥታ ልጄ በደህና ይመልስህ፤ ግን ከማይሆኑ ጓደኞች ጋር አትዋል፤ ብላ ስትመክርህ የተናገርከትን አትከደውም። በእርግጥ ሃገር ስትወረር ማየቱ የሁላችን ፍላጎት አይደለም።ግን መሪዎቻችንን ዘር ብለህ ስትመለከታቸው ያለህን የወገንና የሃገር ፍቅር ያሣጡሐል፤ የሃገርና የወገን ፍቅር የሚለካው እነርሱ በሚሉት መንገድ በሙሉ ያለ ቅዋሜ ስትከተል ብቻ ነው። በወቅቱ ልከየለሽም ልትጠቅምህ የፈለገችው ነገር ቢኖር ያን ነበር። ለሁሉም እንኳንም በደህና ለአካባቢህ አድባር አበቃህ። ጥንት የአባት ግፍ ለልጅ ልጅ ይተሳለፋል፤ ይባላል፤ዘንድሮ በባለቤቱ ላይ ሲፈጸም እየነው።»

ወይዘሮ ልከየለሽም «ለመሆኑ የባለቤትህ አድራሻ ከየት እንደሆነ አውቀህዋል?» በማለት ሲጠይቁት፤ ባልቻም እንዴት የገጠር ከተማ ስም ጠርቶ ከዚያን «ሴተኛ አዳሪ ሆናለች ብለውኛል፤ ሕፃኗንም ብጠይቅ ለወላጆቿ እንደሰጠቻቸው ሰምቻለሁ፤ ተውኝ እማማ ከጦር ግንባር ሆነን የሚነገረን ሚስቶቻችሁ ልጆቻችሁ በእንክብካቤ ተይዘዋል፤ ገበሬ ማሕበሩ መሬታችሁን ያርስላችኋል፤ይህ ዳቦ ቆሎ ቋንጣው፤ከቤተሰባችሁ የተላከ ነው እየተባለ ይታደለናል።ምነው እውነቱ ቢነገር? እኛም ውሸቱ እውነት እየመሰለን እንደሕፃን እያታለሉን ቤተሰብን ብንናፍቅ እንኳን ደህና ከሆኑና ከተከባከቡልን ለሃገራችን ብንሞትላትስ በማለት ሞራላችንን እየገነባን፤ እኔም መጥቼ ለመጠየቅ ይሉታ ይዘኝ ይህው እስከ ዛሬ ሣልጠይቃቸው በሦስት ዓመቴ ይህ አደጋ ደርሶብኝ ለመምጣት ቻልኩኝ። ቆርጠው እንኳን ቤተሰባቸውን ለመጠየቅ ማመልከቻ ያስገቡትን ነገ ዛሬ በማለት ሲያጉላሏቸው እንደውም አልፈው ተርፈው አይመለሱም ብለው በማሰብ ካሉበት የጦር ክፍል ወደሌላ ሲያዛውቸው ሲታይ ደግሞ አለመጠየቁ ይሻላል በማለት እስከዛሬ ቆየሁኝ።» አቶ ተፈራም ለምን ከጅግኖች እንባ እንዳልገባ ይጠይቁታል።ባልቻም ተከዝ ብሎ «አባባ ያሾፋሉ? እንደእኔ ያለ ደሀ እንዴትስ አድርጎ ከዚያን ይገባል?»

ወይዘሮ ልኬለሽም «በአብዮቱ ሁሉም እኩል ነው አልተባልምን??» በማለት ሲጠይት፤«ባልቻም አንገቱን ደፋ አድርጎ እማማ ይህች ሃገር የፈዝ ሃገር ሆናለች።ወሬ እንጂ እንዴት ቁምነገርን የሚሠራ አላየሁም።ለእኛ ለደሆቹ ደርሰው ያዘጋጁልን ነገር ያለ ይመስል፤በደህና አብረን ከምኖራቸው ጋር አጣሉን፤እነርሱ ዘረው ገጠሙ፤ሁለት ገመድ መሬት ተሰጠን የአንዴ ሰብል ሳንበላለት ወደጦር



ግንባር ተላክን፤ከጦርነቱ ይበልጥ በጦሩ ውስጥ ይደረግ የነበረው የእርስ በእርስ ሽኩቻዎች አያደርስ ነበር።አንዱ አንዱን አሳልፎ ለመስጠት የሚደረገው እሽቅድድም፤የሰው አፍ መጠበቅ፤በየዕለቱ የአእይምሮ ማወኪያ ሐሣቦችን ማፍለቅ፤ዛሬ በጦሩ ውስጥ የራስ መጋለጦች ይደረጋሉ አሰሳዎች ይካሄዳሉ፤ፀረ-ሕዝቦች ወረቀት ሊበትኑ ነው፤የማናውቀው ድርጅቶችን ስም እየጠቀሱ በጦሩ ውስጥ ተሰግስገዋል፤ራሳችሁን አጋልጡ ስታገኟቸው ጠቁሙ እየተባለ፤የተጠቆሙትን ያለምንም ማስረጃ እያወጡ ሲመቷቸው እያየን ማን ከማን ይነጋገራል? ማታ ተኝተን ጠዋት መነሣታችንን እናምነውም።»

አቶ ተፈራም «ይሄውልህ አየህው አይደለም? የእኔን በርች የእኔ ናቸው ብለህ ስትወስዳቸው ማን ማስረጃ ጠየቀህ? ሁሉም አደሃሪ ነው አታደምጡት ተብዬ አልነበረምን የተባረርኩት? ባልቻ አንድ ነገር መገንዘብ አለብህ ፍትሕ አንድ ቦታ ላይ ከተጣመመ ከሌላ ሥፍራ ይቃናል ማለት ዘበት ነው። ለማቃናትም ከተፈለገ ከመጀመሪያ ከተበላሸበት ሥፍራ መታረም እንዳለበት ማሰብ አለብህ፤በእርመኛ አንድ ተረት አለ።«ሐሬን ገነማ ቼ ጀደኒ አሪኤን ገልገሏ ኩሪን እንገልቱ።» ያው ጠዋት ቼ ብለው ያበረሯት አህያ ማታ ኩር ኩር ብለው ቢጠሯት አትመጣም ይባላል። የእኛም ሃገር ጉዳይ መሠረቱን ለማጥፋት የተሯሯጥነውን ያህል መልሰን ለመገንባት የቻልነው አልመሰለኝም።»

ባልቻም «እኔ እንኳን ቀደም ሲል ባለማወቄ ያደረኩት ነገር በመሆኑ በየዕለቱ ሳስታውሰው እረፍት እየነሣኝ ነው። ዛሬም ሁኔታውን ለመግለጽ የተገደድሁት ለምን ከጅግኖች እንባ አልገባህም ስለአላችሁኝ ነው፤ እንጂ እኔ ያለ ምንም ሽብርና ወሬ ጥሩ አየር እየተነፍስሁ በደህነት ከዚህ ከገጠር የተቻለኝን ያህል እየሰራሁኝ መኖሩን የመረጥሁበት ወቅት ነው። የእነርሱ የጅግኖች እንባ በአፍንጫዬ ይውጣ።»

አቶ ተፈራም የሰውነቱን መጎዳት ተመልክተው ለሥራ ለመሰማራት መቻል አለመቻሉን ጠይቀውት፤እርሱም በአለበት ሁኔታ ዱሩን መንጥሮ እዳሪ አውጥቶ አምራች መሆን ይቅርና የሚሰጠውን ስንዴ እንኳን አዘጋጅቶ ለመመገብ ያለው ፍላጎት በጣም የቀዘቀዘ መሆኑን ገልጾ፤«በተለይ አንድ ሰው መሣሪያ ተሸክሞ ሸቅብ ቁልቁል ማለት ከጀመረና በካንፕ ተቀምጦ ከተቀለበ በኋላ ዳግመኛ ወደእርሻ ተሰማርቶ አምራች ይሆናል የሚለው ግምት ከራሴ ጀምሬ ስመለከተው የሚቻል አይመስለኝም። እኛን አካለ ስኩሎቹ እንቅርና ደህነኞቹን ብረታችሁን አስቀምጣችሁ ወደልማት ተሰማሩ ቢባሉ አሻፈረን በራሽን ብቻ እናገለግላለን ከማለት አይመለሱም። እኛም ከጦርነት ላይ ተመተን የመጣነውን ሚሊሻዎች እንደችሎታችን ሊያሰራን የሚችል ድረጅት ቀርቶ፤ አብረን እንድሰራ የተላክንበት የገበሬ ማሕበሩም እንደሆን አባላቱ ራሳቸውን መመገብ ተስኖአቸው ከእኛው ጋር ቀለብ ተሰፋሪዎች ሆነዋል። ሁሉም ቆንጥሮ አጉራሽ ፈላጊ እንዲሆን ሆን

ተብሎ የታቀደ ስለሆነ መንግሥት በዚህን በኩል ተቃውሞ የለውም።»

አቶ ተፈራም «የሚሰሩትን አቅርቧቸው አደሃሪ እያላችሁ የመስራት ፍላጐታቸውን ገድላችሁ የተፈለገው ሕዝቡ በልመና ቀለብ እንዲኖር ስለሆነ ቀጥሉበት። ለመሆኑ የምትቀበሉት ራሽን ከየት እንደሚመጣ ታውቀዋለህን?»።

ባልቻም የለበሰውን ብርድልብስ ወደቀኝ እያጣፋ፤ «ጦር ግንባር ሆነን እንደተነገርን የጎጃም ገበሬ እንደኛነቱን ማግኘቱን ሲሆን ሆኖም ጎጃም በስንዴ ስለማይታወቅ ያው እርሲ ይሆናል ብዬ ያ ከቀበሌ የሚሠራው ተማሪ ጥይቶኝ ብመልስለት፤ ከት ብሎ ስቆብኝ ከውጭ ሃገር በእርዳታ ስም የተሰጠን መሆኑን ገለጸልኝ። ከዚያን የነበርን ሚሊሽዎች እፍረን አንገታችንን አቀርቅረን ከመሥሪያ ቤቱ ወጣን። እንደውም በጦር ግንባር ይታደለን የነበረው ከቸሮ ከውጭ አገር በእርዳታ የመጣ ሳይሆን አይቀርም በማለት እየተበሳጨን በየአቅጣጫው ስንበተን፤ መቸም ሆድ ቀን አይሰጥምና አባባ ተፈራ ቢረዱኝ ብዬ ከእስ ዘንድ መጣሁ። ጤንነቴ የተሟላ ቢሆን ኖሮ ይህን በእርዳታ ስም የመጣውን ቀለብ እንዲች ብዬ አልሰፈርም ነበር። ምን ያደርጋል? ሁሉም ነገር መና ቀረ። ኩራታችን አፈር በላ የሰው እጅ እያየን እንድንኖር ተደረግን። ይገርሞታል እማማ ልክየለሽ በሁለት ቀኑ እህል በአፌ ሲዘር ይህ የመጀመሪያው ነው፤» ሲል ወይዘሮ ልኬለሽም ተከዝ ብለው «ምነው ባልቻ መጥተህ እማማ የምበላው ስጪኝ ብትለኝ እያለኝ የለኝም እልህ ይመስልሃል?ምንም ቢሆን ሁላችንም ከሰው ነው የተፈጠርነው ።ይህ የሚያልፍ ቀን እርስ በእርሳችን ቢያለያየንም ጊዜው ያመጣው እንጂ ወደን ያደረግነው አይደለም።በእርግጥ ከአንዳንድ ወገን ከሚያስከፉ ተግባሮችን ከመፈጸም ራስን መቆጣጠሩ ለሰው ልጆች በአጠቃላይ ለሕዝብ ያለንን ፍቅርና አክብሮት ይገልፃል።ሆኖም ግን ያንን ያልተረዱ ጥቂት ወገኖችን ምን ማድረግ እንችላለን? ባልቻ በአንዳንድ ተግባሮችህ እኛ እንድንከፋብህ ብታደርግም፤ምክንያቱ አንተ አይደለህም።ያም በመሆኑ ይሄው ዛሬ ቢቸግርህ ከእኛ ዘንድ መምጣትህ በምን ወቅት እንደምትፈልገን ለመረዳት ችለናል። ይህም የነበረን ሥነምግባር መጥፎ ያለመሆኑን ለመግለጽ ጥሩ ማስረጃ ለሁላችንም ሊሆን ይችላል። ሁላችንም ብንሆን የአንድ ሃገር ሕዝቦች ነን መረዳዳት ግዴታች ነው። እኛም ያለንን ወደኋላ አንልም።በእርግጥ እንደቀድሞው ከጉተራችን የምንዘግነው ምርት የለንም።ሆኖም ግን አልተራብንም። የእርዳታው እህል ከቤታችን አልገባም ማለቴ ነው።ወገን እየተራበ አልተራብኩም ማለቱ እንኳን ግብዝነት ነው። ሆኖም የምንጠግታቸውን ላሞቻችንን አውጥተን እስከመሸጥ ደርሰናል።ያለን ኩራት በግላችን ያለ ቢሆንም፤ግን በአካባቢው ያሉት ጎረቤቶቻችን እየተራቡ እኛ ጠግበን ማደሩ ሊያኮራን አይችልም።የእህል ንፋሽ በታየበት ደጃፍ ምግብ አለ በማለት ከጠዋት እስከማታ ከደጃፍ ሲቀመጡ በዚህ እድሜአችን ለማየት በቅተናል።ልጆቻችን ዛሬ ጾም ሊያድሩብን ነው ብለው የመጡትን ጎረቤቶቻችንን ትፍረድንና



እንዳአርጋቸውን አጥግበን የለንም ብለን መመለስ ይገባናልን? ወተት ንጦ ቅቤ ማውጣቱ ከቀረ ዓመታት አልፈውናል። የተገኘውን እሳቢ ተከፋፍለን እንጨርሰዋለን። አሁንም ባልቻ የአለፈው አልፏል።መልሰን የቤተሰብ ፍቅራችንን እናጠናክር፤ቤተሰብ በትዋ ሕብረተሰብ መገንባት ይቻላልን? ሕብረተሰብን አራርቆና እርስ በእርስ ከፋፍሎ ሃገርን ማሣደግ አይቻልም? ከእኛ ሁኔታ ብዙ መማር እንችላለን።ቀድሞ የነበረን ግንኙነት ለብዙ ጊዜ በመቋረጡ፤የቤተሰብ ፍቅር ጨርሶ በመወገዱ፤የራስ ከማጥበቅ አልፎ ሌላውን ቀምቶ መበልጸግ እንዴን አጥፍቶ ከሥልጣን ለመውጣት ስለተፈለገ ይሄው አሁን ከአለንበት አዘቅጥ ውስጥ እንድንዘፈቅ ተገደናል።የሁላችንም ዓላማ አንድ ከሆነ ዳግመኛ መፈቃቀርን መገናኘትን አብሮ መሥራትን የማንጀምርበት ምንም ምክንያት የለም።አንተም ብትሆን እንደቀድሞው ቅረበን ሌላው ቀርቶ ሚስትህን መልሰህ አምጣት፤ እስከዚያው በምግቡ ዝግጅት እረደሃለሁ።ለአንተ ብዬ ምጣድ አልጥድም።ለራሴ ስጋግር ለአንተም ለሁለት ለሦስት ቀን የሚሆንህን በሰማው ምጣድ ላይ እሰፋልሃለሁ።»

አቶ ተፈራም የባለቤታቸውን ንግግር ካዳመጡ በኋላ እስከመጨረሻው በሕይወት እስካሉ ድረስ የእርዳታ እህል ከቤታቸው እንደማይገባ ጠቅሰው፤«ጉልበቴ ውሎ ይደር እንጅ በደማም ቢሆን ቆፍሬ ጉመንና ድንች ዘርቼ የቤተሰቤን ሕይወት አድናለሁ። ከባሕር ማዶ ተጭኖ የመጣው እህል እንድች ብሎ ከቤቴ አይገባም።ይህችን የመሰለች ሃገር ይዘን በረሃብ ይሰቃዩ ነበር ተብሎ በመጽሐፍ ተጽፎ ተተኪው ትውልዳችን ሲያነበው ምን ዓይነት ትዝብትን ይጥልብናል? ታሪክ እያዳለም እኛ በኖርንበት ዘመን የልጆቻችን ገጽታቸው የአዘውቶቻችን እስከሬናቸው ለዓለም ሕብረተሰብ የረሃብ ማስፈራርቾ ሆነው ሲቀርቡ ተተኪው ትውልድ ምን እስተያየት ይሰጥብናል? አገላብጦ የሚያርሰውን ገና ለገና ሥስልጣን ይሸማናል በማለት ከትንሽ ከተማ እስከ ትልለቅ ከተማዎች ያሉትን ሠራተኞች አጥፍቶ እንዴትስ ሃገር ሊለማ ይችላል? በትምክት በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት ገንዘቡ ለመሣሪያ መግዣ ከዋለ፤የሃገሪቱ ገቢ ምርትን በማይሰጡ ሥራዎች ላይ ለተሰማሩ ባለሥልጣኖች በደመወዝ መልክ ከተከፈለ፤የሥራ መስኮችን ለማቋቋም እጅ መንሸዎች ከተጠየቁ፤በምርት ላይ ተሣትፎ የሌለው የቀበሌ ተመራጭ ሌላው በመረተው ላይ ወሰኝ ከሆነ፤ገበሬው ሆነ ነጋዴው ለመጭው ዘመን በጎተራውም ሆነ በመጋዘኑ ውስጥ ካላኖረ፤እንዴትስ ሃገር ያድገል ረሃብስ ለመቆጣጠር እንዴት ይቻላል? የተሰጠው ማንቃቂያ ቢኖር ሁለት መቶ ኩንታል በርበሬ ያስቀመጠን ነጋዴ መግደል ነበር። ያንን የተመለከተ ገበሬ ለምንጊዜውም ከሚበላው በላይ ማንኛውንም ሰብል ለማምረት ፍላጎቱ አይነሣሣም። የትኛው ይመረጣል? ተዝናንቶ እንዳይሰራና እንዳያመርት በየአቅጣጫው እየተቆጣጠሩ ለሚመጣው ዘመን ምርቱን ከጉተራ ሲያከማች አውጥቶ መግደልና የልመና እህል መቀበል? እኔ በበኩሌ

የዚህን አይነት መመሪያ ከሚቀበል መንግሥት እባል አልሆንም።»

ባልቻም «እሰ ለእህሉ ይቆጫሉ።በሃገራችን የሰፈረው ጦር ሊዋጋልን ወይስ ሊገዛን የመጣ ይመስሎታል?» «እኛ የሃገራችንን ታሪክ እንደምናውቀው ነገሥታቶቻችን ወሰን አልፈው ባሕር አቋርጠው ሲገዙ እንጅ አልፈው ተርፈው የራሳቸውን ወሰን ማስከበር ተስኖአቸው የውጭ ጦር በእርዳታ ሲያስገቡ ሲነገርም አልሰማንም ተጽፎም አላነበብንም። በእርግጥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የእንግሊዝን መንግሥት ኢጣሊያንን ለማስወጣት ትብብረ ጠይቀው ነበር። ያም ደግሞ የጠቀለለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ነበር ለማለት አይቻልም። አርበኞቻችን በቃን ብለው እጅ ሰጥተው አልገበሩም። ግራዚያንን ከአዲስ አበባችን ድረስ በመግባት ለማቁሰል ችለዋል። ደማቸውን በዱር በገደሉ አፍሰዋል፤ አጥንታቸውን ከስክሰዋል። አሁንም እናተ የዘመታችሁበት ጦርነት እስከ ዛሬ አባቶቻችን ከዘመቱበት፡ጦርነት ልቆ የሚታይ አይደለም። ግን የበለጠ አድርገው የገመቱት ጥቂቶች የራሳቸውን ሥልጣን ለማጠናከር ስለሆነ ወገንና የሃገር ሐብት በመውደሙ ቢያሳዝነኝም እንደትልቅ ጦርነት አድርጌ አልወሰደውም። ሁላችንም በገዛ ወገኖቻችን ከጠላት የበለጠ ግፍ ስለተፈጸመብን ጊዜአችንን በቁጭትና በንዴት ከማባለፍ ሌላ አልፈን ተርፈን ለሃገር ለማሰብ የአእይምሮ ሰላም አልነበረንም። ይህን መንግሥት በዚህን ዓይነት መመሪያው በፍጹም አልቀበለውም» ብለው ፊታቸው ሲለዋወጥ የተመለከቱት ወይዘሮ ልክየለሽ ሁልጊዜ የሃገር ጉዳይ ሲነሣ የሚሰማቸውን ንዴት እንዲያቆሙ ይነግሯቸዋል።እሳቸው ብቻ ለሃገር ሐሣቢ ሆነው መቅረብን አግባብ እንዳልሆነ ይጠቁሟቸዋል፤«ሐሣብን መግለጹ መልካም ሆኖ ባለ፤እልፎ ጤንነት እንዲጎዳ ማድረጉ ጭራሽ ራስን የሁለት ጌታ ተገዥ ማድረግ ይሆናል» በማለት ምክራቸውን ይለግሷቸዋል።

«በአጠቃላይ ስለሃገር ችግርም ሆነ ብልጽግና ሲታሰብ በአንድ ዘመን ተወስኖ የሚቀር አይደለም።ችግርን ለማስወገድ በትክክለኛ መንገድ ከተሰራና ሕዝብም ያለአንዳች ተጽኖና የውጭ ኃይል ጣልቃ ሣይገባበት፤ ከቤተሰብ እስከ ሕብረተሰብ ጠንክሮ ከሠራ የማይለወጥበት ምንም ምክንያት የለም። ግን እኔ ከሞትኩ ሠርደ አይብቀል እንደሚባለው ሆኖ ያለውን እሚጦ ገና ያልተወለዱትን የልጅ ልጆቻችንን በዕዳ ውስጥ ጥሎ ማለፍን ሰዎች ከፈለጉት ምን ማድረግ ይቻላል? ጥቂቶች ብቻቸውን ቢፍጨረጨሩም ውጤቱን በቅርብ ስለማያዩት ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችል ይሆናል፤ግን ጥሩ መሠረትን መጣል ካለመሞከር ይመረጣል። እንደሚያውቁት ባለንበት ጊዜ ሐሣብን በትክክል የሚገለጽበት መልካም ሥራን ለማከናወን ፍላጎቶች የተቀሰቀሱበት ጊዜ አይደለም።በሥልጣን ላይ በየቦታው የተመደቡትን ካለአመኪኹ አለመናገሩ ተመርጧል።እንደእቦ ያለ ግለሰብ የታየውን ሲገልጽ ጥቅሙ ስለተነካበት ነው ይባላል።የመብት ጉዳይ መሆኑን



የሚረዱት ጥቂቶች ይሆናሉ።ስህተቶች ሳይታረሙ እንደው በከንቱ ጊዜን ማጥፋቱ ፋይዳ የለውም። ራስን ግን ሕብረተሰብን ከሚጎዱ ተግባሮች መጠበቁ ይመረጣል።ሰው በሚኖርበት አካባቢና ሃገር ጥሩ ስም ይዞ መሞትን ያህል ታላቅ ነገር የለም።ተተኪው ቤተሰብ በደስታና በአክብሮት ሊኖር ይችላል።በቀድሞ ጊዜ ለልጅ እርስትና ገንዘብ አውርሶ ማለፍ የነበረን ወግ ቢሆንም፤በዛሬ ጊዜ ግን ከጥሩ ሥነምግባርና መልካም ሥራ ሌላ ለልጆቻችን የምናስተላልፍላቸው ነገር የለም።እቦም በግል የሚያመጡት ምንም አይነት የመንግሥት ለውጥ ስለሌለ እርፈው ሥራዎን ይስሩ። የፈራነው ረሃብ እኛም ቤት እንዳይገባ መፍጨርጨር ይኖርብናል።» አቶ ተፈራም የባለቤታቸውን ሐሣብ ከተቀበሉ በኋላ ለባልቻ ከማሣው እርፍደ መጥቶ እንዲያስታውሳቸው ነግረውት ከእውነቱ ጋር ለአረም ሥራቸው ሄዱ።